# መጽሐፈ ነገሥት - አንደኛ

## መግቢያ

### አሰያየሙ

በአይሁዳውያን ትውፊት መሠረት ልክ እንደ መጽሐፈ ሳሙኤል አንደኛና መጽሐፈ ሳሙኤል ሁለተኛ፣ እንደ መጽሐፈ ዜና መዋዕል አንደኛና መጽሐፈ ዜና መዋዕል ሁለተኛ ሁሉ፣ መጽሐፈ ነገሥት አንደኛና መጽሐፈ ነገሥት ሁለተኛ እንደ አንድ መጽሐፍ ይቈጠሩ ነበር፤ የሚታወቁትም "ነገሥት" በሚለው መጠሪያ ነበር።

መጽሐፈ ነገሥት ሁለት ቦታ የተከፈለው 200 ዓ.ቅ.ክ. ላይ ሰብዓ ሊቃናት ብሉይ ኪዳንን ከዕብራይስጥ ወደ ጽርዕ (ግሪክ) ቋንቋ በመለሰሱበት ጊዜ ነው። ከዚያም የላቲኑ ቩልጌትና አብዛኞቹ የዘመኑ ቅጆች ይህንኑ መንገድ ተከትለው መጽሐፈ ነገሥትን ለሁለት በመክፈል ሁለት መጽሐፍ አድርገውታል። በ1448 ዓ.ም. መጽሐፈ ነገሥትን ከሁለት የሚከፍል አንድ የዕብራይስጥ ቅጅ ስለ ተገኘ፣ ከዚያ በኋላ የታተሙት ቅዱሳት መጻሕፍት ይህንኑ ፈለግ በመከተል፣ መጽሐፉን ከሁለት ቦታ ከፍለው መጽሐፈ ነገሥት አንደኛና መጽሐፈ ነገሥት ሁለተኛ የሚል ስም ሰጥተውታል። እንዲያውም የመጽሐፈ ሳሙኤልንና የመጽሐፈ ነገሥትን ዝምድና ይበልጥ አጕልቶ ለማሳየት የሰብዓ ሊቃናት ትርጒም አንደኛ፣ ሁለተኛ፣ ሦስተኛና አራተኛ፣ ሁለቱን መጻሕፍት መጽሐፈ መንግሥታት ብሎ ሲጠራቸው፣ ቩልጌት አንደኛ፣ ሁለተኛ፣ ሦስተኛና አራተኛ ደግሞ ነገሥት የሚል ስም ሰጥቶአቸዋል። ሁለቱም የሳሙኤልና የነገሥት መጻሕፍት ከሳሙኤል ዘመን የሚጀምረው የነገሥታቱ አገዛዝ በባቢሎናውያን እጅ ተንኰታኵቶ እስከ ወደቀበት ጊዜ ድረስ ያለውን ታሪክ በሙሉ በአንድ ዐይነት መልክ አዛምደው አቅርበውታል። መጽሐፈ ነገሥት የተከፈለው ከሰሜኑ መንግሥት መሪ ከአክዓብና (22፥37) ከደቡቡ መንግሥት መሪ ከኢዮሣፍጥ ሞት (22፥50) መጠቀስ በኋላ ነው። መጽሐፉ በዚህ ቦታ ላይ መከፈሉ፣ በመጽሐፈ ነገሥት አንደኛ (22፥51-53) መጨረሻ ላይ የሚገኘውን የእስራኤልን ንጉሥ የአካዝያን ዘመን ታሪክ ከመጽሐፈ ነገሥት ሁለተኛ መጀመሪያ (ም 1) ጋር በከፊል እንዲያያዝ ያደርገዋል፤ አብዛኛው አገልግሎቱ በመጽሐፈ ነገሥት አንደኛ (ም 17-19) ላይ የተጻፈለት የኤልያስ ታሪክም በመጽሐፈ ነገሥት ሁለተኛ (1፥1-2፥17) ላይ ተጽፎ ይገኛል። ይህም አካዝያስ የላካቸውን ሰዎች እሳት ከሰማይ ወርዶ እንድትበላቸው ማድረጉንና ልብሱን ለኤልሳዕ መስጠቱን የሚያሳየው ክፍል ነው።

### ጸሐፊው፣ የታሪኩ ምንጭና መጽሐፉ የተጻፈበት ዘመን

ይነስም ይብዛም የመጽሐፈ ነገሥት አንደኛንና የመጽሐፈ ነገሥት ሁለተኛን ጸሐፊ ማንነት የሚያረጋግጥ አስተማማኝ ማስረጃ አለ። ምንም እንኳ የአይሁድ ትውፊት ጸሐፊው ኤርምያስ ነው ቢልም፣ ባሁኑ ጊዜ ይህን ሐሳብ እውነት ነው ብለው የሚቀበሉ ጥቂቶች ናቸው። ጸሐፊው ማንም ይሁን ማን እንደ ብዙዎቹ የእስራኤል ነቢያት ሁሉ የዘዳግምን መጽሐፍ በሚገባ የሚያውቅና ይህን ታሪክ ለማቀነባበር የተለያዩ ምንጮችን የተጠቀመ መሆኑ ግልጽ ነው። ከምንጮቹም ሦስቱ በስም ተጠቅሰዋል፤ እነዚህም፣ "የሰሎሞን የታሪክ መጽሐፍ" (11፥41)፣ "የእስራኤል ነገሥታት የታሪክ መጽሐፍና" (14፥19) "የይሁዳ ነገሥታት የታሪክ መጽሐፍ" (14፥29) ናቸው። በተጨማሪም የታሪክ ምንጭ የሆኑ ጽሑፎች ለዚሁ ተግባር ሳያገለግሉ እንዳልቀሩ ይገመታል።

ምንም እንኳ አንዳንድ ምሁራን በመጽሐፈ ነገሥት አንደኛና በመጽሐፈ ነገሥት ሁለተኛ የተጠቀሱት ሦስቱ ምንጮች በኢየሩሳሌምና በሰማርያ ከነበሩ የነገሥታት ቤተ መዛግብትና ከነገሥታት የፍርድ ችሎት ዕለታዊ ጽሑፎች የተወሰዱ ናቸው ቢሉም፣ እውነቱ ግን ከዚህ የራቀ ነው። ሌላው ቀርቶ የቤተ መንግሥቱ የታሪክ መጻሕፍት በ16፥20 እና በ2ነገ 15፥15 ላይ የተጠቀሱትን መንግሥት ላይ የተደረጉ አድማዎችና ሤራዎች እንዴት ሊያካትቱ ይችላሉ የሚለው እንኳ ነገሩን አጠራጣሪ ሊያደርገው የሚችል ጒዳይ ነው። ከዚህ በተጨማሪ የነገሥታቱ የፍርድ ችሎት ለእንዲህ ዐይነቱ የሕዝቦች ደኅንነት ጥበቃ ዝግጁ ለመሆኑ አጠያያቂ ነው። በአጠቃላይ ይህንና ይህን የመሳሰሉ በርካታ ማስረጃዎች ብዙ ሊቃውንትን እነዚህ ምንጮች ከጥንት ጀምሮ በየዘመኑ በተነሡ የእስራኤል ነቢያት የተዘጋጁ የታሪክ መዛግብት ናቸው ወደሚለው ድምዳሜ ላይ አድርሰአቸዋል። በተለይ መጽሐፈ ዜና መዋዕል አንደኛና መጽሐፈ ዜና መዋዕል ሁለተኛ ከባለ ራእዩ ከሳሙኤል የታሪክ መጽሐፍ (1ዜና 29፥29)፣ ከሴሎናዊው ከአኪያ ትንቢት፣ ከባለ ራእዩ "ከአዶ ራእይ" (2ዜና 9፥29)፣ "ከነቢዩ ከሸማያ የታሪክ መጽሐፍ" (2ዜና 12፥15)፣ "ከአናኒ ልጅ ከኢዩ የታሪክ መጽሐፍ" (2ዜና 20፥34)፣ "ከነገሥታቱ መጽሐፍ" (2ዜና 24፥27)፣ "በአሞጽ ልጅ በኢሳይያስ ከተጻፈው የዖዝያን ታሪክ"፣ (2ዜና 26፥22፤ እንዲሁም 2ዜና 32፥22 ይመ) ይጠቅሳቸዋል፤ ከእነዚህ ውጭ የተጠቀሱ ሌሎች ማስረጃዎችም አሉ፤ ለምሳሌ የኤልያስንና የኤልሳዕን አገልግሎት በተመለከተ ጸሐፊው ምናልባት ሁለቱ ነቢያት ከሙሴና ከኢያሱ ጋር ቀድሞውኑ የተመሳሰሉበትን ታሪክ ከአንድ የትንቢት መጽሐፍ ምንጭ ሳያገኘው እንዳልቀረ ይገመታል።

የመጽሐፈ ነገሥት አንደኛና የመጽሐፈ ነገሥት ሁለተኛ ጥንቅር መልክና ቅርጽ የያዘው ኢዮአቄም ከእስር ከተፈታ በኋላ (562 ዓ.ቅ.ክ. ላይ 2ነገ 25፥27-30)፣ የባቢሎን ምርኮ ከመጠናቀቁ ቀደም ብሎ በ538 ዓ.ቅ.ክ. ላይ ነው የሚሉ አንዳንድ ሊቃውንት አሉ፤ ይሁን እንጂ በመጻሕፍተ ነገሥት አንደኛና

ሁለተኛ ላይ፣ "እስከ ዛሬም ድረስ" የሚለውን ቃል ተንተርሰው (ለምሳሌ:- 8፥8)፣ ከምርኮ በፊት የተደረጉ አንዳንድ ነገሮችን መሠረት በማድረግ ይህን አባባል ለመቀበል የማይፈልጉ አሉ፡፡ እንደ እነዚህ ያሉትን ነገሮች በማጤን፣ ጸሐፊው ከምርኮ በኋላ በባቢሎን የነበረ ሰው ሳይሆን፣ ከምርኮ በፊት በይሁዳ የነበረ ሰው መሆን አለበት የሚል ክርክር ተነሥቶአል:: እንግዲህ ይህ ክርክር ተቀባይነት የሚኖረው ከሆነ፣ መጽሐፉ በመጀመሪያ ተቀናብሮ የቀረበው ኢዮአስ በሞተበት ዘመን ሲሆን፣ ከዚህ ንጉሥ ዘመነ መንግሥት ፍጻሜ በኋላ ያለው ታሪክ የተጻፈው ግን በ550 ዓ.ቅ.ክ. ገደማ በምርኮው ጊዜ ነው ብሎ መደምደም ይቻላል:: በእነዚህ ሁለት ነገሮች ላይ የተመሠረተው አመለካከት፣ "አዎን፣ ሊሆን የሚችል ነው" ቢባልም እንኳ፣ የተቀባይነቱ ሚዛን የሚደፋው፣ "እስከ ዛሬም ድረስ" በሚለው ሐረግ ላይ ነው::

እነዚህ ዐረፍተ ነገሮች ከጸሐፊው ብርዕ የፈለቁ ሳይሆኑ ጸሐፊው ራሱ ከዋናው ምንጭ ቀድቶ ያመጣቸው መሆናቸውን መገንዘብ አንድ አማራጭ ነው:: መጽሐፈ ዜና መዋዕል ሁለተኛ 5፥9ን እና መጽሐፈ ነገሥት አንደኛ 8፥8ን ያገናዘበ፣ የሚደርስበት ትክክለኛ ድምዳሜ ይኸው ብቻ ነው:: መጽሐፈ ዜና መዋዕል ከምርኮ በኋላ የተጻፈ ለመሆኑ የሚያጠራጥር አይደለም፤ ይሁን እንጂ ለታቦቱ መሸከሚያ ጥቅም ላይ የዋሉትን መሎጊያዎች በሚመለከት "እስከ ዛሬም ድረስ በዚያ አሉ" ተብሎ የተነገረው ቃል እንደ ነገሥት መጻሕፍት ሁሉ በዜና መዋዕልም ላይ ተጽፎ ይገኛል:: ምናልባትም የዜና መዋዕል ጸሐፊ ምንጭ አድርጎ በዋቢነት የሚያቀርበው 1ነገ 8፥8ን ሊሆን ይችላል:: በዚህ ዐይን ሲታይ የመጽሐፈ ነገሥት አንደኛና የመጽሐፈ ነገሥት ሁለተኛ ጸሐፊም ከቀድሞ የታሪክ ምንጮች አልቀዳም ለማለት አያስደፍርም:: ይህም፣ ያ ሰው በምርኮው ዘመን እዚያው የቈየና የታሪኩንም ምንጭ በሚፈልገው ዐይነት የተጠቀመበት አንድ ጸሐፊ ነበር ለማለት በር ይከፍታል::

**መሪ ሐሳብ:- ንግሥናና ቃል ኪዳን**

መጽሐፈ ነገሥት አንደኛና መጽሐፈ ነገሥት ሁለተኛ በግልጽ የሚታወቅ ዐላማና መሪ ሐሳብ የላቸውም:: የይዘቱ ነጸብራቅ ግን ጸሐፊው በመጽሐፈ ሳሙኤል አንደኛና በመጽሐፈ ሳሙኤል ሁለተኛ ተጽፎ የሚገኘውን የቃል ኪዳን ግዴታ ያለበትን የንግሥና ታሪክ ፈለግ ተከትሎ ያዘጋጀው መሆኑን በግልጽ ያሳያል:: ባጠቃላይ መጽሐፈ ነገሥት አንደኛና መጽሐፈ ነገሥት ሁለተኛ የእስራኤልንና የይሁዳን ነገሥታት ታሪክ ከእግዚአብሔር ቃል ኪዳን ጋር በማያያዝ ዘርዝረው ያቀርባሉ:: ጸሐፊው የመጽሐፉ መመሪያ በማድረግ ይዞት የሚጓዘው ሐሳብ፣ የእስራኤልና የነገሥታቷ በጎነት የሚረጋገጠው እግዚአብሔር በሙሴ አማካይነት የሰጠውን የቃል ኪዳን ግዴታ ተወጥተውት ሲገኙ ብቻ መሆኑን የሚገልጽ ነው::

ጸሐፊው የእስራኤልን ነገሥታት አገዛዝ ታሪክ ሲያቀርብ፣ ትኵረቱ የዘመኑ የታሪክ ጥናትና ምርምር በሚጠይቀው መሠረት ማኅበራዊ፣ ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ መመሪያዎችን ግንዛቤ ውስጥ ያስገባ እንዳልነበር ግልጽ ነው:: ጸሐፊው የተለያዩ ነገሥታትን አገዛዝ በተመለከተ ይበልጥ ዝርዝር ጕዳዮችን ለማግኘት ይረዳው ዘንድ በመደጋገም ሌሎች የታሪክ ምንጮችን ለአንባቢው ይጠቅስለታል:: (ለምሳሌ 11፥41፤ 14፥19:29፤ 15፥7:31፤ 16፥5:14:20:27 ይመ)፤ የነገሥታቱን አገዛዝ በታላቅ ትኵረት የሚመለከተው፣ ከፍ ያለ ዋጋም የሚሰጠው ከማኅበራዊ፣ ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታው አንጻር ሳይሆን፣ በእነርሱና በእግዚአብሔር መካከል ካለው ቃል ኪዳን ጋር በማያያዝ ነው:: መደበኛ በሆነ የፖለቲካ ታሪክ ጸሐፊ አመለካከት ሲታይ፣ ዖምሪ ከፍ ያለ ግምት ከሚሰጣቸው ከሰሜኑ መንግሥት ገዦች እንደ አንዱ የሚቈጠር ነው:: ጠንካራ ሥርወ መንግሥት መሥርቶአል፤ ሰማርያንም የሰሜኑ መንግሥት መናገሻ ያደረጋት እርሱ ነው:: በሞዓብ የድንጋይ ሰሌዳ ግኝት መሠረት የሰሜኑ መንግሥት ሞዓባውያንን ድል ያደረገው በዖምሪ ዘመነ መንግሥት መሆኑ ተረጋግጦአል:: ዖምሪ ከሞተ ከብዙ ዓመት በኋላ፣ የአሦር ገዦች ኢዩን "የዖምሪ ልጅ" እንደ ሆነ ቈጥረውታል፤ ይህን ያደረጉበት ምክንያት አንድም በስሕተት ሊሆን ይችላል፤ አሊያም ደግሞ እንደ አገራቸው ወግና ሥርዐት አንዱ ንጉሥ ዐልፎ ሌላው ሲተካ፣ በዚሁ ዐይነት ስም መጠራቱ የተለመደ ስለ ነበር ይህንኑ ተከትለው ሊሆን ይችላል:: ዖምሪ ምንም እንኳ በፖለቲካ አመራር የታወቀ ንጉሥ ቢሆንም፣ ታሪኩ የተጠቃለለው በስድስት ቍጥሮች ብቻ ነው (16፥23-28)፤ ለዚያውም የሚደመደመው "በእግዚአብሔር ፊት ክፉ አደረገ፤ ከእርሱ አስቀድሞ ከነበሩት ሁሉ ይልቅ እጅግ ከፋ" (16፥25) ብሎ ነው:: የሰሜኑ መንግሥት በፖለቲካም በኢኮኖሚም ከፍተኛ ደረጃ ላይ ደርሶ በነበረበት ጊዜ የነበረው ንጉሥ ሮብዓም ዳግማዊም ታሪክ የተወሣው እንደዚሁ ባጭሩ ነው (2ነገ 14፥23-29)::

ጸሐፊው ትኵረት የሰጠው ለፖለቲካው ወይም ለኢኮኖሚው ጠቀሜታ ሳይሆን፣ ከቃል ኪዳን ጋር ለተያያዘው ጕዳይ መሆኑን፣ ከይሁዳ ንጉሥ ከኢዮስያስ ታሪክ መረዳት ይቻላል:: በታሪኩ ውስጥ ስለ መጀመሪያው የአገዛዝ ዘመኑ የተጻፈ ምንም ነገር የለም፤ ይሁን እንጂ በነገሠ በ18 ዓመቱ (2ነገ 22፥3-23:28) ስላደረገው የማሻሻል ሥራና ከፍተኛ ግምት ስለ ሰጠው ስለ ቃል ኪዳኑ መታደስ በዝርዝር ተገልጾአል:: ኢዮስያስ ወደ መጊዶ ሄዶ የግብፁን ንጉሥ ፈርዖን ኒካውን ለመውጋት ስለ ተነሣሣበት ወይም ከመልክዐ ምድሩ አቀማመጥና ከወቅቱ የፖለቲካ ነፋስ ጋር በተያያዘ ፊቱን በአንድ ጊዜ ከአሦር ወደ ባቢሎን እንዲያዞር ስለ ተገፋፋበት ምክንያት የተወሣ አንዳች ነገር የለም (የ2ነገ 23፥29-30 ማብ ይመ)::

በመጽሐፈ ነገሥት አንደኛና በመጽሐፈ ነገሥት ሁለተኛ ከፍተኛ ትኵረት የተሰጠው በዘመነ መንግሥታቸው የእግዚአብሔር ቃል ኪዳን እንዲናቅና እንዲቃለል ወይም እንዲጠበቅ ላደረጉ ነገሥታት፣

ወይም ነገሥታቱና የእግዚአብሔር ነቢያት ተባብረው ለፈጸሙት ነው:: የእግዚአብሔር ቃል ኪዳን እንዲ ናቅና፣ እንዲቃለል ካደረጉት ነገሥታት የዖምሪ ልጅ አክዓብ አንዱ ነው (17፥1-22:39):: ስለ የዖምሪ ዘመነ መንግሥት ጸሐፊው ሰፋ ያለ ነገር አቅርቦአል፤ ይህ የሆነበት ምክንያት እስከዚህ የሚደነቅና፣ አንቱ የሚባል የፖለቲካ ጉዳይ ተከናውኖበት ሳይሆን፣ በሰሜኑ መንግሥት የተጀመረው ለእግዚአብሔር ቃል ኪዳን ታማኝ መሆንና ይህንኑ ታማኝነትም በዘላቂነት የመጠበቅ ጉዳይ በእርሱ ዘመነ መንግሥት አባብቂኝ ውስጥ ስለ ገባ ነው:: በመጨረሻም የአክዓብ ሚስት ኤልዛቤል ያሳደረችው የአረማውያን አምልኮና ልማድ ተጽዕኖ በልጇ በጎቶልያ አማካይነት ተባብሶ በይሁዳ ምድር ያሉትን የዳዊት ቤት ወገኖች ጨርሶ ለማጥፋት ምንም ያህል አልቀረውም ነበር (2ነገ 11፥1-3 ይመ)::

በተመሳሳይ ሁኔታ ስማቸው ከሚጠቀሱት ሰዎች አንዱ ምናሴ ነው (2ነገ 21፥1-18)፤ እዚህም ላይ በአጽንዖት ለማሳየት የተፈለገው ቃል ኪዳኑ መቸውንም ገሸሽ መደረጉን እንጂ፣ በዚያን ዘመን በአሦ ርና በግብፅ መንግሥታት መካከል በተነሣው ግጭት ውስጥ ምናሴ ስለ መሳተፉ የተወሳ ነገር የለም (ይህኛው ድርጊት ክብደት አግኝቶ በአሦራውያን የታሪክ መዝገብ ገብቶ ሲገኝ በመጽሐፈ ነገሥት ሁለተኛ ግን ቦታ አልተሰጠውም):: ምናሴ የአባቶቹን አምላክ ትቶ ወደ አሕዛብ አምልኮ ጭልጥ ብሎ የመሄዱ ጉዳይ እግዚአብሔርን ክፉኛ አስቈጥቶታል፤ የይሁዳን ሕዝብ ወደ ምርኮ እንዲሄድ፣ ምር ኮውም እንዲፈጥን አድርጎአል (2ነገ 21፥10-25፤ 23፥26-27):: በአወንታዊ ጐኑ ደግሞ ሕዝቅያስ (2ነገ 18፥1-20፥21) እና ኢዮስያስ (2ነገ 22፥1-23፥29) ቃል ኪዳኑን በማደስ ረገድ በተጫወቱት ሚና በጽሑፉ ውስጥ ሰፊ ቦታ ተሰጥቶአቸዋል::

ለእግዚአብሔር አምላክ ፍጹም ታማኝ ሆነው የተገኙ እነዚህ ሁለቱ ነገሥታት ብቻ በመሆናቸው፣ ጸሐፊው ከፍ ያለ ግምት ሰጥቶአቸዋል (2ነገ 18፥3፤ 22፥2):: የሰሜኑ መንግሥት ነገሥታት ሁሉ በእግዚአብሔር ዘንድ የተጠላ ክፉ ድርጊት ስለ መፈጸማቸውና እስራኤልን እንዲበድሉ ባሳተው በኢዮ ርብዓም መንገድ ስለ መሄዳቸው መጻፉ ተገቢ ነው (ለምሳሌ 16፥26:31፤ 22፥52፤ 2ነገ 3፥3፤ 10፥29 ይመ):: የእስራኤል መንግሥት ለሁለት በተከፈለ ማግስት ኢዮርብዓም በቤቴልና በዳን የወርቅ ጥጃ ምስል አቁሞ እንዲመለክ አድርጎአል (12፥26-33፤ 13፥1-6 ይመ)::

ጸሐፊው፣ እስራኤል በሲና ለተሰጠው ቃል ኪዳን መታዘዟ ወይም አለመታዘዟ ወደ ፊት ለሚጠ ብቃት በጎም ሆነ ክፉ ነገር ወሳኝነት ያለው መሆኑን ይገልጣል:: በዚህም ብቻ ሳይወሰን የዳዊት ቤት (ሥርወ መንግሥት) ለዘላለም ጸንቶ እንደሚኖር በቃል ኪዳን የተሰጠው ተስፋ የኋላ ኋላ በትክክል የሚፈጸም መሆኑን በሚገባ ተረድቶታል፤ ይህም በተለይ እግዚአብሔር ለዳዊት ተስፋ ገብቶለት የነበ ረውን "መብራት" (11፥36፤ 15፥4፤ 2ነገ 8፥19 ይመ፤ እንዲሁም የ2ሳሙ 21፥17 ማብ ይመ) የሚያ ስታውስ ነው:: እንዲሁም ለዳዊት ስለ ተሰጠው ተስፋ አጠቃላይ ማብራሪያ ይሰጣል (8፥20:25)፤ ወደ ፊት በይሁዳ ስለሚከሠተው ልዩ የታሪክ ዕድገት ውጤትም ይገልጣል (11፥12-13:32፤ 2ነገ 19፥34፤ 20፥6):: በተጨማሪም ጸሐፊው የዳዊትን ሕይወትና የአገዛዙን ዘመን ወደ ፊት ለሚነሡት ነገሥታት ሕይ ወት ዋና መለኪያ አድርጎ ተጠቅሞበታል (ለምሳሌ 9፥4፤ 11፥4:6:33:38፤ 14፥8፤ 15፥3:5:11፤ 2ነገ 16፥2፤ 18፥3፤ 22፥2 ይመ)::

በተነገረው ትንቢትና በነገሥታቱ አገዛዝ የታሪክ ዕድገት ሂደት ውስጥ በተፈጸመው መካከል ባለው ግንኙነት ላይ አጽንዖት ማድረጉ የመጽሐፈ ነገሥት አንደኛና የመጽሐፈ ነገሥት ሁለተኛ መሠረታዊ ባሕርይ ነው:: አስቀድሞ ተነግሮ በኋላ የተፈጸመ ቢያንስ በዐሥራ አንድ ቦታ ላይ በተለያየ ሁኔታ የተጠቀሰ አንድ ትንቢት መኖሩ ተጽፎአል (ለምሳሌ 2ሳሙ 7፥13: እና 1ነገ 12፥15፤ 1ነገ 13 እና 2ነገ 23፥16-18 ይመ):: የዚህ አጽንዖት ውጤት መንግሥታዊ ታሪክ የአጋጣሚ ነገሮች ስብስብ ወይም የሰዎች ጥረትና ድካም ሆኖ እንዳልቀረበ ያሳያል:: ታሪኩ ሁሉን የሚያውቀውና ሁሉን ማድረግ የሚችለው እግዚአብሔር፣ በኪነ ጥበቡ የገለጠው የወደፊቱ የእስራኤል ዕድል ፈንታ ታሪክ ነው:: እርሱም ታሪክን ሁሉ የማንም አእምሮ መርምሮ ሊደርስበት በማይችል ዕቅዱና ዐላማው መሠረት እንደ ፈለገው የሚመራ የእስራኤል ቃል ኪዳን ጌታ ነው (8፥56፤ 2ነገ 10፥10 ይመ)::

ጸሐፊው እንደዚሁ የእግዚአብሔር አገልጋይ ስለ ሆኑት ስለ ነቢያቱ ማንነት (ታላቅነት) በአ ጽንዖት የሚለው አለ:: ነገሥታቱና ሕዝቡ ተመልሰው ለቃል ኪዳኑ ታማኝ ይሆኑ ዘንድ (2ነገ 17፥13)፣ ጥሪ እንዲያደርጉ እግዚአብሔር እንደ እነዚህ ያሉትን ነቢያት ለረጅም ጊዜ በተከታታይ ላከ:: የእነርሱ ማስጠንቀቂያና ተግሣጽ አብዛኛውን ጊዜ ሰሚ ጆሮ ሳያገኝ፣ በጭንጫ መሬት ላይ እንደ ወደቀ ዘር ሆነ፤ ከእነዚህ ነቢያት መካከል የአብዛኞቹ ስም በመጻሕፍተ ነገሥት አንደኛና ሁለተኛ ውስጥ ተጠ ቅሶአል (ለምሳሌ አኪያ 11፥29-40፤ 14፥5-18፤ ሸማያ 12፥22-24፤ ሚክያስ 22፥8-28፤ ዮናስ 2ነገ 14፥25፤ ኢሳይያስ 2ነገ 19፥1-7: 20-34፤ ነቢይቱ ሕልዳና 2ነገ 22፥14-20 ይመ)፤ ይሁን እንጂ በእነዚህ መጻሕፍት ውስጥ የተለየ ትኵረት የተሰጠው ለኤልያስና ለኤልሳዕ አገግሎት ነው (1ነገ 17-19፤ 2ነገ 1-13)::

በሁለቱ መጻሕፍት የተንጸባረቀው ሐሳብ በሕዝቡ ላይ ለደረሰው ውርደት ምክንያቱ ቃል ኪዳኑን ደጋግመው በማፍረስ ያሳዩት ግትርነት መሆኑን፣ በምርኮ ለነበሩት ሰዎች ለማሳየት ሲባል እንደ ተጻፈ ይገልጣል:: እግዚአብሔር እጅግ ታግሦ ከቈየ በኋላ ይህን ምርኮ በሕዝቡ ላይ በማምጣት፣ ከመጀመሪያ አንሥቶ ማስጠንቀቂያ አድርጎት የነበረውን የቃል ኪዳኑን ርግማን አወረደባቸው (ዘሌ 26፥27-45፤ ዘዳ 28፥64-68 ይመ):: ይህ ርግማን በሰሜኑ መንግሥት ላይ በትክክል ስለ መፈጸሙ በ2ነገ 17፥7-23፤

18፥10-12፤ በደቡቡ መንግሥት ላይም ስለ መድረሱ በ2ነገ 21 ላይ በግልጽ ተቀምጦአል:: ኢዮስያስ በደቡቡ መንግሥት ላደረገው ተሐድሶ ይህን ያህል ትኩረት አልተሰጠውም (2ነገ 23፥26-27፤ 24፥23 ይመ)::

ባጭሩ መጽሐፉ ወደ ኋላ ሄዶ ያለፈውን የእስራኤልን ታሪክ የሚተነትን ነው:: ሰማርያና ኢየሩሳሌም እንዲሁም ኢየሩሳሌምና ይሁዳ እንዴት እንደ ጠፉ፣ ተማርኮ መሄድ የሚያስከትለውንም መራራ የሕይወት ጽዋ እንዴት እንደ ተጋቱት አንድ ባንድ ይገልጻል፤ ይህም ቢሆን ለወደፊቱ ተስፋ የለም ማለት አይደለም፤ እስራኤላውያን ስለ ወደፊቱ ነገር ተስፋ ማድረግ እንጂ ተስፋ መቊረጥ እንደማይገባቸው ለማስገንዘብ ሲል፣ ለዳዊት የተሰጠውን ተስፋ መጽሐፉ ደጋግሞ ያነሣዋል:: ከዚህ ጋር በተያያዘም አራቱ የመጽሐፉ የመጨረሻ ቊጥሮች (2ነገ 25፥27-30) የሚያወሱት የዮአኪን ከባቢሎን እስር ቤት መውጣትና በቤተ መንግሥቱም ያገኘው የክብር ስፍራ እንደ ተጨማሪ ዋና ቊም ነገር ተደርገው ተወስደዋል:: እግዚአብሔር ለዳዊት ቤት የገባውን ቃል ኪዳን በታማኝነት ስለሚፈጽም መጪው ዘመን ለዚሁ ተግባር ክፍት ሆኖ ይቈያል::

ጸሐፊው ምንም እንኳ ወደ ባቢሎን ተማርኮ የተወሰደ ሰው ለመሆኑ ቅንጣት ታህል የሚያጠራጥር ባይሆንም፣ ይህን ታሪክ በጻፈበት ዘመን ሰሜኑ የእስራኤል መንግሥት ከወደቀ፣ ሕዝቡም ከተበታተነ አንድ ምእት ዓመት አስቈጥሮአል፤ ነገር ግን ጸሐፊው ልዩ ትኩረት የሰጠው የኪዳን ሕዝብ ለሆነው ለእስራኤል ሁሉ መሆኑን መረዳት አስፈላጊ ነው:: ጸሐፊውም ሆነ ነቢያቱ የእስራኤልን መንግሥት ከሁለት መከፈል፣ ዐሥሩ ነገዶች እስከ መጨረሻው ተቈራርጠው ከቀሩት ሁለቱ ነገዶች እንደ ተለዩ አድርገው አይመለከቱትም:: ከዚያ በፊት የነበረውን የሰሜኑን መንግሥት ሕዝብ መማረክም፣ ከወደፊቱ የእስራኤል ተስፋ ወጥተው እስከ ወዲያኛው የተለዩበት አድርገውም አያዩትም::

## የታሪኮችና የድርጊቶች ቅደም ተከተል

መጻሕፍተ ነገሥት አንደኛና ሁለተኛ ለአንባቢ ጠቃሚ የሆኑ፣ ብዙ መረጃዎችን የሚሰጡ መጽሐፎች ናቸው:: በሁለቱ መጽሐፍት ተጽፎ የምናገኘው እያንዳንዱ ንጉሥ ምን ያህል ዘመን እንደ ገዛ ብቻ ሳይሆን፣ አንዱ የእስራኤል መንግሥት ከሁለት ተከፍሎ በነበረበት ጊዜ፣ አንዱ ንጉሥ በሰሜኑ ወይም በደቡቡ ላይ ገና መንገሥ ሲጀምር የዘመነ መንግሥቱ ዕድሜ አቈጣጠር በሌላው ክፍል ከሚገዛው ንጉሥ የአገዛዝ ዘመን ጋር ተቀናጅቶ የሚቈጠር መሆኑንም ጭምር ነው፤ ንጉሡ በትረ መንግሥቱን ሲጨብጥ (ሥልጣን ላይ ሲወጣ) የነበረውም ዕድሜ ዐልፎ ዐልፎ ተጽፎ ይገኛል::

የመጽሐፍ ቅዱሱን ጠቃሚ መረጃዎች ከአሦር ተከታታይ የታሪክ መዛግብት ጋር በማገናዘብ 853 ዓ.ቅ.ክ.ን አክዓብ የሞተበት ዘመን፣ 841 ዓ.ቅ.ክ.ን ደግሞ ኢዩ መግዛት የጀመረበት ዘመን እንደ ነበረ መወሰን ይቻላል:: አክዓብና ኢዩ ከአሦር ንጉሥ ከስልምናሶር ሣልሳዊ ጋር ግንኙነት ያደረጉባቸውን ዓመታት፣ ቀኖችንም ከአሦራውያን መዛግብት የተገኘውን የፀሐይ ግርዶሽ ቀን መሠረት በማድረግ በትምህርተ ከዋክብት ጥናት ስሌት መንገድ ለይቶ ማስቀመጥ ይቻላል:: እንግዲህ እነዚህን ነገሮች መነሻ ነጥብ አድርጎ በመያዝ፣ የእስራኤልንና የይሁዳን ነገሥታት መስመር ተከትሎ ወደ ኋላም ወደ ፊትም በመሄድ፣ በእያንዳንዱ ንጉሥ ታሪካዊ ድርጊት የተፈጸመባቸውን ዕለታት ለይቶ ማስቀመጥ ይቻላል:: በዚሁ መሠረት በ930 ዓ.ቅ.ክ. የእስራኤል መንግሥት ከሁለት የተከፈለበትን ጊዜ፣ ከ722-721 ዓ.ቅ.ክ. ሰማርያ በአሦር መንግሥት እጅ የወደቀችበትን ጊዜ፣ እንዲሁም በ586 ዓ.ቅ.ክ. ኢየሩሳሌም በባቢሎናውያን እጅ የወደቀችበትን ዕለት ለይቶ ማስቀመጥ ይቻላል::

እርስ በርስ የተያያዙት የይሁዳና የእስራኤል ነገሥታት የአገዛዝ ዘመናት መረጃዎች በቀላሉ ሊደረስባቸው የማይችሉ አንዳንድ ችግሮች እንዳሏቸው፣ ከብዙ ጊዜ በፊት አንሥቶ የሚታወቅ ነገር ነው፤ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ግን የአንዱ ንጉሥ አገዛዝ ከሌላው ጋር በመደረቡ፣ አባትና ልጅ በአንድነት በመግዛታቸው፣ አንድ ንጉሥ በይፋ የነገሠበት ዘመን በውል ተለይቶ ባለመታወቁ፣ አንድ ንጉሥ በሚነግሥበት በመጀመሪያው ዓመት አቈጣጠር ረገድ ባለው ልዩነት ከእነዚህ ችግሮች አብዛኞዎቹ ተወግደዋል (ለምሳሌ የ15፥33፤ የ2ነገ 8፥25 ማብ ይመ)::

## የመጽሐፉ ይዘት

መጻሕፍተ ነገሥት አንደኛና ሁለተኛ ከዳዊት ዘመነ መንግሥት ፍጻሜ እስከ ባቢሎን ምርኮ ድረስ ያለውን የእስራኤል ነገሥታት ታሪክ አንድ ባንድ ይዘረዝራሉ:: የሰሎሞን ዘመነ መንግሥት ታሪክ በስፋት ከተወሣ በኋላ፣ የመንግሥቱን ለሁለት መከፈል የሚተርከው ክፍል ይቀጥላል፤ ከዚያም በሁለቱ መንግሥታት መካከል እንደ ገና እርስ በርሱ እየተቈራኘ የሚሄደው የግንኙነት ሥዕል ይቀርባል:: በሰሜኑ ክፍል የነበረው የነገሥታቱ አገዛዝ አለመረጋጋትና ዐመፅ የሚጠናወተው ነበር:: መንግሥቱ ለሁለት ከተከፈለበት ከ930 ዓ.ቅ.ክ. አንሥቶ፣ ሰማርያ በአሦር መንግሥት እጅ እስከ ወደቀችበት እስከ 722-721 ዓ.ቅ.ክ. ድረስ፣ ለሁለት መቶ ሃያ ዓመት ያህል ከዘጠኝ ሥርወ መንግሥት የወጡ ሃያ ነገሥታት ተፈራርቀውበታል:: በደቡቡም መንግሥት እንዲሁ ሃያ ነገሥታት ገዝተዋል:: ጎቶልያ ጣልቃ ገብታ ለጥቂት ጊዜ ከማጨናገፏ በስተቀር ሁሉም የዳዊት ዘሮች ነበሩ:: የእስራኤል መንግሥት ለሁለት ከተከፈለ በኋላ፣ የደቡቡ መንግሥት ኢየሩሳሌም በባቢሎን መንግሥት እጅ እስከ ወደቀችበት እስከ 586 ዓ.ቅ.ክ. ድረስ ለ345 ዓመት ዘልቆአል::

**አስተዋፅኦ፤**

የመጽሐፈ ነገሥት አንደኛና የመጽሐፈ ነገሥት ሁለተኛ አስተዋፅኦ፣ ከሚገልጻቸው ዋና ዋና ታሪካዊ ወቅቶችና እንዲሁም ከኤልያስና ከኤልሳዕ አገግሎቶች ጋር ይዘቶቹን በማዛመድ በስፋት ሊ ቀርብ ይችላል።

1. የሰሎሞን ዘመነ መንግሥት (1፥1-12፥24)
   - ሀ. ሰሎሞን በአባቱ ዙፋን መቀመጡ (1፥1-2፥12)
   - ለ. የሰሎሞን መንግሥት መጽናቱ (2፥13-46)
   - ሐ የሰሎሞን ጥበብ (ም 3)
   - መ. የሰሎሞን መንግሥት ገጽታ (ም 4)
   - ሠ. የሰሎሞን ቤተ መቅደስ መታነጽ (5፥1-9፥9)
     1. ቤተ መንግሥቱን ለመሥራት የተደረገ ዝግጅት (ም 5)
     2. የቤተ መቅደሱ ግንባታ (ም 6)
     3. የቤተ መንግሥቱ ግንባታ (ም 7፥1-12)
     4. ለቤተ መቅደሱ ሥራና አገልግሎት የዋሉ ዕቃዎች (7፥13-51)
     5. የቤተ መቅደሱ መመረቅ (ም 8)
     6. የእግዚአብሔር መልስና ማስጠንቀቂያ (9፥1-9)
   - ረ. የሰሎሞን መንግሥት ገጽታ (9፥10-10፥29)
   - ሰ. ሰሎሞን የፈጸማቸው ክፉ ድርጊቶች (11፥1-13)
   - ሸ. የሰሎሞን መንግሥት ውድቀት ዋዜማ (11፥14-43)
   - ቀ. ሮብዓም በአባቱ እግር መተካቱ (12፥1-24)
2. እስራኤልና ይሁዳ ከቀዳማዊ ኢዮርብዓም /ሮብዓም እስከ አክዓብ/አሳ (12፥25-16፥34)
   - ሀ. የእስራኤል ንጉሥ ቀዳማዊ ኢዮርብዓም (12፥25-14፥20)
   - ለ. የይሁዳ ንጉሥ ሮብዓም (14፥21-31)
   - ሐ. የይሁዳ ንጉሥ አብያ (15፥1-8)
   - መ. የይሁዳ ንጉሥ አሳ (15፥9-24)
   - ሠ. የእስራኤል ንጉሥ ናዳብ (15፥25-32)
   - ረ. የእስራኤል ንጉሥ ባኦስ (15፥33-16፥7)
   - ሰ. የእስራኤል ንጉሥ ኤላ (16፥8-14)
   - ሸ. የእስራኤል ንጉሥ ዘምሪ (16፥15-20)
   - ቀ. የእስራኤል ንጉሥ ዘንበሪ (16፥21-28)
   - በ. የእስራኤል ንጉሥ አክዓብ (16፥29-34)
3. ከአክዓብ/አሳ እስከ ኢዮራም/ኢዮሣፍጥ ድረስ ባለው ጊዜ የኤልያስና የኤልሳዕ እንዲሁም የሌሎቹ ነቢያት አገልግሎት (17፥1-2ነገ 8፥15)
   - ሀ.ኤልያስና ሌሎች ነቢያት በአክዓብ ዘመነ መንግሥት (17፥1-22:40)
     1. ኤልያስና የድርቁ ዘመን (ም 17)
     2. ኤልያስ በቀርሜሎስ ተራራ ላይ (ም 18)
     3. ኤልያስ ወደ ኮሬብ መሸሹ (ም 19)
     4. አክዓብ ወልደ አዴርን ሳይገድለው በመቅረቱ በነቢይ መገሠጹ (ም 20)
     5. የናቡቴን የወይን ተክል ቦታ በመቀማቱ ኤልያስ አክዓብን መገሠጹ (ም 21)
     6. ሚክያስ አክዓብ እንደሚሞት የተነበየው ትንቢትና የትንቢቱ መፈጸም (22፥1-40)
   - ለ. የይሁዳ ንጉሥ ኢዮሣፍጥ (22፥41-50)
   - ሐ. የእስራኤል ንጉሥ አካዝያስ፣ የኤልያስ የመጨረሻ ትንቢት (22፥51-2ነገ 1፥18)
   - መ. ኤልያስ ወደ ሰማይ መወሰዱ፤ ኤልሳዕ በኤልያስ እግር መተካቱ (2ነገ 2፥1-18)
   - ሠ. ኤልሳዕ በኢዮራም ዘመነ መንግሥት (2ነገ 2፥19-8፥15)
     1. ኤልሳዕ በመጀመሪያ ያደረጋቸው ታምራት (2፥19-25)
     2. ኤልሳዕ በሞዓብ ላይ በተደረገው ዘመቻ ወቅት (ም 3)
     3. ኤልሳዕ ለእስራኤል ችግረኞች ያበረከተው አገልግሎት (ም 4)
     4. ኤልሳዕ ንዕማንን መፈወሱ (ም 5)
     5. ኤልሳዕ ከነቢያት አንዱን መታደጉ (6፥1-7)
     6. ኤልሳዕ ኢዮራምን ከአራማውያን ወራሪዎች መታደጉ (6፥8-23)
     7. ኤልሳዕ በተናገረው ትንቢት መሠረት የአራማውያን ወረራ መቀስቀሱ (6፥24-7፥20)
     8. የሱናማዊቷ ሴት ርስት መመለሱ (8፥1-6)
     9. አዛሄል እስራኤልን እንደሚያስጨንቅ ኤልሳዕ ትንቢት መናገሩ (8፥ 7-15)

4. እስራኤልና ይሁዳ ከኢዮራም ዘመነ መንግሥት እስከ እስራኤል ምርኮ (2ነገ 8፥16–17፥41)
   ሀ. የይሁዳ ንጉሥ ኢዮራም (8፥16-24)
   ለ. የይሁዳ ንጉሥ አካዝያስ (8፥25-29)
   ሐ. የኢዩ ዐመፅና አገዛዙ (ምዕ 9-10)
      1. ኤልሳዕ ኢዩ እንዲቀባ ማዘዙ (9፥1-13)
      2. ኢዩ ኢዮራምንና አካዛያስን ማስገደሉ (9፥14-29)
      3. ኢዩ ኤልዛቤልን ማስገደሉ (9፥30-37)
      4. ኢዩ የአክዓብን ቤተ ሰብ ማሳረዱ (10፥1-17)
      5. ኢዩ የበአልን አምልኮ ማስወገዱ (10፥18-36)
   መ. ጎቶልያና የይሁዳ ንጉሥ ኢዮአስ፣ የቤተ መቅደስ መታደስ (ም 11-12)
   ሠ. የእስራኤል ንጉሥ ኢዮአካዝ (13፥1-9)
   ረ. የእስራኤል ንጉሥ ዮአስ፤ የኤልሳዕ የመጨረሻ ትንቢት (13፥10-25)
   ሰ. የይሁዳ ንጉሥ አሜስያስ (14፥1-22)
   ሸ. የእስራኤል ንጉሥ ዳግማዊ ኢዮርብዓም (14፥23-29)
   ቀ. የይሁዳ ንጉሥ ዓዛርያስ (15፥1-7)
   በ. የእስራኤል ንጉሥ ዘካርያ (15፥8-12)
   ተ. የእስራኤል ንጉሥ ሰሎም (15፥13-16)
   ቸ. የእስራኤል ንጉሥ ምናሔም (15፥17-22)
   ኀ. የእስራኤል ንጉሥ ፋቂስያስ (15፥23-26)
   ነ. የእስራኤል ንጉሥ ፋቁሔ (15፥27-31)
   ኘ. የይሁዳ ንጉሥ ኢዮአታም (15፥32-38)
   አ. የይሁዳ ንጉሥ አካዝ (ም 16)
   ከ. የእስራኤል ንጉሥ ሆሴዕ (17፥1-6)
   ኸ. የእስራኤል መማረክ፣ በምድሪቱ ላይ ዳግም መስፈራቸው (17፥7-41)
5. ይሁዳ ከሕዝቅያስ ዘመነ መንግሥት እስከ ባቢሎን ምርኮ (2ነገ 18-25)
   ሀ. ሕዝቅያስ (ም 18-20)
      1. የሕዝቅያስ መልካም አገዛዝ (18፥1-8)
      2. ይአሦራውያን ማስፈራራት፤ የእግዚአብሔር ትድግና (18፥9-19፥37)
      3. የሕዝቅያስ መታመም፣ ከባቢሎን ጋር ያደረገው ትብብር (ም 20)
   ለ. ምናሴ (21፥1-18)
   ሐ. አሞጽ (21፥19-26)
   መ. ኢዮስያስ (22፥1-23፥30)
      1. የቤተ መቅደሱ መታደስ፣ የሙሴ ሕግ መጽሐፍ መገኘቱ (ም 22)
      2. የቃል ኪዳኑ መታደስ፤ የኢዮአስ ዘመነ መንግሥት ፍጻሜ (23፥1-30)
   ሠ. ኢዮአክስ ወደ ግብፅ መሰደዱ (23፥31-35)
   ረ. ኢዮአቄም፤ የመጀመሪያው የባቢሎናውያን ወረራ (23፥36-24፥7)
   ሰ. ኢዮአቄም፤ ሁለተኛው የባቢሎናውያን ወረራ (24፥8-17)
   ሸ. ሴዴቅያስ (24፥18-20)
   ቀ. ባቢሎናውያን ይሁዳን ማርከው መውሰዳቸው (25፥1-21)
   በ. የአይሁድ ቅሬታዎች ወደ ግብፅ መወሰዳቸው (25፥22-26))::
   ተ. ዮአኪን በባቢሎን ከፍ ከፍ ማለቱ (25፥27-30)

## አዶንያስ ለመንገሥ እንደ ፈለገ

1 ንጉሥ ዳዊት እየሸመገለና ዕድሜው በጣም
እየገፋ ሲሄድ፣ ልብስ ቢደራርቡለትም
እንኳ ሊሞቀው አልቻለም። 2ስለዚህ አገል
ጋዮቹ፣ "ንጉሡን የምትንከባከብና የምታገለ
ግል ወጣት ድንግል እንፈልግ፤ እርሷም
ጌታችን ንጉሡ እንዲሞቀው በጉኑ ትተኛ
ለች" አሉት።
3ከዚያም በመላው እስራኤል ቈንጆ ልጃ
ገረድ ፈልገው ሱነማዊቷን አቢሳን አገኙ፤
ለንጉሡም አመጡለት። 4ልጃገረዲቱ እጅግ
ቈንጆ ነበረች፤ ንጉሡንም ትንከባከበውና
ታገለግለው ነበር፤ ንጉሡ ግን ከእርሷ ጋር
ግንኙነት አልነበረውም።
5በዚህ ጊዜ ከአጊት የተወለደው አዶን
ያስ፣ "እነግሣለሁ" ብሎ ተነሣ፤ ስለዚህ ሠረ
ገሎችንና[ሀ] ፈረሶችን እንዲሁም ከፊት ከፊቱ
የሚሄዱ አምሳ ሰዎችን አዘጋጀ። 6አባቱም፣
"ለምን እንዲህ ታደርጋለህ?" ብሎ ገሥ
ጾት አያውቅም ነበር፤ አዶንያስም እጅግ
መልከ መልካምና የአቤሴሎም ታናሽ ወን
ድም ነበር።
7አዶንያስ ከጽሩያ ልጅ ከኢዮአብና ከካ
ህኑ ከአብያታር ጋር ተመካከረ፤ እነርሱም
ድጋፋቸውን ሰጡት። 8ነገር ግን ካህኑ
ሳዶቅ፣ የዮዳሄ ልጅ በናያስ፣ ነቢዩ ናታን፣
ሳሚ፣ ሬሲና[ለ] የዳዊት የክብር ዘበኞች
ከአዶንያስ ጋር አልተባበሩም።
9ከዚያም አዶንያስ በዓይንሮጌል አቅራቢያ
ባለው የዞሔልት ድንጋይ አጠገብ በጎችን፣
በሬዎችንና የሰቡ ጥጆችን ሠዋ፤ ወንድሞቹን
ሁሉ፣ የንጉሡን ልጆች እንዲሁም የቤተ
መንግሥቱ ሹማምት የነበሩትን የይሁዳ
ሰዎች ሁሉ ጠራ፤ 10ይሁን እንጂ ነቢዩ
ናታንንም ሆነ በናያስን፣ የክብር ዘበኞቹ
ንም ሆነ ወንድሙን ሰሎሞንን አልጠራም።
11ከዚያም ናታን የሰሎሞንን እናት ቤር
ሳቤህን እንዲህ አላት፤ "ጌታችን ዳዊት
ሳያውቅ የአጊት ልጅ አዶንያስ መንገሡን
አልሰማሽምን? 12አሁንም የራስሽንና የልጅ
ሽን የሰሎሞንን ሕይወት እንዴት ማዳን
እንደምትችዪ ልምከርሽ፤ 13ወደ ንጉሥ ዳዊት
ሂጂና፣ 'ጌታዬ ንጉሥ ሆይ፤ ልጅሽ ሰሎ
ሞን ከእኔ ቀጥሎ ይነግሣል፤ በዙፋኔም
ይቀመጣል' ብለህ 'ለእኔ ለአገልጋይህ አል
ማልህልኝም ነበር? ታዲያ አዶንያስ የነገ
ሠው ስለ ምንድን ነው?' በዪው፤ 14አንቺ
እዚያው ሆነሽ ይህን በምትነግሪው ጊዜ እኔ
እገባና ያልሽው ትክክል መሆኑን አረጋግ
ጣለሁ።"
15ስለዚህ ቤርሳቤህ፣ ሱነማዊቷ አቢሳ
በምታገለግልበት ክፍል አርጅና የተጫጫነ
ውን ንጉሥ ለማነጋገር ሄደች። 16ቤርሳቤ
ህም ለጥ ብላ እጅ ከነሣች በኋላ እፊቱ
በጒልበቷ ተንበረከከች።
ንጉሡም፣ "ምን ትፈልጊያለሽ?" ሲል ጠየ
ቃት።

[ሀ]5 ወይም *ሠረገለኞች* ተብሎ ሊተረጐም ይችላል።
[ለ]8 ወይም *እና ጓደኞቹ* ተብሎ ሊተረጐም ይችላል።

1፥3 ቍ15ኢሱ19፥18፤2ሳሙ37፤1ነገ2፥17:22
1፥5 1ሳሙ8፥11፤2ሳሙ3፥4
1፥6 1ሳሙ3፥13
1፥7 1ሳሙ22፥20፤2ሳሙ2፥13:18
1፥8 1ሳሙ2፥35፤2ሳሙ7፥2፤8፥17:18፤23፥8፤1ነገ4፥18
1፥9 2ሳሙ17፥17፤1ዜና29፥24
1፥10 ቍ26፤2ሳሙ12፥24
1፥11 2ሳሙ3፥4፤12፥24
1፥12 ምሳ15፥22
1፥13 ቍ17:30
1፥15 ቍ3

*1፥1-12፥24፤* የሰሎሞንን ዘመን የያዘው ይህ ትረካ፣ የጽሑፋዊ ቅደም ተከተል መለዋወጥን የሚያሳይ ጥሩ ምሳሌ ሲሆን፣ ዘጠኝ ክፍሎችንም ይዞአል። የመጀመሪያውና የመጨረሻው፣ እንዲሁም ሁለተኛውና ስምንተኛው ተመሳሳይ ሐሳብ አላቸው። በመጽሐፉ መዋቅር ውስጥ ማዕከላዊ ሥፍራ የያዘው አምስተኛው ክፍል ሲሆን፣ ከሁሉም ይልቅ ረዘም ያለና የሰሎሞንን የሕንጻ ሥራ የሚገልጽ ነው።

1፥1 *ዕድሜው በጣም እየገፋ፤* በ2ሳሙ 5፥4 ላይ ዳዊት ዕድሜው ሰባ ዓመት ገደማ በሆነው ጊዜ እንደ ሞተ ተገልጾአል (ከ1ነገ 2፥11 ጋር ያነጻጽሩ)።

1፥3 *ሱነማዊቷን፤* አቢሳ የመጣችው ከሱነም ሲሆን፣ (2ነገ 4፥8፤ ኢሱ 19፥18፤ 1ሳሙ 28፥4)፣ ይህም የይሳኮርም ነገድ ግዛት ከሆነው፣ ኢይዝራኤል አጠገብ የሚገኝ ነው።

1፥4 *ከእርሷ ጋር ግንኙነት አልነበረውም፤* ዳዊት ከሞተ በኋላ ሚስት ትሆነው ዘንድ፣ አዶንያስ አቢሳን የጠየቀበት ዋና ምክንያት ይህ ነው (የ2፥17:22 ማብ ይመ)።

1፥5 *አዶንያስ፤* የዳዊት አራተኛ ልጅ ሲሆን (2ሳሙ 3፥4 ይመ) በዚህ ጊዜ ዕድሜው በግምት ሠላሳ አምስት ዓመት ሳይሆን አይቀርም፤ በሕይወት ካሉት የዳዊት ልጆች መካከልም ትልቁ እርሱ ነው (የ2ሳሙ 13፥28 ማብ እንዲሁም 2ሳሙ 18፥14 ይመ)። *ተነሣ፤* ዳዊት የሚተካውን ሰው ለመሾም ያለውን መብት በመጋፋት፣ አዶንያስ በራሱ ውሳኔ ሥልጣን ከአባቱ ሊነጥቅ ሙከራ አደረገ (አዶንያስ ቢያንስ ሰሎሞን በአባቱ ፊት ሞገስ እንዳገኘ ማወቅ ነበረበት፤ ቍ 10 ይመ)። ተሳክቶለት ቢሆን ኖሮ፣ ሰሎሞን በእግዚአብሔርና በዳዊት ዘንድ መመረጡን የሚያደናቅፍ ይሆን ነበር (ቍ 13:17:30፤ 1ዜና 22፥9-10 እንዲሁም የ2ሳሙ 12፥25 ማብ ይመ)። *ከፊት ከፊቱ የሚሄዱ አምሳ ሰዎችን፤* እዚህ ላይ አዶንያስ ያደረገው፣ ከእርሱ በፊት የነበረውን የአቤሴሎምን ምሳሌ በመከተል ነው (የ2ሳሙ 15፥1 ማብ ይመ)።

1፥6 *ገሥጾት አያውቅም፤* ዳዊት ልጆችን ከመቅጣት ችላ ያለ ይመስላል (የ2ሳሙ 13፥21፤ 14፥33 ማብ ይመ)።

1፥7 *ከጽሩያ ልጅ ከኢዮአብና፤* የ1ሳሙ 26፥6፤ የ2ሳሙ 2፥13፤ 19፥13፤ 20፥10:23 ማብ ይመ። ኢዮአብን ከአዶንያስ ጋር እንዲተባበር የገፋፋው፣ ከበናያስ ጋር ለሥልጣን ያደርግ የነበረው ሽኩቻ ሳይሆን አይቀርም (ቍ 8፤ 2ሳሙ 8፥18፤ 20፥23፤ 23፥20-23 ይመ)። ኢዮአብ በሥልጣኑ ጸንቶ የቈየው፣ በሰራዊቱ ዘንድ በነበረው ድጋፍ እንጂ፣ በዳዊት ዘንድ በነበረው ተወዳጅነት አልነበረም (2፥5-6 ይመ)። *ከካህኑ አብያታር፤* የ2ሳሙ 8፥17 ማብ ይመ።

1፥8 *ካህኑ ሳዶቅ፤* የ2ሳሙ 8፥17 ማብ ይመ። *የዮዳሄ ልጅ በናያስ፤* የ2ሳሙ 23፥20 ማብ ይመ። *ነቢዩ ናታን፤* 2ሳሙ 12፥1-25 ይመ። *ሳሚ፤* በ2፥8:46 እና በ2ሳሙ 16፥5-8 የተጠቀሰው ሳይሆን፣ የኤላ ልጅ ሳሚ ሳይሆን አይቀርም (4፥18)። *ሬሲና፤* አማራጭ ትርጒሙን ይመ። የተጸውዖ ስም ነው ከተባለ፣ ከብሉይ ኪዳን ሌላ ተጨማሪ ማስረጃ ማግኘት አይቻልም። *የዳዊት የክብር ዘበኞች፤* 2ሳሙ 23፥8-39 ይመ።

1፥9 *አዶንያስ... ሠዋ፤* እዚህም ላይ (የቍ 5 ማብ ይመ) አዶንያስ የአቤሴሎምን ምሳሌነት ተከትሎአል (2ሳሙ 15፥7-12 ይመ። *በዓይንሮጌል፤* ከኢየሩሳሌም በስተ ደቡብ በቄድሮን ሸለቆ የሚገኝ "የሮጌል ምንጭ" ማለት ነው። ምንጩ ያለበት ቦታ፣ አሁን ሊሆን ላለው ነገር የቆመ ጒልሕ ትእምርት ነበር (ቍ 33 እና ማብ ይመ)።

1፥11 *የሰሎሞንን እናት ቤርሳቤህን፤* የንጉሡ እናት በቤተ መንግሥት ውስጥ ከፍተኛ ክብር ያለው ቦታ ነበራት (2፥19፤ 15፥13፤ 2ነገ 10፥13፤ 2ዜና 15፥16 ይመ)። *መንገሡን፤* ቀደም ባለው ትረካ ውስጥ የአዶንያስ ንጉሥ መሆን በይፋ ባይገለጽም፣ ንጉሥ መሆኑ ግን ይታወቅ ነበር። (ቍ 25፤ 2፥15 ይመ፤ ከ2ሳሙ 15፥10 ጋር ያነጻጽሩ)።

1፥12 *የራስሽንና የልጅሽን የሰሎሞንን ሕይወት...ማዳን፤* በጥንት የቅርብ ምሥራቅ አገሮች ሥልጣን የሚቀማ ሰው፣ ሥልጣኑን አስተማማኝ ለማድረግ፣ ዙፋኑ ይገባኛል ብለው ጥያቄ ሊያቀርቡ የሚችሉትን ሁሉ ማስወገድ የተለመደ ነበር (15፥29፤ 2ነገ 10፥11፤ 11፥1 ይመ)።

1፥13 *አልማልህልኝም ነበር?* ሰሎሞን ዙፋኑን እንደሚወርስ አባቱ ዳዊት ለመማሉ በ2ሳሙኤል ተገልጾ ባይገኝም፣ ሥርወ መንግሥቱ ለዘላለም እንደሚቀጥል፣ እግዚአብሔር ለዳዊት የሰጠው ተስፋ የሚፈጸመው፣ በልጁ በሰሎሞን በኩል እንደሆን ያመለክታል (የቍ 5 ማብ ይመ)።

17እርሷም እንዲህ አለችው፣ "ጌታዬ
ሆይ፤ 'ልጅሽ ሰሎሞን ከእኔ ቀጥሎ ይነግ
ሣል፤ በዙፋኔም ይቀመጣል' ብለህ አንተው
ራስህ ለአገልጋይህ በስም ማለህ *በእግዚአብሔር*
ምለህልኝ ነበር:: 18እነሆ፤ አሁንም አዶንያስ
ነግሦአል፤ ንጉሥ ጌታዬ አንተ ግን ስለዚህ
ነገር አታውቅም:: 19እርሱ በሬዎችን፣ ኮር
ማዎችንና በጎችን በብዛት ሠውቶአል፤
የንጉሡን ልጆች በሙሉ፣ ካህኑን አብያ
ታርንና የሰራዊቱን አዛዥ ኢዮአብን ጠር
ቶአል፤ አገልጋይህን ሰሎሞንን ግን አልጠራ
ውም:: 20ጌታዬ ንጉሥ ሆይ፤ ከአንተ
ቀጥሎ በጌታዬ በንጉሡ ዙፋን ላይ ማን
መቀመጥ እንዳለበት እንድታሳውቀው የእ
ስራኤል ዐይን ሁሉ አንተን ይመለከታል::
21ያለበለዚያ ግን ንጉሥ ጌታዬ ከአባቶቹ
ጋር በሚያንቀላፋበት ጊዜ እኔና ልጄ
ሰሎሞን እንደ ወንጀለኞች እንቈጠራለን::"
22እርሷ ከንጉሡ ጋር በመነጋገር ላይ ሳለች
ነቢዩ ናታን ገባ:: 23ለንጉሡም፣ "ነቢዩ
ናታን መጥቶአል" ብለው ነገሩት፤ እርሱም
ንጉሡ ፊት ቀርቦ ለጥ ብሎ እጅ ነሣ::
24ናታንም እንዲህ አለው፤ "ጌታዬ ንጉሥ
ሆይ፤ ለመሆኑ አዶንያስ ከአንተ ቀጥሎ
እንደሚነግሥ፣ በዙፋንህም እንደሚቀመጥ
አስታውቀሃልን? 25በዛሬው ቀን ታች ወርዶ
ብዙ በሬዎች፣ ኮርማዎችና በጎች ሠው
ቶአል፤ የንጉሡን ልጆች በሙሉ፣ የሰራዊቱን
አዛዦችና ካህኑን አብያታርንም ጠርቶአል፤
እነሆ፤ አሁን፣ 'አዶንያስ ለዘላለም ይኑር'
እያሉ ከእርሱ ጋር በመብላትና በመጠጣት
ላይ ናቸው:: 26ነገር ግን እኔን አገልጋይ
ህን፣ ካህኑን ሳዶቅን፣ የዮዳሄን ልጅ በናያስ
ንና አገልጋይህን ሰሎሞንን አልጠራም፤
27ታዲያ ከእርሱ ቀጥሎ በንጉሥ ጌታዬ
ዙፋን ላይ የሚቀመጠውን አገልጋዮቹን
ሳያሳውቅ ይህ እንዲሆን ንጉሡ ፈቅዶ
አልን?"

1፥17 ቍ13
1፥19 ቍ9
1፥21 ዘፍ15፥15፤ 1ነገ2፥10
1፥26 ቍ10
1፥29 2ሳሙ4፥9
1፥30 ቍ13፤1ዜና 23፥1
1፥32 1ሳሙ2፥35
1፥33 ቍ38፤መሳ 10፥4፤2ዜና32፥30፤ 33፥14፤ዘካ9፥9
1፥34 1ሳሙ2፥35፤ 10፥1፤2ሳሙ15፥10
1፥37 ቍ47፤ኢሱ 1፥5:17
1፥38 ቍ8:33፤ 1ሳሙ30፥14፤2ሳሙ 15፥18

## ዳዊት ሰሎሞን እንዲነግሥ አደረገ

1፥28-53 ተጓ ምብ - 1ዜና 29፥21-25

28ከዚያም ንጉሥ ዳዊት፣ "ቤርሳቤህን
ጥሩልኝ" አለ፤ እርሷም ንጉሡ ወዳለበት
ገብታ በፊቱ ቆመች::
29ከዚያም ንጉሡ እንዲህ ሲል ማለ፤ "ነፍ
ሴን ከመከራ ሁሉ ያዳናት ሕያው *እግዚአ
ብሔርን*! 30'ልጅሽ ሰሎሞን ከእኔ ቀጥሎ
ይነግሣል፤ በእኔም ምትክ በዙፋኔ ይቀመ
ጣል' ብዬ በእስራኤል አምላክ *በእግዚአብሔር*
የማልሁልሽን ዛሬ በእውነት እፈጽማለሁ"
31ቤርሳቤህም ለጥ ብላ እጅ ከነሣች በኋላ፣
በንጉሡ ፊት ተንበርክካ፣ "ጌታዬ ንጉሥ
ዳዊት ለዘላለም ይኑር!" አለች::
32ንጉሥ ዳዊትም፣ "ካህኑን ሳዶቅን፣ ነቢ
ዩን ናታንንና የዮዳሄን ልጅ በናያስን ጥሩ
ልኝ" አለ:: እነርሱም ንጉሡ ፊት በቀረቡ
ጊዜ፣ 33እንዲህ አላቸው፤ "የጌታችሁን አገ
ልጋዮች ይዛችሁ በመሄድ ልጄን ሰሎሞንን
በራሴ በቅሎ ላይ አስቀምጡት፤ ወደ ግዮ
ንም ይዛችሁት ውረዱ:: 34በዚያም ካህኑ
ሳዶቅና ነቢዩ ናታን ቀብተው በእስራኤል
ላይ ያንግሡት፤ ቀንደ መለከት ነፍታች
ሁም፣ 'ንጉሥ ሰሎሞን ለዘላለም ይኑር!'
ብላችሁ ጩኹ:: 35አጅባችሁት ወደ ላይ
ውጡ፤ ከዚያም መጥቶ በዙፋኔ ላይ ይቀ
መጥ፤ በእኔም ምትክ ይግዛ፤ በእስራኤልና
በይሁዳ ላይ ሾሜዋለሁ::"
36የዮዳሄ ልጅ በናያስም ለንጉሡ እንዲህ
ሲል መለሰ፤ "አሜን! የጌታዬ የንጉሡ አም
ላክ *እግዚአብሔር* ይህንኑ ያጽናው:: 37*እግዚ
አብሔር* ከጌታዬ ከንጉሡ ጋር እንደ ነበረ
ሁሉ፣ ከሰሎሞንም ጋር ይሁን፤ ዙፋኑንም
ከጌታዬ ከንጉሥ ዳዊት ዙፋን የበለጠ ያድ
ርገው::"
38ስለዚህ ካህኑ ሳዶቅ፣ ነቢዩ ናታን፣ የዮ
ዳሄ ልጅ በናያስ፣ ከሊታውያንና ፈሊታው
ያን ወርደው ሰሎሞንን በንጉሥ ዳዊት

1፥17 *አንተው ራስህ... በአምላክህ በእግዚአብሔር ምለ ህልኝ ነበር፤* በእግዚአብሔር ስም የተደረገ መሐላ የማይጣስ ነው (ዘፀ 20፥7፤ ዘሌ 19፥12፤ ኢሱ 9፥15:18:20፤ መሳ 11፥30:35፤ መክ 5፥4-7 ይመ)::

1፥21 *ከአባቶቹ ጋር በሚያንቀላፋበት ጊዜ፤* የአንድን ሰው ሞት ለመናገር የሚያገለግል የተለመደ አገላለጽ ነው (ዘፍ 47፥30፤ ዘዳ 31፥16 ይመ)::

*1፥24፤* የተፈጠረውን አስቸጋሪ ሁኔታ ግልጽ የሚያደርግ ጥያቄ በመጠየቅ፣ ናታን ዳዊትን በዘዴ አናገረው:: ምክንያቱም ለቤርሳብህና ለሰሎሞን የገባውን መሐላ በማፍረስ፣ አዶንያስ ዙፋን ይገባኛል እንዲል ዳዊት በምስጢር አበረታትቶታል ወይም አዶንያስ በዳዊት ላይ ለማመፅ ይህን አድርጐአል ብሎ በማሰቡ ነው:: (ቍ 27 ይመ)::

1፥25 *'አዶንያስ ለዘላለም ይኑር'፤* አዲሱን ንጉሥ መቀበላቸውንና ማክበራቸውን የሚያመለክት አባባል ነው (1ሳሙ 10፥24 ፤ 2ሳሙ 16፥16፤ 2ነገ 11፥12 ይመ)::

1፥31 *ጌታዬ ንጉሥ ዳዊት ለዘላለም ይኑር፤* በማጋነን የሚነገር፣ የተለመደ የቤተ መንግሥት ቋንቋን በመጠቀም፣ ቤርሳቤህ ምስጋናዋን ለዳዊት አቀረበች (ነህ 2፥3፤ ዳን 2፥4፤ 3፥9፤ 5፥10፤ 6፥21 ይመ)::

1፥33 *የጌታችሁን አገልጋዮች፤* ከሊታውያንንና ፈሊታውያንን የሚያካትት ይሆናል (ቍ 38 ይመ):: *በራሴ በቅሎ፤* በሙሴ ሕግ ማዳቀል የተከለከለ ቢሆንም (ዘሌ 19፥19)፣ በዳዊት ዘመን በቅሎዎች (ምናልባት ከሌላው አገር በማስመጣት ሕዝ 27፥14) ንጉሥ የሆነ ሰው እንዲቀመጥባቸው ይደረግ ነበር (2ሳሙ 13፥29፤ 18፥9):: ሰሎሞን በዳዊት በቅሎ ላይ መቀመጡ፣ ዙፋን መውረሱ በዳዊት የጸደቀ መሆኑን በግልጽ የሚያሳይ ነው (ዘፍ 41፥43፤ አስ 6፥7-8 ይመ):: *ግዮን፤* በጽዮን ተራራ ምሥራቃዊ ተዳፋት ላይ የሚገኝ ምንጭ ያለበት አካባቢ ነው (የቍ 9፤ 2ሳሙ 5፥8 ማብ ይመ)::

1፥34 *ቀብተው፤* የ1ሳሙ 2፥10፤ 9፥16 ማብ ይመ:: *ቀንደ መለከት ነፍታችሁም፤* 2ነገ 9፥13፤ 2ሳሙ 15፥10፤ 20፥1 ይመ:: *ንጉሥ ሰሎሞን ለዘላለም ይኑር፤* የቍ 25 ማብ ይመ::

1፥35 *በእስራኤልና በይሁዳ፤* በእስራኤልና በይሁዳ መካከል ያለው ልዩነት፣ ዳዊት በእነዚህ ሁለት የነገድ ክፍሎች ላይ በተለያየ ጊዜ ንጉሥ በሆነበት ሁኔታ (2ሳሙ 2፥4፤ 5፥3 ይመ) ላይ የተመሠረተ ነው::

1፥36 *አሜን ... እግዚአብሔር ... ያጽናው፤* ኤር 28፥6 ይመ::

1፥37 *የበለጠ፤* ዳዊት ያከናወነውን ነገር ለማጣጣል ሳይሆን፣ የዳዊትንና የሰሎሞንን ፍጹም ታማኝነት ለመግለጽ ነው:: ወራሹ እንዲሆን ለመረጠው ሰው ምኞቱ እንዲፈጸም፣ በናያስ የዳዊትን ሐሳብ ደግፎአል (ቍ 47-48 ይመ)::

1፥38 *ከሊታውያንና ፈሊታውያን፤* የ2ሳሙ 8፥18 ማብ ይመ::

በቅሎ አስቀምጠው በማጀብ ወደ ግዮን
አመጡት:: [39]ካህኑ ሳዶቅም የዘይቱን ቀንድ
ከመገናኛው ድንኳን ወስዶ ሰሎሞንን ቀባው፤
ከዚያም ቀንደ መለከቱን ነፉ፤ ሕዝቡም
በሙሉ፣ “ንጉሥ ሰሎሞን ለዘላለም ይኑር!”
በማለት ዳር እስከ ዳር አስተጋቡ:: [40]ሕዝቡ
ሁሉ እንቢልታ እየነፋና እጅግ እየተደሰተ
አጀበው፤ ከድምፁ የተነሣም ምድሪቱ
ተናወጠች::

[41]አዶንያስና የተጠሩት እንግዶች ሁሉ
ግብዣውን በማገባደድ ላይ ሳሉ፣ ይህንኑ
ሰሙ፤ ኢዮአብም የመለከቱን ድምፅ ሲሰማ፣
“ይህ በከተማዪቱ ውስጥ የሚሰማው ድምፅ
ምንድን ነው?” ሲል ጠየቀ::

[42]ኢዮአብ ገና ተናግሮ ሳይጨርስ፣ የካ
ህኑ የአብያታር ልጅ ዮናታን ደረሰ፤ አዶን
ያስም፣ “እንዳንተ ያለ ታማኝ ሰው መል
ካም ዜና ሳይዝ አይመጣምና ግባ” አለው::

[43]ዮናታንም እንዲህ ሲል መለሰ፣ “ነገሩ
ከቶ እንዲህ አይደለም! ጌታችን ንጉሥ
ዳዊት ሰሎሞንን አንግሦታል:: [44]ንጉሡ
ካህኑ ሳዶቅ፣ ነቢዩ ናታን፣ የዮዳሄ ልጅ
በናያስ፣ ከሊታውያንና ፈሊታውያን አብረ
ውት እንዲሄዱ አድርጎአል፤ እነርሱም በንጉሡ
በቅሎ አስቀመጡት:: [45]ካህኑ ሳዶቅና ነቢዩ
ናታን በግዮን ቀብተው አንግሠውታል::
ከዚያም ደስ ብሎአቸው ወጥተዋል፤ ከተ
ማዪቱም ይህንኑ አስተጋብታለች፤ እንግዲህ
የሰማችሁት ድምፅ ይኸው ነው:: [46]ከዚህም
ሌላ ሰሎሞን በመንግሥቱ ዙፋን ላይ ተቀ
ምጦአል:: [47]የመንግሥቱ ሹማምትም ወደ
ጌታችን ወደ ንጉሥ ዳዊት መጥተው፣
‘ስምባከህ የሰሎሞንን ስም ከአንተ ስም
የላቀ፣ ዙፋኑንም ከአንተ ዙፋን የበለጠ
ያድርገው’ በማለት መልካም ምኞታቸውን
ገልጸውለታል:: ንጉሡም ዐልጋው ላይ ሆኖ
በመስገድ፣ [48]‘ዛሬ በዙፋኔ ላይ የሚቀመጠ

1፥39 ቍ34፤ዘፀ 26፥1፤27፥21፤29፥7፤ ዘኍ23፥21፤1ሳሙ 10፥1፤2ሳሙ15፥10፤ 2ነገ11፥12:14፤መዝ 47፥5፤89፥20፤ ዘካ9፥9
1፥40 1ሳሙ10፥5
1፥41 2ዜና23፥12:13
1፥42 2ሳሙ15፥27:36፤18፥26
1፥45 ቍ40
1፥46 ዘዳ17፥18
1፥47 ቍ37
1፥48 ነገ3፥6
1፥50 ዘ27፥2
1፥52 1ሳ14፥45
2፥1 ዘፍ27፥2፤ ዘኍ27፥13
2፥2 ኢሱ1፥6፤ 23፥14
2፥3 ዘዳ4፥6፤10፥12፤17፥1420፤ኢሱ 1፥7፤1ዜና22፥13
2፥4 2ሳሙ7፥13: 15፤2ነገ18፥36፤20፥3፤ 2ዜና23፥3፤መዝ26፥13፤132፥12

ውን ወራሽ ዐይኔ እንዲያይ የፈቀደ፣ የእስ
ራኤል ስምባከ እግዚአብሔር፣ ምስጋና
ይድረሰው’ አለ::”

[49]በዚህም አዶንያስና የጠራቸው እንግዶች
በሙሉ ደንግጠው ተነሡ፤ በየአቅጣጫውም
ተበታተኑ:: [50]አዶንያስ ግን ሰሎሞንን በመ
ፍራት ሄዶ፣ የመሠዊያውን ቀንድ ያዘ::
[51]ከዚያም፣ ለሰሎሞን፣ “አዶንያስ እነሆ፣
ንጉሥ ሰሎሞንን በመፍራት የመሠዊያውን
ቀንድ ይዞ ተማጥኖአል፤ እርሱም፣ ‘ባሪያ
ውን በሰይፍ እንዳይገድለው ንጉሡ ሰሎ
ሞን ዛሬውኑ ይማልልኝ’ ብሎአል” ብለው
ነገሩት::

[52]ሰሎሞንም፣ “አካሄዱን ካሳመረ ከራስ
ጠጕሩ አንዲቱ እንኳ መሬት ላይ አትወ
ድቅም፤ ጥፋት ከተገኘበት ግን ይሞታል”
ሲል መለሰ:: [53]ከዚያም ንጉሥ ሰሎሞን
ሰዎች ልኮ ከመሠዊያው ላይ አወረዱት::
አዶንያስም መጥቶ ለንጉሥ ሰሎሞን እጅን
ብሶ እጅ ነሣ፤ ሰሎሞንም፣ “ብል ወደ ቤትህ
ሂድ” አለው::

### ዳዊት ለሰሎሞን የሰጠው መመሪያ

2፥10-12 ተጓ ምብ - 1ዜና 29፥26-28

**2** ዳዊት የሚሞትበት ጊዜ እንደ ተቃረ
በም፣ ልጁን ሰሎሞንን እንዲህ ሲል
አዘዘው፤

[2]“እነሆ፤ እኔ የምድሩን ሁሉ መንገድ ልሄድ
ነው፤ እንግዲህ በርታ፤ ሰውም ሁን:: [3]የአምላክህን
የእግዚአብሔርን ትእዛዝ ጠብቅ፤
የምታደርገው ሁሉ እንዲከናወንልህ፣ በምት
ሄድበትም ሁሉ እንዲሳካልህ፣ በሙሴ ሕግ
እንደ ተጻፈው በመንገዶቹ ተመላለስ፣ ሥርዐ
ቶቹንና ትእዛዛቱን፣ ሕግጋቱንና ደንቦቹን
ጠብቅ፤ [4]እግዚአብሔርም፣ ‘ዘሮችህ መንገዳ
ቸውን ቢጠብቁ፣ እንዲሁም በፍጹም ልባቸው፣
በፍጹም ነፍሳቸው በታማኝነት በፊቴ ቢመ

1፥39 *ሳዶቅም... ሰሎሞንን ቀባው፤* ከሥርወ መንግሥት ውጭ በእግዚአብሔር የተመረጡ ነገሥታት የሚቀቡት፣ በነቢያት ነበር (ሳኦል:- 1ሳሙ 9፥16፤ ዳዊት:- 1ሳሙ 16፥21፤ ኢዩ 2ነገ 9)፤ በሥርወ መንግሥቱ መሠረት የሚነግሡት ደግሞ በክህናት ይቀቡ ነበር (በዚህ ክፍል ሰሎሞን፣ ኢዮአስ 2ነገ 11፥12)፤ ይኸውም፣ ካህናት ይህን የሚፈጽሙት በሕጉ መሠረት ሲሆን፣ ነቢያት ግን አዲስ መለኮታዊ አመራርን በመከተል ነበር:: *የዘይቱን ቀንድ፤* በዘፀ 30፥22-23 ላይ የተጠቀሰውን ለመቀባት የሚውለውን ዘይት የያዘ ይሆናል:: *ከመገናኛው ድንኳን፤* በገባኦን የነበረው የመገናኛ ድንኳን ሳይሆን (3፥4 እንዲሁም 2ዜና 1፥3 ይመ)፣ ዳዊት ለእግዚአብሔር ታቦት በኢየሩሳሌም የተከለው ድንኳን ነበር (2ሳሙ 6፥17 ይመ)::

1፥41 *ሰሙ፤* ከዓይንሮጌል ሆኖ ግዮንን ለማየት ባይቻልም፣ ብዙም የሚርቅ ባለመሆኑ፣ ድምፁ እስከ ቄድሮን ሸለቆ ድረስ ዘልቆ ይሰማ ነበር::

1፥42 *የአብያታር ልጅ ዮናታን፤* 2ሳሙ 17፥17-21 ይመ::

1፥47 *የላቀ፤* የቊ 37 ማብ ይመ::

1፥48 *ወራሽ፤* ዳዊት፣ ሰሎሞን ዙፋኑን በመውረሱ፣ በ2ሳሙ 7፥12:16 የተሰጠው ተስፋ የተፈጸመ መሆኑን አስተዋለ::

1፥49 *ተበታተኑ፤* ባልተሳካው ሙከራ፣ ማንም ከአዶንያስ ጋር ተባባሪ እንደ ሆነ እንዲታወቅበት አልፈለገም ነበር::

1፥50 *የመሠዊያውን ቀንድ ያዘ፤* በየማእዘኑ እንዲቆም ተደርጐ የተሠራ ሲሆን፣ በመሠዊያ ላይ ከለላ መፈለግ፣ በሙሴ የሕግ መጻሕፍት ላይ የተመሠረተ ነው (ዘፀ 21፥13-14 ይመ):: በመሥዋዕት ማቅረቢያ ጊዜ፣ ካህኑ የመሥዋዕቱን ደም በመሠዊያው ቀንድ ላይ ይቀባ ነበር (ዘፀ 29፥12፤ ዘሌ 4፥7:18: 25:30:34 ይመ)፤ ስለዚህም አዶንያስ ሕይወቱን በእግዚአብሔር ጥበቃ ሥር ለማድረግ ፈለገ::

1፥52 *አካሄዱን ካሳመረ፤* የሰሎሞንን ሥልጣንና መንግሥት በመቀበል ተስማምቶ ራሱን ዝቅ አድርጐ ቢኖር ለማለት ነው:: *ጥፋት ከተገኘበት፤* ሰሎሞን ዙፋን በመውረሱ ቀንቶ ተቃውሞ ቢያደርግ ለማለት ነው::

2፥1 *አዘዘው፤* ሙሴ (ዘዳ 31፥1-8)፣ ኢያሱ (ኢሱ 23፥1-16) እና ሳሙኤል (1ሳሙ 12፥1-25) የእግዚአብሔር ወኪል እንደ መሆናቸው፣ ከመሞታቸው ጥቂት ቀደም ብለው የመጨረሻ መመሪያና ምክር ሰጥተዋል::

2፥2 *የምድሩን ሁሉ መንገድ፤* መደ መቃብር ማለት ነው (ኢሱ 23፥14 ይመ):: *በርታ፤* ዘዳ 31፥7:23፤ ኢሱ 1፥6-7:9:18 ይመ::

2፥3 *የአምላክህን የእግዚአብሔር ትእዛዝ ጠብቅ፤* ዘፍ 26፥5፤ ዘሌ 18፥30፤ ዘዳ 11፥1 ይመ:: *እንዲከናወንልህ፣* ዘዳ 29፥9 ይመ:: *በመንገዶቹ ተመላለስ፤* የቃል ኪዳን ግዴታን በተመለከተ፣ በዘዳግም መጽሐፍ ላይ ተደጋግሞ የሚታይ አገላለጽ ነው (ዘዳ 5፥33፤ 8፥6፤ 10፥12፤ 11፥22፤ 19፥9፤ 26፥17፤ 28፥9፤ 30፥16):: *ሥርዐቶቹንና ትእዛዛቱን፣ ሕግጋቱንና ደንቦቹን፤* የቃል ኪዳን ግዴታን የሚያመለክቱ አራት ተመሳሳይ ቃላት ናቸው (6፥12፤ 8፥58፤ 2ነገ 17፥37፤ ዘዳ 8፥11፤ 11፥1፤ 26፥17፤ 28፥15:45፤ 30፥10:16 ይመ::

2፥4 *በፍጹም ልባቸው፣ በፍጹም ነፍሳቸው፤* ዘዳ 4፥29፤

ላለሱ፣ በእስራኤል ዙፋን የሚቀመጥ ሰው
ከዘርህ አላሳጣህም’ ሲል የሰጠኝን ተስፋ
ይፈጽምልኛል፡፡
[5]የጽሩያ ልጅ ኢዮአብ በእኔ ላይ ያደረ
ገውን፣ እንዲሁም በእስራኤል ሰራዊት አዛ
ዦች በኔር ልጅ በአበኔርና በዬቴሩ ልጅ
በአሜሳይ ላይ የፈጸመውን አንተው ራስህ
ታውቃለህ፤ ጦርነት ሳይኖር በሰላሙ ጊዜ
ደማቸውን አፍሶአል፤ በዚህም ደም ወገቡ
ላይ የታጠቀውን ቀበቶና በእግሩ ላይ ያደረ
ገውን ጫማ በክሎአል፡፡ [6]መደረግ ያለበትን
በጥበብህ አድርግ፤ ከነሽበቱ በሰላም ወደ
መቃብር* እንዲወርድ አታድርግ፡፡
[7]“ከወንድምህ ከአቤሴሎም በሸሸሁ ጊዜ
መልካም ነገር አድርገውልኛልና ለገለዓዳ
ዊው ለቤርዜሊ ልጆች ግን በጎ ነገር አድር
ግላቸው፤ ማእድህን ከሚካፈሉ ሰዎችም
ጋር አብረው ይብሉ፡፡
[8]“ወደ መሃናይም በሄድሁ ጊዜ፣ ክፉኛ
የረገመኝ የባሑሪም ሰው የብንያማዊው የጌራ

2፥5 1ሳሙ 14፥50፤ 2ሳሙ 2፥18፤3፥27፤ 17፥25
2፥6 ቍ 9
2፥7 ዘፍ 40፥14፤ 2ሳሙ 9፥7፤17፥27፤ 19፥3139
2፥8 ቍ 36-46፤ ዘፍ 32፥2፤2ሳሙ 16፥ 5-13፤19፥18-23
2፥9 ቍ 6
2፥10 2ሳሙ 5፥7፤ ሐሥ 2፥29
2፥11 2ሳሙ 5፥4፡5
2፥12 ቍ 46፤1ዜና 17፥14፤29፥23፤2ዜና 1፥1፤9፥8፤12፥13፤ 17፥1፤21፥4
2፥13 1ሳሙ 16፥4፤ 2ሳሙ 3፥4

ልጅ ሳሚ እነሆ፤ ከአንተ ዘንድ ይገኛል፤ ሊቀ
በለኝ ወደ ዮርዳኖስ ሲወርድ፣ ‘በሰይፍ አል
ገድልህም’ ብዬ *በእግዚአብሔር* ስም ምዬለ
ታለሁ፤ [9]አሁን ግን በደል እንደሌለበት
ሰው አትተወው፤ ጥበበኛ ነህና መደረግ
ያለበትን ታውቃለህ፤ ሽበቱን በደም ወደ
መቃብር አውርድ፡፡”
[10]ከዚያም ዳዊት ከአባቶቹ ጋር አንቀላፋ፤
በዳዊትም ከተማ ተቀበረ፡፡ [11]ዳዊት በኬብ
ሮን ሰባት ዓመት፣ በኢየሩሳሌም ሠላሳ
ሦስት ዓመት ባጠቃላይ አርባ ዓመት በእስ
ራኤል ላይ ነገሠ፡፡ [12]ስለዚህ ሰሎሞን
በአባቱ በዳዊት ዙፋን ተቀመጠ፤ *መንግሥ
ቱም* እጅግ የጸና ሆነ፡፡

## የሰሎሞን መንግሥት መጽናት

[13]በዚህ ጊዜ የአጊት ልጅ አዶንያስ ወደ
ሰሎሞን እናት ወደ ቤርሳቤህ ሄደ፤ ቤርሳ
ቤህም፣ “የመጣኸው በሰላም ነውን?” ስትል
ጠየቀችው፤

*6 በዚህ ስፍራና በቍጥር 9 ላይ ዕብራይስጡ ሲኦል ይላል፡፡

6፥5፤ 10፥12፤ 30፥6 ይመ፡፡ *በእስራኤል ዙፋን የሚቀመጥ ሰው ከዘርህ አላሳጣህም፤* ሰሎሞንና ልጆቹ የተሰጣቸውን የኪዳን ግዴታዎች ሊጠብቁ አልቻሉም፤ ይህም የመንግሥቱን መከፈልና በመጨረሻም የሰሜኑና የደቡቡ መንግሥት ምርኮኛ መሆንን አስከተለ፡፡ የወደቀችው የዳዊት ድንኳን የምትነሣውና መንግሥቱም ለዘላለም የጸናች እንደምትሆን የተሰጠው ተስፋ የሚፈጸመው፣ በክርስቶስ መምጣት ብቻ ነው (የአሞ 9፥11-15፤ የሐሥ 15፥16 ማብ ይመ)፡፡ ሕዝቡና ንጉሡ በሲና ተራራ ላይ የገቡትን ኪዳን ከመፈጸም ወደ ኋላ ባሉ ጊዜ፣ የደረሰባቸው የኪዳኑ በረከት ሳይሆን እርግማን ነው፤ በዚህ ሁሉ ግን እግዚአብሔር ለአብርሃምና ለዳዊት የገባውን ኪዳን በመጠበቅ በታማኝነቱ ጸንቶአል (ዘሌ 26፥42-45፤ ኢሳ 9፥6-7፤ 11፥1-16፤ 16፥5፤ 55፥3፤ ኤር 23፥5-6፤ 30፥9፤ 33፥17:20-22:25-26፤ ሕዝ 34፥23-24፤ 37፥24-28 ይመ)፡፡ *የሰጠኝን ተስፋ ይፈጽምልኛል፤* እዚህ ላይ፣ ዳዊት መንግሥቱ ለዘላለም የጸና ሥርወ መንግሥት እንደሚሆን በነቢዩ ናታን በኩል አምላክ በኪዳን የገባለትን ተስፋ ይጠቅሳል (የ2ሳሙ 7፥11-16 ማብ ይመ)፡፡ ለዳዊት የተሰጠው የኪዳን ተስፋ ያለ ምንም ቅድመ ሁኔታ ቢሆንም፣ የዳዊት ልጆች ግን ይህን በረከት የሚያገኙት በሙሴ በኩል የተሰጠውን የኪዳን ሕግ በመታዘዝ ብቻ ነበር (2ዜና 7፥17-22 ይመ)፡፡

2፥5 *የጽሩያ ልጅ ኢዮአብ፤* የ1፥7 ማብ ይመ፡፡ *በኔር ልጅ በአበኔርና፤* የ2ሳሙ 3፥25-32 ማብ ይመ፡፡ *በዬቴሩ ልጅ በአሜሳይ፤* 2ሳሙ 20፥10 ይመ፡፡ *በሰላሙ ጊዜ ደማቸውን አፍሶአል፤* ኢዮአብ የፈጸመው ይህ ግድያ ሕገ ወጥ ሲሆን (ዘዳ 19፥1-13፤ 21፥1-9)፣ ይህንም ያደረገው የራሱን ፍላጐት በመከተል ነበር፡፡

2፥7 *ለቤርዜሊ ልጆች፤* የ2ሳሙ 17፥27 ማብ ይመ፡፡ *ማእድህን...ይብሉ፤* ሌሎች ጥቅሞችን የሚያስገኝ የክብር ሥፍራ ነበር (18፥19፤ 2ነገ 25፥29፤ 2ሳሙ 9፥7፤ 19፥28፤ ነህ 5፥17 ይመ)፡፡

*2፥8፤* 2ሳሙ 16፥5-13 ይመ፡፡ *የብንያማዊው የጌራ ልጅ ሳሚ፤* ጌራ የሳሚ አባት እንደ ሆነ መጠቀሱ የእርሱ ወላጅ ሆኖ ሳይሆን፣ በእርሱ የዘሩ ሐረግ ውስጥ ላሉት ሁሉ አባት በመሆኑ ነው (ዘፍ 46፥21፤ መሳ 3፥15 ይመ)፡፡

2፥9 *በደል እንደሌለበት ሰው አትተወው፤* በሙሴ ሕግ፣ አለቃ የሆነውን ሰው መርገም የተከተለ ነው (21፥10፤ ዘፀ 22፥28)፡፡

2፥10 *ከአባቶቹ ጋር አንቀላፋ፤* የ1፥21 ማብ ይመ፡፡ *በዳዊትም ከተማ፤* የ2ሳሙ 5፥7 እና ማብ ይመ፡፡ ጴጥሮስ በእርሱ ዘመን እንኳ፣ የዳዊት መቃብር ይታወቅ እንደ ነበር ያመለክታል (ሐሥ 2፥29)፡፡


2፥11 *አርባ ዓመት፤* 2ሳሙ 5፥4-5 ይመ፡፡ ዳዊት ዓ.ቅ.ክ ከ1010-970 ዓመት ድረስ ገዝቶአል፡፡

2፥13 *የአጊት ልጅ አዶንያስ፤* የ1፥5 ማብ ይመ፡፡ *የመጣኸው በሰላም ነውን? ጥያቄው* (1ሳሙ 16፥4፤ 2ነገ 9፥22 ይመ) ከአዶንያስ ፍላጎት አንጻር (1፥5 ይመ) የቤርሳቤህን ፍርሀት ይገልጻል፡፡

## ኢየሩሳሌም በሰሎሞን ዘመን
## 950 ዓ.ቅ.ክ

ሰሎሞን ከተማዋን ከቀድሞ አቀማመጧ ወደ ሰሜን አቅጣጫ በማስፋት አስደናቂውን ቤተ መቅደሱን ሠራ፡፡

ቤተ መንግሥቱም እዚያው አጠገብ ነበር፡፡ ሆኖም የሕንጻው አሠራርና የተሠራበት ሥፍራ አይታወቅም፡፡



እርሱም፣ “አዎን በሰላም ነው” ብሎ
መለሰ:: 14ከዚያም፣ “የምነግርሽ ጉዳይ አለኝ”
አላት::
እርሷም፣ “እሺ ተናገር” ብላ መለሰች::
15እርሱም፣ “መንግሥቱ የእኔ እንደ ነበ
ረና እስራኤልም ሁሉ እኔ እንድነግሥ ዐይ
ናቸውን ጥለውብኝ እንደ ነበር አንቺ ራስሽ
ታውቂአለሽ፤ ሆኖም ነገሩ *ከእግዚአብሔር*
የተቈረጠለት ሆነና ሁኔታዎች ተለዋውጠው፣
መንግሥቱ ለወንድሜ ተላለፈ:: 16አሁንም
አንዲት ነገር እለምንሻለሁ፤ አታሳፍሪኝ”
አላት::
እርሷም፣ “በል እሺ ተናገር” አለችው::
17እርሱም፣ “ንጉሥ ሰሎሞን መቼም እምቢ
አይልሽምና ሱነማዊቷን አቢሳን እንዲድር
ልኝ ለምኚልኝ” አላት::
18ቤርሳቤህም፣ “መልካም ነው፤ ይህንኑ
ለንጉሡ እነግርልሃለሁ” ብላ መለሰች::
19ስለዚህም ቤርሳቤህ የአዶንያስን ጒዳይ
ልትነግረው ወደ ንጉሥ ሰሎሞን ሄደች፤
ንጉሡም ሊቀበላት ተነሣ፤ እጅ ከነሣትም
በኋላ በዙፋኑ ላይ ተቀመጠ፤ ንጉሡም ለእ
ናቱ ሌላ ዙፋን አስመጥቶ በቀኙ አስቀመጣት::
20እርሷም፣ “የምለምንህ አንዲት ነገር አለ
ችኝና እባክህ እሺ በለኝ” አለችው::
ንጉሡም፣ “እናቴ ሆይ፤ አላሳፍርሽምና
ንገሪኝ” ሲል መለሰላት::
21ስለዚህም፣ “ሱነማዊቷን አቢሳን ወንድ
ምህ አዶንያስ ቢያገባትስ?” አለችው::
22ንጉሥ ሰሎሞንም እናቱን፣ “ስለምን
ሱነማዊቷን አቢሳን ብቻ ለአዶንያስ ትጠይ
ቂለታለሽ? ታላቅ ወንድሜ ስለ ሆነ መንግ
ሥቱንም ጠይቂለት እንጂ፤ ለእርሱ ብቻ
ሳይሆን እንዲሁም ለካህኑ ለአብያታርና
ለጽሩያ ልጅ ለኢዮአብ ጠይቂላቸው” አላት::
23ከዚያም ንጉሥ ሰሎሞን *በእግዚአብሔር*

2፥17 1ነገ1፥3
2፥19 1ነገ15፥13፤ 2ነገ10፥13፤24፥15፤ 2ዜና15፥16፤መዝ45፥9፤ኤር13፥18፤22፥26፤29፥2
2፥21 1ነገ1፥3
2፥22 ዘፍ22፥24፤ 1ሳሙ22፥20፤1ነገ1፥3፤1ዜና3፥2
2፥23 ሩት1፥17
2፥24 2ሳሙ7፥11
2፥25 2ሳሙ8፥18፤ 12፥10
2፥26 ኢሱ21፥18፤ 1ሳሙ22፥20፤2ሳሙ 15፥14፡24
2፥27 1ሳሙ2፥ 27-36
2፥28 ዘፀ27፥2
2፥29 ቍ 25፤ዘፀ 21፥14
2፥30 ዘፀ21፥14፤ 2ነገ11፥15

ስም እንዲህ ሲል ማለ፤ “አዶንያስ ይህን
ስለ ጠየቀ በሞት ሳይቀጣ ቢቀር፣ *እግዚአ
ብሔር* ይፍረድብኝ፤ ከዚህ የባሰም ያምጣ
ብኝ፤ 24አሁንም በሚገባ ያጸናኝ፣ በአባቴ
በዳዊት ዙፋን ያስቀመጠኝና በሰጠውም
ተስፋ መሠረት ሥርወ መንግሥትን የመ
ሠረተልኝ ሕያው *እግዚአብሔርን* አዶንያስ
ዛሬ ይሞታል!” 25ስለዚህም አዶንያስን እን
ዲገድለው ንጉሥ ሰሎሞን፣ የዮዳሄን ልጅ
በናያስን አዘዘው፤ በናያስም አዶንያስን
መቶ ገደለው::
26ንጉሡም ካህኑን አብያታርን፣ “ሞት
የሚገባህ ሰው ነበርህ፤ ነገር ግን ልዑል
*እግዚአብሔርን* ታቦት በአባቴ በዳዊት ፊት
ስለ ተሸከምህ፣ አባቴ የተቀበለውንም መከራ
ሁሉ አብረኸው ስለ ተቀበልህ፣ እኔ አሁን
አልገድልህም፤ ዓናቶት ወዳለው ዕርሻህ
ሂድ” አለው:: 27ስለዚህ *እግዚአብሔር* ስለ ዔሊ
ቤት በሴሎ የተናገረውን ቃል ለመፈጸም፣
ሰሎሞን አብያታርን *ከእግዚአብሔር* ክህ
ነት አስወገደው::
28ከአቤሴሎም ጋር ሳይሆን ከአዶንያስ
ጋር አሢሮ የነበረው ኢዮአብም ይህን በሰማ
ጊዜ፣ ወደ *እግዚአብሔር* ድንኳን ሸሽቶ
የመሠዊያውን ቀንድ ያዘ:: 29ኢዮአብ ወደ
*እግዚአብሔር* ድንኳን ሸሽቶ መሄዱንና
በመሠዊያው አጠገብ መሆኑን ንጉሥ ሰሎ
ሞን በሰማ ጊዜ፣ የዮዳሄን ልጅ በናያስን፣
“ሂድና ግደለው!” ብሎ አዘዘው::
30ስለዚህም በናያስ ወደ *እግዚአብሔር*
ድንኳን ገብቶ ኢዮአብን፣ “ንጉሡ፣ ‘ከዚህ
ውጣ’ ይልሃል” አለው::
እርሱ ግን “አልወጣም፣ እዚሁ እሞታ
ለሁ” አለው::
በናያስም፣ “ኢዮአብ የሰጠኝ መልስ ይህ
ነው” በማለት ለንጉሡ ተናገረ::

---

2፥15 *መንግሥቱ የእኔ እንደ ነበረና፤* 1፥11 ይመ:: *እስ ራኤልም ሁሉ እኔ እንድነግሥ፤* በጣም የተጋነነና ትክክለኛ ያል ሆነ አባባል ነው (1፥7-8 ይመ):: *ነገሩ ከእግዚአብሔር የተቈረጠለት፤* ሰሎሞን በአምላክ ፈቃድ ንጉሥ እንደ ሆነና፣ ከዚህም በኋላ አዶ ንያስ ሥልጣን ለመያዝ ፍላጎት እንደሌለው በግልጽ አመልክቶአል::

2፥17 *ሱነማዊቷን አቢሳን እንዲድርልኝ፤* አቢሳ ዳዊትን በመንከባከብ በቈየችበት ጊዜ ሁሉ ድንግል ስለ ነበረች፣ (1፥1-4፤ ዘዳ 22፥30 ይመ)፣ የአዶንያስ ጥይቄ ተንኰል የሌለበት ይመስ ላል (ሆኖም የቍ 22 ማብ ይመ)::

2፥19 *በቀኙ፤* የክብርን ሥፍራ ያመለክታል (መዝ 110፥1፤ ማቴ 20፥21)::

2፥20 *የምለምንህ አንዲት ነገር፤* ለቤርሳቤህ፣ የአዶንያስ ጥያቄ ትልቅ መስሎ አልታያትም::

2፥22 *መንግሥቱንም ጠይቂለት እንጂ፤* አዶንያስ ይህን ጥያቄ ሲያቀርብ፣ ዙፋኑ ላይ ለመቀመጥ ሌላ ሙከራ እያደረገ መሆኑን ሰሎሞን ወዲያው ተገነዘበ:: የንጉሥን ሚስት ማግባት፣ ዙፋን ለመያዝ መብት እንደሚያስገኝ ይታመናል (የ2ሳሙ 3፥7፤ 12፥8፤ 16፥21 ማብ ይመ):: አቢሳ ድንግል ብትሆንም፣ ብሕዝቡ ዘንድ የምትታወቀው የዳዊት ሚስት በመሆን ነው፤ ስለዚህ አቢ ሳን ማግባቱ፣ አዶንያስ ዙፋን ይገባኛል በማለት ያነሣውን ጥያቄ ሊያጠናክርለት ይችላል:: *ለካህኑ ለአብያታርና ለጽሩያ ልጅ ለኢዮአብ፤* የ1፥7 ማብ ይመ:: አብያታርና ኢዮአብ ክሕደት ለተ ሞላበት ለአዶንያስ ዕቅድ ተባባሪዎች መሆናቸውን ሰሎሞን ደርሶ በታል::

2፥23 *እግዚአብሔር ይፍረድብኝ፤ ከዚህ የባሰም ያምጣብኝ፤* መሐላን የሚያመለክት የተለመደ አባባል ነው (የ1ሳሙ 3፥17 ማብ ይመ)::

2፥24 *በሰጠውም ተስፋ መሠረት፤* 1ዜና 22፥9-10 ይመ:: *ሥርወ መንግሥትን የመሠረተልኝ፤* የሰሎሞን ዙፋን ወራሽ የሆ ነው ልጅ ሮብዓም የተወለደው፣ ሰሎሞን ከመንገሡ ጥቂት ቀደም ብሎ ነበር (ከ11፥42፤ 14፥21 ጋር ያነጻጽሩ)::

2፥25 *የዮዳሄን ልጅ በናያስን፤* የ1፥7 እና የ2ሳሙ 23፥20 ማብ ይመ::

2፥26 *ታቦት ... ስለ ተሸከምህ፤* የ2ሳሙ 15፥24-25:29፤ 1ዜና 15፥11-12 ይመ:: *አባቴ የተቀበለውንም መከራ ሁሉ አብ ረኸው ስለ ተቀበልህ፤* 1ሳሙ 22፥20-23፤ 23፥6-9፤ 30፥7 2ሳሙ 17፥15፤ 19፥11 ይመ::

2፥27 *እግዚአብሔር ስለ ዔሊ ቤት በሴሎ የተናገረውን ቃል ለመፈጸም፤* የ1ሳሙ 2፥30-35 ማብ ይመ::

2፥28 *ከአዶንያስ ጋር አሢሮ፤* 1፥7 ይመ:: *በሰማ ጊዜ፤* ስለ አዶንያስ ሞትና ስለ አብያታር ከክህነት መወገድ ማለት ነው:: *ወደ እግዚአብሔር ድንኳን፤* የ1፥39 ማብ ይመ:: *የመሠዊያውን ቀንድ ያዘ፤* የ1፥50 ማብ ይመ::

2፥29 *ሂድና ግደለው፤* መጠጊያ የማግኘት መብት የሚሰጠው፣ በድንገት ሰው ለገደለ ብቻ ነው (ዘፀ 21፥14 ይመ) ኢዮአብ፣ ከአዶንያስ ሤራ ጋር በመተባበሩ ብቻ ሳይሆን፣ አበኔርንና አሜሳይን በመግደሉ (ቍ 31-33 ይመ)፣ ሰሎሞን ይህን መብት ከእርሱ መንፈጉ ሙሉ በሙሉ ትክክል ነበር:: በዚህ ሁኔታ፣ ሰሎሞን አባቱ የሰጠውን ትእዛዝ ለመፈጸም ለማድረግ ጥሩ አጋጣሚ አግኝቶአል (ቍ 5-6 ይመ)::

31ንጉሡም በናያስን እንዲህ ሲል አዘ
ዘው፤ "በል እንዳለው አድርግ፤ ግደልና ቅበ
ረው፤ ኢዮአብ በከንቱ ካፈሰሰው ንጹሕ
ደምም እኔንና የአባቴን ቤት አንጻን።
32አባቴ ዳዊት ሳያውቅ ኢዮአብ በሁለቱ
ሰዎች ላይ አደጋ ጥሎ በሰይፍ ገድሎአቸ
ዋልና ስላፈሰሰው ደም እግዚአብሔር ይበቀ
ለዋል። የእስራኤል ሰራዊት አዛዥ የኔር
ልጅ አበኔርና የይሁዳ ሰራዊት አዛዥ
የዬቴሩ ልጅ አሜሳይ ሁለቱም ከእርሱ
የተሻሉና ይበልጥ ትክክለኛ ሰዎች ነበሩ።
33የደማቸውም ዕዳ ለዘላለም በኢዮአብና
በዘሩ ራስ ላይ ይሁን። ነገር ግን በዳዊትና
በዘሩ፣ በቤቱና በዙፋኑ ላይ የእግዚአብሔር
ሰላም ለዘላለም ጸንቶ ይኑር።"
34ስለዚህም የዮዳሄ ልጅ በናያስ ወጣ፤
ኢዮአብንም መቶ ገደለው፤ እርሱም በም
ድረ በዳ ባለው በገዛ ምድሩ* ተቀበረ።
35ንጉሡም በኢዮአብ ቦታ የዮዳሄን ልጅ
በናያስን በሰራዊቱ ላይ ሾመ፤ በአብያታ
ርም ቦታ ካህኑን ሳዶቅን ተካ።
36ከዚያም ንጉሡ ሳሚን አስጠርቶ እንዲህ
አለው፤ "በኢየሩሳሌም ቤት ሠርተህ እዚያው
ተቀመጥ፤ ከዚያ ግን የትም እንዳትሄድ፤
37ነገር ግን ከዚያ ወጥተህ የቄድሮንን ሸለቆ
ከተሻገርህ እንደምትሞት ዕወቅ፤ ደምህም
በራስህ ላይ ይሆናል።"
38ሳሚም መልሶ ንጉሡን፣ "መልካም፤
ባሪያህ ጌታዬ ንጉሡ ያለውን ይፈጽማል"
አለው፤ እርሱም በኢየሩሳሌም ብዙ ጊዜ
ተቀመጠ።
39ከሦስት ዓመት በኋላ ግን፣ ከሳሚ አገ
ልጋዮች ሁለቱ ወደ ጌት ንጉሥ፣ ወደ
መዓካ ልጅ ወደ አንኩስ ኰበለሉ፤ ለሳሚም፣
"እነሆ፣ አገልጋዮችህ በጌት ናቸው" ተብሎ
ተነገረው። 40ሳሚ ይህን ሲሰማም አህዮቹን
ጭኖ አገልጋዮቹን ለመፈለግ ጌት ወዳለው
ወደ አንኩስ ሄደ፤ አገልጋዮቹንም ከጌት
መልሶ አመጣቸው።
41ሳሚ ከኢየሩሳሌም ወደ ጌት ሄዶ መመ
ለሱን ሰሎሞን በሰማ ጊዜ፣ 42ንጉሡ ሳሚን
አስጠርቶ እንዲህ አለው፤ " 'ወደ ሌላ ቦታ
የሄድህ ዕለት እንደምትሞት ዕወቅ' ብዬ በእ
ግዚአብሔር ስም አስምዬ አስጠንቅቄህ
አልነበረምን? በዚያን ጊዜ አንተም፣ 'መል
ካም ነው፤ እኔም እታዘዛለሁ' ብለኸኝ ነበር፤
43ታዲያ ለእግዚአብሔር የማልኸውን መሐላ
ያልጠበቅኸውና እኔም የሰጠሁህን ትእዛዝ
ያልፈጸምኸው ለምንድን ነው?"
44ንጉሡም መልሶ ሳሚን እንዲህ አለው፤
"በአባቴ በዳዊት ላይ ያደረግህበትን ክፉ
ነገር ሁሉ ልብህ ያውቀዋል፤ ስለዚህ እግዚ
አብሔር ስለ ክፉ ሥራህ ብድሩን ይከፍል
ሃል። 45ንጉሥ ሰሎሞን ግን ይባረካል፤ የዳ
ዊትም ዙፋን በእግዚአብሔር ፊት ለዘላ
ለም ጸንቶ ይኖራል።"
46ከዚያም ንጉሡ የዮዳሄን ልጅ በናያስን
አዘዘው፤ በናያስም ወጣ፤ ሳሚንም መቶ
ገደለው።
በዚህ ጊዜም መንግሥቱ በሰሎሞን እጅ
ጸና።

### ሰሎሞን ጥበብን ከእግዚአብሔር መለመኑ

3፥4-15 ተጓ ምብ - 2ዜና 1፥2-13

3ሰሎሞን የግብፅ ንጉሥ ፈርዖን ወዳጅ
ሆነ፤ የፈርዖንንም ልጅ አገባ። እርሱም
ቤተ መንግሥቱን፣ የእግዚአብሔርን ቤተ
መቅደስና የኢየሩሳሌምን ዙሪያ ቅጥር
ሠርቶ እስኪጨርስ ድረስ በዳዊት ከተማ
አስቀመጣት።
2በዚያን ጊዜ ለእግዚአብሔር ስም ገና
ቤተ መቅደስ ስላልተሠራ፣ ሕዝቡ አሁንም
መሥዋዕት የሚያቀርበው በማምለኪያ ኰረብታ

2፥31 ዘዳ19፥13
2፥32 ዘፍ4፥14፤ መሳ9፥24:57፤2ሳሙ 17፥25፤2ዜና21፥13
2፥34 ቍ 25፤ 2ሳሙ2፥18
2፥35 1ሳሙ2፥35፤ 2ሳሙ8፥18
2፥36 2ሳሙ16፥5
2፥37 ዘሌ20፥9፤ 2ሳሙ15፥23፤ዮሐ 18፥1
2፥39 1ሳሙ27፥2
2፥42 2ሳሙ19፥23
2፥44 2ሳሙ16፥5-13
2፥45 2ሳሙ7፥13
2፥46 ቍ8:12፤ 2ሳሙ818
3፥1 2ሳሙ5፥7፤7፥2፤1ነገ2፥10፤7፥8፤9፥10:24፤11፥1፤13፤2ዜና 8፥11
3፥2 ዘሌ17፥35፤26፥30፤ዘዳ12፥14፤14፥23፤1ነገ15፥14፤22፥43
3፥3 ቍ 2፤ዘሌ17፥35፤ዘዳ6፥5፤10፥12፤17፥19፤ኢሱ1፥7፤1ነገ 14፥8፤2ነገ12፥3፤15፥4:35፤16፥4፤21፥3፤ መዝ31፥23፤145፥20

*34 ወይም በገዛ መቃብሩ ተብሎ ሊተረጐም ይችላል

2፥32 *በሁለቱ ሰዎች ላይ አደጋ ጥሎ…ገድሎአቸዋልና፤* 2ሳሙ 3፥27፤ 20፥9-10 ይመ። *የእስራኤል ሰራዊት፤* 2ሳሙ 2፥8-9 ይመ። *የይሁዳ ሰራዊት፤* 2ሳሙ 20፥4 ይመ።

2፥34 *በገዛ ምድሩ፤* የኢዮአብ አባት መቃብር የሚገኘው በቤተ ልሔም አቅራቢያ ነበር (2ሳሙ 2፥32 ይመ)። *በምድረ በዳ፤* ከይሁዳ ቤተ ልሔም በስተ ምሥራቅ ያለው ነው።

2፥35 *የዮዳሄን ልጅ በናያስን፤* የ2ሳሙ 23፥20 ማብ ይመ። *ካህኑን ሳዶቅን፤* የ1ሳሙ 2፥35 እና የ2ሳሙ 8፥17 ማብ ይመ።

2፥36 *ከዚያ ግን የትም እንዳትሄድ፤* ሳሚ ከኢየሩሳሌም እንዳይወጣ መደረጉ፣ የሰሎሞንን አገዛዝ ከሚቃወሙ ከቀሩት የሳኦል ተከታዮች ጋር ለማበር ያለውን ዕድል (ቍ 8 ይመ)፣ በእጅጉ ይቀንስበታል።

2፥39 *ወደ ጌት ንጉሥ ወደ መዓካ ልጅ አንኩስ፤* ጌት የፍልስጥኤም ዋና ከተማ ነው (ኢሱ 13፥3፤ 1ሳሙ 6፥16-17 ይመ)። መዓካ፣ ትልቁ አንኩስ፣ (1ሳሙ 27፥2)፣ አሜህና በዚህ ክፍል ደግሞ ትንሹ አንኩስ ጌትን ተራ በተራ ገዝተዋል።

2፥46 *ሳሚንም መቶ ገደለው፤* ይህ፣ በናያስ የፈጸመው ሦስተኛው ግድያ ነው (ቍ 25:34 ይመ)፤ ይህም ዳዊት ከመ ሞቱ ጥቂት ቀደም ብሎ (ቍ 6:9) ለልጁ ለሰሎሞን የሰጠውን ትእዛዝ ሙሉ በሙሉ እንዲፈጽም አስችሎታል።

3፥1 *የፈርዖን ወዳጅ ሆነ፤* ሰሎሞን የጋብቻ ወዳጅነቱን የፈጠረው፣ በግብፅ ሃያ አንደኛው ሥርወ መንግሥት ውስጥ የመጨረሻ ንጉሥ ከሆነው ከሲያሙን ወይም ከዳግማዊ ሱብነስ ጋር ይሆናል (በብሉይ ኪዳን ስሙ የተጠቀሰው የመጀመሪያው ፈርዖን ሺሻቅ ሲሆን 11፥40፤ 14፥25-26፤ እርሱም ዓ.ቅ.ክ. በ945 ገደማ ሃያ ሁለተኛውን የግብፅ ሥርወ መንግሥት መሠረተ)። ይህ ዐይነቱ ወዳጅነት፣ እየኋላ የመጣውን የእስራኤልን መንግ ሥት አስፈላጊነትና ጥንካሬ ግብፃውያን እየተረዱ እንደ መጡ ያመለክታል። የፈርዖን ልጅ ሰሎሞንን ባገባች ጊዜ፣ ፈርዖን የከነዓና ውያንን ከተማ ጌዝርን፣ በጥሎሽ መልክ እንደ ሰጣት በ1ነገ 9፥16 ላይ ተገልጾአል። ጌዝር የሁለት ዋና መንገዶች መተላለፊያ ከተማ ናት። ከጌዝር በስተ ምዕራብ ያለው መንገድ፣ ከግብፅ ወደ ሰሜን የሚያመራ ሲሆን፣ ለግብፅ የንግድ እንቅስቃሴ በጣም አስፈላጊ ነበር። ሌላው ከጌዝር በስተ ሰሜን የሚገኘው ደግሞ፣ ከኢየሩሳሌም ወደ ሜዲትራንያን ባሕርና ወደ ኢዮጴ ወደብ የሚያመራ ነው፣ ሰሎሞንም ለሕንጻው ሥራ የሚያስፈልጉትን ዕቃዎች የሚያገኘው በዚህ መሥመር በመገልገል ስለ ሆነ ጌዝር ለእርሱ ጠቃሚ ነበረች። ሰሎሞንና ፈርዖን በጋብቻ መተሳሰራቸው፣ በምጣኔ ሀብትና በፖለቲካ ረገድ የጋራ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ረድቶአቸዋል። የጋብቻ ግንኙነቱ የጀመረው ሰሎሞን በነገሠ በሦስተኛው ወይም በአራተኛው ዓመት ቢሆንም (2፥39 ይመ)፣ መቼ እንዳበቃ ትክክለኛው ጊዜ ተለይቶ አይታወቅም። ሰሎሞን የቤተ መቅደሱን ግንባታ የጀመረው በነገሠ በአራተኛው ዓመት ሲሆን (6፥1)፣ የጌዝርን አካባቢ መቈጣጠሩ ለጀመረው የሕንፃ ሥራ በጣም ያስፈልገው ነበር። *በዳዊት ከተማ፤* ከሃያ ዓመት በኋላ፣ ቤተ መንግሥት እስኪሠራላት ድረስ (7፥8፤ 9፥10፤ 2ዜና 8፥11)፣ ግብፃዊቷን ንግሥት በጥንቱ ከተማ ጊዜያዊ መኖሪያ ሰጥቶአት ነበር (2ሳሙ 5፥7 ይመ)።

3፥2 *በማምለኪያ ኰረብታ፤* እስራኤላውያን ከነዓን በገቡ

ላይ ነበር። 3ሰሎሞን እግዚአብሔርን ይወድ
ነበር፤ በአባቱ በዳዊት ሥርዐትም ይሄድ
ነበር፤ ይሁን እንጂ፣ በኰረብታዎች ላይ
መሥዋዕት ይሠዋና ዕጣን ያጥን ነበር።
4ከሁሉ የሚበልጠው የማምለኪያ ኰረብታ
ገባዖን ስለ ነበረ፣ ንጉሡ መሥዋዕት ለማ
ቅረብ ወደዚያ ሄደ። ሰሎሞን በዚያ መሠ
ዊያ ላይ አንድ ሺህ የሚቃጠል መሥዋዕት
አቀረበ። 5በገባዖንም እግዚአብሔር ለሰሎ
ሞን ሌሊት በሕልም ተገለጠለት፤ ስምባክሙ፣
"እንድሰጥህ የምትፈልገውን ሁሉ ለምን"
አለው።

6ሰሎሞን እንዲህ ሲል መለሰ፤ "አባቴ
ዳዊት በእውነት፣ በጽድቅና በቅን ልቡና
በፊትህ ስለ ተመላለሰ፣ ለባሪያህ ታላቅ ቸር
ነትን አሳይተኸዋል፤ ይህ ታላቅ ቸርነት እን
ዲቀጥል በማድረግ ዛሬም በዙፋኑ ላይ የሚ
ቀመጥ ልጅ ሰጥተኸዋል።

7"እግዚአብሔር ስምባኪ ሆይ፤ ባሪያህ በአ
ባቴ በዳዊት እግር ተተክቼ እንድነግሥ
አድርገሃል፤ እኔ ግን ገና ትንሽ ልጅ ስለ
ሆንሁ፣ መውጫና መግቢያዬን አላውቅም።
8ባሪያህ አንተ በመረጥኸው ሕዝብ፣ ከብዛ
ቱም የተነሣ ሊቈጠር በማይችል ታላቅ ሕዝብ
መካከል ይገኛል። 9ስለዚህ መልካሙንና
ክፉውን በመለየት ሕዝብህን ማስተዳደር
እንዲችል ለባሪያህ አስተዋይ ልብ ስጠው፤

3፥4 ኢሱ9፥3
3፥5 1ነገ9፥2፤11፥9፤ ማቴ7፥7፤27፥9
3፥6 ዘፍ17፥1፤ 1ነገ1፥48
3፥7 ዘኍ27፥17፤ 1ዜና22፥5፤29፥1፤ ኤር1፥6
3፥8 ዘፍ12፥2፤ ዘዳ7፥6፤1ዜና27፥23
3፥9 ዘዳ1፥16፤ 2ሳሙ14፥17፤2ቆሮ 2፥16፤ዕብ5፥14፤ ያዕ1፥5
3፥11 1ዜና22፥12፤ ያዕ4፥3
3፥12 2ሳሙ14፥ 20፤1ነገ4፥29:30:31፤ 5፥12፤10፥23፤መክ 1፥16፤1ዮሐ5፥1415
3፥13 1ነገ10፥23፤ 2ዜና9፥22፤ኅህ13፥26፤ ምሳ3፥12:16፤8፥18፤ ማቴ6፥33፤ኤፌ3፥20
3፥14 1ነገ9፥4፤መዝ 25፥13፤61፥6፤101፥2 ፤128፥1፤ምሳ3፥12:16
3፥15 ቍ5፤ዘፍ28፥ 16፤ዘሌ6፥813፤7፥11- 21፤አስ1፥3:9፤2፥18፤ 5፥8፤6፥14፤9፥17፤ዳን 5፥1

እለዚያማ ይህን ታላቅ ሕዝብህን ማን ሊያ
ስተዳድር ይችላል?"

10ሰሎሞን ይህን በመለመኑ ጌታ ደስ አለው፤
11ስለዚህ እንዲህ አለው፤ "ለራስህ ረጅም
ዕድሜ፣ ብልጽግና እንድታገኝ ወይም ጠላ
ቶችህ እንዲጠፉልህ ሳይሆን፣ በትክክል
ማስተዳደር እንድትችል ማስተዋልን ስለ ጠየ
ቅህ፣ 12ይህንኑ አደርግልሃለሁ፤ ከአንተ በፊት
ማንም ያልነበረውን፣ ከአንተም በኋላ ማንም
የማያገኘውን ጥበብና አስተዋይ ልቡና እሰ
ጥሃለሁ፤ 13ከዚህም በላይ አንተ ያልጠየቅኸ
ውን ብልጽግናና ክብር እሰጥሃለሁ፤ ይኸ
ውም በሕይወት ዘመንህ የሚተካከልህ ማንም
ንጉሥ እንዳይኖር ነው። 14አባትህ ዳዊት
እንዳደረገው በመንገዴ ብትሄድ፣ ሥርዐቴ
ንና ትእዛዜን ብትጠብቅ ዕድሜህን አረዝ
መዋለሁ።" 15ሰሎሞንም ከእንቅልፉ ነቃ፤
እነሆ ሕልም መሆኑን ተረዳ።

ከዚያም ወደ ኢየሩሳሌም ተመልሶ፣ በጌታ
ኪዳን ታቦት ፊት ቆመ፤ የሚቃጠል መሥ
ዋዕትና የኅብረት መሥዋዕት[ሙ] አቀረበ፤
ለሹማምቱም ሁሉ ግብዣ አደረገ።

### ጥበብን የተሞላ ፍትሕ

16በዚህን ጊዜ ሁለት ዝሙት አዳሪዎች
ወደ ንጉሡ መጥተው ከፊቱ ቆሙ። 17ከእነ

ሙ15 በትውፊት *የሰላም መሥዋዕት* ይባላል

ጊዜ፣ ምናልባት የከነዓናውያንን ልማድ በመከተል በኰረብታዎች ላይ ምናልባትም በፊት በአል በሚመለክበት ኰረብታዎች ላይ መሠዊያቸውን ሠርተው አምላካቸውን እግዚአብሔርን ያመልኩ ነበር። በእነዚህ ኰረብታዎች ላይ፣ እስራኤላውያን አምልኮ ያካሂዱ ነበር የሚለው አመለካከት አከራካሪ ነው። እስራኤላውያን በአሕዛብ መሠዊያዎችና ኰረብታዎች ላይ፣ እግዚአብሔርን እንዳያመልኩ ታዝዘዋል (ዘኍ 33፥52፤ ዘዳ 7፥5፤ 12፥3)። መሠዊያዎች የሚሠሩት፣ እግዚአብሔር በመረጠው ሥፍራ ብቻ መሆን እንደ አለበት ግልጽ ነው (ዘፀ 20፥24፤ ዘዳ 12፥5:8:13-14 ይመ)። ከላይ የተጠቀሱትን ሁኔታዎች ተፈጻሚ ለማድረግ፣ ብዙ መሠዊያዎችን መሥራት ክልክል መሆኑ ወይም አለመሆኑ ግልጽ አይደለም (19፥10:14፤ ዘሌ 26፥30-31፤ ዘዳ 12፤ 1ሳሙ 9፥12 ይመ)። በሰሎሞን ዘመን፣ እነዚህን ትእዛዞች ችላ ብለው፣ በአሕዛብ የማ ምለኪያ ኰረብታዎች ላይ፣ እግዚአብሔርን ማምለክ የጀመሩ ይመስላል። ይህ ሁኔታ እግዚአብሔርን ከማምለክ እንዲያፈገፍጉና እግዚአብሔርን ከከነዓናውያን አማልክት ጋር አጣምረው እንዲያመልኩ ስለሚያደርግ፣ (2ነገ 17፥7-18፤ 21፥2-9፤ 23፥4-25) በጥብቅ የተከለከለ ነው። *ቤተ መቅደስ ስላልተሠራ፤* ቤተ መቅደስ ከመሠራቱ በፊት፣ በተለያዩ ቦታዎች ላይ እግዚአብሔርን ማምለክ፣ ትክክል ነው ተብሎ ይታመን ነበር (መሳ 6፥24፤ 13፥19፤ 1ሳሙ 7፥17፤ 9፥12-13 ይመ)።

3፥3 *ይሁን እንጂ፤* የሰሎሞን ዋነኛው ስሕተት፣ በዘመነ መንግሥቱ መጀመሪያ ገደማ ላይ የማምለኪያ ቦታዎችን አጠቃቀም በተመለከተ፣ የሙሴን ሕግ አለመፈጸሙ ነው።

3፥4 *ከሁሉ የሚበልጠው የማምለኪያ ኰረብታ፤* ገባዖን እስፈላጊ ከተማ ልትሆን የቻለችበት ምክንያት፣ የማደሪያው ድንኳንና ጥንታዊው የናስ መሠዊያ በዚያ ስለ ነበሩ ሲሆን፣ (1ዜና 21፥29፤ 2ዜና 1፥2-6 ይመ)። ፍልስጥኤማውያንም ሴሎን ባወደሙ ጊዜ (የ1ሳሙ 7፥1 ማብ ይመ)፣ እነዚህ ከጥፋት ተርፈው ነበር። *ገባዖን፤* እስራኤላውያን፣ ከነዓንን ድል ባደረጉበት ጊዜ (ኢያ 9፥3-27)፣ ገባዖናውያን የሰላም ስምምነት ለመፈጸም ኢያሱንና እስራኤልን አታለሉ። ይህች ከተማ በመጀመሪያ ለብንያም ነገድ ተሰጥታ ነበር፤ በኋላ ግን ለሌዋውያን ተሰጠች (ኢያ 18፥25፤ 21፥17)። ከገባዖናውያን ጋር የተደረገውን ስምምነት ሳኦል በማፍረሱ ከዘሩ ሰባት ሰዎችን በመግደል ዳዊት ተበቀለው (2ሳሙ 21፥1-9 ይመ)።

3፥5 *በሕልም፤* በሕልም የሚሰጥ መገለጥ፣ በብሉይ ኪዳን እንደሚገኝ ሁሉ (ዘፍ 28፥12፤ 31፥11፤ 46፥2፤ ዘኍ 12፥6፤ መሳ 7፥13፤ ዳን 2፥4፤ 7፥1 ይመ)፣ በአዲስ ኪዳንም ይገኛል (ማቴ 1፥20፤ 2፥12:22 ይመ)።

3፥6 *ቸርነትን፤* የዕብራይስጡ ቃል፣ ኪዳኑ የተነሣ እግዚአብሔር የሚያደርገውን በጎነት ያመለክታል (የ2ሳሙ 7፥15 ማብ ይመ)። ለዳዊት የሰጠውን ተስፋ ስለ ፈጸመ (2ሳሙ 7፥8-16)፣ ሰሎሞን እግዚአብሔርን አመሰገነ።

3፥7 *ገና ትንሽ ልጅ ስለ ሆንሁ፤* ዳዊት በነገሠ በአርባኛው ዓመት አጋማሽ ሰሎሞን እንደ ተወለደ ይገመታል፤ ይኸውም ሰሎሞን በዙፋን ላይ በተቀመጠ ጊዜ የሃያ ዓመት ጕልማሳ ስለ ነበረ፣ (2፥11-12) የተሰጠውን ኀላፊነት ለመወጣት በቂ ልምድና ችሎታ አልነበረውም (ከኤር 1፥6 ጋር ያነጻጽሩ)።

3፥8 *ከብዛቱም የተነሣ ሊቈጠር በማይችል ታላቅ ሕዝብ፤* በግብፅ ይኖር ከነበረው ቤተ ሰብ አነስተኛ ቍጥር ተነሥቶ (ዘፍ 46፥26-27፤ ዘጸ 7፥7)፣ እግዚአብሔር ለአብርሃም (ዘፍ 13፥16፤ 22፥17-18) እና ለያዕቆብ (ዘፍ 32፥12) በሰጠው ተስፋ መሠረት ብዛቱ እስከማይቈጠር ድረስ፣ የእስራኤላውያን ቍጥር እየጨመረ ሄደ፤ 4፥20 ይመ።

3፥11 *ረጅም ዕድሜ፣ ብልጽግና … ጠላቶችህ እንዲጠፉልህ፤* ይህ የቅርብ ምሥራቅ አገሮች ነገሥታት የተለመደ ምኞት ነበር።

3፥12 *ማንም ያልነበረውን፤* 4፥29-34፤ 10፥1-13 ይመ።

3፥13 *ያልጠየቅኸውን … እሰጥሃለሁ፤* በሉቃ 12፥31 ኢየሱስ ከሰጠው ተስፋ ጋር ያነጻጽሩ።

3፥14 *በመንገዴ ብትሄድ … ዕድሜህን አረዝመዋለሁ፤* ከዘዳ 6፥2፤ 17፥20፤ 22፥7 ይመ። ሰሎሞን አባቱ ዳዊት እንዳደረገው ሁሉ በኪዳኑ ታማኝ በመሆንና በመታዘዝ አልጸናም፤ ከዚህም የተነሣ ከሥልሳ ዓመት በላይ አልኖረም (የቍ 7 ማብ ይመ፤ ከ11፥42 ጋር ያነጻጽሩ)።

3፥15 *በጌታ ኪዳን ታቦት፤* የ6፥19፤ የ2ሳሙ 6፥2 ማብ ይመ። *የኅብረት መሥዋዕት፤* 1ሳሙ 11፥15 ማብ ይመ።

3፥16 *ሁለት ዝሙት አዳሪዎች፤* እነዚህ ዝሙት አዳሪዎች ከእስራኤላውያን ወይም ከኢያቡሳውያን ወገን መሆናቸው አይታወቅም፣ ምናልባት ግን ኢያቡሳውያን ሳይሆኑ አይቀሩም። *ወደ ንጉሡ መጥተው፤* እስራኤላውያን (በግዛቷ የሚኖሩ ሌሎች ሕዝቦችም) የበታች ዳኞችን ዐልፈው (ዘዳ 16፥18)፣ በቀጥታ ንጉሡ ዘንድ በመቅረብ፣ ጕዳያቸውን ሊያሰሙ ይችሉ ነበር (2ነገ 8፥3፤ 2ሳሙ 15፥2 ይመ)።

ርሱም አንዲቱ እንዲህ አለች፣ “ጌታዬ
ሆይ፤ ይህች ሴትና እኔ በአንድ ቤት አብ
ረን እንኖራለን፤ አብራኝ እያለችም እኔ
ልጅ ወለድሁ፤ [18]እኔ ከወለድሁ ከሦስት
ቀን በኋላም፣ ይህች ሴት ወለደች፤ ያለነው
እኛ ብቻ ነን፤ ከሁለታችን በቀር በዚያ
ቤት ማንም አልነበረም።
[19]“የዚህች ሴት ሕፃን ልጅ ስለ ተኛችበት
ሌሊት ሞተ። [20]ስለዚህም በእኩለ ሌሊት
ተነሥታ፣ እኔ አገልጋይህ ተኝቼ ሳለሁ
ልጄን ከአጠገቤ ወሰደችው፤ ከዚያም የእኔን
ልጅ ራሷ ታቅፋ፣ የሞተ ልጇን አምጥታ
በዕቅፌ አደረገችው። [21]በማግሥቱ ልጄን
ላጠባ ስነሣ እነሆ ሞቶአል፤ ነገር ግን በማ
ለዳ ብርሃን ትክ ብዬ ስመለከተው እኔ የወ
ለድሁት ልጅ አለመሆኑን ተገነዘብሁ።
[22]ሌላዪቱም ሴት፣ “ነገሩ አንቺ እንደ
ምትዪው አይደለም፤ የሞተው የአንቺ፣ በሕ
ይወት ያለውም የእኔ ነው” አለች።
የመጀመሪያዋ ሴት ግን አጠንክራ፣ “አይ
ደለም! የሞተው የአንቺ፣ በሕይወት ያለው
ግን የእኔ ልጅ ነው” አለች፤ በዚህ ሁኔ
ታም በንጉሡ ፊት ተከራከሩ።
[23]ንጉሡም፣ “ይህችኛዪቱ፣ ‘የእኔ ልጅ
በሕይወት ያለው ነው፣ የአንቺ የሞተው
ነው’ ትላለች፤ ያችኛዪቱ ደግሞ፣ ‘አይደለም
የአንቺ ልጅ ሞቶአል፣ በሕይወት ያለው
የእኔ ነው’ ትላለች” አለ።
[24]ከዚያም ንጉሡ፣ “እንግዲያውስ ሰይፍ
አምጡልኝ” አለ፤ ለንጉሡም ሰይፍ አመጡ
ለት። [25]በዚህ ጊዜ ንጉሡ፣ “በሉ በሕይወት
ያለውን ልጅ ከሁለት ክፈሉና ለአንዷ ግማ
ሹን፣ ለሌላዪቱም ግማሹን ስጡ” ብሎ አዘዘ።
[26]በሕይወት ያለው ልጅ እናት ለልጇ
እጅግ ስለ ራራች ንጉሡን፣ “ጌታዬ ሆይ፤
እባክህ በሕይወት ያለውን ሕፃን ለእርሷ
ስጣት፤ አትግደለው” አለች።
ሌላዪቱ ግን፣ “ለእኔም ሆነ ለአንቺ አይ

3፥26 ዘፍ43፥30፤ ኢሳ49፥15፤63፥15፤ ኤር31፥20፤ ሆሴ11፥8
3፥28 2ሳሙ14፥20፤ ቈላ2፥3
4፥2 1ነገ12፥6፤ 1ዜና6፥10፤2ዜና26፥17፤ ኢዮ12፥12
4፥3 2ሳሙ8፥16:17
4፥4 2ሳሙ8፥17:18
4፥6 ዘፍ41፥40፤ 49፥15፤2ሳሙ20፥24
4፥7 ቍ27
4፥8 ኢያ24፥33
4፥9 ኢያ15፥10፤ መሳ1፥35
4፥10 ኢያ12፥17፤ 15፥35

ሰጥም፤ ሁለት ላይ ይከፈል!” አለች።
[27]ከዚህ በኋላ ንጉሡ፣ “በሉ በሕይወት
ያለውን ሕፃን ለመጀመሪያዪቱ ሴት ስጧት፤
አትግደሉት፤ እናቱ እርሷ ናት” አለ።
[28]እስራኤላውያን ሁሉ ንጉሡ የሰጠውን
ፍርድ ሲሰሙ ፈሩት፤ ፍትሕ ለመስጠት
የእግዚአብሔርን ጥበብ የታደለ መሆኑን አይተዋልና።

## የሰሎሞን ሹማምት

4 ንጉሥ ሰሎሞን በእስራኤል ሁሉ ላይ
ነገሠ፤ [2]ዋና ዋናዎቹ ሹማምቱም እነዚህ
ነበሩ፤

የሳዶቅ ልጅ ዓዛርያስ፣ ካህን፤
[3]የሺሻ ልጆች ኤሊሖሬፍና
አኪያ፣ ጸሓፊዎች፤
የአሒሉድ ልጅ ኢዮሣፍጥ፣ ታሪክ
ጸሓፊ፤
[4]የዮዳሄ ልጅ በናያስ፣ የሰራዊቱ ዋና
አዛዥ፤
ሳዶቅና አብያታር፣ ካህናት፤
[5]የናታን ልጅ ዓዛርያስ፣ የአውራጃ
ገዦች የበላይ ኀላፊ፤
የናታን ልጅ ዛቡድ፣ ካህንና የንጉሡ
የቅርብ አማካሪ፤
[6]አሒሳር፣ የቤተ መንግሥቱ አዛዥ፤
የዓብዳ ልጅ አዶኒራም የግዳጅ ሥራ
ተቈጣጣሪ።

[7]እንዲሁም ሰሎሞን ለንጉሡና ለንጉሡ
ቤት የሚሆነውን ቀለብ ከመላው እስራኤል
የሚሰበስቡ ዐሥራ ሁለት የአውራጃ ገዦች
ነበሩት፤ እነዚህም እያንዳንዳቸው በዓመት
ውስጥ የወር ቀለብ የሚያቀርቡ ነበሩ። [8]ስማ
ቸውም እንደሚከተለው ነው፤

ቤንሑር፣ በኰረብታማው በኤፍሬም
ምድር፤
[9]ቤንዴቄር፣ በማቃጽ፣ በሻዓልቢም፣
በቤትሳሚስ፣ በኤሎንቤትሐናን፤
[10]ቤንሔሴድ፣ በአሩቦት ውስጥ
የሚገኙት ሰኰትና የአፌር አገር

3፥17 *በአንድ ቤት አብረን እንኖራለን፤* በጥንት የቅርብ ምሥራቅ አገሮች ከተሞች የዝሙት አዳሪ ቤቶች ነበሩ።

3፥28 *የአምላክን ጥበብ የታደለ መሆኑን አይተዋልና፤* መልካሙንና ክፉውን የሚለይ አስተዋይ ልቡና (ቍ 9:12) እንዲኖረው በለመነው መሠረት፣ እግዚአብሔር የጠየቀውን እንደ ሰጠው ይህ ሁኔታ በሚገባ ይገልጻል።

4፥1 *በእስራኤል ሁሉ ላይ ነገሠ፤* አባቱ ዳዊት እንደ ነገሠው ሁሉ (2ሳሙ 8፥15 ይመ) ሰሎሞንም የነገሠው በአልተከፋፈለው የእስራኤል መንግሥት ላይ ነበር።

4፥2 *ልጅ፤* በ2ሳሙ 15፥27:36 እና በ1ዜና 6፥8-9 እንደ ተመለከተው፣ ዓዛርያስ የአኪማአስ ልጅ፣ የሳዶቅም የልጅ ልጅ ነበር (የ2፥8 ማብ ይመ)። የሳዶቅ ልጅ አኪማአስ በመሞቱ፣ የልጅ ልጅ የሆነው ዓዛርያስ ሳዶቅን ተክቶታል። *የሳዶቅ፤* 2፥27:35 ይመ።

4፥3 *የሺሻ፤* የ2ሳሙ 8፥17 ማብ ይመ። *ጸሓፊዎች፤* የ2ሳሙ 8፥17 ማብ ይመ። *የአሒሉድ ልጅ ኢዮሣፍጥ፤* በዳዊት ቤተ መንግሥት ያገለግል የነበረ ሰው ነው (2ሳሙ 8፥16 ይመ)። *ታሪክ ጸሓፊ፤* የ2ሳሙ 8፥16 ማብ ይመ።

4፥4 *በናያስ፤* የሰራዊቱ ዋና አዛዥ በመሆን፣ ኢዮአብን የተካ ሰው ነው (2፥35፤ 2ሳሙ 8፥18 ይመ)። *ሳዶቅና አብያታር፤* በሰሎሞን ዘመነ መንግሥት መጀመሪያ፣ አብያታር ከክህነቱ ሲወገድ (2፥27:35)፣ ሳዶቅ ደግሞ የልጅ ልጁ በሆነው በዓዛርያስ ተተክቶ ነበር (ቍ 2)።

4፥5 *የናታን፤* ነቢዩ ናታን (1፥11) ወይም የዳዊት ልጅ (2ሳሙ 5፥14) ሊሆን ይችላል። *የአውራጃ ገዦች፤* ቍ 7-19 ይመ። *ካህንና፤* የ2ሳሙ 8፥18 ማብ ይመ። *የንጉሡ የቅርብ አማካሪ፤* የ2ሳሙ 15፥37 ማብ ይመ።

4፥6 *የቤተ መንግሥቱ አዛዥ፤* በብሉይ ኪዳን ለመጀመሪያ ጊዜ፣ በአንደኛና በሁለተኛ ነገሥት በተደጋጋሚ (1ነገ 16፥9፤ 18፥3፤ 2ነገ 18፥18:37፤19፥2) የተጠቀሰ ኀላፊነት ነው፤ የቤተ መንግሥትም አስተዳዳሪና የንጉሡ ሀብት ጠባቂ፣ ይኸው ባለ ሥልጣን ሊሆን ይችላል። *አዶኒራም፤* በሰሎሞን ዘመነ መንግሥት ብቻ ሳይሆን፣ ከእርሱ በፊት በዳዊት (2ሳሙ 20፥24) በኋላም በሮብዓም ዘመነ መንግሥት (1ነገ 12፥18) አገልግሎአል። *የግዳጅ ሥራ፤* የ9፥15፤ የ2ሳሙ 20፥24 ማብ ይመ።

4፥7 *ሰሎሞን... ዐሥራ ሁለት የአውራጃ ገዦች ነበሩት፤* ዐሥራ ሁለቱ ነገዶች፣ በእርሻ ምርት ውጤታቸው የተለያዩ ስለሚሆኑ፣ የአውራጃዎች አከፋፈል፣ ከነገዶች ግዛት ጋር ተመሳሳይነት የለውም። የሰሎሞን አገዛዝ የተከተለው የአስተዳደር ሥርዐት ግን፣ ነገዶች በታማኝነት የሚተዳደሩበትን ቀደም ሲል የነበረውን የግዛት ድንበር የሚቀበል አልነበረም፤ ይህም ምናልባት ለመንግሥቱ መናጋት ከፍተኛ አስተዋፅኦ ነበረው።

4፥8 *ቤንሑር፤* በዕብራይስጥ “ቤን” ማለት ልጅ ማለት ነው።

በሙሉ የእርሱ ነበር፤
11ቤን አሚናዳብ፤ በናፎት[ሀ] ዶር፣
እርሱም የሰሎሞንን ልጅ ጣፈትን
አግብቶ የነበረ ነው፤
12የአሒሉድ ልጅ በዓና፣ በታዕናክና
በመጊዶ እንዲሁም ከጻርታን ቀጥሎ
ቍልቍል እስከ ኢይዝራኤል ባለው
በቤትሳን ሁሉ፣ ከዚያም ዮቅምዓምን
ተሻግሮ እስከ አቤልምሖላና ድረስ፣
13ቤንጌበር፣ በገለዓድ ራሞት ከተማ
እዚያው ገለዓድ ውስጥ የምናሴ
ልጅ የኢያዕር መንደሮች፣ በባሳንም
የአርጎብ አውራጃ እንዲሁም በሮቻ
ቸው የናስ መወርወሪያ በሆኑ ሥልሳ
ባለ ቅጥር ታላላቅ ከተሞች፤
14የዒዶ ልጅ አሒናዳብ፤ በማሃናይም፣
15አኪማአስ በንፍታሌም፣ እርሱም
የሰሎሞንን ልጅ ባስማትን አግብቶ
የነበረ ነው፤
16የኩሲ ልጅ በዓና፤ በአሴርና በበዓሎት፣
17የፋሩዋ ልጅ ኢዮሣፍጥ በይሳኮር፣
18የኤላ ልጅ ሳሚ በብንያም፣
19የኡሪ ልጅ ጌበር፤
በአሞራውያን ንጉሥ በሴዎን ምድር፣
በባሳን ንጉሥ በዐግ አገር፣ እርሱም
የአውራጃው ብቸኛ ገዥ ነበር።

## ለሰሎሞን በየቀኑ የሚገባለት ቀለብ

20የይሁዳና የእስራኤል ሕዝቦች ብዛታቸው
እንደ ባሕር ዳር አሸዋ ሆነ፤ ይበሉ፣ ይጠ
ጡና ይደሰቱም ነበር። 21ሰሎሞንም ከወንዙ[ለ]
አንሥቶ እስከ ፍልስጥኤማውያን ምድር፣ ከዚያም
እስከ ግብፅ ዳርቻ ያሉትን መንግሥታት
ሁሉ ገዛ፤ እነዚህም አገሮች ግብር አመጡለት፤
በሕይወት ዘመኑም ሁሉ ተገዙለት።
22ለሰሎሞን በየቀኑ የሚገባለትም ቀለብ
ይህ ነበር፤ ሠላሳ ኮር[ሐ] ማለፊያ ዱቄት፣
ሥልሳ ኮር[መ] መናኛ ዱቄት፣ 23ዐሥር
ቅልብ ሰንጋዎች፣ ሃያ ግጦሽ መሬት ላይ
የሚውሉ በሬዎች፣ መቶ በግና ፍየል እንዲ
ሁም ዋሊያ፣ ሚዳቋ፣ የበረሓ ፍየልና ምርጥ
አዕዋፍ። 24ከወንዙ በስተ ምዕራብ፣ ከቲፍሳ
እስከ ጋዛ ያሉትን መንግሥታት ስለ ገዛ፣
በሁሉም አቅጣጫ ሰላም ሆኖለት ነበር።
25በሰሎሞን ዘመን ሁሉ ከዳን አንሥቶ እስከ
ቤርሳቤህ ያለው ይሁዳና እስራኤል፣
እያንዳንዱ ሰው ከወይኑና ከበለሱ ጥላ ሥር
በሰላም ለመኖር በቃ።
26ሰሎሞን ሠረገላ የሚጐትቱ ፈረሶች የሚ
ያድሩበት አራት ሺህ ጋጣና ዐሥራ ሁለት
ሺህ ፈረሶች[ሠ] ነበሩት[ረ]።
27የየአውራጃው ሹማምትም በየወር ተራ
ቸው ንጉሡን ሰሎሞንንና ወደ ንጉሡ ማእድ
የሚቀርቡትን ሁሉ ምንም ሳያጓድሉ ይቀ
ልቡ ነበር፤ 28እንዲሁም ለሠረገላ ፈረሶችና
ለፈጣን ፈረሶች የተመደበውን ገብስና ጭድ
ከተፈለገው ቦታ ድረስ ያመጡ ነበር።

## የሰሎሞን ጥበብ

29እግዚአብሔር ለሰሎሞን ጥበብንና እጅግ ታላቅ
ማስተዋልን እንዲሁም በባሕር ዳር እንዳለ
አሸዋ የልብ ስፋትን ሰጠው። 30የሰሎሞን
ጥበብ ከምሥራቅ ሰዎች ሁሉ ጥበብ በጣም
የላቀ ከግብፅም ጥበብ ሁሉ የበለጠ ነበር፤
31እርሱም ከማንም ሰው ይልቅ ጥበበኛ ነበር፣
ከኢይዝራኤላዊው ከኤታን፣ ከማሖል ልጆች
ከሄማንና ከከልቀድ ደግሞም ከደራል ይልቅ
ጥበበኛ ነበር፤ ዝናውም በዙሪያው ባሉት
አሕዛብ ሁሉ ተሰማ። 32እርሱም ሦስት ሺህ
ምሳሌዎችን ተናገረ፤ የመሐልዩም ቍጥር

4፥11 ኢሱ11፥2
4፥12 ኢሱ3፥16፤ 17፥11፤መሳ7፥22፤ 1ዜና6፥68
4፥13 ዘኁ32፥40፡ 41፤ዘዳ3፥4
4፥14 ኢሱ13፥26
4፥15 2ሳሙ15፥27
4፥16 2ሳሙ15፥32
4፥18 1ነገ1፥8
4፥19 ዘዳ3፥810፤ ኢሱ12፥2፡4
4፥20 ዘፍ12፥2፤ 32፥12፤1ዜና22፥9
4፥21 ዘፍ2፥14፤ዘፀ 23፥31፤መሳ3፥15፤ 2ዜና9፥26፤ዕዝ4፥20፤ መዝ72፥8፡11፤ሰቆ 1፥1፤ሕዝ16፥13
4፥22 1ነገ10፥5
4፥23 ነህ5፥18
4፥24 ኢሱ14፥15፤ 2ነገ15፥16
4፥25 ዘዳ8፥8፤መሳ 20፥1፤2ነገ18፥31፤ 1ዜና22፥9፤መዝ105፥ 33፤ኢሳ36፥16፤ኤር 5፥17፤23፥6፤ሕዝ28፥ 26፤39፥26፤ኢል2፥ 22፤ሚክ4፥4፤ዘካ3፥10
4፥26 ዘዳ17፥16
4፥27 ቍ7
4፥29 ዘፍ32፥12፤ 1ነገ3፥12
4፥30 ዘፍ25፥6፤ መሳ6፥3፤ኢሳ19፥11፤ ዳን1፥20፤ማቴ2፥1፤ ሐሥ7፥22
4፥31 1ነገ3፥12
4፥32 መዝ78፥63፤ ምሳ1፥1፤10፥1፤25፥1፤ መክ12፥9፤ማሕ 1፥1፤ሕዝ33፥32

[ሀ]11 ወይም *በናፎት ቆመት* ተብሎ ሊተረጐም ይችላል
[ለ]21 በዚህና በቍ 24 ላይ የተጠቀሰው የኤፍራጥስ ወንዝ ነው።
[ሐ]22 6.6 ኪሎ ግራም ያህል ነው።
[መ]22 13.2 ኪሎ ግራም ያህል ነው።
[ሠ]26 ዕብራይስጡና አንዳንድ የሰብዓ ሊቃናት ትርጒሞች *አርባ* ይላሉ።
[ረ]26 ወይም *ሠረገለኞች* ተብሎ መተርጐም ይችላል።

4፥11 *ቤን አሚናዳብ፤* የዳዊት ወንድም የአቢናዳብ (1ሳሙ 16፥18፤ 17፥13 ይመ) ልጅ ሲሆን፣ እርሱም ለሰሎሞን የአኅት ልጅና የልጁም ባል ነበር።

4፥12 *የአሒሉድ ልጅ በዓና፤* የታሪክ ጸሓፊው የኢዮሣፍጥ (ቍ 3) ወንድም ሳይሆን አይቀርም።

4፥16 *የኩሲ ልጅ በዓና፤* (የ2ሳሙ 15፥32፡37 ማብ ይመ)። የዳዊት ታማኝ አማካሪ የነበረው ሰው ልጅ ይሆናል።

4፥18 *የኤላ ልጅ ሳሚ፤* በ1፥8 ላይ የተጠቀሰው ሳሚ ሊሆን ይችላል።

4፥20 *ብዛታቸው እንደ ባሕር ዳር አሸዋ፤* 3፥8 እና ማብ እንዲሁም ቍ 29፤ ዘፍ 22፥17፤ 2ሳሙ 17፥11፤ ኢሳ 10፥22፤ ኤር 33፥22፤ ሆሴ 1፥10 ይመ ከዘፍ 41፥49፤ ኢሱ 11፥4፤ መሳ 7፥12፤ ከመዝ 78፥27 ጋር ያነጻጽሩ። *ይበሉ፣ ይጠጡና ይደሰቱም ነበር፤* ይሁዳና እስራኤል በለጸጉ (5፥4 ይመ)።

4፥21 *ከወንዙ አንሥቶ እስከ ፍልስጥኤማውያን ምድር፣ ከዚያም እስከ ግብፅ ዳርቻ፤* የሰሎሞን መንግሥት የግዛት ዳርቻ፣ ለአብርሃም ተስፋ የተሰጠውን ምድር የሚያካልል ነበር (የ2ሳሙ 8፥3 ማብ ይመ)። ነገር ግን ኤዶምያስና (11፥14-21) ደማስቆስ (11፥23-25) ያምፁበት ነበር።

4፥22 *ለሰሎሞን በየቀኑ የሚገባለትም ቀለብ፤* ይህም ለቤተ ሰቡ፣ በቤተ መንግሥቱ ውስጥ ላሉ አገልጋዮች፣ ለባለ ሥልጣኖችና ለቤተ ሰቦቻቸው የሚሰጥ ነበር።

4፥24 *ከቲፍሳ፤* በኤፍራጥስ ወንዝ ምዕራባዊ ዳርቻ አካባቢ የምትገኝ ከተማ ነበረች። *ጋዛ፤* በሜድትራኒያን ጠረፍ አካባቢ የምትገኝ የፍልስጥኤማውያን ደቡባዊ ከተማ ነበረች። *በሁሉም አቅጣጫ ሰላም ሆኖለት ነበር፤* በሰሎሞን ዘመነ መንግሥት፣ እስ ራኤል የነበራት ድል፣ ሰላምና ብልጽግና ከፍተኛ ደረጃ ላይ ደርሶ ነበር (ቍ 20-28)። በፖለቲካና ለኑሮ በሚያስፈልጉ ነገ ሮች፣ የሰሎሞን ዘመነ መንግሥት ድል የተገኘበት ቢሆንም ሰሎ ሞን ጣዖትን ወደ ማምለክ በማዘንበሉ፣ ከመንፈሳዊ ሁኔታ አን ጻር ሲታይ፣ የእርሱ ዘመነ መንግሥት መንፈሳዊ ውድቀትን ያስ ከተለ ነበር (11፥1-8)።

4፥26 *አራት ሺህ፤* በ1ነገ 10፥26 እና በ2ዜና 1፥14 ላይ ሰለሞን አንድ ሺህ አራት መቶ ሠረገሎች እንደ ነበሩት ተገ ልጾአል፤ ይህም፣ እያንዳንዱን ሠረገላ የሚጐትቱ ሁለት ፈረሶች እና አንድ ሺህ ሁለት መቶ ተጠባባቂ ፈረሶች የሚይዝ ጋጣ ማዘ ጋጀቱን ያመለክታል።

4፥29 *በባሕር ዳር እንዳለ አሸዋ፤* የቍ 20 ማብ ይመ።

4፥30 *ከምሥራቅ ሰዎች፤* ይህ ሐረግ ጠቅለል ባለ መልኩ ግብፅ እስራኤልን እንደምታዋስን ሁሉ ይህ ሐረግ በሰሜን ምሥ ራቅና በምሥራቅ በኩል እስራኤልን የሚያዋስኗትን የመስጴጦ ምያንና (ዘፍ 29፥1 ይመ) የዐረቢያን (ኤር 49፥28፤ ሕዝ 25፥4፡10 ይመ) ሕዝቦች ጠቅለል ባለ መልኩ የሚያመለክት ነው። *ከግብፅም ጥበብ፤* ዘፍ 41፥8፤ ዘፀ 7፥11፤ ሐሥ 7፥22 ይመ። የግብፅ ጥበብ ጽሑፍ ለአብነት ያህል፣ በታሆቴፕ እና በአሜኔሞፔ ምሳሌዎች ውስጥ ይገኛሉ።

4፥31 *ከማንም ሰው ይልቅ ጥበበኛ ነበር፤* (ሉቃ 11፥31 ይመ)። *ከኢይዝራኤላዊው ከኤታን፤* የመዝ 89 ርእስ ይመ። *ከሄ ማንና፣ ከከልቀድ፣...ከደራል፤* የ1ዜና 2፥6-7 ማብ ይመ።

4፥32 *ሦስት ሺህ ምሳሌዎችን፤* ከእነዚህ ጥቂቶቹ ብቻ

ሺህ አምስት ነበር። 33ከሊባኖስ ዝግባ አን
ሥቶ በቅጥር ግንብ ላይ እስከሚበቅለው
ሂሶጵ ስለ ዕፀዋት ተናግሮአል፤ እንዲሁም
ስለ እንስሳት፣ ስለ ወፎች፣ በሆዳቸው ስለ
ሚሳቡ እንስሳትና ስለ ዓሦችም ተናግሮ
አል፤ 34ጥበቡን ከሰሙት ከዓለም ነገሥታት
ሁሉ የተላኩ፣ የየአገሩ ሰዎች ሁሉ የሰሎሞ
ንን ጥበብ ለማድመጥ መጡ።

### ቤተ መቅደሱን ለመሥራት የተደረገ ዝግጅት

5፥1-16 ተጓ ምብ - 2ዜና 2፥1-18

5 የጢሮስ ንጉሥ ኪራም በዘመኑ ሁሉ
ለዳዊት ወዳጅ ስለ ነበር፣ ሰሎሞን በአ
ባቱ እግር ለመተካት መቀባቱን በሰማ ጊዜ፣
መልእክተኞቹን ወደ ሰሎሞን ላከ። 2ሰሎሞ
ንም እንዲህ የሚል መልእክት ወደ ኪራም
መልሶ ላከ፤

3"አባቴ ዳዊት በዙሪያው ሁሉ ከገጠ
መው ጦርነት የተነሣ፣ እግዚአብሔር ጠላ
ቶቹን ከእግሩ በታች እስኪጥልለት
ድረስ ስለ ስሙ ለእግዚአብሔር ስም
ቤተ መቅደስ መሥራት እንዳልቻለ
ታውቃለህ። 4አሁን ግን ስለ ስሙ እግዚ
አብሔር በዙሪያዬ ሁሉ ሰላም ሰጥቶ
ኛል፤ ጠላትም የለብኝም። 5እነሆ፣ እግ
ዚአብሔር ለአባቴ ለዳዊት፣ 'ለስሜ
ቤተ መቅደስ የሚሠራልኝ ከአንተ
ቀጥሎ በዙፋንህ የማስቀምጠው ልጅህ
ነው' ብሎ እንደ ነገረው፣ ስለ ስሙ ለእ
ግዚአብሔር ስም ቤተ መቅደስ ለመ
ሥራት አስቤአለሁ።

6"ስለዚህ የሊባኖስ ዝግባ እንዲቈረ
ጥልኝ ትእዛዝ ስጥ፤ ሰዎቼ ከሰዎችህ
ጋር አብረው ይሠራሉ፤ የሰዎችህንም
ደመወዝ አንተ በወሰንኸው እከፍልሃ
ለሁ፤ ከሰዎቼ መካከል እንደ ሲዶናው
ያን ዕንጨት በመቍረጥ እስከዚህ የሠ
ለጠነ ሰው አለመኖሩን ራስህም ታው
ቃለህና።"

7ኪራም የሰሎሞን መልእክት በደረሰው
ጊዜ እጅግ ደስ ስላለው፣ "ይህን ታላቅ ሕዝብ
እንዲመራ ለዳዊት ጥበበኛ ልጅ ሰጥቶታ
ልና ዛሬ ምስጋና ለእግዚአብሔር ይግባው"
አለ።

8ስለዚህ ኪራም፣ ለሰሎሞን እንዲህ ሲል
ላከበት፤

"የላክኸው መልእክት ደርሶኛል፤ የዝ
ግባውንና የጥዱን ግንድ በማቅረብ ረገድ
የምትፈልገውን ሁሉ ለማድረግ ዝግጁ
ነኝ፤ 9ሰዎቼ ግንዱን ከሊባኖስ እስከ
ባሕሩ ድረስ ጐትተው ያወርዳሉ፤ እኔም
ግንዱ ሁሉ ታስሮ አንተ እስከ ወሰንኸው
ስፍራ በባሕር ተንሳፎ እንዲደርስ አደ
ርጋለሁ፤ እዚያም እኔ እፈታዋለሁ፣ አን
ተም ትወስደዋለህ፤ አንተም ለቤተ ሰቤ
ቀለብ በመስጠት ፍላጎቴን ታሟላለህ።"

10በዚህ ሁኔታ ኪራም ለሰሎሞን የሚያስ
ፈልገውን የዝግባና የጥድ ግንድ በሙሉ
ያቀርብለት ጀመር፤ 11ሰሎሞን ደግሞ ለኪ
ራም ቤተ ሰው ቀለብ እንዲሆን ሃያ ሺህ
የቆሮስ መስፈሪያ[*] ስንዴ፣ ሃያ ሺህ ኮር[†] ንጹሕ[‡]
የወይራ ዘይት ሰጠው፤ ይህን ባለ ማቋረጥ
በየዓመቱ ለኪራም ይሰጥ ነበር። 12እግዚአብሔ
ርም በገባለት ተስፋ መሠረት ለሰሎሞን

4፥33 ዘሌ14፥49
4፥34 2ዜና9፥23
5፥1 2ሳሙ5፥11
5፥3 2ሳሙ7፥5፤ 22፥40፤1ዜና22፥8፤ 28፥3፤መዝ8፥6፤ 110፥1፤ማቴ22፥44፤ 1ቆሮ15፥25
5፥4 ኢሱ14፥15፤ 1ነገ11፥14:23፤1ዜና 22፥9፤ሉቃ2፥14
5፥5 ዘዳ12፥5፤ 2ሳሙ7፥13፤1ዜና17፥ 12፤1ቆሮ3፥16፤ራእ 21፥22
5፥6 1ዜና14፥1፤ 22፥4
5፥7 1ነገ10፥9፤ ኢሳ 60፥6
5፥9 ቍ11፤ ዕዝ3፥7፤ሕዝ 27፥17፤ሐሥ12፥20
5፥11 ቍ9

[*]11 4400 ኪሎ ሊትር ያህል ነው።
[†]11 ዕብራይስጡና የሰብዓ ሊቃናት ትርጒም ሃያ ኮር ይላሉ (2ዜና 2፥10 ይመ)
[‡]11 440 ኪሎ ሊትር ያህል ነው።

በመጽሐፈ ምሳሌ ውስጥ ተጽፈዋል።

4፥33 *ስለ እንስሳት፣ ስለ ወፎች፣ በሆዳቸው ስለሚሳቡ እንስሳትና ስለ ዓሦችም፤* ስለ እነዚህ እንስሳት ሰሎሞን ያለውን ዕውቀት ለአብነት ያህል በምሳ 6፥6-8፤ 26፥2-3:11፤ 27፥8፤ 28፥1:15 መመልከት ይቻላል።

4፥34 *ከዓለም ነገሥታት ሁሉ ... የየአገሩ ሰዎች ሁሉ፤* የቅርብ ምሥራቁን ዓለም የሚያመለክት ጠቅለል ያለ አገላለጽ ነው (ከዘፍ 41፥57 ጋር ያነጻጽሩ)።

5፥1 *የጢሮስ ንጉሥ ኪራም፤* ኪራም፣ ከዓ.ቅ.ክ. 978-944 ድረስ ጢሮስን ይገዛ ነበር፤ ቀደም ሲል በዓ.ቅ.ክ 993 በፊትም ከአባቱ ከአቢበዓል ጋር በአንድነት ይገዛ ነበር። ሰሎሞን ከመወለዱ በፊት፣ ኪራም ለዳዊት ቤተ መንግሥት ግንባታ የሚሆን የዝግባ እንጨትና ባለሙያ ሠራተኞችን ልኮአል (2ሳሙ 5፥11 ይመ)።

5፥3 *ቤተ መቅደስ መሥራት እንዳልቻለ፤* ዳዊት ቤተ መቅደሱን የመሥራት ዕድል ባይሰጠውም፣ የሥራውን ዕቅድና ለግንባታ አስፈላጊ የሆኑትን ዕቃዎች ሁሉ አዘጋጅቶ ነበር (1ዜና 22፥2-5፤ 28፥2 ይመ፤ እንዲሁም ከመዝ 30 ርእስ ጋር ያነጻጽሩ)።

5፥4 *ሰላም፤* እዚህ ላይ፣ "ጠላት ወይም አደጋ" እንደ ሌለባቸው የሚገልጽ ነው። እግዚአብሔር ለሕዝቡ (ዘፀ 33፥14፤ ዘዳ 25፥19፤ ኢሱ 1፥13:15) እና ለዳዊት (2ሳሙ 7፥11) የሰጠው ተስፋ በመፈጸሙ፣ (8፥56 ይመ) እስራኤላውያን ጕልበታቸውንና ሀብታቸውን ለታላቁ ንጉሥ በሚሠራው ቤት ላይ ለማዋል አመቺ ሁኔታ ነበር (የ2ሳሙ 7፥11 ማብ ይመ)።

5፥5 *ለስሜ፤* የተገለጠውን የእግዚአብሔን ባሕርይ ወይም እግዚአብሔር ራሱን መግለጹን ያመለክታል (8፥16፤ ዘፀ 20፥24፤ ዘዳ 12፥5፤ 2ሳሙ 6፥2፤ 7፥13 ይመ)። *እግዚአብሔር ለአባቴ ለዳዊት ... እንደ ነገረው፤* 2ሳሙ 7፥12-13፤ 1ዜና 22፥8-10 ይመ።

5፥6 *ስለዚህ...ትእዛዝ ስጥ፤* ሰሎሞን ወደ ጢሮስ ንጉሥ ወደ ኪራም የላከው መልእክት ዝርዝር ሐሳብ በ2ዜና 2፥3-10 ላይ ይገኛል። *የሊባኖስ ዝግባ፤* የጥንት የቅርብ ምሥራቅ አገሮች ቤተ ጣዖትና ቤተ መንግሥት ለመሥራት በብዛት ይጠቀሙበት የነበረ ዛፍ ነው።

5፥7 *ምስጋና ለእግዚአብሔር ይግባው፤* በአምልኮተ አማልክት ተከታዮች ዘንድ የአንድ አገር ሕዝብ የሌላውን ሕዝብ አማልክት (10፥9፤ 11፥5 ይመ) ኀይላቸውንም መናገር (2ነገ 18፥25፤ 2ዜና 2፥12 ይመ) የተለመደ ነበር።

5፥9 *አንተ እስከ ወሰንኸው ስፍራ፤* እስከ ኢዮጴ ድረስ ነው (2ዜና 2፥16፤ እንዲሁም የ1ነገ 3፥1 ማብ ይመ)። *ለቤተ ሰቤ ቀለብ በመስጠት ፍላጎቴን ታሟላለህ፤* በኪራም ቤተ መንግሥት ለሚኖሩ ሠራተኞች ቀለብ ማቅረብ፣ የእንጨቱን ዋጋ ብቻ የሚሸፍን ይመስላል። ከዚህም በተጨማሪ፣ ሰሎሞን ለፊንቄያውያን ሠራተኞች ደሞዝ መክፈል ይኖርበታል (ቍ 6)። ቍ 11 ከ2ዜና 2፥10 ጋር ስናነጻጽር፣ ለኪራም ቤተ መንግሥት ከተላከው ስንዴና የወይራ ዘይት በተጨማሪ፣ ለሠራተኞች ደሞዝ ይሆን ዘንድ ሰሎሞን ገብስና ወይን ጨምሮ መላኩን ያረጋግጣል። ኪራም ሠራተኞቹ ደሞዝ ለመክፈል፣ ከተላከለት ቀለብ ጥቂቱን ሸጦ ይሆናል።

5፥11 *ሃያ ሺህ የቆሮስ መስፈሪያ ስንዴ፤* ወደ ሰሎሞን ቤተ መንግሥት በየዓመቱ የሚገባው የእህል ግምት፣ ዐሥር ሺህ ዘጠኝ መቶ አምሳ ቆሮስ የላመ ዱቄትና ሃያ አንድ ሺህ ዘጠኝ መቶ ቆሮስ ያልላመ ዱቄት ነበር (4፥22 ይመ)። ሰሎሞን ለኪራም የከፈለው ጠቅላላ እህል ሃያ ሺህ ቆሮስ ስንዴና ሃያ ሺህ ቆሮስ ገብስ (2ዜና 2፥10) ሲሆን፣ ይህም ሃያ ስድስት ሺህ ስድስት መቶ ሥልሳ ስድስት ቆሮስ መልካም ዱቄትና ያልላመ ዱቄት፣ ወይም ከሰሎሞን ቤተ መንግሥት የዓመት ፍጆታ ሃያ በመቶ የሚያንስ ዱቄት ሊሆን ይችላል።

ጥበብን ሰጠው፤ በኪራምና በሰሎሞን መካከ
ልም መልካም ግንኙነት ነበር፤ ሁለቱም ቃል
ኪዳን አደረጉ።
13ንጉሥ ሰሎሞን ከመላው እስራኤል የጕ
ልበት ሠራተኞችን መለመለ፤ ቍጥራቸ
ውም ሠላሳ ሺህ ነበር። 14እነዚህንም አንድ
ወር በሊባኖስ እንዲሠሩ፣ ሁለት ወር በቤ
ታቸው እንዲያርፉ በማድረግ፣ ዐሥር ዐሥር
ሺዉን ወር ተራ አግብቶ ላካቸው። የጕል
በት ሠራተኞቹም አለቃ አዶኒራም ነበር።
15ሰሎሞንም በኰረብታማው አገር ሰባ ሺህ
ተሸካሚዎችና ሰማንያ ሺህ ድንጋይ ጠራቢ
ዎች ነበሩት፤ 16እንዲሁም ሥራውን የሚቈ
ጣጠሩ ሦስት ሺህ ሦስት መቶ[ፐ] ኀላፊዎች
ነበሩ። 17እነርሱም በንጉሡ ትእዛዝ ለቤተ
መቅደሱ መሠረት የሚሆን ታላላቅና ምርጥ
ድንጋይ ፈልፍለው በማውጣት የተጠረበ
ድንጋይ አዘጋጁ። 18የሰሎሞንና የኪራም
የእጅ ባለሙያዎች እንዲሁም የጌባል ሰዎች[ሰ]
ለቤተ መቅደሱ የሚያስፈልገውን ዕንጨትና
ድንጋይ ፈልጠው አዘጋጁ።

## ሰሎሞን ቤተ መቅደሱን መሥራት ጀመረ

6፥1-29 ተጓ ምብ - 2ዜና 3፥1-14

6 እስራኤላውያን ከግብፅ በወጡ በአራት
መቶ ሰማንያ[ከ] ዓመት፣ ሰሎሞን በእስራ
ኤል ላይ በነገሠ በአራተኛው ዓመት፣ ዚፍ
በተባለው በሁለተኛው ወር ሰሎሞን የእግዚ
አብሔርን ቤተ መቅደስ መሥራት ጀመረ።
2ንጉሥ ሰሎሞን ለእግዚአብሔር የሠራው
ቤተ መቅደስ ርዝመቱ ሥልሳ ክንድ፣ ወርዱ
ሃያ ክንድ፣ ቁመቱ ሠላሳ ክንድ[ኸ] ነበር።
3በቤተ መቅደሱ ዋነኛ አዳራሽ ፊት ለፊት
ያለው በረንዳ ወርዱ እንደ ቤተ መቅደሱ
ወርድ ሁሉ ሃያ ክንድ[ወ] ሲሆን፣ ርዝመቱ
ዐሥር ክንድ[ዐ] ወደ ውጭ የወጣ ነበር።
4ለቤተ መቅደሱም ባለ ዐይነ ርግብ መስኮ
ቶች አበጀ። 5በዋናው ቤተ መቅደስና በቅ
ድስተ ቅዱሳኑ ግድግዳ ዙሪያ ልዩ ክፍሎች
ያሉት ተቀጥላ ግንብ ሠራ። 6የምድር ቤቱ
ወርድ አምስት ክንድ፣[ዘ] የመካከለኛው ፎቅ
ስድስት ክንድ፣[ዠ] የሦስተኛው ፎቅ ሰባት
ክንድ[የ] ነበር፤ የቤተ መቅደሱን ግድግዳ ዘልቆ
እንዳይገባም፣ ከቤተ መቅደሱ ግንብ ውጭ
ዙሪያውን እርከኖች አደረገ።
7ቤተ መቅደሱ የተሠራው እዚያው ድን
ጋዩ ተቈፍሮ ከወጣበት ቦታ በተዘጋጀ ድን
ጋይ በመሆኑ የመራጃ፣ የመሮ ወይም የሌላ
ብረት ነክ መሣሪያ ድምፅ በቤተ መቅደሱ
አካባቢ አልተሰማም ነበር።
8የምድር[ደ] ቤቱ መግቢያ በስተ ደቡብ
በኩል ባለው የቤተ መቅደሱ ጐን ሲሆን ወደ
መካከለኛውና ከዚያም ወደ መጨረሻው
ፎቅ የሚያስወጣ ደረጃ ነበረው። 9ቤተ መቅ
ደሱንም በዚሁ ሁኔታ ሠርቶ ጨረሰ፤ ለጣ
ራው ተሸካሚ አደረገለት፤ በዝግባ ሳንቃም
ከደነው። 10በቤተ መቅደሱም ዙሪያ በሙሉ፣
ቁመታቸው አምስት አምስት ክንድ የሆነ
ክፍሎች ሠራ፤ እነዚህንም ከቤተ መቅደሱ
ጋር በዝግባ አግዳሚ ዕንጨቶች አያያዛቸው።
11የእግዚአብሔርም ቃል እንዲህ ሲል
ወደ ሰሎሞን መጣ፤ 12"ስለምትሠራው ስለዚህ

5፥12 ኢሱ9፥7፤ 1ነገ3፥12፤15፥19፤ አሞ1፥9
5፥13 ዘፍ49፥15፤ ዘሌ25፥39፤1ነገ9፥15
5፥14 2ሳሙ20፥24፤1ነገ4፥6፤2ዜና10፥18
5፥16 1ነገ9፥23
5፥17 1ነገ6፥7፤ 1ዜና22፥2
5፥18 ኢሱ13፥5፤ 2ሳሙ5፥11
6፥1 ዕዝ3፥8፤5፥11
6፥2 ዘፀ26፥1
6፥3 ሕዝ40፥49
6፥4 ሕዝ41፥16
6፥5 ኤር35፥2፤ ሕዝ41፥56
6፥7 ዘፀ20፥25፤ ዘዳ27፥5
6፥9 ማሕ1፥17
6፥11 1ነገ12፥22፤ 13፥20፤16፥1፡7፤17፥2፤21፥17፤ኤር40፥1

[ፐ]16 ዕብራይስጡና አንዳንድ የሰብዓ ሊቃናት ትርጒም ሦስት ሺህ ስድስት መቶ ይላሉ
[ሰ]18 ይኸውም ቢብሎስ የተባለው ስፍራ ነው
[ከ]1 ዕብራይስጡና የሰብዓ ሊቃናት ትርጒም አራት መቶ አርባ ይላሉ
[ኸ]2 ርዝመቱ 27 ሜትር፣ ወርዱ 9 ሜትር እንዲሁም ቁመቱ 13.5 ሜትር ያህል ነው
[ወ]3 16.9 ሜትር ያህል ነው
[ዐ]3 4.5 ሜትር ያህል ነው
[ዘ]6 በዚህ እንዲሁም በቍ 10 እና 24 ላይ 2.3 ሜትር ያህል ነው
[ዠ]6 2.7 ሜትር ያህል ነው
[የ]6 3.1 ሜትር ያህል ነው
[ደ]8 የሰብዓ ሊቃናት ትርጒም እንዲሁም ዕብራይስጡ፤ የመካከለኛ ይላሉ

5፥13 *የጕልበት ሠራተኞችን መለመለ፤* የ9፥15፤ የ2ሳሙ 20፥24 ማብ ይመ። በዚህ መንገድ ሰዎችን አስገድዶ ማሠራቱ ሕዝብን ለዐመፅ ስላነሣሣ፣ ሰሎሞን ከሞተ በኋላ ወዲያው መንግሥቱ እንዲከፈል አስተዋፅኦ አድርጎአል። (12፥1-18)።

5፥15 *ሰባ ሺህ ተሸካሚዎችና ሰማንያ ሺህ ድንጋይ ጠራቢዎች፤* ዳዊት በጦርነት አሸንፎ ከግዛቱ ጋር ከቀላቀላቸው (2ዜና 2፥17-18 ይመ) እስራኤላውያን ካልሆኑ ሕዝቦች የተመለመሉ ናቸው። *በኰረብታማው፤* በፓሌስቲና የኖራ ድንጋይ የሚገኝበት ስፍራ ተራራ ሲሆን ከዚህም ድንጋይ ይወጣ ነበር።

5፥16 *ሦስት ሺህ ሦስት መቶ ኀላፊዎች፤* በ1ነገ 9፥23 ላይ ሰሎሞን አምስት መቶ አምሳ ተቈጣጣሪዎች እንዳደረገ ተመልክቶአል። እነዚህ በተለያየ ምድብ የሚገኙ ተቈጣጣሪዎች ከሆኑ፣ ጠቅላላ ቍጥራቸው ሦስት ሺህ ስምንት መቶ አምሳ ይሆናል። በ2ዜና 2፥2 ሦስት ሺህ ስድስት መቶ፣ በ2ዜና 8፥10 ደግሞ ሁለት መቶ አምሳ ተቈጣጣሪዎች እንደ ነበሩ ተገልጾአል፤ ይህም ሲደመር፣ ሦስት ሺህ ስምንት መቶ አምሳ ይሆናል ማለት ነው።

5፥17 *ታላላቅና ምርጥ ድንጋይ፤* የእነዚህ ድንጋዮች መጠን ምን ያህል እንደሚሆን ለመረዳት 7፥10 ይመ። እንደ እነዚህ ያሉትን ታላላቅ ድንጋዮች ወደ ኢየሩሳሌም ለማጓጓዝ፣ ብዛት ያለው የሰው ኀይል ያስፈልግ ነበር።

5፥18 *የጌባል ሰዎች፤* ሕዝ 27፥9 ይመ።

6፥1-38 በ [ ]ገጽ ላይ ያለውን የሰሎሞንን ቤተ መቅደስ አሠራር የሚያሳየውን ሥዕል ይመ።

6፥1 *በአራት መቶ ሰማንያ ዓመት ... በአራተኛው ዓመት፤* የአሦራውያን የታሪክ ጽሑፍ እንደሚያስረዳው፣ የሰሎሞን ዘመነ መንግሥት አራተኛው በ966 ዓ.ቅ.ክ. ሲሆን፣ እስራኤላውያን ከግብፅ የወጡት ከዚሁ ዘመን አራት መቶ ሰማንያ ዓመት አስቀድሞ በ1446 ዓ.ቅ.ክ ነበር። ይህም ዘመን፣ ዐሥራ ስምንተኛው የፈርዖን ሥርወ መንግሥት ዳግማዊ አሙንሆቴፕ ይገዛ የነበረበት ነው። ነገር ግን አንዳንድ ሰዎች በዘፀ 1፥11 ላይ የተጠቀሰውን ሐሳብና ሌሎች ታሪካዊ ሁኔታዎችን መሠረት በማድረግ፣ እስራኤላውያን ከግብፅ የወጡት የዐሥራ ዘጠነኛው የግብፅ ሥርወ መንግሥት ፈርዖን የነበረው ዳግማዊ ራምሴ ከነበረበት ጊዜ ቀደም ብሎ እንዳልሆነ ይስማማሉ፤ ስለዚህም እስራኤላውያን ከግብፅ የወጡት ዓ.ቅ.ክ. በ1290 ነበር (የዘፍ 47፥11 ማብ ይመ)።

6፥2 *ንጉሥ ሰሎሞን...የሠራው ቤተ መቅደስ፤* የቤተ መቅደሱ አሠራር እንደ ማደሪያው ድንኳን ዐይነት ሲሆን (በአጠቃላይ በጊዜው ከነበሩት ሌሎች ቤተ መቅደሶች አሠራር ጋር ተመሳሳይ ነበር)፣ ሦስት ዋና ክፍሎች ነበሩት፤ እነዚህም ቅድስተ ቅዱሳን፣ ቅድስትና የውጨኛው አደባባይ ናቸው። የቅድስተ ቅዱሳኑ ቅርጽ፣ ምናልባት በማደሪያው ድንኳን እንደነበረው ዐይነት ስድስት ማእዘን ያለው ካሬ ይመስል ነበር። የቤተ መቅደሱ ስፋት የማደሪያውን ድንኳን ሁለት ዕጥፍ ይሆናል (ዘፀ 26፥15-30፤ 36፥20-34 ይመ)።

6፥6 *እርከኖች፤* በቤተ መቅደሱ ግድግዳ ላይ ምንም ክፍተት እንዳይኖር ለማድረግ የሚያገለግሉ ሲሆን፣ ከጐን ባሉት ሦስት ክፍሎች ላይ ለሚገኙ አውታሮች መደገፊያ የሚሆኑ እቃፊዎች ናቸው። አሠራራቸውም በእያንዳንዱ ደርብ ላይ እንዳሉት ክፍሎች ወርድ መጠን ነበር።

6፥8 *የምድር ቤቱ መግቢያ፤* ግራና ቀኝ ላሉት ክፍሎች መግቢያ በር ማለት ነው።

6፥11 *የእግዚአብሔርም ቃል...ወደ ሰሎሞን መጣ፤* የቤተ መቅደሱ ሥራ ሊፈጸም ጥቂት ሲቀረው እግዚአብሔር ለሰሎሞን ተናገረው (3፥5፡11-14፤ 9፥2-9 ይመ) ምናልባትም እግዚአብሔር የተናገረው ስሙ ባልተገለጸ ነቢይ በኩል ይሆናል።

ቤተ መቅደስ ሥርዐቴን ብትከተል፣ ፍር
ዴን በተግባር ብትገልጸው፣ ትእዛዞቼን ብትጠ
ብቅና ብትመላለስባቸው ለአባትህ ለዳዊት
የሰጠሁትን ተስፋ በአንተ እፈጽመዋለሁ፤
13በእስራኤላውያን መካከል እኖራለሁ፤
ሕዝቤን እስራኤልንም አልተወውም።”
14ስለዚህ ሰሎሞን ቤተ መቅደሱን ሠርቶ
ፈጸመ፤ 15የውስጡን ግድግዳ ከቤተ መቅደሱ
ወለል እስከ ጣራው ድረስ በዝግባ ሳንቃ ለበጠ፤
የቤተ መቅደሱንም ወለል የጥድ ሳንቃ አለ
በሰው። 16በቤተ መቅደሱም ውስጥ በስተ ኋላ
በኩል፣ ሃያውን ክንድ ቅድስተ ቅዱሳን
እንዲሆን፣ ከወለሉ አንሥቶ እስከ ጣራው
ድረስ በዝግባ ሳንቃዎች ጋረደው፤ 17በቅ
ድስተ ቅዱሳኑ ፊት ለፊት ያለው ዋና አዳ
ራሽ ርዝመቱ አርባ ክንድ[ж] ነበር። 18የቤተ
መቅደሱም፣ ውስጡ በሙሉ በዝግባ የተለ
በጠ ሲሆን፣ ይህም በእንቡጥ አበቦችና በፈኩ
አበቦች ቅርጽ የተጌጠ ነበር፤ በሙሉ ዝግባ
እንጂ የሚታይ ድንጋይ አልነበረም።
19በቤተ መቅደሱም ውስጠኛ ክፍል የእ
ግዚአብሔር የቃል ኪዳኑ ታቦት የሚቀመ
ጥበትን ቅድስተ ቅዱሳን ሠራ። 20ቅድስተ
ቅዱሳኑም ርዝመቱ ሃያ ክንድ፣ ወርዱ ሃያ
ክንድ፣ ቁመቱም ሃያ ክንድ[ו] ነበር፤ ውስጡን
በንጹሕ ወርቅ ለበጠው፤ ከዝግባ የተሠራው
ንም መሠዊያ በወርቅ ለበጠው። 21ሰሎሞ
ንም ቤተ መቅደሱን በውስጥ በኩል በንጹሕ
ወርቅ ለበጠው፤ በወርቅ በተለበጠው ቅድስተ
ቅዱሳን ፊት ለፊትም የወርቅ ሰንሰለቶች
ዘረጋ። 22ስለዚህ ውስጡን በሙሉ በወርቅ
ለበጠው፤ በቅድስተ ቅዱሳኑ ውስጥ ያለውን
መሠዊያም እንደዚሁ በወርቅ ለበጠው።
23በቅድስተ ቅዱሳኑም ውስጥ ቁመታቸው

6፥12 2ሳሙ7፥12-16፤1ነገ9፥5፤11፥10
6፥13 ዘሌ26፥11፤ ዘዳ31፥6፤ዮሐ14፥18፤ ዕብ13፥5
6፥14 1ዜና28፥20፤ 2ዜና5፥1፤ሐሥ7፥47
6፥15 1ነገ7፥7፤ ሕዝ41፥1516
6፥16 ዘ26፥33
6፥18 ቍ29፤መዝ 74፥6፤ሕዝ41፥18
6፥19 ዘፀ25፥10፤ 1ሳሙ3፥3፤1ነገ8፥6
6፥20 ዘፀ30፥1፤ ሕዝ41፥34

[ж]17 18 ሜትር ያህል ነው
[ו]20 ርዝመቱ፣ ወርዱና ቁመቱ 9 ሜትር ያህል ነው

6፥12 *ሥርዐቴን ብትከተል... የሰጠሁትን ተስፋ በአንተ እፈጽመዋለሁ፤* ለኪዳን ታማኝ ቢሆን፣ ለዳዊት የሰጠውን ተስፋ በመፈጸም ሥርወ መንግሥቱን እንደሚያጸናለት (2ሳሙ 7፥12-16 ይመ) እግዚአብሔር ለሰሎሞን ተናገረው (የ2፥1-4 ማብ ይመ)።

6፥13 *በእስራኤላውያን መካከል እኖራለሁ፤* በመሠራት ላይ በነበረው ቤተ መቅደስ ውስጥ ማለት ነው (9፥3 ይመ)። ከእ ነርሱ ጋር ስለመሆኑ በእስራኤላውያን ዘንድ ምንም ሥጋት እን ዳይኖር ለማድረግ (ከመዝ 78፥60፤ ከኤር 26፥6:9 ጋር ያነጻጽሩ፤ እንዲሁም የ1ሳሙ 7፥1 ማብ ይመ)፣ እግዚአብሔር በመካከላ ቸው እንደሚኖር አረጋገጠላቸው (8፥10-13፤ ዘሌ 26፥11 ይመ)።


6፥16 *ቅድስተ ቅዱሳን፤* በመገናኛው ድንኳን ውስጥ ታቦቱ የሚገኝበት የውስጠኛው መቅደስም የሚጠራው በዚሁ ቃል ነበር (ዘፀ 26፥33-34፤ ዘሌ 16፥2:16-17:20:23 ይመ)።

6፥19 *የእግዚአብሔር የቃል ኪዳኑ ታቦት፤* ዐሠርቱ ትእ ዛዛት፣ በዘፀ 34፥28 “የኪዳኑ ቃሎች” ተብለው ተጠርተዋል። ዐሠ ርቱ ትእዛዛት የተጻፉበት የድንጋይ ጽላቶች (ዘዳ 9፥9 ላይ “የቃል ኪዳን ጽላቶች” ተብለዋል። ጽላቱ የሚቀመጥበት ታቦት (ዘፀ 25፥16:21፤ 40፥20፤ ዘዳ 10፥1-5 ይመ)፣ የእግዚአብሔር የኪዳኑ ታቦት ተብሎ ይጠራል (ዘዳ 10፥8፤ 31፥9:25፤ ኢሱ 3፥11 ይመ)። በሌላ ቦታ ደግሞ ታቦቱ “የእግዚአብሔር ታቦት” (ኢሱ 3፥13፤ 4፥11)፣ “የምስክሩ ታቦት” (ዘፀ 30፥6፤ 31፥7) እንዲሁም “የአምላክ ታቦት” (1ሳሙ 3፥3፤ 4፥11:17:21፤ 5፥1-2) በመባል በተለያየ ስም ይጠራል።

6፥20 *በንጹሕ ወርቅ፤* በቤተ መቅደሱ ሥራ ላይ በብዛት የሚያብለጨልጭ ወርቅ የዋለው፣ ምናልባት ለእግዚአብሔር ክብ ርና በሰማይ ላለው ቤተ መቅደስ (ከራእ 21፥10-11:18:21 ጋር ያነጻጽሩ) ትእምርት ሆኖ ነው።

6፥21 *የወርቅ ሰንሰለቶች፤* ወደ ቅድስተ ቅዱሳን በሚያስ ገባው በር ላይ ያለው መጋረጃ የተንጠለጠለው በእነዚህ ሰንሰለ ቶች ሳይሆን አይቀርም (2ዜና 3፥14፤ ማቴ 27፥51፤ ዕብ 6፥19 ይመ)።

6፥22 *ቅድስተ ቅዱሳኑ ውስጥ ያለውን መሠዊያም፤* የዕ ጣን መሠዊያው ማለት ነው (7፥48፤ ዘፀ 30፥1:6፤ 37፥25-28፤ ዕብ 9፥3-4 ይመ)።




የሰሎሞን ቤተ መቅደስ ከንጉሡ ቤተ መንግሥት
ጉን የተቀመጠ ሲሆን፣ እንደ እግዚአብሔር ዙፋን
መቀመጫና ለእስራኤላውያን ደግሞ ብሔራዊ የአምልኮ
ማዕከል ሆኖ ያገለግል ነበር።

ዐሥር ክንድ[ሠ] የሆነ ሁለት የኪሩቤል ቅርጽ
ከወይራ ዕንጨት ሠራ፤ 24የአንደኛው ኪሩብ
አንዱ ክንፍ አምስት ክንድ ሲሆን፣ ሌላ
ውም ክንፉ እንደዚሁ አምስት ክንድ ነበር፤
ይህም ከአንዱ ክንፍ ጫፍ እስከ ሌላው ክንፍ
ጫፍ ዐሥር ክንድ ማለት ነው። 25የሁለተኛ
ውም ኪሩብ ክንፍ እንደዚሁ ዐሥር ክንድ
ሆነ፣ ሁለቱ ኪሩቤል በመጠንና በቅርጽ
አንድ ዐይነት ነበሩና። 26የእያንዳንዱም
ኪሩብ ቁመት ዐሥር ክንድ ነበር። 27ክንፎ
ቻቸው እንደ ተዘረጋ፣ ኪሩቤልን ወስዶ በቅ
ድስተ ቅዱሳኑ አኖራቸው፤ የአንዱ ኪሩብ
ክንፍ አንዱን ግድግዳ ሲነካ፣ የሌላው ኪሩብ
ክንፍ ደግሞ ሌላውን ግድግዳ ይነካ ነበር፤
ሌሎቹ ክንፎቻቸውም በቅድስተ ቅዱሳኑ መካ
ከል እርስ በርሳቸው ይነካኩ ነበር። 28ኪሩቤ
ልንም በወርቅ ለበጣቸው።

29በመቅደሱ ግድግዳ ዙሪያ ላይ ሁሉ በው
ስጥም በውጭም ኪሩቤልን፣ ከዘንባባ ዛፎ
ችና ከፈነዱ አበቦች ጋር ቀረጸ። 30እንዲ
ሁም የቅድስተ ቅዱሳኑንና የመቅደሱን ወለል
በሙሉ በወርቅ ለበጠ።

31ለቅድስተ ቅዱሳኑም መግቢያ የወይራ ዕን
ጨት ደጃፎች ሠራ፤ መቃኖቻቸውንና መድ
ረኮቻቸውን ባለ አምስት ማእዘን አደረገ።
32በሁለቱ የወይራ ዕንጨት መዝጊያዎችም
ላይ ኪሩቤልን፣ የዘንባባ ዛፎችንና የፈነዱ
አበቦችን ቀረጸ፤ በወርቅም ለበጣቸው። 33እን
ዲሁም ለዋናው አዳራሽ መግቢያ ባለ አራት
ማእዘን የወይራ ዕንጨት መቃን ሠራ፤ 34እያን
ዳንዳቸው በማጠፊያ የተያያዙ ሁለት ሁለት
ሳንቃዎች ያሏቸው ሁለት መዝጊያዎች አበጀ።
35ኪሩቤልን፣ የዘንባባ ዛፎችንና የፈኩ አበቦ
ችንም ቀረጸባቸው፤ ቅርጹን ሠራ፤ ጥሩ አድ
ርጎም በወርቅ ለበጠው።

36የውስጠኛውን አደባባይ በሦስት ረድፍ
ጥርብ ድንጋይና በአንድ ረድፍ የዝግባ ሳንቃ
ሠራው።

37የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስም በአራተ
ኛው ዓመት ዚፍ በተባለው ወር መሠረቱ
ተጣለ፤ 38በዐሥራ አንደኛው ዓመት ቡል በተ
ባለውም በስምንተኛው ወር ቤተ መቅደሱ
በዝርዝር ጥናቱ መሠረት እንደ ታቀደው
ተፈጸመ፤ ሠርቶ የጨረሰውም በሰባት ዓመት
ጊዜ ውስጥ ነበር።

### ሰሎሞን ቤተ መንግሥቱን ሠራ

7 ሰሎሞን የራሱን ቤተ መንግሥት ሠርቶ
ለመጨረስ ዐሥራ ሦስት ዓመት ወስዶ
በታል፤ 2የሊባኖስ ዱር የተባለ ቤተ መንግ
ሥት ሠራ፤ ይህም ርዝመቱ መቶ ክንድ፣
ወርዱ አምሳ ክንድ፣ ቁመቱ ሠላሳ ክንድ
ሲሆን፣ በአራት ረድፍ የቆሙ የዝግባ ምሰ
ሶዎች ደግፈው የያዟቸው አግዳሚ የዝግባ
ተሸካሚዎች ነበሩት። 3ቤቱ ከምሰሶዎቹ
ላይ ያረፉ አግዳሚ ተሸካሚዎች አሉት፤
በእያንዳንዱ ዐምድ ላይ ዐሥራ አምስት፣
በድምሩ አርባ አምስት ተሸጋጋሪዎች ሲኖሩ፣
ከእነዚህም ተሸጋጋሪዎች በላይ ከዝግባ የተ
ሠራ የጣሪያ ክዳን ነበር። 4መስኮቶቹም
ከፍ ብለው የተሠሩ በሦስት ምድብ የተከ
ፈሉና ትይዩ ነበሩ። 5በሮቹ በሙሉ ባለ አራት
ማእዘን መቃኖች ያሏቸው፣ በሦስት ምድብ
የተከፈሉና ትይዩ[ሰ] ነበሩ።

6ሰሎሞን፣ "ባለ ብዙ ምሰሶ አዳራሽ" የተ
ባለ ቤት ሠራ፤ የዚህም ርዝመቱ አምሳ ክንድ፣
ወርዱ ሠላሳ ክንድ፣[ሸ] ነበር፤ በስተ ፊት በኩ
ልም ባራ ያለውና በአዕማድ የተደገፈ መመ
ላለሻ ነበረው።

7ዳኝነት የሚያይበትንም የዙፋን ችሎት
አዳራሽ ሠራ፤ ይኸውም የፍትሕ አዳራሽ
የተባለው ነው፤ ይህንንም ከወለሉ አንሥቶ
እስከ ጣራው[ቀ] ድረስ በዝግባ ሳንቃ ሸፈ
ነው። 8ከአዳራሹ በስተ ጀርባ ባለው አደባ
ባይ መኖሪያው እንዲሆን የተሠራው ቤት

6፥23 ዘፀ37፥7
6፥27 ዘፍ3፥24፤ ዘፀ25፥18
6፥29 ቍ18፡32፡ 35፤ሕዝ41፥18፡25
6፥32 ሕዝ41፥23
6፥36 1ነገ7፥12፤ 2ዜና4፥9፤ዕዝ6፥4
6፥38 ዘፀ25፥9፤ 1ዜና28፥19፤ዕብ8፥5
7፥1 2ሳሙ7፥2
7፥2 2ሳሙ7፥2፤ 1ነገ10፥17፤2ዜና 9፥16፤ኢሳ22፥8፤ 37፥24፤ኤር22፥6፡23
7፥7 1ሳሙ7፥15፤ 1ነገ6፥15፤መዝ122፥5 ፤ምሳ20፥8
7፥8 1ነገ3፥1

ሠ23 4.5 ሜትር ያህል ነው
ረ2 ርዝመቱ 46 ሜትር፣ ወርዱ 23 ሜትር እንዲሁም ቁመቱ 13.5 ሜትር ያህል ነው
ሰ5 በዕብራይስጥ የክፍሉ መልእክት በትክክል አይታወቅም።
ሸ6 ርዝመቱ 23 ሜትር፣ ወርዱ 13.5 ሜትር ያህል ነው።
ቀ7 ቩልጌትና የሱርስቱ ትርጉም ከዚህ ጋር ሲስማሙ ዕብራይስጡ ግን፣ ወለል ይላል

6፥23 *የኪሩቤል፤* የዘፀ 25፥18 ማብ ይመ። እንደ ጠባቂ በታቦቱ ጐን እና ጐን የሚቆሙ ናቸው (8፥6-7፤ 2ዜና 3፥10-13)። በስርየት መክደኛው ላይ፣ ሌሎች ሁለት ኪሩቤል በታቦቱ ላይ ቆመው ነበር (ዘፀ 25፥17-22)። *ዐሥር ክንድ፤* ኪሩቤል የቆሙ በት ቅድስተ ቅዱሳን ቁመቱ ሃያ ክንድ ነበር (ቍ 16)።

*6፥29 ኪሩቤልን... ቀረጸ፤* ከዐሠርቱ ትእዛዛት ሁለተኛውን ትእዛዝ በመተላለፍ አይደለም (የዘፀ 20፥4 ማብ ይመ)። *ከዘንባባ ዛፎችና ከፈነዱ አበቦች፤* ቀደምት የአይሁድ ምኵራቦች እነዚህን በሚመስሉ ቅርጻ ቅርጾች ያጌጡ ነበሩ። የኪሩቤል፣ ውብ የሆኑ ዛፎችና አበቦች ቅርጽ፣ በኀጢአት ምክንያት ሰው የተባረረበትን (ዘፍ 3፥24) የኤደን ገነትን የሚያስታውስ ነው። ትእምርታዊነቱ፣ አሁን ወደ እግዚአብሔር ገነት መመለስ የሚቻለው፣ በመቅደሱ ውስጥ በሚደረገው የኀጢአት ስርየት አማካይነት ብቻ መሆኑን ነው።

6፥36 *የውስጠኛውን አደባባይ፤* በውጭም አደባባይ መኖሩን ያመለክታል (8፥64 ይመ)። በ2ዜና 4፥9 ላይ "የካህናቱ አደባባይ" (ውስጠኛው) እና "ትልቁ አደባባይ" (የውጭው) ተጠቅሰዋል። ውስጠኛው አደባባይ፣ ላይኛው አደባባይም ተብሎ ይጠራል (ኤር 36፥10)፤ ይኸውም ወደ ቤተ መቅደሱ ከሚያስገባው በር ከፍ ብሎ የሚገኝ በመሆኑ ነው።

6፥37 *በአራተኛው ዓመት፤* ሰሎሞን በነገሠ ማለት ነው (የቍ 1 ማብ ይመ)።

6፥38 *በዐሥራ አንደኛው ዓመት፤* ሰሎሞን በነገሠ በዐሥራ አንደኛው ዓመት ማለት ነው ዓ.ቅ.ክ. 959)።

7፥1 *ዐሥራ ሦስት ዓመት፤* ሰሎሞን የራሱን ቤት ለመሥራት የፈጀበት ጊዜ፣ የእግዚአብሔርን ቤት ለመሥራት ከወሰደበት ጊዜ ዕጥፍ ያህል ነው (6፥38 እንዲሁም ሐጌ 1፥2-4 ይመ)።

7፥2 *የሊባኖስ ዱር የተባለ ቤተ መንግሥት፤* በቤተ መንግሥቱ ውስጥ በአራት ረድፍ የቆሙ የዝግባ ምሰሶዎች፣ በጥቅጥቅ ደን ውስጥ የመሆንን ስሜት የሚያሳድሩ ነበሩ። ርዝመቱ መቶ ክንድ፣ ወርዱ አምሳ ክንድ፣ ቁመቱ ሠላሳ ክንድ፤ በ6፥2 ላይ ከተጠቀሰው የቤተ መቅደስ ስፋት ጋር ያነጻጽሩ።

7፥3 *በእያንዳንዱ ዐምድ ላይ ዐሥራ አምስት...አርባ አምስት ተሸጋጋሪዎች፤* ምድር ቤት ካለው ከዋናው አዳራሽ በላይ፣ ሕንጻው ሦስት ፎቆች እንደነበሩት ያመለክታል። ሕንጻውም ለመሣሪያ ማከመቻ የሚሆን መጋዘን ነበረው (10፥16-17 ይመ)።

7፥6 *በአዕማድ፤* ወደ ሊባኖስ ዱር ቤት የሚያመራ መግቢያ አዳራሽ ሲሆን፣ ርዝመቱ (አምሳ ክንድ) የቤተ መንግሥቱን ወርድ ያኽላል።

7፥7 *የዙፋን ችሎት አዳራሽ፤* "በሊባኖስ ዱር ቤት" ውስጥ የዙፋን ችሎት አዳራሽ፣ የፍርድ አዳራሽ፣ የሰሎሞን የራሱ መኖሪያ ቤት (ቍ 8) እና የፈርኦን ልጅ ቤተ መንግሥት የተለያዩ ሕንጻዎች ይሁኑ ወይም አይሁኑ በግልጽ አይታወቅም።

መንግሥትም የዚሁ ተመሳሳይ ነበር። ስሎ
ሞን ላገባት ለፈርዖን ልጅ ይህንኑ ቤተ
መንግሥት የመሰለ አዳራሽ ሠራ።
[9]ከውጭ እንሥቶ እስከ ትልቁ አደባባይ፣
ከመሠረቱ እንሥቶ እስከ ድምድማቱ ያለው
የሕንጻ ሥራ በሙሉ፣ በውስጥም በውጭም
በልክ በልኩ በተቈረጠና አምሮ በተስተካ
ከለ ምርጥ ድንጋይ የተሠራ ነበር። [10]መሠ
ረቱም ዐሥርና[ሐ] ስምንት ክንድ[ተ] ርዝመት
ባላቸውና ምርጥ በሆኑ ታላላቅ ድንጋዮች
የተሠራ ነበር። [11]በላዩም ላይ ምርጥ የሆኑ፣
በልክ በልኩ የተቈረጡ ድንጋዮችና የዝግባ
ሳንቃዎች ነበሩ። [12]*የእግዚአብሔር* ቤተ
መቅደስ ውስጠኛ አደባባይ ከመመላለሻ በረ
ንዳው ጭምር እንደ ትልቁ አደባባይ አምሮ
በተጠረበ ሦስት ረድፍ ድንጋይና ተስተካ
ክሎ በተከረከመ በአንድ ረድፍ የዝግባ ሳንቃ
የታጠረ ነበር።

7፥12 1ነገ6፥36
7፥13 ቍ45፤ 2ዜና2፥13፤4፥16
7፥14 ዘ31፥25፤ 35፥31፤2ዜና4፥11
7፥15 2ነገ11፥14፤ 23፥3፤25፥17፤2ዜና 3፥15፤23፥13፤ 34፥31፤ኤር27፥19፤5 2፥17:21፤ሕዝ40፥49
7፥16 ቍ20:42፤ 2ነገ25፥17፤ ኤር52፥22

## የቤተ መቅደሱ ዕቃዎች

7፥23-26 ተጓ ምብ - 2ዜና 4፥2-5
7፥38-51 ተጓ ምብ - 2ዜና 4፥6፤10-5፥1

[13]ንጉሥ ሰሎሞንም መልእክተኛ ልኮ
ኪራም[ሀ] የተባለውን ሰው ከጢሮስ አስመጣ፤
[14]የኪራም እናት ከንፍታሌም ነገድ ስትሆን፣
እርሷም መበለት ነበረች፤ አባቱ የጢሮስ ሰው
ሲሆን፣ የናስ ሥራ ባለሙያ ነበር። ኪራም በማ
ናቸውም የናስ ሥራ ጥበብን፣ ማስተዋል
ንና ዕውቀትን የተሞላ ሰው ነበር፤ እርሱም
ወደ ንጉሥ ሰሎሞን መጥቶ የተመደበለ
ትን ሥራ ሁሉ አከናወነ።
[15]ኪራም የእያንዳንዱ ቁመት ዐሥራ ስም
ንት ክንድ፣ ዙሪያው ዐሥራ ሁለት ክንድ[ሰ]
የሆነ፣ ሁለት የናስ ምሰሶዎች ሠራ። [16]እን
ዲሁም በምሰሶዎቹ አናት ላይ የሚሆኑ፣ ሁለት

[ሐ]10 4.5 ሜትር ያህል ነው። [ተ]10 3.6 ሜትር ያህል ነው።
[ሀ]13 በዚህ ስፍራ እንዲሁም በቍ 40 እና 45 ላይ ኪራም የሚ ለው ዕብራይስጡ ሂራም ይለዋል።
[ሰ]15 ቁመቱ 8.1 ሜትር፣ ዙሪያው 5.4 ሜትር ያህል ነው።

7፥9 *በተስተካከለ፤* በፓሌስቲና ምሥራቅ ደብዘዝ ያለ የኖራ ድንጋይ፣ ወዲያው እንደ ወጣ በቀላሉ የሚቈረጥ ሲሆን፣ ቈይቶ ግን ይጠነክራል።

7፥12 *ትልቁ አደባባይ፤* አሠራሩ እንደ ውስጠኛው የቤተ መቅደሱ አደባባይ ነበር (6፥36)።


7፥13 *ንጉሥ ሰሎሞንም... ልኮ፤* የቤተ መቅደሱ ሥራ ከመጠናቀቁና የሰሎሞን ቤተ መንግሥት ግንባታ ከመጀመሩ በፊት መሆኑ ነው (2ዜና 2፥7:13-14 ይመ)። *ኪራም፤* ሙሉ ስሙ ኪራምአቢ ነው (2ዜና 2፥13)።

7፥14 *ከንፍታሌም ነገድ ... መበለት፤* የኪራምአቢ እናት ከዳን ወገን እንደ ሆነች በ2ዜና 2፥14 ላይ ተጠቅሶአል። የተወለደችውም በሰሜናዊ እስራኤል በዳን ነገድ ከተማ ከንፍታሌም አጠገብ ሲሆን፣ የመጀመሪያ ባሏም ከንፍታሌም ነገድ ነው። ይህች ሴት የመጀመሪያ ባሏ ከሞተ በኋላ፣ ከጢሮስ ወገን የሆነ ሰው አገባች። *በማናቸውም የናስ ሥራ፤* ኪራም አቢ ልዩ ልዩ ዐይነት የጥበብ ሥራዎች ለመሥራት ችሎታ ነበረው (2ዜና 2፥7:14 ይመ)።


7፥15 *ሁለት የናስ ምሰሶዎች፤* በዋናው የቤተ መቅደስ በር ግራና ቀኝ ቆመው ነበር (ቍ 21)። እነዚህ ምሰሶዎች ያጌጡ ከመሆናቸውም በላይ፣ በግልጽ የማይታወቅ ትእምርት

## የቤተ መቅደስ እቃዎች

በጥበቡ የተሠራውን በ1ነገ 6-7 የተጠቀሰውን የሰለሞን ቤተ መቅደስን ውበት ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በታዩት ግኝቶች ውስጥ ማግኘት ይቻላል።





የኪሩቤል በክንፎቻቸው የከበረውን ስፍራ መሸፈናቸው በግብጻውያንና በፊንቂያውያን ሥነ ጥበብ ግልጥ ሆኖ ይታያል።





በቤተ መቅደስ አደባባይ እንደነበረው ዓይነት ተመሳሳይ ተንቀሳቃሽ ሰሀን በቆጵሮስ አገር ተገኝቶቷል። ይህ ግኝት በመጽሐፍ ቅዱስ ከተጠቀሰው ጋር የሚመሳሰል ነው።

ዐሥር መቅረዞች በመቅደሱ ውስጥ አምስቱ በግራ አምስቱ በቀኝ ከዐሥር የኅብስት ገበታዎች ጋር ይቀመጣሉ (1ነገ 7:49)፤ 2ዜና 4:8)።










በድንጋይ የተሠራ በአራት ማዕዘናት ቀንዶች የሚመስሉ ያሉት የእጣን መሠዊያ በመጊዶ ተገኝቷል። ይህ ግኝት በቤተ መቅደሱ ውስጥ የነበረውን የወርቅ የእጣን መሠዊያ ምን ይመስል እንደ ነበር በግልጽ ያስረዳል። ለኅብስቱ ማስቀመጫ የነበረው ገበታም ከወርቅ የተሠራ ነው።

ጕልላት ከቀለጠ ናስ ሠራ፤ የእያንዳንዱም
ጕልላት ቁመት አምስት ክንድ[ሀ] ነበር።
17በምሰሶዎቹ አናት ላይ ላሉት ጕልላቶችም
ጌጥ እንዲሆኑ፣ ለእያንዳንዳቸው ሰባት የመ
ረብ ሰንሰለት አበጀ፤ 18ደግሞም በምሰሶዎቹ
ላይ ያሉትን ጕልላቶች ለማስጌጥ የእያን
ዳንዱን መረብ ዙሪያ የሚከቡ ሮማኖች
በሁለት ረድፍ[ለ] ሠራ፤ ለሁለቱም ጕልላቶች[ሐ]
ያደረገው ተመሳሳይ ነበር። 19በመመላለሻው
ምሰሶዎች አናት ላይ ያሉት ጕልላቶች ቁመ
ታቸው አራት ክንድ[መ] ሲሆን፣ የሱፍ አበባ ቅርጽ
ነበራቸው። 20በሁለቱም የምሰሶ ጕልላቶችና
ከመርከቡ ቀጥሎ ባለው የክብ ቅርጽ ላይ
ዙሪያውን በሙሉ ሁለት መቶ ሮማኖች በተ
ርታ ነበሩ። 21ምሰሶዎቹንም በቤተ መቅደሱ
መመላለሻ ላይ አቆመ፤ በስተ ደቡብ ያቆ
መውን ምሰሶ ያቂም፣[ሠ] በስተ ሰሜን በኩል
ያለውንም ቦዔዝ[ረ] ብሎ ጠራው። 22አናቱ
ላይ ያሉት ጕልላቶች የሱፍ አበባ ቅርጽ ነበ
ራቸው። የምሰሶዎቹም ሥራ በዚህ ሁኔታ
ተፈጸመ።
23ቅርጹ ክብ፣ ስፋቱ ከዳር እስከ ዳር
ዐሥር ክንድ፣[ሰ] ቁመቱ አምስት ክንድ የሆነ
ክብ ገንዳ ከቀለጠ ብረት ሠራ፤ ዙሪያውም
ሲለካ ሠላሳ ክንድ[ሸ] ሆነ። 24ከከንፈሩም ዝቅ
ብሎ፣ በእያንዳንዱ ክንድ ላይ እንደ ቅል
ያሉ ዐሥር ቅርጾች ዙሪያውን በሁለት ረድፍ
ከበውታል፤ እነዚህም ከገንዳው ጋር አንድ
ወጥ ሆነው በሁለት ረድፍ ተሠርተው ነበር።
25ገንዳውም፣ ሦስቱ ፊታቸውን ወደ ሰሜን፣
ሦስቱ ወደ ደቡብ፣ ሦስቱ ወደ ምዕራብ፣
ሦስቱ ወደ ምሥራቅ ባዞሩ የዐሥራ ሁለት
በሬዎች ምስሎች ላይ የተቀመጠ ሲሆን፣
ገንዳው በላያቸው ሆኖ የሁሉም የኋላ አካል
በመካከል ላይ የገጠመ ነበር። 26የገንዳው
ውፍረት አንድ ጋት[ቀ] ሲሆን፣ የከንፈሩ ጠርዝ
ደግሞ እንደ አበባ ቅርጽ ሆኖ፣ የጽዋ ከን
ፈር የመሰለ ነው፤ ይህም አርባ ሁለት ሺህ
ሊትር[በ] ያህል ውሃ የሚይዝ ነበር።
27እንዲሁም ከቦታ ቦታ የሚንቀሳቀሱ ዐሥር
ባለ መንኰራኵር የዕቃ ማስቀመጫዎች
ከመዳብ ሠራ፤ የእያንዳንዱም ርዝመት አራት
ክንድ፣ ወርድ አራት ክንድ፣ ቁመትም
ሦስት ክንድ[ተ] ነበር። 28የዕቃ ማስቀመጫዎቹ
የተሠሩት እንደዚህ ነው፤ እነዚህም ቀጥ
ብለው ከቆሙ ደጋፊዎች ጋር የተያያዙ ባለ
አራት ማእዘን ጠፍጣፋ ናሶች ነበሯቸው።
29ዳርና ዳር ባሉት ድጋፎች መካከል በሚገ
ኙት ጠፍጣፋ ናሶች ላይ የአንበሶችን፣ የኮ
ርማዎችንና የኪሩቤልን ምስል አደረገ፤ በድ
ጋፎቹም ላይ እንደዚሁ አደረገ። ከአንበሶቹና
ከኮርማዎቹ በላይና በታች በኩል ደግሞ
የአበባ ጕንጕን የሚመስሉ ተቀጥቅጠው
የተሠሩ ቅርጾች ነበሩ። 30እያንዳንዱ የዕቃ
ማስቀመጫ አራት የናስ መንኰራኵርና
መንኰራኵሮቹ የሚሽከረከሩባቸው የናስ ወስ
ከምቶች እንዲሁም እያንዳንዳቸው በአራቱም
ማእዘን ገጽ ላይ የአበባ ጕንጕን ቀልጦ የተሠ
ራባቸው የመታጠቢያ ገንዳ መደገፊያዎች
ነበረው። 31በዕቃ ማስቀመጫወቹም ውስጥ
ጥልቀቱ አንድ ክንድ[ቸ] የሆነ ባለ ክብ ክፍ
ተት ነበር፤ ይህም ክፍተት ድቡልቡል ሆኖ
ከታች ከመቆሚያው በኩል ደግሞ አንድ
ክንድ ተኩል[ኀ] ወርድ ሲኖረው፣ በክፍተቱም
ዙሪያ ቅርጾች ነበሩ፤ ክፈፎቹ ግን ባለ አራት
ማእዘን እንጂ ክብ አልነበሩም። 32አራቱ
መንኰራኵሮች በዕቃ ማስቀመጫው ጠፍ
ጣፋ ናስ ሥር ሲሆኑ፣ የመንኰራኵሮቹ
ወስከምቶች ደግሞ ከዕቃ ማስቀመጫዎቹ
ጋር የተያያዙ ነበሩ፤ የእያንዳንዱም መንኰ
ራኵር ስፋት አንድ ክንድ ተኩል ነበር።
33መንኰራኵሮቹ የሠረገላ መንኰራኵር መሰል
ሲሆኑ፣ ወስከምቶቹ የመንኰራኵሮቹ ክፈፎ
ችና ዐቃፊዎቻቸው እንዲሁም ወስከምቶቹ
የሚገቡባቸው ቧምቧዎች በሙሉ ከቀለጠ
ብረት የተሠሩ ነበሩ።
34እያንዳንዱ የዕቃ ማስቀመጫ አራት ወጣ
ያለ እጀታ ነበረው። 35በዕቃ ማስቀመጫው
ጫፍ ላይ ግማሽ ክንድ[ነ] የሆነ ዙሪያ ክብ
ነበረበት፤ ድጋፎቹና ጠፍጣፋ ናሶቹ ከዕቃ
ማስቀመጫው አናት ጋር የተያያዙ ነበሩ።
36እርሱም በድጋፎቹና በጠፍጣፋ ናሶቹ ላይ
ባለው ቦታ ሁሉ፣ ዙሪያውን የአበባ ጕን
ጕን እያደረገ ኪሩቤልን፣ አንበሶችንና የዘን
ባባ ዛፎችን ቀረጸ። 37ዐሥሩም የዕቃ ተሽካ
ሚዎች የተሠሩት በዚህ ሁኔታ ነበር፤ ሁሉም

7፥20 ቍ 18፤ 2ዜና3፥16፤4፥13
7፥21 2ዜና3፥17
7፥22 2ነገ25፥17
7፥23 ቍ47፤2ነገ 25፥13፤1ዜና18፥8፤ 2ዜና4፥18፤ኤር31፥39፤52፥17፤ዘካ2፥1፤ ራእ4፥6
7፥25 ኤር52፥20
7፥27 2ነገ16፥17
7፥30 2ነገ16፥17

[ሀ]16 በዚህና በቍ 23 ላይ 2.3 ሜትር ያህል ነው።
[ለ]18 ሁለት የዕብራይስጥ ቅጆችና የሰብዓ ሊቃናት ትርጕም ከዚህ ጋር ሲስማሙ፣ አብዛኞዎቹ የዕብራይስጥ ቅጆች ግን፣ *በሁለት ረድፍ አዕማዶች ሥራ* ይላሉ።
[ሐ]18 ብዙ የዕብራይስጥ ቅጆችና የሱርስቱ ትርጕም ከዚህ ጋር ሲስ ማሙ፣ አብዛኞዎቹ የዕብራይስጥ ቅጆች ግን *ሮማኖች* ይላሉ።
[መ]19 በዚህና በቍ 38 ላይ 1.8 ሜትር ይላል።
[ሠ]21 ምናልባት *አነጸ* ማለት ሊሆን ይችላል።
[ረ]21 ምናልባት *በእርሱ ዘንድ ጥንካሬ አለ* ማለት ሊሆን ይችላል
[ሰ]23 4.5 ሜትር ያህል ነው። [ሸ]23 13.5 ሜትር ያህል ነው።
[ቀ]26 8 ሴንቲ ሜትር ያህል ነው።
[በ]26 44 ኪሎ ሊትር ያህል ነው። የሰብዓ ሊቃናት ትርጕም ይህን ዐረፍተ ነገር አይጨምርም።
[ተ]27 ርዝመቱና ወርዱ 1.8 ሜትር ያህል ሲሆን ቁመቱ 1.3 ሜትር ያህል ነው። [ቸ]31 0.5 ሜትር ያህል ነው።
[ኀ]31 በዚህና በቍ 32 ላይ 0.7 ሜትር ያህል ነው።
[ነ]35 0.2 ሜትር ያህል ነው።

የያዙ ሳይሆኑ አይቀርም፤ ደግሞም ጣሪያን ለመደገፍ የቆሙ እንጂ፣ እንዲሁ እንዳልቆሙ ይገመታል።

7፥21 *በስተ ደቡብ... ምሰሶ፤* ቀደም ሲል እንደነበረው የማደ ሪያ ድንኳን፣ የመቅደሱ ፊቱ ወደ ምስራቅ የዞረ ነበር (ሕዝ 8፥16 ይመ)።

7፥23 *ክብ ገንዳ ከቀለጠ ብረት፤* ትልቅ የውሃ ማከማቻ ሲሆን፣ ለመገናኛው ድንኳን ከተሠራው የናስ ሳሕን ጋር የሚመ ሳሰል ነበር (ዘፀ 30፥17-21፤ 38፥8 ይመ)፤ ውሃውም ካህናት የመ ንጻት ሥርዓት ለመፈጸም ይጠቀሙበት ነበር። *ሠላሳ ክንድ፤* በማጠ ጋጋት የተወሰደ ቍጥር ወይም አለካኩ ከገንዳው ከከንፈሩ ዝቅ በማ ድረግ ወይም በውስጥ በኩል ያለውን ዙሪያ በመለካት የተገኘ ሊሆን ይችላል (ቍ 26 ይመ)።

7፥24 *በእያንዳንዱ ክንድ... ዐሥር፤* ለአንድ ክንድ ዐሥር ጉብጉቦች በማድረግ፣ በበርሜሉ ዙሪያ ሦስት መቶ ጉብጉቦች ወይም በሁለት ረድፍ ያሉት ሲቈጠሩ ስድስት መቶ ጉብጉቦች ነበሩ።

7፥27 *የሚንቀሳቀሱ ዐሥር ... ማስቀመጫዎች፤* እነዚህ ተን ቀሳቃሽ የናስ ማስቀመጫዎች፣ ከናስ ሳሕኑ በጣም ያነሰ መጠን ያላቸውን የውሃ ሳሕኖች (ቍ 38) ለመያዝ የተሠሩ ናቸው። በሳሕኑ ውስጥ የነበረው ውሃ፣ ለሚቃጠል መሥዋዕት የታረዱ ትን እንስሳት አንዳንድ ብልት፣ እንዲታጠብ በታዘዘው መሠረት

ከአንድ ቅርጽ ቀልጠው የወጡ ስለ ሆነ፣
በመጠንና በቅርጽ ፍጹም ተመሳሳይ ነበሩ።
38ከዚያም ለእያንዳንዱ የዕቃ ማስቀመጫ
የሚሆን፣ እያንዳንዱ ስምንት መቶ ሰማንያ
ሊትር የሚይዝ ዐሥር የናስ መታጠቢያ
ገንዳ ሠራ፤ ስፋቱም አራት ክንድ ነበር።
39ከዕቃ ማስቀመጫዎቹም አምስቱን ከመቅ
ደሱ በስተ ደቡብ፣ አምስቱን በስተ ሰሜን
በኩል አኖረ፤ ገንዳውንም ከቤተ መቅደሱ
በደቡብ ምሥራቅ ጫፍ ላይ በስተ ደቡብ
አኖረው። 40እንዲሁም ምንቸቶችን፣ መጫ
ሪያዎችንና ድስቶችን ሠራ፤

ኪራምም በዚህ ሁኔታ ለንጉሥ ሰሎሞን የሠራውን *የእግዚአብሔርን* ቤተ መቅደስ ሥራ እንደሚከተለው ፈጸመ፤

41ሁለቱን ምሰሶዎች፣
በምሰሶዎቹ አናት ላይ

በክብ ቅርጽ የተሠሩ ሁለት
ጒልላቶችን፤
በምሰሶዎቹ ላይ ያሉትን በክብ
ቅርጽ የተሠሩትን ሁለት
ጒልላት ያስጌጡትን ሁለት መረቦች፤
42በምሰሶዎቹ አናት ላይ ያሉትንና
ክብ ቅርጽ የያዙትን፣
በሁለት ረድፍ የተቀረጹትን መረቦች፣
የሚያስጌጡትን አራት መቶ ሮማኖች፤
43ዐሥሩን የዕቃ ማስቀመጫዎች፣
ከዐሥር መታጠቢያ ገንዳዎቻቸው ጋር፤
44ገንዳውንና በሥሩ ያሉትን ዐሥራ
ሁለት በሬዎች፤
45ድስቶችን፣ መጫሪያዎችንና ጐድጓዳ
ሳሕኖችን።

ኪራም *ለእግዚአብሔር* ቤተ መቅደስ አገ
ልግሎት እንዲውሉ እነዚህን ዕቃዎች ሁሉ
ለንጉሥ ሰሎሞን የሠራለት ከተወለወለና
ከሚብረቀረቅ ናስ ነበር። 46ንጉሡም እነዚ
ህን በማቅለጥ በሸክላ ቅርጽ ውስጥ ፈሰው
እንዲወጡ ያደረገው በሱኮትና በጻርታን
መካከል ባለው በዮርዳኖስ ሸለቆ ነበር።
47ሰሎሞን ከብዛታቸው የተነሣ እነዚህ ሁሉ
ዕቃዎች እንዲመዘኑ አላደረገም፣ ስለዚህም
የናሱ ክብደት ምን ያህል እንደ ነበረ አል
ታወቀም።

48እንዲሁም ሰሎሞን *ለእግዚአብሔር* ቤተ መቅደስ አገልግሎት እንዲውሉ ከዚህ የሚ ከተሉትን ዕቃዎች ሁሉ ሠራ፤

የወርቅ መሠዊያን፣
ገጸ ኅብስቱ የሚቀመጥበትን
የወርቅ ጠረጴዛ፤
49በቅድስተ ቅዱሳኑ ፊት ለፊት
አምስቱ በቀኝ፣ አምስቱ
በግራ የሚቀመጡ፣ ከንጹሕ
ወርቅ የተሠሩ መቅረዞችን፣ ከወርቅ
የተሠሩ
አበቦችን፣ የመብራት ቀንዲሎችንና
መቈስቈሻዎችን፤
50የንጹሕ ወርቅ ሳሕኖችን፣ የመብራት
መኰስተሪያዎችን፣
ለመርጫ የሚሆኑ ጐድጓዳ ሳሕኖችንና
ጭልፋዎችን፣
የዕጣን ማቅረቢያ ዕቃዎችን፣
ለውስጠኛው ክፍል ለቅድስተ
ቅዱሳኑ በሮችና እንዲሁም ለቤተ
መቅደሱ በሮች የሚሆኑ የወርቅ
ማጠፊያዎችን።

51ንጉሥ ሰሎሞን *የእግዚአብሔርን* ቤተ መቅደስ ሥራ ሁሉ ከፈጸመ በኋላ አባቱ ዳዊት *ለእግዚአብሔር* የለየውን ብሩንና ወርቁን እንዲሁም ዕቃውን አምጥቶ *በእግዚአብሔር* ቤተ መቅደስ ግምጃ ቤት አኖረ።

### ታቦቱ ወደ ቤተ መቅደሱ ገባ

8፥1-21ተጓ ምብ - 2ዜና 5፥2-6፥11

8 ከዚያም ንጉሥ ሰሎሞን *የእግዚአብሔርን* የኪዳኑን ታቦት ከዳዊት ከተማ ከጽዮን ለማምጣት፣ የእስራኤልን ሽማግሌዎች፣

7፥38 ዘፀ30፥18
7፥40 ዘፀ27፥3፤ ኤር52፥18
7፥42 ቍ16
7፥45 ቍ13፤ዘፀ 27፥3፤ኤር52፥18
7፥46 ዘፍ13፥10፤ 33፥17፤ኢሱ3፥16
7፥47 ቍ23፤ዘፀ 36፥57፤1ዜና22፥3፤ ኤር52፥20
7፥48 ዘፀ25፥23፡ 30፤39፥32-43
7፥49 ዘፀ25፥31
7፥50 ዘኍ7፥14፤ 2ነገ25፥13፤ኤር52፥ 19
7፥51 2ሳሙ8፥11፤ 2ነገ12፥13፤24፥13፤ ኤር27፥19
8፥1 ዘኍ7፥2፤1ሳሙ 3፥3፤2ሳሙ5፥7፤ ራእ11፥19

(ዘሌ 1፥9:13፤ 2ዜና 4፥6 ይመ) ለማጠብ የሚያገለግል ነበር።

7፥36 *ኪሩቤልን፣ አንበሶችንና የዘንባባ ዛፎችን ቀረጸ፤* የ6፥29 ማብ ይመ።

7፥40 *ምንቸቶችን፤* በኅብረት መሥዋዕት ጊዜ የሚበላውን ሥጋ ለመቀቀል የሚያገለግሉ ዕቃዎች ሳይሆኑ አይቀርም (ዘሌ 7፥11-17፤ 22፥21-23 ይመ)። *መጫሪያዎችንና፤* ከመሠዊያው ላይ ዐመድ ለማንሣት የሚጠቀሙበት ነው። *ድስቶችን፤* ካህናት የተለያዩ ሥርዐቶችን ለመፈጸምና ደምን ወይም ውሃን ለመር ጨት ይጠቀሙባቸው ነበር (ዘፀ 27፥3 ይመ)።

7፥41 *ሁለት መረቦች፤* ቍ 17 ይመ።

7፥42 *አራት መቶ ሮማኖች፤* ቍ 18:20 ይመ።

7፥43 *ዐሥሩን የዕቃ ማስቀመጫዎች፣ ከዐሥር መታጠቢያ ገንዳዎቻቸው ጋር፤* ቍ 27-37 ይመ።

7፥44 *ገንዳውንና...ዐሥራ ሁለት በሬዎች፤* ቍ 23-26 ይመ።

7፥45 *ድስቶችን፣ መጫሪያዎችንና ጐድጓዳ ሳሕኖችን፤* ቍ 40 ይመ።

7፥46 *በሱኮትና፤* ከዮርዳኖስ በስተ ምሥራቅ (ዘፍ 33፥17፤ ኢሱ 13፥27፤ መሳ 8፥4-5)፣ ከያቦቅ ወንዝም በስተ ሰሜን በኩል የሚገኝ ነው። በንጉሣዊ አገዛዝ ዘመን፣ ሱኮት የብረታ ብረት ሥራ ማዕከል እንደ ነበረ፣ በዚህ አካባቢ በተደረገው የሥነ ቅርስ ቁፋሮ ተረጋግጦአል። *በጻርታን፤* በአዳምና (ኢሱ 3፥16 ይመ) በአቤል ምሖላ (4፥12) አጠገብ የሚገኝ ነው።

7፥48 *የወርቅ መሠዊያን፤* 6፥22 ይመ። *የወርቅ ጠረጴዛ፤* የኅብስተ ገጹ ማኖሪያ ነበር (ዘፀ 25፥23-30፤ 1ዜና 9፥32፤ 2ዜና 13፥11፤ 29፥18 ይመ)። በ1ዜና 28፥16 እና በ2ዜና 4፥8:19 ላይ እንደዚህ ዐይነት ዐሥር የወርቅ ጠረጴዛዎች የነበሩ ሲሆን፣ በመቅደሱ ውስጥ የጠረጴዛዎቹ አቀማመጥ አምስቱ ዐስተ ሰሜን፣ አምስቱ ደግሞ በስተ ደቡብ በኩል ነበር።

7፥49 *ከንጹሕ ወርቅ የተሠሩ መቅረዞችን፤* በማደሪያ ድን ኳኑ ውስጥ፣ ከኅብስተ ገጹ መቀመጫ ጠረጴዛ ፊት ለፊት ሰባት ቅርንጫፎች ያሉት አንድ መቅረዝ ብቻ ቆሞ ነበር (ዘፀ 25፥31-40፤ 26፥35)። በመቅደሱ ውስጥ የሚገኙት ዐሥሩ መቅረዞች፣ አምስቱ በስተ ሰሜን፣ አምስቱ ደግሞ በስተ ደቡብ በኩል ሆነው፣ በማብራት፣ ጠባብ መንገድ የሚመስል ብርሃን በቅስቱ ውስጥ ይፈጥሩ ነበር። *ከወርቅ የተሠሩ አበቦችን፤* ዘፀ 25፥33 ይመ። *የመብራት፤* ዘፀ 25፥37 ይመ። *መቈስቈሻዎችን፤* 2ዜና 4፥21፤ ኢሳ 6፥6 ይመ።

7፥50 *የዕጣን ማቅረቢያ ዕቃዎችን፤* 2ነገ 25፥15፤ 2ዜና 4፥22፤ ኤር 52፥18-19 ይመ)።

7፥51 *አባቱ ዳዊት ለእግዚአብሔር የለየውን፤* በምርኮ የተገኙ ወይም በንጉሥ ዳዊት ዘንድ ሞገስ ለማግኘት ከሚሹ ነገ ሥታት ግብር የተሰጡ (2ሳሙ 8፥9-12፤ 1ዜና 18፥7-11፤ 2ዜና 5፥1 ይመ)፣ የከበሩ የብርና የወርቅ ዕቃዎች ናቸው። *በእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ ግምጃ ቤት፤* 15፥18፤ 2ነገ 12፥18፤ 1ዜና 9፥26፤ 26፥20-26፤ 28፥12 ይመ።

8፥1 *የእግዚአብሔርን የኪዳኑን ታቦት... ለማምጣት፤* ቀደም

የእስራኤልን ነገድ አለቆችና የእስራኤልን
ጐሣዎች ሹማምት ሁሉ እርሱ ወዳለበት
ወደ ኢየሩሳሌም ጠራቸው:: [2]በዓሉ በሚከበ
ርበት ኤታኒም በተባለው በሰባተኛው ወር፣
የእስራኤል ወንዶች ሁሉ ንጉሥ ሰሎሞን
ወዳለበት ተሰበሰቡ::
[3]የእስራኤል ሽማግሌዎች ሁሉ በመጡ
ጊዜም ካህናቱ ታቦቱን አነሡ፤ [4]*የእግዚአ
ብሔርን* ታቦት፣ የመገናኛውን ድንኳንና
በውስጡ ያሉትን ንዋያተ ቅድሳት ሁሉ
አመጡ፤ ካህናቱና ሌዋውያኑም ይህን ሁሉ
ተሸከሙ:: [5]ንጉሥ ሰሎሞንና አብሮት በዚያ
የተሰበሰበው መላው የእስራኤል ጉባኤም
በታቦቱ ፊት በመሆን ስፍር ቍጥር የሌለው
በግና በሬ ሠዋ::
[6]ከዚያም ካህናቱ *የእግዚአብሔርን* የኪዳኑን
ታቦት አምጥተው በቤተ መቅደሱ ውስጥ
ወዳለው ማደሪያው፣ ወደ ቅድስተ ቅዱሳኑ
በማስገባት ከኪሩቤል ክንፍ በታች አኖሩት::
[7]ኪሩቤልም ታቦቱ ባለበት ቦታ ላይ ክንፋ
ቸውን ዘርግተው፣ ታቦቱንና መሎጊያዎቹን
ጋረዱ:: [8]መሎጊያዎቹ ከመርዘማቸው የተ
ነሣ ጫፎቻቸው ከቅድስተ ቅዱሳኑ ፊት
ለፊት ካለው ከመቅደሱ ሆኖ ይታዩ ነበር፤
ከመቅደሱ ወዲያ ላለ ሰው ግን አይታዩም
ነበር፤ እስከ ዛሬም ድረስ እዚያው ይገኛሉ::
[9]የእስራኤል ልጆች ከግብፅ ምድር በወጡ
ጊዜ *እግዚአብሔር* ከእስራኤል ጋር ኪዳን
በገባበት በኮሬብ፣ ሙሴ በታቦቱ ውስጥ
ካስቀመጣቸው ሁለት የድንጋይ ጽላቶች
በቀር በታቦቱ ውስጥ ምንም አልነበረም::
[10]ካህናቱ ከቤተ መቅደሱ በወጡ ጊዜ፣
ደመና *የእግዚአብሔርን* ቤተ መቅደስ ሞላው::
[11]*የእግዚአብሔር* ክብር ቤተ መቅደሱን ሞል
ቶት ስለ ነበር፣ ካህናቱ በደመናው ምክን
ያት አገልግሎታቸውን ማከናወን አልቻሉም
ነበር::
[12]ከዚያም ሰሎሞን እንዲህ አለ፤ “*እግዚአ
ብሔር* ጥቅጥቅ ባለ ደመና ውስጥ እንደ
ሚኖር ተናግሯል፤ [13]እነሆ፣ እኔም ለዘላለም
የምትኖርበትን ታላቅ ቤተ መቅደስ ሠር
ቼልሃለሁ::”
[14]መላው የእስራኤል ጉባኤ በዚያ ቆሞ
ሳለ፣ ንጉሡ ፊቱን ወደ እነርሱ መልሶ ጉባ
ኤውን ባረከ:: [15]ከዚያም እንዲህ አለ፤
“ለአባቴ ለዳዊት በገዛ አፉ ተናግሮ
የሰጠውን ተስፋ፣ እርሱ ራሱ በእጁ
የፈጸመ የእስራኤል አምላክ *እግዚአብሔር*
የተመሰገነ ይሁን፤ እርሱም እንዲህ
ብሎ ነበርና፤ [16]‘ሕዝቤን እስራኤልን
ከግብፅ ምድር ካወጣሁበት ዕለት አን
ሥቶ፣ ስሜ በዚያ እንዲጠራና ቤተ
መቅደስ እንዲሠራበት ከመላው የእስ
ራኤል ነገድ አንድም ከተማ አልመረ
ጥሁም፤ ሕዝቤን እስራኤልን እንዲመራ
ግን ዳዊትን መረጥሁት::’
[17]“አባቴ ዳዊት ለእስራኤል አምላክ
*ለእግዚአብሔር* ስም ቤተ መቅደስ ለመሥ
ራት በልቡ አስቦ ነበር፤ [18]*እግዚአብሔር*
ግን አባቴን ዳዊትን እንዲህ አለው፤
‘ለስሜ ቤተ መቅደስ ለመሥራት አስ
በሃልና፣ ይህን በልብህ ማሰብህ መል
ካም ነው፤ [19]ይሁን እንጂ ቤተ መቅደ
ሱን የምትሠራው አንተ ሳትሆን፣ ከአ
ንተ የሚወለደው ልጅህ ነው፤ አዎን
ለስሜ ቤተ መቅደስ የሚሠራው እርሱ
ነው::’
[20]“*እግዚአብሔር* የሰጠውን ተስፋ
ፈጽሞአል፤ *እግዚአብሔር* በሰጠው ተስፋ
መሠረት በአባቴ በዳዊት እግር ተተክ
ቻለሁ፤ በእስራኤል ዙፋን ተቀምጫለሁ፤
እንዲሁም ለእስራኤል አምላክ *ለእግዚአ
ብሔር* ስም ቤተ መቅደስ ሠርቻለሁ::
[21]ከግብፅ ባወጣቸው ጊዜ ከአባቶቻችን
ጋር የገባው *የእግዚአብሔር* ኪዳን በው
ስጡ ላለበት ታቦት መኖሪያ ስፍራ
በዚያ አዘጋጅቻለሁ::”

### ሰሎሞን በምረቃው ላይ ያቀረበው ጸሎት

8፥22-53 ተጓ ምብ - 2ዜና 6፥12-40

[22]ከዚያም ሰሎሞን መላው የእስራኤል
ጉባኤ ባለበት *በእግዚአብሔር* መሠዊያ ፊት
ቆመ፤ እጆቹንም ወደ ሰማይ ዘርግቶ፣ [23]እን
ዲህ አለ፤
“የእስራኤል አምላክ *እግዚአብሔር*
ሆይ፤ በፊትህ በፍጹም ልባቸው ጸንተው

8፥2 ቍ65፤ዘሌ23፥34:36፤ዘኍ29፥12፤ነህ8፥17
8፥3 ኢሱ3፥3
8፥4 ዘሌ17፥4፤1ዜና15፥13
8፥5 2ሳሙ6፥13፤2ዜና30፥24
8፥6 ዘፍ3፥24፤ዘፀ25፥18፤26፥33፤2ሳሙ6፥17፤ራእ11፥19
8፥7 ዘፀ25፥20
8፥8 ዘፀ25፥13-15
8፥9 ዘፀ16፥34፤25፥16፤ዕብ9፥4
8፥10 ዘፀ16፥10፤ዘሌ16፥2፤ራእ15፥8
8፥11 ዘፀ16፥7፤29፥43፤2ዜና7፥2፤ራእ15፥8
8፥12 ዘፀ40፥34፤2ሳሙ22፥10
8፥13 ዘፀ15፥17፤መዝ132፥13፤135፥21፤ማቴ23፥21
8፥14 ዘፀ39፥43
8፥15 1ዜና16፥36፤ሉቃ1፥68
8፥16 ዘፀ3፥10፤ዘዳ12፥5፤1ሳሙ9፥16፤16፥1፤መዝ89፥34
8፥17 1ሳሙ10፥7፤2ሳሙ7፥27፤1ዜና22፥7፤መዝ26፥8፤132፥5፤ሐሥ7፥46
8፥19 2ሳሙ7፥5:13
8፥20 2ሳሙ7፥12፤1ዜና28፥6
8፥22 ዘፀ9፥29
8፥23 ዘፀ9፥14፤ዘዳ7፥9:12፤ነህ1፥5፤9፥32፤ዳን9፥4

ሲል ዳዊት ታቦቱን ከአሚናዳብ ቤት ወደ ኢየሩሳሌም አም
ጥቶት ነበር (2ሳሙ 6 ይመ):: *ከዳዊት ከተማ ከጽዮን፤* የ2ሳሙ
5፥7 ማብ ይመ::

8፥2 *በዓሉ፤* ሰሎሞን የሠራውን ቤተ መቅደስ፣ በዓመቱ
ሰባተኛ ወር በሚከበረው በዳስ በዓል (ዘሌ 23፥34፤ ዘዳ 16፥13-
15) ላይ፣ ለእግዚአብሔር ለማቅረብ፣ ዐሥራ አንድ ወር ሙሉ
የጠበቀ ይመስላል (6፥38 ይመ):: *በሰባተኛው ወር፤* ሰሎሞን በነገሠ
በዐሥራ ሁለተኛው ዓመት ሊሆን ይችላል::

8፥4 *የመገናኛውን ድንኳንና፤* በገባዖን በጥንቃቄ ተቀምጦ
የነበረው የማደሪያው ድንኳን ማለት ነው (የ3፥4 እና የ1ሳሙ
7፥1 ማብ፣ እንዲሁም 2ዜና 5፥4-5 ይመ)::

8፥6 *ከኪሩቤል ክንፍ በታች አኖሩት፤* 6፥23-28 ይመ::

8፥8 *ጫፎቻቸው... ይታዩ ነበር፤* ተሸካሚ መሎጊያዎቹ ሁል
ጊዜ፣ በታቦቱ የወርቅ ቀለበት ውስጥ ሊሆኑ ይገባ ነበር (ዘፀ 25፥15)
*እስከ ዛሬም ድረስ እዚያው ይገኛሉ፤* ይህ ሐሳብ፣ የነገሥትን
መጻሕፍት በመጨረሻ ያጠናቀረው ሰው ሐሳብ ሳይሆን፣ ቤተ
መቅደሱን ለእግዚአብሔር ለማስረከብ ጥረት በሚደረግበት ወቅት
የነበረውን ሁኔታ የጻፈው የመጀመሪያው ጸሓፊ አገላለጽ መሆን
አለበት (በመጽሐፉ መግቢያ ላይ፣ ጸሓፊው፣ የጽሑፉ ምንጭና
የተጻፈበት ዘመን የሚለውን ይመ፤ እንዲሁም 2ዜና 5፥9 ይመ)::

8፥9 *እግዚአብሔር... ኪዳን በገባበት፤* ዘፀ 24 ይመ::
*ሁለት የድንጋይ ጽላቶች፤* ዘፀ 25፥16፤ 40፥20 ይመ::

8፥10 *ደመና ... ቤተ መቅደስ ሞላው፤* የእግዚአብሔር
ክብር በሲና በነበረው መገናኛው ድንኳን ላይ በግልጽ እንደ ወረደ፣
እግዚአብሔር መኖሪያውን በዚህ ቤተ መቅደስ ሊያደርግ መጣ
(ዘፀ 40፥33-35፤ ሕዝ 10፥3-5:18-19፤ 43፥4-5)

8፥12 *እግዚአብሔር ጥቅጥቅ ባለ ደመና ውስጥ እንደሚ
ኖር፤* ዘፀ 19፥9፤ 24፥15:18፤ 33፥9-10፤ 34፥5፤ ዘሌ 16፥2፤ ዘዳ
4፥11፤ 5፥22፤ መዝ 18፥10-11 ይመ::

8፥15 *የሰጠውን ተስፋ፤* 2ሳሙ 7፥5-16 ይመ::

8፥16 *ስሜ፤* እግዚአብሔር ራሱን ያመለክታል (የ5፥5
ማብ ይመ)::

8፥23 *እንዳንተ ያለ አምላክ ከቶ የለም፤* ለዘመናት የሰጠ
ውን የኪዳን ተስፋ ይፈጽም ዘንድ (ዘፀ 15፥11፤ ዘዳ 4፥39፤ 7፥9፤

ለሚኖሩ አገልጋዮችህ ኪዳንህን የም
ትጠብቅ፣ ጽኑ ፍቅርህን የምትገልጥ
አንተ ነህ፤ በላይ በሰማይ፣ በታችም በም
ድር እንዳንተ ያለ ስምባክ ኩቶ የለም፤
24ለባሪያህ ለአባቴ ለዳዊት የሰጠኸውን
ተስፋ ጠብቀሃል፤ በአፍህ ተናገርህ፤ ይህ
ንኑም በዛሬው ዕለት በእጅህ ፈጸምኸው።
25"አሁንም የእስራኤል ስምባክ *እግዚ
አብሔር* ሆይ ለአባቴ ለባሪያህ ለዳዊት፣
'አንተ እንዳደረግኸው ሁሉ፣ ልጆችህ
በፊቴ ለመመላለስ በሚያደርጉት ሁሉ
ይጠንቀቁ ብቻ እንጂ በእስራኤል ዙፋን
ላይ በፊቴ የሚቀመጥ ሰው አታጣም'
ስትል የሰጠኸውን ተስፋ ፈጽምለት።
26አሁንም የእስራኤል ስምባክ ሆይ፤ ለባ
ሪያህ ለአባቴ ለዳዊት የሰጠኸው የተ
ስፋ ቃል ይፈጸም።
27"ነገር ግን ስምባክ በእርግጥ በምድር
ላይ ይኖራልን? እነሆ፤ ሰማይ፣ ከሰማ
ያትም በላይ ያለው ሰማይ እንኳ ይይ
ዝህ ዘንድ አይችልም፤ ታዲያ እኔ የሠ
ራሁት ይህ ቤተ መቅደስማ ምኑ ሊበቃ!
28ስምባክ *እግዚአብሔር* ሆይ፤ ይህም ሆኖ
የባሪያህን ጸሎትና ልመና ስማ፤ በዛ
ሬው ዕለት ባሪያህ በፊትህ የሚያቀር
በውን ጩኸትና ልመና አድምጥ። 29ባሪ
ያህ ወደዚህ ቦታ የሚያቀርበውን ጸሎት
ትሰማ ዘንድ፣ 'ስሜ በዚያ ይሆናል'
ወዳልኸው በዚህ ስፍራ ወዳለው ቤተ
መቅደስ ዐይኖችህ ሌትና ቀን የተ
ከፈቱ ይሁኑ። 30ባሪያህና ሕዝብህ እስ
ራኤል ወደዚህ ስፍራ ጸሎት በሚያ
ቀርቡበት ጊዜ፣ ልመናቸውን ተቀበል፤
መኖሪያህ በሆነው በሰማይ ስማ፤ ሰም
ተህም ይቅር በል።
31"አንድ ሰው ባልንጀራውን በድሎ
መማል ኖሮበት ቢመጣና በዚህ ቤተ

8፥25 2ሳሙ 7፥15፤ 1ዜና 17፥23፤ 2ዜና 1፥9
8፥26 2ሳሙ 7፥25
8፥27 ዘዳ 10፥14፤ 2ዜና 2፥6፤ መዝ 139፥7-16፤ ኢሳ 66፥1፤ ኤር 23፥24፤ ሐሥ 7፥48፤ 17፥24
8፥29 ቍ 52፤ ዘዳ 11፥12፤ 12፥11፤ 2ሳሙ 7፥13፤ 2ነገ 19፥16፤ 2ዜና 7፥15፤ ነህ 1፥6፤ መዝ 5፥1፤ 28፥2፤ 31፥2፤ 102፥17፤ 130፥2፤ 138፥2፤ ኢሳ 37፥17፤ ዳን 6፥10
8፥30 ቍ 39:47፤ ዘፀ 34፥7:9፤ ዘሌ 26፥40-42፤ ነህ 1፥6፤ መዝ 34፥6፤ 85፥2፤ ኤር 29፥12፤ ዳን 9፥4
8፥31 ዘፀ 22፥11
8፥32 ዘዳ 25፥1፤ ሕዝ 18፥20
8፥33 ዘሌ 26፥17:39፤ ኢሳ 37፥1:14:38
8፥35 ዘዳ 28፥24፤ 2ሳሙ 1፥21፤ ኤር 5፥25
8፥36 ቍ 35፤ ዘዳ 8፥3፤ 1ሳሙ 12፥23፤ 1ነገ 17፥1፤ 18፥1:45፤ መዝ 5፥8፤ 27፥11፤ 107፥7፤ ምሳ 11፥5፤ ኢሳ 45፥13፤ ኤር 5፥24፤ 6፥16፤ 7፥23፤ 10፥3፤ 14፥22፤ 31፥21፤ ዘካ 10፥1
8፥37 ዘፀ 10፥13፤ 30፥12፤ ዘሌ 26፥25:26፤ ዘዳ 28፥22፤ መዝ 105፥34
8፥38 ዘ 9፥29
8፥39 ቍ 30፤ ኢሱ 22፥22፤ መዝ 44፥21፤ 130፥4፤ ዮሐ 2፥24፤ ራእ 2፥23

መቅደስ ውስጥ በመሠዊያህ ፊት ቢምል፣
32ይህን በሰማይ ሆነህ ስማ፤ አድርግም፤
በባሪያዎችህ መካከል ፍረድ፤ ለበደለ
ኛው ስለ አድራጎቱ የእጁን ክፈል፤ ከበ
ደል ነጻ ለሆነውም ንጽሕናውን ይፋ በማ
ድረግ ይህንኑ አረጋግጥለት።
33ሕዝብህ እስራኤል አንተን ከመበደ
ላቸው የተነሣ፣ በጠላቶቻቸው ድል በሚ
ሆኑበት ጊዜ፣ ወደ አንተም ተመልሰው
ስምህን ቢጠሩ፣ በዚህም ቤተ መቅደስ
ወደ አንተ ቢጸልዩና ልመናቸውን ቢያ
ቀርቡ፣ 34በሰማይ ሆነህ ስማ፤ የሕዝብህ
የእስራኤልን ኀጢአት ይቅር በል፤ ለአ
ባቶቻቸው ወደ ሰጠሃቸውም ምድር
መልሰህ አግባቸው።
35"ሕዝቡም አንተን ከመበደላቸው የተ
ነሣ፣ ሰማዩ ተዘግቶ ዝናብ ሳይዘንብ
ቢቀር፣ ወደዚህ ስፍራ ቢጸልዩና ስም
ህን ቢጠሩ፣ ስላስጨነቅሃቸውም ከበደላ
ቸው ቢመለሱ፣ 36በሰማይ ሆነህ ስማ፤
የባሪያዎችህን የሕዝብህን የእስራኤልን
ኀጢአት ይቅር በል፤ የሚሄዱበትን ቀና
ውን መንገድ አስተምራቸው፤ ርስት አድ
ርገህ ለሕዝብህ ለሰጠሃትም ምድር
ዝናብ አውርድ።
37"በምድሪቱ ላይ ራብ ወይም ቸነ
ፈር በሚመጣበት፣ ዋግ ወይም አረማሞ
በሚከሠትበት፣ አንበጣ ወይም ኵብ
ኵባ በሚወርድበት ወይም በምድራቸው
ውስጥ ባሉት ከተሞቻቸው ጠላት ቢከ
ባቸው እንዲሁም ማንኛውም ዐይነት ጥፋት
ወይም በሽታ በሚመጣባቸው ጊዜ፣
38ከሕዝብህ ከእስራኤል ማንኛውም ሰው
የልቡን ጭንቀት ዐውቆ እጆቹን ወደዚህ
ቤት በመዘርጋት ጸሎትና ልመና በሚ
ያቀርብበት ጊዜ ሁሉ፣ 39በማደሪያህ
በሰማይ ሆነህ ስማ፤ ይቅር በል፤ አድ
ርግም። አንተ ብቻ የሰውን ሁሉ ልብ

መዝ 86፥8-10 ይመ)፣ *ታላላቅ ታምራትን የሚያደርግ*፣ እንደ እስራኤል አምላክ እንደ እግዚአብሔር ያለ ሌላ አምላክ በታሪክ አልታየም።

8፥24 *የሰጠኸውን ተስፋ፤* ቍ 15፤ 2ሳሙ 7፥5-16 ይመ።

8፥25 *ልጆችህ በፊቴ ለመመላለስ፤* 9፥4-9፤ 2ዜና 7፥17-22 እንዲሁም የ1ነገ 2፥4 ማብ ይመ።

8፥27 *እኔ የሠራሁት ይህ ቤተ መቅደስማ ምኑ ሊበቃ!* የቤተ መቅደሱ መሠራትና የእግዚአብሔር ክብር በዚያ መገለጥ፣ እግዚአብሔር ሕዝቡን ለመርዳትና የሰጠውን ተስፋ ለመፈጸም፣ በመቅደሱ ይኖራል የሚል የተሳሳተ አመለካከት በቀላሉ ሊያስከትል ይችላል (ኤር 7፥4-14፤ ሚክ 3፥11 ይመ)። በአንድ በተወሰነ ቦታ እግዚአብሔር በሕዝቡ መካከል ለመኖር ቢመርጥም፣ ሰማይና ምድር እንኳ እርሱን ይይዙ ዘንድ እንደማይችሉ ሰሎሞን ይገልጻል።

8፥29 *ስሜ፤* እግዚአብሔር ማለት ነው (የ5፥5 ማብ ይመ)።

8፥30 *ወደዚህ ስፍራ ጸሎት በሚያቀርቡበት ጊዜ፤* አንድ እስራኤላዊ በቤተ መቅደስ ተገኝቶ ሊጸልይ ባይችል፣ እግዚአብሔር በሕዝቡ መካከል ለመገኘት ቃል በመግባት ሊኖርበት ወደ መረጠው መቅደስ ፊቱን መልሶ መጸለይ ይገባዋል (ዳን 6፥10) *መኖሪያህ በሆነው በሰማይ፤* የቍ 27 ማብ ይመ።

8፥31 *ቢምል፤* ቃል የገቡትን ነገር አለመፈጸም (ዘፀ 22፥10-12 ) ወይም እንደ ዝሙት (ዘኍ 5፥11-31) በመሳሰሉት ጉዳዮች ላይ የሚቀርበው ክስ ተገቢ መሆኑን ለማጽናት በቂ ማስረጃ በማይኖርበት ጊዜ፣ ተከሳሹ ከበደል ንጹሕ መሆኑን ለማረጋገጥ ወደ ቤተ መቅደሱ መጥቶ እንዲምል ይደረግ ነበር። በረከትን ወይም መርገምን የሚያስከትለው እንደዚህ ዐይነቱ መሐላ፣ ንጹሑንና በደለኛውን ለመለየት ከአምላክ የተሰጠ መመሪያ ነበር።

8፥32 *በሰማይ ሆነህ ስማ፤* ሰሎሞን ይህን መሐላ የተረዳው በአስማት እንደሚሠራ ቅጽበታዊ ኀይል ሳይሆን፣ አንድ ነገር እንዲፈጸም ለእግዚአብሔር የሚቀርብ ጥያቄ ነው።

8፥33 *አንተን ከመበደላቸው የተነሣ፣ በጠላቶቻቸው ድል በሚሆኑበት ጊዜ፤* እስራኤላውያን የገቡትን ቃል ኪዳን ባይጠብቁ ከሚደርስባቸው ርግማኖች አንዱ በጠላት መሸነፍ እንደ ሆነ በዘዳ 28፥25 ላይ ተጠቅሶአል። እግዚአብሔር ለሕዝቡ የሰጠው የቃል ኪዳን ግዴታዎችና አለመታዘዝም የሚያስከትለው ቅጣት ምን እንደ ሆነ በሰሎሞን ጸሎት ተንጸባርቆአል።

8፥34 *ወደ ሰጠሃቸውም ምድር መልሰህ አግባቸው፤* በጦርነት ተማርከው የተወሰዱትን እስረኞች ያመለክታል።

8፥35 *ዝናብ ሳይዘንብ ቢቀር፤* በዘዳ 28፥22-24 ላይ በዝርዝር ከተጻፉት ርግማኖች አንዱ ድርቅ ነው።

8፥36 *ቀናውን መንገድ፤* በኪዳኑ ሕግ ላይ የተመሠረተ ማለት ነው (ዘዳ 6፥18፤ 12፥25፤ 13፥18፤ 1ሳሙ 12፥23 ይመ)።

8፥37 *ራብ፤* ዘዳ 32፥24 ይመ። *ቸነፈር፤* ዘዳ 28፥21-22፤ 32፥24 ይመ። *አንበጣ ወይም ኵብኵባ፤* ዘዳ 28፥38:42 ይመ። *በምድራቸው ውስጥ ባሉት ከተሞቻቸው ጠላት ቢከባቸው፤* ዘዳ 28፥52 ይመ። *ጥፋት፤* ዘዳ 28፥61፤ 31፥29፤ 32፥23-25 ይመ። *በሽታ፤* ዘዳ 28፥22 ይመ።

8፥38 *ማንኛውም ሰው የልቡን ጭንቀት ዐውቆ፤* አንድ

የምታውቅ ስለ ሆንህ ልቡን ለምታው
ቀው ለእያንዳንዱ ሰው እንደ ሥራው
ሁሉ ክፈለው፤ 40ይህም እነርሱ ለአባቶ
ቻችን በሰጠሃቸው ምድር በሚኖሩበት
ጊዜ ሁሉ፣ አንተን እንዲፈሩ ነው።
41“ከሕዝብህ ከእስራኤል ወገን ያል
ሆነ፣ ግን ከስምህ ታላቅነት የተነሣ
ከሩቅ የመጣ የባዕድ አገር ሰው ቢኖር፣
42ሰዎች ከሩቅ የሚመጡት ስለ ታላቁ
ስምህ፣ ስለ ጠንካራዪቱ እጅህ፣ ስለ
ተዘረጋችው ክንድህ ሰምተው ነውና፤
እንግዳው መጥቶ ወደዚህ ቤተ መቅ
ደስ ቢጸልይ፣ 43አንተ በማደሪያህ በሰ
ማይ ሆነህ ስማ፤ የጠየቀህንም ሁሉ
ፈጽምለት፤ ይኸውም የምድር ሕዝቦች
ሁሉ ስምህን ዐውቀው፣ ሕዝብህ እስራ
ኤል አንተን እንደሚፈሩት ሁሉ እንዲ
ፈሩህ፣ እኔ የሠራሁትም ይህ ቤት በስ
ምህ መጠራቱን እንዲያውቁ ነው።
44“ሕዝብህ ጠላታቸውን ለመውጋት
አንተ ወደምትልካቸው ወደ የትኛውም
ቦታ ለጦርነት በሚወጡበት ጊዜ፣ አንተ
ወደ መረጥሃት ከተማና እኔ ለስምህ
ወደ ሠራሁት ቤተ መቅደስ ፊታቸውን
መልሰው *ለእግዚአብሔር* ቢጸልዩ፣ 45ጸሎ
ትና ልመናቸውን በሰማይ ሆነህ ስማ፤
ርዳቸውም።
46“መቼም ኀጢአት የማይሠራ የለ
ምና ሕዝብህ በአንተ ላይ ኀጢአት ቢሠሩ
አንተም ተቈጥተህ ሩቅ ወይም ቅርብ
ወደ ሆነው ምድሩ ማርኮ ለሚወስደው
ጠላት አሳልፈህ ብትሰጣቸው፣ 47ተማ
ርከው በሚኖሩበት አገር ሳሉ ልባቸው
ቢመለስ፣ በተማረኩበትም ምድር ሆነው
ንስሓ ቢገቡና ‘ኀጢአት ሠርተናል፤
በድለናል፤ ክፉ ድርጊትም ፈጽመናል’
ብለው ቢለምኑህ፣ 48እንዲሁም ማርከው
በወሰዷቸው ጠላቶቹ ምድር ሳሉ በፍ
ጹም ልባቸውና በፍጹም ነፍሳቸው ወደ
አንተ ቢመለሱ፣ ለአባቶቻቸው ወደ
ሰጠሃት ወደዚህች ምድር ወደ መረጥሃ
ትም ወደዚህች ከተማና እኔም ለስምህ
ወደ ሠራሁት ቤተ መቅደስ ፊታቸ
ውን መልሰው ቢጸልዩ፣ 49ከማደሪያህ
ከሰማይ ሆነህ ጸሎታቸውን ስማ፤ ልመ
ናቸውንም ተቀበል፤ ርዳቸውም። 50በአ
ንተ ላይ ስለ ሠሩት ኀጢአት፣ አንተንም
ስለ በደሉህ በደል ሁሉ ሕዝብህን ይቅር
በል፤ የማረኳቸውም እንዲራሩላቸው አድ
ርግ። 51ከዚያች እንደ ብረት ማቅለጫ እቶን
እሳት ከሆነችው፣ ከግብፅ ምድር ያወጣ
ሃቸው ሕዝብህም ርስትህም ናቸውና።
52“አሁንም ዐይኖችህ ለባሪያህና ለሕ
ዝብህ ለእስራኤል ልመና የተከፈቱ
ይሁኑ፤ ወደ አንተ በሚጮኹበትም ጊዜ
ሁሉ ስማቸው፤ 53ልዑል ጌታ *እግዚአብሔር*
ሆይ፤ አባቶቻችንን ከግብፅ ባወጣህ ጊዜ፣
በባሪያህ በሙሴ አማካኝነት እንደ ተና
ገርኸው ሁሉ፣ ርስትህ ይሆኑ ዘንድ
ከምድር ሕዝቦች ሁሉ ለይተሃቸዋልና።”

54ሰሎሞንም ይህን ሁሉ ጸሎትና ልመና
*ለእግዚአብሔር* አቅርቦ ከፈጸመ በኋላ፣
እጆቹን ወደ ሰማይ በመዘርጋት፣ በጕልበቱ
ተንበርክኮ ከነበረበት *ከእግዚአብሔር* መሠ
ዊያ ፊት ተነሣ። 55ከዚያም ቆሞ መላውን
የእስራኤልን ጉባኤ ከፍ ባለ ድምፅ እንዲህ
ሲል መረቀ፤

56“በሰጠው ተስፋ መሠረት ለሕዝቡ
ለእስራኤል ዕረፍትን ለሰጠ *እግዚአብሔር*
ምስጋና ይግባው፤ በባሪያው በሙሴ አማ
ካይነት ከተሰጠው መልካም ተስፋ ሁሉ
አንድም ቃል አልቀረምና። 57ልዑል አምላካችን
*እግዚአብሔር* ከአባቶቻችን ጋር እንደ
ነበረ ሁሉ፣ ከእኛም ጋር ይሁን፤ አይተ
ወን፤ አይጣለንም። 58በመንገዱም ሁሉ
እንድንሄድ፣ ለአባቶቻችን የሰጣቸውን ትእ
ዛዞች፣ ሥርዐቶችና ደንቦች እንድንጠብቅ

8፥40 ቍ3940፤ዘዳ 6፥13፤12፥1፤መዝ 103፥11፤130፥4
8፥41 ዘፍ31፥15፤ ኢሳ56፥3:6፤61፥5
8፥42 ዘዳ3፥24፤ 1ነገ10፥1፤ኢሳ 60፥3፤ሐሥ8፥27
8፥43 ዘዳ28፥10፤ ኢሱ4፥24፤1ሳሙ 17፥46፤መዝ102፥15
8፥44 1ዜና5፥20፤ 2ዜና14፥11
8፥45 መዝ9፥4፤ 140፥12
8፥46 ዘሌ26፥33-39፤ዘዳ4፥27፤21፥10፤ 28፥64፤2ነገ25፥21፤ መዝ130፥3፤143፥2፤ ምሳ20፥9፤ሮሜ3፥9
8፥47 ቍ30፤ዘሌ 5፥5፤ዕዝ9፥7:15፤ ነህ1፥6፤መዝ106፥6፤ ኤር3፥25፤14፥20
8፥48 ዘዳ4፥29:30፤ 12፥11-14፤ነህ1፥9፤ መዝ5፥7፤11፥4፤ኤር 23፥3፤31፥8፤ዮና2፥4፤ 1ዮሐ1፥810
8፥50 2ነገ25፥28፤ 2ዜና30፥9፤መዝ106፥ 46፤ዳን1፥9
8፥51 ዘፀ1፥13፤ 34፥9፤ዘዳ9፥29፤ኢሳ 48፥10፤ኤር11፥4
8፥52 ቍ29፤ኢዮ 30፥20፤መዝ3፥4፤22፥ 2፤77፥1፤142፥1
8፥53 ዘ19፥5፤34፥9
8፥55 ዘፀ39፥43፤ ዘኍ6፥23
8፥56 ዘፀ33፥14፤ዘዳ 12፥10፤ኢሱ23፥15፤ ኤር29፥10፤ዕብ4፥8
8፥57 ዘዳ4፥31፤ 31፥6፤ማቴ28፥20፤ ዕብ13፥5
8፥58 ኢሱ24፥23

ሰው በሠራው ኀጢአት ተጸጽቶ፣ ከእግዚአብሔር ምሕረትንና ጸጋን ለማግኘት፣ በንስሓ ወደ እግዚአብሔር ሲቀርብ ማለት ነው (2ዜና 6፥29፤ መዝ 38፥17-18፤ ኤር 17፥9 ይመ)።

8፥39 *እንደ ሥራው ሁሉ ክፈለው፤* ሕዝቡን ለማስቀናትና በቃል ኪዳኑ መንገድ ለመምራት (ቍ 40፤ ምሳ 3፥11፤ ዕብ 12፥5-15 ይመ) እግዚአብሔር በጥበቡ የሚያመጣውን ማንኛውንም ቅጣት ከመመኘት እንጂ፣ አንድ ሰው ለፈጸመው በደል የሚገባውን ቅጣት እንዲያገኝ የተደረገ ጸሎት አይደለም።

8፥40 *አንተን እንዲፈሩ፤* እግዚአብሔርን እንዲያከብሩትና በመታዘዝም እንዲያገለግሉት ማለት ነው (ዘዳ 5፥29፤ 6፥1-2፤ 8፥6፤ 31፥13፤ 2ዜና 6፥31፤ መዝ 130፥4 ይመ)።

8፥41 *ከሕዝብህ ከእስራኤል ወገን ያልሆነ…የባዕድ አገር ሰው፤* በቤተ መቅደስ ወደ እስራኤል አምላክ ለመጸለይ ከሌላ አገር የመጣ፣ ነዋሪነቱም በዚያ እንዳልሆነ የሚታወቅ እንግዳ ሰው ማለት ነው።

8፥42 *ሰዎች…ሰምተው፤* (በአጠቃላይ የሌላ አገር ሕዝብ ማለት ነው)፤ 10፥1 (የሳባ ንግሥት)፤ ኢሱ 2፥9-11 (ረዓብ)፤ 1ሳሙ 4፥6-8 (ፍልስጥኤማውያን) ይመ። *ስለ ታላቁ ስምህ፣ ስለ ጠንካራዪቱ እጅህ፣ ስለ ተዘረጋችው ክንድህ፤* በሕዝቡ ታሪክ ውስጥ የተገለጸው የእግዚአብሔር ታላቅ ኀይል ማለት ነው (ዘዳ 4፥34፤ 5፥15፤ 7፥19፤ 11፥2፤ 26፥8 ይመ)።

8፥44 *አንተ ወደምትልካቸው ወደ የትኛውም ቦታ ለጦርነት በሚወጡበት ጊዜ፤* በመለኮት ፈቃድ የሚመራ ወታደራዊ እንቅስቃሴን ያመለክታል (ዘሌ 26፥7፤ ዘዳ 20፤ 21፥10፤ 1ሳሙ 15፥3፤ 23፥2:4፤ 30፥8፤ 2ሳሙ 5፥19:24 ይመ)። *አንተ ወደ መረጥሃት ከተማና፤* የቍ 30 ማብ ይመ።

8፥46 *ማርኮ ለሚወስደው ጠላት፤* በዘሌ 26፥33-45 እና በዘዳ 28፥64-68፤ 30፥1-5 ላይ በተጠቀሰው መሠረት ልብን አደንድኖ ካለመታዘዝ ከተስፋዪቱ ምድር አውጥቶ ለስደት እንደሚዳርግ ሰሎሞን ተረድቶአል።

8፥51 *እንደ ብረት ማቅለጫ እቶን እሳት፤* ዘዳ 4፥20 እና ማብ ይመ።

8፥53 *ርስትህ ይሆኑ ዘንድ ከምድር ሕዝቦች ሁሉ ለይተሃቸዋልና፤* ሰሎሞን የጸሎቱ መጀመሪያ ያደረገው እግዚአብሔር ለዳዊት የገባውን ኪዳን ሲሆን፣ (ቍ 23-30) የጸሎቱ መደምደሚያ ያደረገው ደግሞ፣ የሲናን ኪዳን ነው (ዘፀ 19፥5፤ ዘሌ 20፥24:26 ፤ ዘዳ 7፥6፤ 32፥9 ይመ)።

8፥54 *በጕልበቱ ተንበርክኮ፤* ከቍ 22፤ 2ሳሙ 7፥18፤ 2ዜና 6፥13፤ ሉቃ 22፥41፤ ኤፌ 3፥14 ጋር ያነጻጽሩ።

8፥56 *እግዚአብሔር ምስጋና ይግባው፤* እግዚአብሔር ለኪዳን ታማኝ ለመሆኑ ይህ ታሪካዊ ቀን፣ ምስክር እንደ ሆነ ሰሎሞን ተረድቶአል። *ለሕዝቡ… ዕረፍትን ለሰጠ፤* በኢያሱ መሪነት ከነዓን ድል ከተደረገች በኋላ፣ ሳይወረስ የቀረ ብዙ መሬት ቢኖርም (ኢሱ 13፥1፤ መሳ 1)፣ እግዚአብሔር እስራኤላውያንን ከጠ

ልባችንን ወደ እርሱ ይመልስ:: 59በየዕ
ለቱም ባሪያውንና ሕዝቡን እስራኤልን
በሚያስፈልጋቸው ሁሉ እንዲረዳቸው፣
ይህች *በእግዚአብሔር ፊት ያቀረብኋት*
የራሴ ልመና በቀንና በሌሊት ወደ
ስምባካችን ወደ *እግዚአብሔር ፊት* ትቅ
ረብ:: 60ይኸውም የምድር ሕዝቦች ሁሉ
*እግዚአብሔር* ብቻ ስምባክ እንደ ሆነና
ከእርሱ በቀር ሌላ እንደ ሌለ ያውቁ
ዘንድ ነው:: 61ስለዚህ እንደ ዛሬው ዕለት
ሁሉ፣ በሥርዐቱ እንድትኖሩና ትእዛዙን
እንድትጠብቁ ልባችሁ ስምባካችሁ *ለእግዚአ
ብሔር* የተገዛ ይሁን::"

## የቤተ መቅደሱ መመረቅ

8፥62-66 ተጓ ምብ - 2ዜና 7፥1-10

62ከዚያም ንጉሡና ከእርሱ ጋር ያሉት
እስራኤል ሁሉ *በእግዚአብሔር ፊት መሥ
ዋዕት* አቀረቡ:: 63ሰሎሞንም ሃያ ሁለት ሺህ
በሬ፣ መቶ ሃያ ሺህ በግና ፍየል የኅብረት
*መሥዋዕት*[ሀ] አድርጎ *ለእግዚአብሔር* አቀረበ፤
ንጉሡና እስራኤላውያንም ሁሉ *የእግዚአ
ብሔርን* ቤተ መቅደስ በዚህ ሁኔታ ቀደሱ::
64በዚያኑ ዕለትም ንጉሡ *በእግዚአብሔር*
ቤተ መቅደስ ፊት ለፊት ያለውን የአደባ
ባዩን መካከለኛ ክፍል ቀደሰ፤ በዚያም የሚ
ቃጠለውን *መሥዋዕት*፣ የእህል ቍርባንና
የኅብረት መሥዋዕቱን ስብ አቀረበ፤ ይህን
ያደረገውም *በእግዚአብሔር ፊት* የነበረው የናስ
መሠዊያ ከትንሽነቱ የተነሣ የሚቃጠለውን
መሥዋዕት የእህሉን ቍርባንና የኅብረት
መሥዋዕቱን ስብ መያዝ ባለመቻሉ ነበር::
65በዚያን ጊዜም ሰሎሞን አብረውት ካሉት
የእስራኤል ሕዝብ ሁሉ ጋር፣ ማለትም
ከሐማት መተላለፊያ እስከ ግብፅ ደረቅ
ወንዝ[ሁ] ካለው ምድር ከተሰበሰበው ታላቅ
ጉባኤ ጋር በዓሉን አከበረ:: እነርሱም ሰባት
ቀን፣ በተጨማሪም ሌላ ሰባት ቀን በድ
ምሩ ዐሥራ አራት ቀን በስምባካችን *በእግዚ
አብሔር ፊት* በዓሉን አከበሩ:: 66በሚቀጥ
ለው ቀን ሕዝቡን አሰናበተ፤ ሕዝቡም ንጉ
ሡን መረቁ፤ *እግዚአብሔር* ለባሪያው ለዳ
ዊትና ለሕዝቡ ለእስራኤል ባደረገው በጎ
ነገር ሁሉ ከልብ ተደስተው ሐሤት በማድ
ረግ ወደየቤታቸው ተመለሱ::

8፥60 ሀዳ4፥35፤ኢሱ 4፥24
8፥61 ዘዳ6፥5፤1ነገ 9፥4፤11፥4፤15፥3፥14፤ 22፥43፤2ነገ20፥3፤ 1ዜና28፥9፤29፥19፤ 2ዜና16፥9፤17፥6፤ 25፥2፤መዝ119፥80፤ ኢሳ38፥3
8፥62 2ሳሙ6፥13፤ 1ዜና29፥21፤ ሕዝ45፥17
8፥63 ዕዝ6፥16
8፥64 ዘፀ27፥1፤ 29፥13፤2ሳሙ6፥17፤ 2ነገ16፥14፤2ዜና4፥1፤ 8፥12፤15፥8፤ ሕዝ43፥13-17
8፥65 ቍ2፤ዘፍ 15፥18፤ዘኍ13፥21
8፥66 ዘፀ18፥9
9፥1 2ሳሙ7፥2
9፥2 1ነገ3፥5
9፥3 ዘፀ20፥24፤ዘዳ 11፥12፤12፥5፤1ሳሙ 9፥16፤2ነገ19፥20፤ 20፥5፤መዝ10፥17፤ 34፥17
9፥4 ዘፍ17፥1፤ዘዳ 17፥20፤1ነገ3፥14፤ 14፥8፤15፥5፤1ዜና28፥ 9፤ምሳ4፥4
9፥5 2ሳሙ7፥15፤ 1ዜና22፥10
9፥6 ዘዳ28፥15፤ 2ሳሙ7፥14፤1ነገ11፥ 10፤2ነገ18፥12፤ኤር 17፥27፤26፥4፤32፥23 ፤44፥23
9፥7 ዘሌ18፥24-28፤ ዘዳ4፥26፤12፥5፤28፥ 37፤ኢሱ23፥13፤2ነገ 17፥23፤ኢዮ17፥6፤ መዝ44፥14፤ኤር7፥14 ፤24፥9፤10፤ሕዝ5፥15፤ ኢል2፥17
9፥8 ዘሌ26፥32፤ ዘዳ29፥24፤ኤር7፥4-15፤ማቴ23፥38

## *እግዚአብሔር* ለሰሎሞን ዳግመኛ ተገለጠ

9፥1-9 ተጓ ምብ - 2ዜና 7፥11-22

9 ሰሎሞን *የእግዚአብሔርን* ቤተ መቅደ
ስና የራሱን ቤተ መንግሥት ሠርቶ
ከጨረሰና ለመሥራት የፈለገውንም ሁሉ
ካከናወነ በኋላ፣ 2*እግዚአብሔር* ለሰሎሞን
በገባዖን ተገልጦለት እንደ ነበረ ሁሉ ዳግም
ተገለጠለት:: 3*እግዚአብሔርም* እንዲህ አለው፤
"በፊቴ ያቀረብኸውን ጸሎትና ልመና
ሰምቻለሁ፤ ይህን የሠራኸውንም ቤተ
መቅደስ ስሜን በዚያ ለዘላለም እንዲኖር
በማድረግ ቀድሼዋለሁ፤ ዐይኖቼና ልቤ
ምን ጊዜም በዚያ ይሆናሉ::
4"አንተም አባትህ ዳዊት እንዳደረገው፣
በልበ ቅንነትና በትክክለኛነት ብትሄድ፣
የማዝህን ሁሉ ብትፈጽም፣ ሥርዐቴንና
ሕጌን ብትጠብቅ፣ 5ለአባትህ ለዳዊት፣
'በእስራኤል ዙፋን ላይ የሚቀመጥ ከዘ
ርህ ሰው አታጣም' በማለት በሰጠሁት
ተስፋ መሠረት ዙፋንህን በእስራኤል ላይ
ለዘላለም አጸናለሁ::
6"ነገር ግን አንተም[ሂ] ሆንህ ልጆችህ
እኔን ከመከተል ወደ ኋላ ብትመለሱ፣
የሰጠኋችሁን ትእዛዞችና ሥርዐቶች ሳት
ጠብቁ ብትቀሩ፣ ሄዳችሁም ሌሎችን
አማልክት ብታመልኩና ብትሰግዱላ
ቸው፣ 7እኔም እስራኤልን ከሰጠኋቸው
ምድር እነቅላቸዋለሁ፤ ስለ ስሜ የቀደ
ስሁትን ይህን ቤተ መቅደስም እተወ
ዋለሁ፤ ከዚያም እስራኤል በሕዝቦች
ሁሉ ዘንድ መተረቻና መዘባበቻ ይሆ
ናሉ፤ 8ይህ ቤተ መቅደስ አሁን የሚያ
ስገርም ቢሆንም እንኳ፣ የፍርስራሽ
ክምር ይሆናል፤ ዐላፊ አግዳሚውም ሁሉ
ይገረማል፤ እያፌዘም፣ '*እግዚአብሔር*
በዚህች ምድርና በዚህ ቤተ መቅደስ ላይ

[ሀ]63 በዚህና በቍ 64 ላይ በትውፊት፣ *የሰላም መሥዋዕት* ይባላል::
[ሁ]65 ወይም *ከመግቢያው ጀምሮ* ተብሎ መተርጐም ይችላል::
[ሂ]6 የዕብራይስጡ ትርጕም የብዙ ቍጥርን ያመለክታል

ላቶቻቸው አሳርፎአቸው ነበር (ኢሱ 11፥23፤ 21፥44፤ 22፥4):: ሆኖም አስተማማኝ ዕረፍት የተገኘው፣ ዳዊት ባስገኘው ድል ነበር (2ሳሙ 7፥1 እንዲሁም የ1ነገ 5፥4 ማብ ይመ)::

8፥58 *ልባችንን ወደ እርሱ ይመልስ፤* ለኪዳኑ ታማኝ እንዲሆኑ የሚያስችላቸውን ጸጋ እግዚአብሔር ለሕዝቡ እንዲሰጣቸው ሰሎሞን ጸለየ (ዘዳ 30፥6፤ መዝ 51፥10፤ ፊል 2፥13 ይመ)::

8፥59 *ባሪያውንና፤* በእግዚአብሔር የተቀባ ስለ ሆነ እግዚአብሔርን ወክሎ ሕዝቡን በመምራት የሚያገለግለው ንጉሡ ነው (የመዝ 2፥2:7 ማብ ይመ)::

8፥60 *ሁሉ ... ያውቁ ዘንድ፤* የመዝ 46፥10 ማብ ይመ::

8፥63 *ሃያ ሁለት ሺህ በሬ፣ መቶ ሃያ ሺህ በግና ፍየል፤* ይህ ቍጥር ከፍተኛ ቢሆንም፣ ቤተ መቅደሱን ለእግዚአብሔር ለመቀደስ ለዐሥራ አራት ቀንም በቈየው በዓል ላይ የተገኘ ሕዝብ፣ በጣም ብዙ ነበር (ቍ 1-2 እንዲሁም ቍ 65 ይመ):: *የኅብረት መሥዋዕት፤* በኅብረት ማዕድ መቍረስን የሚያካትት ነበር (የ1ሳሙ 11፥15 ማብ ይመ)::

8፥65 *ከሐማት፤* የሕዝ 47፥15 ማብ ይመ:: *እስከ ግብፅ ደረቅ ወንዝ፤* ቤተ መቅደሱን ለእግዚአብሔር ለመቀደስ፣ የሰሎሞን ግዛት ከሆነው አካባቢ ሁሉ (የ4፥21 ማብ ይመ) ሰዎች ወደ ኢየሩሳሌም መጥተው ነበር:: *ሰባት ቀን፣ በተጨማሪም ሌላ ሰባት ቀን በድምሩ ዐሥራ አራት ቀን፤* ቤተ መቅደሱን ከመቀደስ ክብረ በዓል በመቀጠል፣ በሰባተኛው ወር ከዐሥራ አምስተኛው እስከ ሃያ አንደኛው ቀን ድረስ የተከበረውን የሰባቱን ቀን የዳስ በዓል የሚያጠቃልል ነው (የቍ 2 ማብ ይመ)::

9፥1 *ሰሎሞን... ሠርቶ ከጨረሰና... በኋላ፤* በሰሎሞን መንግሥት ዘመን በሃያ አራተኛው ዓመት (4+7+13=24) (6፥1:37-38፤ 7፥1፤ 9፥10 ይመ) ዓ.ቅ.ክ. 946 ማለት ነው::

9፥2 *በገባዖን ተገልጦለት፤* 3፥4-15 ይመ::

9፥3 *ስሜን በዚያ ለዘላለም እንዲኖር፤* 8፥10-13 ይመ:: *ዐይኖቼና ልቤ ምን ጊዜውም በዚያ ይሆናሉ፤* 8፥29 ይመ::

9፥4-5 *በልበ ቅንነትና... ብትሄድ... ዙፋንህን በእስራኤል ላይ ለዘላለም አጸናለሁ፤* 8፥25 እንዲሁም የ2፥4 ማብ ይመ:: መርገ ምን ሳይሆን በረከትን እንዲያገኝ፣ ኪዳኑን መታዘዝ አስፈላጊ እንደ ሆነ፣ እግዚአብሔር ለሰሎሞን በአጽንዖት ገለጸለት:: የሰሎሞን መንግሥት እየታወቀና በሀብት እያደገ በሄደበት በዚህ ጊዜ፣ ከብልጽግናው የተነሣ ኪዳኑን እንዳያፈርስ ይህን ዐይነት ምክር ማግኘቱ ጠቃሚ ነበር (ዘዳ 8፥12-14:17፤ 31፥20፤ 32፥15 ይመ)::

9፥6 *ሌሎችን አማልክት ብታመልኩና ብትሰግዱላቸው፤*

እንዲህ ያለውን ነገር ያደረገው ስለምን
ይሆን?' ይላል፤ [9]ራሱ መልሱም፣ 'አዎን
እግዚአብሔር ይህን ሁሉ ጥፋት ያመጣ
ባቸው አባቶቻቸውን ከግብፅ ምድር ያወ
ጣውን ስምላካቸውን እግዚአብሔርን ትተው
ሌሎች አማልክትን በመከተል ስለ ሰገ
ዱላቸውና ስላመለኳቸው ነው' ይላል።"

## ሰሎሞን ያከናወናቸው ሌሎች ሥራዎች

9፥10-28 ተጓ ምብ - 2ዜና 8፥1-18

[10]ሰሎሞን ሁለቱን ሕንጻዎች፣ ማለትም
የእግዚአብሔርን ቤተ መቅደስና የንጉሡን
ቤተ መንግሥት ሠርቶ በፈጸመ በሃያኛው
ዓመት መጨረሻ፣ [11]ንጉሥ ሰሎሞን በገሊላ
የሚገኙትን ሃያ ከተሞች ለጢሮስ ንጉሥ
ለኪራም ሰጠው፤ ንጉሡ ይህን ያደረገውም፣
የሚያስፈልገውን ሁሉ ዝግባ፣ ጥድና ወርቅ
ኪራም ሰጥቶት ስለ ነበር ነው፤ [12]ይሁን እንጂ
ኪራም ከጢሮስ ተነሥቶ ሰሎሞን የሰጠውን
ከተሞች ለማየት በሄደ ጊዜ አልተደሰተባ
ቸውም፤ [13]እርሱም፣ "ወንድሜ ሆይ፤ እነዚህ
የሰጠኸኝ ከተሞች ምንድን ናቸው?" አለ፤
እነዚህንም 'ከቡል[a] ምድር' አላቸው፤ እስከ
ዛሬም በዚሁ ስም ይጠራሉ። [14]በዚያን ጊዜ
ኪራም ለንጉሡ መቶ ሃያ መክሊት[b] ወርቅ
ልኮለት ነበር።
[15]ንጉሥ ሰሎሞን የእግዚአብሔርን ቤተ
መቅደስ፣ የራሱን ቤተ መንግሥት፣ ሚሎን፣
የኢየሩሳሌምን ቅጥር፣ ሐጾርን፣ መጊዶንና
ጌዝርን ለመሥራት የጕልበት ሠራተኞች
መልምሎ ነበር። [16]የግብፅ ንጉሥ ፈርዖን
ወጥቶ በጌዝር ላይ አደጋ ጥሎ ያዛት፤ አቃጠ
ላትም፤ ነዋሪዎቿን ከነዓናውያንን ገድሎ ለልጁ
ለሰሎሞን ሚስት መዳሪያ አድርጎ ሰጥቶአት
ነበር፤ [17]ሰሎሞንም ጌዝርን መልሶ ሠራት፤
እንዲሁም የታችኛውን ቤትሖሮንን፣ [18]ባዕ
ላትን፣ በይሁዳ ምድር በምድረ በዳው የም
ትገኘውን ተድሞርን[c] ሠራ፤ [19]ደግሞም ማና
ቸውንም በኢየሩሳሌም፣ በሊባኖስና በሌሎች
ግዛቶቹ ሁሉ ለመሥራት የፈለገውን፣ ሥንቅ
የሚከማችባቸውን፣ ሠረገሎች[d] የሚጠበቁባ
ቸውን እንዲሁም ፈረሰኞች የሚቀመጡባ
ቸውን ከተሞችና መንደሮች ሁሉ ሠራ።
[20]ከእስራኤል ሕዝብ ያልሆኑትን ከአሞራ
ውያን፣ ከኬጢያውያን፣ ከፌርዛውያን፣ ከኤ
ውያውንና ከኢያቡሳውያን ሕዝቦች ሁሉ
የተረፉትን፣ [21]እስራኤላውያን ዘሮቻቸውን
ለማጥፋት[e] ያልቻሉትንና በምድሪቱ የቀሩ
ትን እነዚህን እስከ ዛሬ እንደሚደረገው ሁሉ፣
ሰሎሞን ለግዳጅ ሥራ መለመላቸው። [22]ይሁን
እንጂ ሰሎሞን ከእስራኤላውያን ማንንም
ባሪያ አላደረገም፤ እነርሱ ወታደሮቹ፣ ሹማ
ምቱ፣ የጦር አለቆቹ፣ ሻምበሎቹ፣ ባልደራ
ሶቹ ነበሩ። [23]እነዚህም ሰሎሞን የሚያሠራ
ውን የሕንጻ ሥራ የሚያከናውኑትን ሠራተ
ኞች የሚቈጣጠሩ ናቸው፤ ቍጥራቸውም
አምስት መቶ አምሳ ነበር።
[24]የፈርዖን ልጅ ከዳዊት ከተማ ሰሎሞን
ወዳሠራላት ቤተ መንግሥት ከመጣች በኋላ
ሰሎሞን ሚሎንን ሠራ።
[25]ሰሎሞንም ለእግዚአብሔር ባሠራው መሠ
ዊያ ላይ በዓመት ሦስት ጊዜ የሚቃጠል
መሥዋዕትና የኅብረት መሥዋዕት[f] በማቅ
ረብ፣ ከዚሁ ጋር በእግዚአብሔር ፊት ዕጣን
ያሳርግ ነበር፤ በዚህ ሁኔታም የቤተ መቅደ
ሱን ግዳጅ ተወጣ።

9፥9 ዘኍ25፥3፤ዘዳ 29፥25፤31፥29፤2ነገ 22፥17፤ኤር5፥19፤ 13፥22፤16፥11፡13፤ 22፥9፤40፥3፤44፥23፤ ሰቆ4፥12
9፥11 ቍ14
9፥13 ኢሱ19፥27
9፥14 ቍ11
9፥15 ኢሱ10፥33፤ 11፥10፤12ሳሙ5፥9፤ 1ነገ5፥13
9፥16 1ነገ3፥1፤መዝ 45፥12፤68፥29፤ 72፥10
9፥17 ኢሱ10፥10
9፥18 ኢሱ19፥44
9፥19 ዘፀ1፥11፤ዘዳ 17፥16፤1ነገ4፥26፤ 2ዜና1፥14፤9፥25
9፥20 ዘኍ13፥29፤ ኢሱ11፥3
9፥21 ዘፍ9፥2526፤ 49፥15፤ዘፀ1፥11፤ ዘዳ20፥11፤ኢሱ15፥63
9፥22 ዘሌ25፥39
9፥23 1ነገ5፥16
9፥24 2ሳሙ5፥9፤ 1ነገ3፥1፤11፥27
9፥25 ዘፀ23፥14

[a] 13 ከቡል የሚለው የዕብራይስጥ ቃል፣ *የመልካም ነገር ተምሳሌት* ከሚለው የዕብራይስጥ ቃል ጋር ተመሳሳይ የሆነ ድምፅ አለው።
[b] 14 4 ሜትሪክ ቶን ያህል ነው
[c] 18 በዕብራይስጥ፣ *ታማር* ተብሎ ይነበባል
[d] 19 ወይም *ሠረገለኞች* ተብሎ መተርጐም ይችላል
[e] 21 የዕብራይስጡ ቃል ሰውን ወይም ቍስን ፈጽሞ በማጥፋት ለእግዚአብሔር መስጠት የሚለውን ያመለክታል
[f] 25 በትውፊት፣ *የሰላም መሥዋዕት* ይባላል

11፥4-8 ይመ።

9፥7 *በሕዝቦች ሁሉ ዘንድ መተረቻና መዘባበቻ፤* በዘዳ 28፥37 ላይ የተጠቀሰውን የኪዳን ርግማን ይመ።

9፥9 *እግዚአብሔር ይህን ሁሉ ጥፋት ያመጣባቸው፤* ዘዳ 29፥22-28፤ ኤር 22፥8-30 ይመ።

9፥11 *ሰሎሞን በገሊላ የሚገኙትን ሃያ ከተሞች ለጢሮስ ንጉሥ ለኪራም ሰጠው፤* ቍ 10-14 ከ5፥1-12 ጋር ሲነጻጸር፣ ሰሎሞን በሃያ ዓመቱ የግንባታ ሥራ ወቅት የሠራተኞችን (5፥6) እና የዕንጨት (5፥10-11) ዋጋ ለመክፈል መጀመሪያ ተስማ ምቶ (5፥9) ከተገመተው በላይ የኪራም ባለ ዕዳ መሆኑን ያመለክታል። በቍ 11:14 ላይ እንደ ተጠቀሰው ሰሎሞን ከሠራተኛና ከዕንጨት ሌላ፣ መጠኑ ከፍተኛ የሆነ ወርቅ ከኪራም ማግኘት ፈልጎ ነበር። በፊንቄና በገሊላ ድንበር የሚገኙ ሃያ ከተሞችን ሰሎሞን ለኪራም የሰጠው፣ የወሰደውን ወርቅ እንደሚከፍል ዋስ ትና ለመስጠት ነበር። ሰሎሞን ከኦፊር ዘመቻ መልስ (1ነገ 9፥26-28፤ 10፥11) ወይም ከሳባ ንግሥት ጕብኝት በኋላ (10፥1-13) የወርቁ ሀብት በበዛ ጊዜ፣ በ2ዜና 8፥1-2 እንደ ተገለጸው፣ የነበረበትን ዕዳ በመክፈል በዋስትና ያስያዘውን ሃያ ከተሞች ከኪራም አስመልሰዋል።

9፥15 *ቅጥር፤* ሰሎሞን ኢየሩሳሌምን ከዳዊት ከተማ በስተ ሰሜን እስከሚገኘው ጉብታ ድረስ ለማስፋፋት ዕቅድ የተነሣ ያሠ ራው ይመስላል (የ2ሳሙ 5፥9 ማብ ይመ)። *ሐጾር፤* ሰሎሞን ጥን ታዊ ከተሞች በሆኑት ሐጾር፣ በመጊዶና በጌዝር የነበረው የግ ንባታ ሥራ ዓላማው፣ ጠላትን ለመከላከል ጠቀሜታ ያላቸው በመ ሆናቸው፣ በዚያ የነበሩትን ምሽጎች ለማጠናከር አስቦ ነው። ሐጾር፣ ከኤፍራጥስ ወንዝ እስከ ግብፅ ድረስ ያለውን የንግድ መስመር ለመቈጣጠር ምቹ የሆነ በሰሜናዊ የገሊላ አውራጃ ምሽግ ነበር። *መጊዶና፤* በትልቁ ሰሜን ደቡብ የንግድ መስመር አቅጣጫ የተሠራ ቅጥር ሲሆን፣ ይህም ከኢያዝራዔል ሜዳ ጀምሮ በሳሮን የባሕር ዳርቻ እስከሚገኘው ሜዳ ድረስ ያለውን የቀርሜሎስ ተራራ መተ ላለፊያ ለመቈጣጠር ይጠቅም ነበር። *ጌዝርን፤* የ3፥1 ማብ ይመ። *የጕልበት ሠራተኞች፤* በቋሚነት የሚሠሩ እስራኤላውያን ያል ሆኑ ባሪያዎች ሲሆኑ፣ በተቃራኒው ደግሞ እስራኤላውያን በ5፥13-16 እንደ ተገለጸው ለጊዜው ብቻ ተገደው የሚሠሩ ናቸው።

*9፥16 ነዋሪዎቿን ከነዓናውያንን ገድሎ፤* ከነዓንን በሚይዙ በት ጊዜ ኢያሱ (ኢሱ 10፥33፤ 12፥12) የጌዝርን ንጉሥ ቢገድ ልም፣ የኤፍሬም ነገድ ሰዎች ግን ነዋሪዎቹን ለማስለቀቅ አልቻ ሉም ነበር (ኢሱ 16፥10፤ መሳ 1፥29)።

9፥17 *የታችኛውን ቤትሖሮንን፤* ከኢየሩሳሌም በስተ ሰሜን ምዕራብ ዐሥራ ሦስት ኪሎ ሜትር ያህል ርቀት ላይ የሚገኝ፣ ከባሕር ጠረፍ ወደ ይሁዳ ተራራማ ቦታዎችና ወደ ኢየሩሳሌም ሜዳማ ቦታዎች መተላለፊያ መግቢያ በር ነው።

9፥18 *ባዕላትን፤* በኢሱ 15፥24 ላይ የተጠቀሰው በይሁዳ ነገድ ግዛት በደቡብ ኬብሮን የሚገኘው በዓሎት ወይም በዳን ነገድ ደቡብ ምዕራብ የሚገኘው ባዕላት ነው (ኢሱ 19፥44)። *ተድሞርን፤* 2ዜና 8፥4፤ ሕዝ 47፥19 ይመ።

9፥20 *ከአሞራውያን... ከኢያቡሳውያን፤* ዘዳ 7፥1፤ 20፥17 ይመ እንዲሁም የዘፍ 10፥15-18፤ 13፥7፤ 15፥16፤ 23፥9፤ የኢሱ 5፥1 ፤ የመሳ 3፥3፤ 6፥10፤ የ2ሳሙ 21፥2 ማብ ይመ።

9፥22 *ሰሎሞን ከእስራኤላውያን ማንንም ባሪያ አላደረገም፤* የቍ 15 ማብ ይመ።

9፥23 *ሠራተኞች የሚቈጣጠሩ... አምስት መቶ አምሳ፤* የ5፥16 ማብ ይመ።

[26]እንዲሁም ንጉሡ ሰሎሞን በኤዶምያስ
ምድር፣ በኤሎት አጠገብ፣ በቀይ ባሕር[t]
ዳርቻ ላይ ባለችው በዔጽዮንጋብር መርከ
ቦችን ሠራ:: [27]በመርከቦቹም ላይ ከሰሎሞን
ሰዎች ጋር አብረው እንዲሠሩ፣ ኪራም
ባሕሩን የሚያውቁ የራሱን መርከበኞች ላከ::
[28]እነዚያም ወደ ኦፊር ሄደው አራት መቶ
ሃያ መክሊት[m] ወርቅ ይዘው ተመለሱ፤ ይህ
ንም ለንጉሥ ሰሎሞን ሰጡት::

## ንግሥተ ሳባ ሰሎሞንን እንደ ጐበኘች

10፥1-13 ተጓ ምብ - 2ዜና 9፥1-12

**10** ንግሥተ ሳባ የሰሎሞንን ዝና እና
*ከእግዚአብሔር* ስም ጋር ያለውን
ግንኙነት በሰማች ጊዜ፣ አስቸጋሪ በሆኑ
ጥያቄዎች ልትፈትነው መጣች:: [2]ታላቅ
አጀብ አስከትላ ሽቶ፣ እጅግ ብዙ ወርቅና
የከበሩ ዕንቍች በግመል አስጭና ኢየሩሳሌም
ከደረሰች በኋላ፣ ወደ ሰሎሞን ገብታ በልቧ
ያለውን ጥያቄ ሁሉ አቀረበችለት:: [3]ሰሎ
ሞንም የጠየቀችውን ሁሉ መለሰላት፤ ንጉሡ
አቅቶት የቀረ አንዳች ጥያቄ አልነበረም::
[4]ንግሥተ ሳባ የሰሎሞንን ጥበብ ሁሉ፣ የሠ
ራውንም ቤተ መንግሥት ስትመለከት [5]እን
ዲሁም በገበታው ላይ የሚቀርበውን መብል፣
የሹማምቱን አቀማመጥ፣ አሳላፊዎቹን ከነ
ደንብ ልብሳቸው፣ ጠጅ አሳላፊዎቹን፣ ደግ
ሞም *በእግዚአብሔር* ቤተ መቅደስ ያቀረበ
ውን የሚቃጠል መሥዋዕት[w] ስታይ እጅግ
ተደነቀች::

[6]ንጉሡንም እንዲህ አለችው፤ "ስላከናወ
ንኸው ሥራና ስለ ጥበብህ ባገሬ ሳለሁ የሰ
ማሁት ትክክል ነው፤ [7]ይሁን እንጂ፣ ራሴ
መጥቼ እነዚህን ነገሮች በዐይኔ እስካይ
ድረስ አላመንሁም ነበር፤ በእርግጥ ግማሹን
እንኳ አልነገሩኝም፤ ጥበብህና ብልጽግናህ
ከሰማሁት በላይ ነው::' [8]ሰዎችህ እንዴት
ያሉ ዕድለኞች ናቸው! ሁል ጊዜ በፊትህ
ቆመው ጥበብህን የሚሰሙ ሹማምትህስ
እንዴት የታደሉ ናቸው! [9]በአንተ ደስ ተሰ
ኝቶ በእስራኤል ዙፋን ላይ ያስቀመጠህ
*እግዚአብሔር* ስምላክህ የተመሰገነ ይሁን፤
*እግዚአብሔር* በዘላላም ፍቅሩም እስራኤልን
ከመውደዱ የተነሣ፣ ፍትሕና ጽድቅ እንዲ
ሰፍን አንተን ንጉሥ አድርጎ አስነሣህ::"

[10]ለንጉሡም መቶ ሃያ መክሊት[a] ወርቅ፣
እጅግ ብዙ ሽቶና የከበረ ድንጋይ ሰጠችው፤
ንግሥተ ሳባ ለንጉሥ ሰሎሞን ያበረከተችለ
ትን ያን ያህል ብዛት ያለው ሽቶ ከዚያ
በኋላ ከቶ አልመጣም::

[11]ከኦፊር ወርቅ ያመጡት የኪራም መር
ከቦች፣ እጅግ ብዙ የሰንደል ዕንጨትና[x]
የከበሩ ዕንቍችም አመጡ:: [12]ንጉሡም የሰን
ደሉን ዕንጨት ለ*እግዚአብሔር* ቤተ መቅ
ደስና ለቤተ መንግሥቱ መደገፊያ፣ ለበገናና
ለመሰንቆ መሥሪያ አዋለው:: ይህን ያህል ብዛት
ያለው የሰንደል ዕንጨት እስከ ዛሬ ድረስ ከቶ
አልመጣም፤ አልታየምም::

[13]ንጉሥ ሰሎሞንም ለንግሥተ ሳባ ከቤተ
መንግሥቱ በልግስና ከሚሰጣት ሌላ፣ የፈለ
ገችውንና የጠየቀችውን ሁሉ ሰጣት፤ ከዚ
ያም ከአጀቢዎቿ ጋር ወደ አገሯ ተመለሰች::

9፥26 ዘኍ33፥35፤ 1ነገ10፥22፤22፥48፤2ነገ14፥22፤16፥6፤2ዜና 20፥37፤ኢሳ2፥16
9፥27 ሕዝ27፥8
9፥28 ቍ14፤ዘፍ 10፥29፤1ነገ10፥10፡11፡14፡21፤2ዜና1፥15 1መክ2፥8
10፥1 ዘፍ10፥7፡28፤25፥3፤ዘኍ12፥8፤መሳ 14፥12፤ሕዝ16፥14፤ማቴ12፥42፤ሉቃ 11፥31
10፥2 ዘፍ24፥10
10፥5 1ነገ4፥22
10፥7 ዘፍ45፥26፤1ዜና29፥25
10፥8 ምሳ8፥34
10፥9 ዘዳ7፥8፤1ነገ 5፥7፤መዝ11፥7፤33፥5፤72፥2፤99፥4፤103፥6፤ኢሳ42፥10
10፥10 1ነገ9፥28፤ኢሳ60፥6
10፥11 ዘፍ10፥29

[t]26 የዕብራይስጡ፣ *ያም ሱፍ* ይለዋል፤ ይኸውም የደንገል ባሕር ማለት ነው
[m]28 14.5 ሜትሪክ ቶን ያህል ነው
[w]5 ወይም፣ *ወደ ላይ የሚወጣባቸው ደረጃዎች* ተብሎ መተርጐም ይችላል
[a]10 4 ሜትሪክ ቶን ያህል ነው
[x]11 በዚህና በቍ 12 ላይ፣ *የአልጉም ዕንጨት* ከሚባለው ጋር ተመሳሳይ ሊሆን ይችላል::

9፥25 *በዓመት ሦስት ጊዜ፤* በዓመት ውስጥ በሚደረጉ ዋና በዓላት ይኸውም፣ የቂጣ በዓል፣ የመከር በዓልና የዳስ በዓል በሚከበሩበት ወቅት ማለት ነው (ዘፀ 23፥14-17፤ 2ዜና 8፥13 ይመ)::

9፥26 *መርከቦችን ሠራ፤* ከፍተኛ የንግድ ዕቃ የሚጫንባቸውና ለሰሎሞንም ብዙ ሀብት የሚያመጡ ናቸው (ቍ 28፤ 10፥11 ይመ):: *በዔጽዮንጋብር፤* በአካባ የባሕር ሰላጤ ሰሜናዊ ጫፍ የምትገኝ ቦታ ናት (22፥48፤ ዘኍ 33፥35፤ ዘዳ 2፥8 ይመ):: *በቀይ ባሕር፤* በዕብራይስጥ "የም ሱፍ" ይባላል፤ ትርጓሜውም "የሸ ምበቆ ባሕር" ማለት ሲሆን፣ እስራኤላውውያን ከግብፅ በወጡ ጊዜ የተሻገሩት ነበር (የዘፀ 13፥18፤ 14፥2 ማብ ይመ):: ይህ ቃል "ያም ሶፋ" ተብሎ ሊነበብም ይችላል፤ ትርጓሜውም "የም ድር ጫፍ ባሕር" ማለት ሲሆን፣ "ቀይ ባሕር" የሚለውን ቃል የሚገልጽ በምሥራቅ አካባቢ የባሕር ሰላጤ የሚገኝ ነው::

9፥28 *ኦፊር፤* ወርቅ (2ዜና 8፥18፤ ኢዮ 28፥16፤ መዝ 45፥9፤ ኢሳ 13፥12)፣ የሰንደል እንጨት፣ የከበረ ድንጋይ (10፥11) ብር፣ የዝሆን ጥርስ፣ ጦጣና ዝንጀሮ (10፥22) የሚገኝበት ቦታ ነው:: ይህ ቦታ የት እንደሚገኝ ባይታወቅም፣ የተለያዩ ቦታዎች በግምት ተጠቅሰዋል፤ እነዚህም ደቡብ ምሥራቅ ዐረቢያ፣ ደቡብ ምዕራብ ዐረቢያ፣ የሰሜን ምሥራቅ አፍሪካ የባሕር ጠረፍ (የሶማሊያ ግዛት)፣ ሕንድና ዚምባቡዌ ናቸው:: ኦፊር የምትገኘው በዐረቢያ ከሆነ፣ ከሩቅ ምሥራቅና ከምሥራቅ አፍሪካ ለሚመጡ ሸቀጦች፣ የንግድ ማዕከል ልትሆን ትችላለች:: ነገር ግን የሰሎሞን የንግድ መርከቦች ጉዞው ሦስት ዓመት የወሰደባቸው በመሆኑ (10፥22) ስፍራው ከዐረቢያ የባሕር ጠረፍ ራቅ ያለ መሆኑን ያመለክታል::

10፥1 *ሳባ፤* በደቡብ ምዕራብ ዐረቢያ የምትገኝ ስሟም የገነነ የንግድ ከተማ እንደ ነበረች፤ የሥነ ቅርስ ቍፋሮ መረጃዎች ያመለክታሉ (የዘፍ 10፥28፤ የኢል 3፥8 ማብ ይመ):: ይህችም የንግድ ከተማ፣ ከሕንድና ከምሥራቅ አፍሪካ የሚመጡ ውድ ዕቃዎችን በዐረብ በረሓ በኩል ወደ ደማስቆና ወደ ጋዛ በግመል እየላከች ብዙ ትርፍ ታስገኝ ነበር:: የሰሎሞን የጦር መርከቦች፣ እያየለ የመጣውን ይህን የሳባን የንግድ እንቅስቃሴ ለመግታት ሳይሞክሩ አልቀሩ:: *ከእግዚአብሔር ስም ጋር ያለውን ግንኙነት፤* የሳባ ንግሥት በሰሎሞን ጥበብና በሚያገለግለው እግዚአብሔር መካከል ያለውን ግንኙነት አስተዋለች:: ኢየሱስ በእርሱ ዘመን ለነበሩ ሰዎች የሳባን ንግሥት በምሳሌነት በመጥቀስ፣ "ከሰሎሞን የሚበልጥ" በመካከላቸው እንዳለ ባለማስተዋላቸው ኰነናቸው (ማቴ 12፥42፤ ሉቃ 11፥31)::

10፥9 *እግዚአብሔር አምላክህ የተመሰገነ ይሁን፤* የሳባ ንግሥት ምስክርነት በሚገባ የተዘገበ ሲሆን፣ ይህም እስራኤል ከእግዚአብሔር ጋር ያላትን የቃል ኪዳን ግንኙነት፣ የሳባ ንግሥት በሚገባ እንደ ተረዳች ያመለክታል፤ ይሁን እንጂ፣ ይህ ምስክርነት እግዚአብሔር የእስራኤል አምላክ እንደ ሆነ ከራሷ አምልኮተ አማልክት አንጻር ከመነገሩ በስተቀር የሚያመለክት ነገር የለም (የ5፥7 ማብ ይመ፤ እንዲሁም 2ዜና 2፥12፤ ዳን 3፥28-29 ይመ):: የሳባ ንግሥት የራሷን አምልኮተ አማልክት ትታ፣ የሰሎሞንን አምላክ ስለመቀበሏ የሚናገር ምስክርነት የለም::

10፥10 *መቶ ሃያ መክሊት ወርቅ፤* የ9፥11፡28 ማብ ይመ::

10፥11 *የኪራም መርከቦች፤* 9፥26-28 ይመ:: ኪራም ዕንጨት፣ መርከበኞችንና የሕንፃ መሐንዲሶችን ለሰሎሞን ላከለት:: *የሰንደሉን ዕንጨትና፤* 2ዜና 9፥10-11 ይመ:: አንዳንዶች የጥድ ዕንጨት ነው ቢሉም፣ የዕንጨቱ ዐይነት ግን በውል አይታወቅም:: ሆኖም ግን ይህ ዕንጨት የሚመጣው ከሊባኖስና ከኦፊር ነው (2ዜና 2፥8)::

10፥13 *የፈለገችውንና የጠየቀችውን ሁሉ ሰጣት፤* በሰሎ

## የሰሎሞን ብልጽግናና ክብር

10፥14-29 ተጓ ምብ - 2ዜና 1፥14-17፤ 9፥13-28

14ለሰሎሞን በየዓመቱ የሚገባለት ስድስት
መቶ ሥልሳ ስድስት መክሊት ወርቅ ነበር።
15ይህም ከንግድና ከሌላ ገቢ ላይ የሚከፈ
ለውን ቀረጥ፣ የዐረብ ነገሥታት ሁሉ የሚ
ያገቡትንና አገረ ገዦች የሚሰበስቡትን ግብር
ሳይጨምር ነው።
16ንጉሥ ሰሎሞን ከተጠፈጠፈ ወርቅ ሁለት
መቶ ታላላቅ ጋሻ አሠራ፤ በእያንዳንዱም
ጋሻ የገባው ሦስት መቶ ሰቅል[ረ] ወርቅ ነበር።
17እንዲሁም ከተጠፈጠፈ ወርቅ ሦስት መቶ
ትንንሽ ጋሻ አሠራ፤ በእያንዳንዱ ጋሻ የገ
ባው ደግሞ ሦስት ምናን[ፐ] ወርቅ ነው።
ንጉሡም እነዚህን የሊባኖስ ዱር በተባለው
ቤተ መንግሥት አኖረ።
18ከዚያም ንጉሡ ከዝሆን ጥርስ ትልቅ
ዙፋን አሠርቶ በንጹሕ ወርቅ አስለበጠው።
19ዙፋኑ ባለ ስድስት ደረጃ ነው፤ በስተ ኋላ
ውም ዐናቱ ላይ ክብ ቅርጽ ሲኖረው፣ ግራና
ቀኙ ባለመደገፊያ ነው፤ በመደገፊያዎቹም
አጠገብ ሁለት አንበሶች ቆመዋል። 20በስድ
ስቱም ደረጃ ጫፍ ላይ ግራና ቀኝ ስድስት
ስድስት አንበሶች ቆመዋል። ይህን የመ
ሰለም ዙፋን በየትኛውም አገር መንግሥት
ከቶ ተሠርቶ አያውቅም። 21ንጉሥ ሰሎሞን
የሚጠጣበት ዋንጫ ሁሉ የወርቅ ሲሆን፣
የሊባኖስ ዱር በተባለው ቤተ መንግሥት
ውስጥ የነበረው ዕቃ በሙሉ ከንጹሕ ወርቅ
የተሠራ ነበር፤ በሰሎሞን ዘመነ መንግሥት
ብር ይህን ያህል ዋጋ ስላልነበረው፣ ከብር
የተሠራ ዕቃ ፈጽሞ አልነበረም። 22ንጉሡ
ከኪራም መርከቦች ጋር አብረው በባሕር
ላይ የሚጓዙ የተርሴስ የንግድ መርከቦች[ሀ]
ነበሩት። እነዚህም በየሦስት ዓመቱ አንድ
ጊዜ ወርቅ፣ ብርና የዝሆን ጥርስ፣ ጦጣ
ችና ዝንጀሮዎች ያመጡ ነበር።
23ንጉሥ ሰሎሞንም በሀብትና በጥበብ
ከምድር ነገሥታት ሁሉ ይበልጥ ነበር። 24ዓለሙ
ሁሉ እግዚአብሔር በሰሎሞን ልብ ያኖረውን
ጥበብ ለመስማት ወደ እርሱ መምጣት
ይፈልግ ነበር። 25በየዓመቱም የሚመጣውን
ሰው ሁሉ የብርና የወርቅ ዕቃ፣ ልብስ፣
የጦር መሣሪያ፣ ሽቶ፣ ፈረስና በቅሎ ስጦታ
አድርጎ ያመጣለት ነበር።
26ሰሎሞን ሠረገሎችና[ሰ] ፈረሶች ሰበሰበ፤
አንድ ሺህ አራት መቶ ሠረገሎችና ዐሥራ
ሁለት ሺህ ፈረሶች ነበሩት። እነዚህንም
ሁሉ ሠረገሎች በሚያኖርበት ከተሞችና ራሱ
በሚኖርበት በኢየሩሳሌም እንዲሆኑ አደረገ።
27ንጉሡም ብሩን በየቦታው እንደሚገኝ ድን
ጋይ አደረገ፤ የዝግባውም ዕንጨት ብዛት
በቈላ እንደሚበቅል ሾላ ሆነ። 28የሰሎሞን
ፈረሶች የመጡት ከግብፅና[ሐ] ከቀዌ[መ] ሲሆን፣
እነዚህንም ከቀዌ ገዝተው ያመጧቸው የቤተ
መንግሥቱ ንግድ ሰዎች ነበሩ። 29እንዱን
ሠረገላ ከግብፅ የሚያመጡት በስድስት መቶ
ሰቅል[ሠ] ብር ሲሆን፣ ፈረሱን ደግሞ በመቶ
አምሳ ሰቅል[ረ] ብር ያመጡ ነበር፤ ለኬጢ
ያውያንና ለሶርያ ነገሥታትም አምጥተው
ይሸጡላቸው ነበር።

## የሰሎሞን ሚስቶች

11 ንጉሥ ሰሎሞን ከፈርዖን ልጅ ሌላ
ብዙ የባዕድ አገር ሴቶችን ማለትም
ሞዓባውያትን፣ አሞናውያትን፣ ኤዶማውያ
ትን፣ ሲዶናውያትን፣ ኬጢያውያትን አፈቀረ።
2እነዚህም እግዚአብሔር እስራኤላውያንን፣
"ልባችሁን ወደ አማልክታቸው በእርግጥ
ይመልሱታልና ከእነርሱ ጋር መጋባት የለባ
ችሁም" ካላቸው አሕዛብ ወገን ነበሩ፤ ሆኖም
ሰሎሞን ከእነዚሁ ጋር ፍቅሩ ጠና። 3እር
ሱም ከነገሥታት የተወለዱ ሰባት መቶ
ሚስቶችና ሦስት መቶ ቁባቶች ነበሩት፤
ሚስቶቹም ልቡ ወደ ሌላ እንዲያዘነብል

10፥14 1ነገ9፥28
10፥16 2ሳሙ8፥7
10፥17 1ነገ7፥2
10፥21 ኢሳ60፥17
10፥22 1ነገ9፥26፤ 27፤መዝ48፥7፤ኢሳ 2፥16፤23፥1፤14፤ 60፥6፤9
10፥23 1ነገ3፥12፤ 13፤ማቴ6፥29፤12፥42
10፥24 2ሳሙ 14፥20
10፥25 1ሳሙ 10፥27
10፥26 ዘዳ17፥16
10፥27 ዘዳ17፥17፤ 1ዜና27፥28፤ኢዮ 27፥16፤ኢሳ60፥17፤ አሞ7፥14
10፥29 ዘኍ13፥29
11፥1 ቍ3፤ዘፀ34፥ 16፤1ነገ14፥21፤31
11፥2 ዘፀ34፥16፤ 1ነገ16፥31
11፥3 ቍ1፤ዘፍ 22፥24፤ዘዳ17፥17፤ ነህ13፥26፤አስ2፥14፤ ምሳ31፥3

[ሀ]14 23 ሜትሪክ ቶን ያህል ነው [ረ]16 3.5 ኪሎ ግራም ያህል ነው
[ፐ]17 1.7 ኪሎ ግራም ያህል ነው
[ሀ]22 ዕብራይስጡ፣ የተርሴስ መርከቦች ይላል
[ሰ]26 ወይም ሠረገለኞች ተብሎ መተርጐም ይችላል
[ሐ]28 በዚህና በቍ 29 ላይ ምናልባት በቂልቂያ የምትገኘው ሙጽር ልትሆን ትችላለች
[መ]28 ምናልባትም፣ ኪልቂያ ልትሆን ትችላለች
[ሠ]29 7 ኪሎ ግራም ያህል ነው [ረ]29 1.7 ኪሎ ግራም ያህል ነው

ሞንና በሳባ ንግሥት መካከል የተደረገው የስጦታ ልውውጥ ብቻ ሳይሆን፣ የንግድ ስምምነት ሳያደርጉ እንዳልቀረ ይገመታል (የቍ 1 ማብ ይመ)። የሳባ ንግሥት ከሰሎሞን ፀንሳ፣ ከኢየሩሳሌም እንደ ተመለሰች ቢነገርም ተጨባጭ ማስረጃ ግን አይገኝም።

10፥15 *የዐረብ ነገሥታት...ግብር፤* የበደዊን ሕዝብ አለቆች በእስራኤል ግዛት ሲያልፉ ከሚከፍሉት ግብር የሚገኝ ነው። *አገረ ገዦች፤* 4፥7-19 ይመ።

10፥16 *ታላላቅ ጋሻ፤* አራት ማእዘን ቅርጽ ያለውና ለመከላከያ የሚያገለግል ነው (ክብ ቅርጽ ያለው አነስተኛ ጋሻ አለ)። እነዚህ የወርቅ ጋሻዎች የተሠሩት ለጦርነት ሳይሆን በሃይማኖታዊ ክብረ በዓላት ላይ፣ ለእስራኤል ሀብትና ክብር ትእምርት ሆነው እንዲያገለግሉ ነው። ጋሻዎቹም ከዕንጨት ተሠርተው በወርቅ የተለበጡ ሳይሆን አይቀርም። የሰሎሞን ልጅ ሮብዓም በነገሠ በአምስተኛው ዓመት፣ የግብፅ ንጉሥ ሺሻቅ እነዚህን ጋሻዎች ማርኮ ወስዶአቸዋል (14፥25-26 ይመ)።

10፥22 *የንግድ መርከቦች፤* 2ዜና 9፥21 ይመ። በቍ 11፤ 9፥26-28 የተጠቀሱት እነዚሁ መርከቦች ናቸው። "የተርሴስ መርከቦች" ሲል፣ ወደ/ተርሴስ የሚጓዙ መርከቦችን ለማለት ሳይሆን (ዮና 1፥3) ታላላቅ የንግድ መርከቦችን ለማለት ነው።

10፥26 *ሠረገሎችና... ፈረሶች፤* የ4፥26 ማብ ይመ። አንድ ንጉሥ በሠረገሎችና በፈረሶች ብዛት እንዳይመካ፣ የሙሴ ሕግ ይከለክላል (ዘዳ 17፥11)።

10፥29 *የሚያመጡት... ነበር፤* ሰሎሞን በወኪሎቹ አማካይነት ብዙ ትርፍ ያለው ንግድ ያካሂድ ነበር። ፈረሶችን ከሰሜን (በትንሹ እስያ ከሚገኙ ከሙጽርና ከቀዌ) እያስመጣ ወደ ደቡብ እየወሰደ ይሸጥ ነበር፤ እንዲሁም ሠረገሎችን ከደቡብ (ከግብፅ) እያስመጣ ወደ ሰሜን እየወሰደ ይሸጥ ነበር።

11፥1 *ብዙ የባዕድ አገር ሴቶችን... አፈቀረ፤* ሰሎሞን ብዙ ሴቶችን ሊያገባ የቻለው፣ ከታላላቅም ሆነ ከታናናሽ መንግሥታት ጋር ዓለም ዓቀፍ ግንኙነት ለመመሥረት አስቦ እንደ ሆነ ምንም ጥርጥር የለውም። ለዚህ ዓላማ ሲባል ብዙ ሴቶችን ማግባት በጥንት መካከለኛ ምሥራቅ አገሮች ዘንድ የተለመደ ተግባር ነበር። የሰሎሞን ድርጊት አንድ ንጉሥ ብዙ ሚስቶችን እንዳያገባ የሚከላከለውን ሕግ የተላለፈ ብቻ ሳይሆን (ዘዳ 17፥17) እስራኤላውያን በሚኖሩበት ምድር ያሉትን የአሕዛብን ሴቶች እንዳያገቡ የሚያዘውንም ሕግ ተላልፎ ነበር (ዘፀ 34፥16፤ ዘዳ 7፥1-3፤ ኢያ 23፥12-13፤ እዝ 9፥2፤ 10፥2-3፤ ነህ 13፥23-27 ይመ)። *ሞዓባውያትን፤* የዘፍ 19፥36-38 ማብ ይመ። *አሞናውያትን፤* የዘፍ 19፥36-38 ማብ እንዲሁም 14፥21፤ ዘዳ 23፥3 ይመ። *ኤዶማውያትን፤* የዘፍ 25፥26፤ 36፥1፤ የአሞ 1፥11፤ 9፥12 እንዲሁም ዘዳ 23፥7-8 ይመ። *ሲዶናውያትን፤* 16፥31 ይመ።

11፥2 *ልባችሁን ወደ አማልክታቸው በእርግጥ ይመል*

አደረጉት:: [4]ሰሎሞን በሸመገለ ጊዜ ሚስ
ቶቹ ልቡን ወደ ሌሎች አማልክት መለሱት፤
የአባቱ የዳዊት ልብ እንደ ተገዛ ሁሉ፣ በፍ
ጹም ልቡ በስምባቱ *ለእግዚአብሔር* አልተ
ገዛም:: [5]ሰሎሞንም የሲዶናውያንን ሴት
አምላክ አስታሮትን፣ አስጸያፊውን የአሞና
ውያንን አምላክ ሚልኮምን ተከተለ::
[6]ስለዚህ ሰሎሞን *በእግዚአብሔር* ፊት ክፉ
ድርጊት ፈጸመ፤ እንደ አባቱ እንደ ዳዊ
ትም *እግዚአብሔርን* እስከ መጨረሻው አል
ተከተለም::
[7]ሰሎሞን ከኢየሩሳሌም በስተ ምሥራቅ
ባለው ተራራ ላይ ለአስጸያፊው የሞዓብ አም
ላክ ለካሞሽ እንዲሁም አስጸያፊ ለሆነው
ለአሞናውያን አምላክ ለሞሎክ ማምለኪያ
ኮረብታ ሠራ:: [8]ለአማልክቶቻቸው ዕጣን
ለሚያጥኑና መሥዋዕት ለሚያቀርቡ ለሌሎቹ
ሚስቶቹም ሁሉ በዚሁ ዐይነት ሠራላቸው::
[9]ሰሎሞን ሁለት ጊዜ ከተገለጠለት ከእስ
ራኤል ስምባቱ *ከእግዚአብሔር* ልቡ ስለ
ሸፈተ፣ *እግዚአብሔር* ተቈጣው:: [10]ምንም
እንኳ ሌሎች አማልክትን እንዳይከተል ሰሎ
ሞንን ቢከለክለውም፣ ሰሎሞን *የእግዚአ
ብሔርን* ትእዛዝ አልጠበቀም፤ [11]ስለዚህ
*እግዚአብሔር* ሰሎሞንን እንዲህ አለው፤
"ይህን በማድረግህ ያዘዝሁህን ኪዳኔንና
ሥርዐቴንም ባለመጠበቅህ፣ መንግሥትህን
ከአንተ ወስጄ ከአገልጋዮችህ ለአንዱ እሰጠ
ዋለሁ፤ [12]ይህን ግን ስለ አባትህ ስለ ዳዊት
ስል በዘመንህ አላደርገውም፤ መንግሥትህን
የምቀዳት ከልጅህ እጅ ነው:: [13]ይህም ሆኖ
መንግሥቱን በሙሉ አልነጥቀውም፤ ነገር
ግን ስለ ባሪያዬ ስለ ዳዊትና ስለ መረጥ
ኋት ስለ ኢየሩሳሌም ስል ለልጅህ አንድ
ነገድ እሰጠዋለሁ::"

### የሰሎሞን ጠላቶች

[14]*እግዚአብሔር* ከኤዶም ንጉሣዊ ቤተ
ሰብ ኤዶማዊውን ሃዳድን በሰሎሞን ላይ
አስነሣው:: [15]ከዚያ በፊት ዳዊት ከኤዶም
ጋር በተዋጋ ጊዜ፣ የሞቱትን ለመቅበር
መጥቶ የነበረው የሰራዊቱ አዛዥ ኢዮአብ
የኤዶምን ሰዎች ሁሉ ፈጅቶ ነበር:: [16]ኢዮ
አብና እስራኤላውያን ሁሉ፣ በኤዶም ያሉትን
ወንዶች በሙሉ እስኪያጠፉ ድረስ፣ እዚ
ያው ስድስት ወር ቈይተው ነበርና:: [17]ሃዳድ
ግን ገና በልጅነቱ አባቱን ካገለገሉ ጥቂት
ኤዶማውያን ጋር ወደ ግብፅ ሸሸ፤ [18]እነር
ሱም ከምድያም ተነሥተው ወደ ፋራን ሄዱ፤
ከፋራንም ሰዎች ይዘው ወደ ግብፅ በመም
ጣት፣ ወደ ግብፅ ንጉሥ ወደ ፈርዖን ገቡ::
ንጉሡም ለሃዳድ ቤትና መሬት ሰጠው፤
ቀለብም አዘዘለት::
[19]ፈርዖንም ሃዳድን እጅግ ወደደው፤ ስለ
ዚህም ከሚስቱ ከንግሥት ጣፍኔስ እኅት
ጋር አጋባው:: [20]የጣፍኔስም እኅት ጌንባት
የተባለውን ልጅ ወለደችለት፤ ጣፍኔስ በፈ
ርዖን ቤት አሳደገችው፤ ጌንባትም ከፈርዖን
ልጆች ጋር አደገ::
[21]ሃዳድ በግብፅ ሳለ ዳዊት ከአባቶቹ ጋር
ማንቀላፋቱን፣ የሰራዊቱ አዛዥ ኢዮአብም
መሞቱን ሰማ:: ሃዳድም ፈርዖንን፣ "ወደ
አገሬ እንድመለስ አሰናብተኝ" አለው::
[22]ፈርዖንም፣ "እዚህ ምን ጐደለብህና ነው
ወደ አገርህ ለመግባት የፈለግኸው?" ሲል
ጠየቀው::

11፥4 ዘፀ34፥16፤ 1ነገ8፥61፤1ዜና 29፥19
11፥5 ቍ7፤ዘሌ 18፥21፤መሳ2፥13፤ ኢሳ57፥9፤ሶፎ1፥5
11፥6 ዘዳ4፥25
11፥7 ዘሌ18፥21፤ 20፥25፤ዘኍ21፥29፤ 2ነገ23፥13፤ ሐሥ7፥43
11፥9 1ነገ3፥5
11፥10 1ነገ6፥12፤ 9፥6
11፥11 ቍ31፤ዘሌ 18፥4፤1ሳሙ15፥27፤ 2ነገ17፥21፤ ማቴ21፥43
11፥12 መዝ89፥33
11፥13 ዘዳ12፥11፤ 2ሳሙ7፥15፤1ነገ 12፥20
11፥14 1ነገ5፥4
11፥15 1ዜና18፥12
11፥18 ዘኍ10፥12

ሱታልና፤ ቀደም ባለው የእስራኤል ታሪክ ውስጥ ይህ ነገር እንደ ተፈጸመ በዘኍ 25፥1-15 ላይ ተጠቅሷል::

11፥3 *ሰባት መቶ... ሦስት መቶ፤* ከማሕ 6፥8 ጋር ያነጻ ጽሩ፤ በዚያም የሚገኘውን ማብ ይመ::

11፥4 *በፍጹም ልቡ ለአምላኩ ለእግዚአብሔር አልተገዛም፤* 8፥61 ይመ:: በባዕዳን ሚስቶቹ አማካይነት ወደ ሰሎሞን ቤተ መንግሥት የገባው አምልኮተ ጣዖት ሰሎሞንን ቀስ በቀስ ወደ ተቀያየጠ ሃይማኖታዊ ልምምድ ውስጥ እንዲገባ አደረገው::

11፥5 *አስታሮትን፤* ቍ 33፤ 14፥15፤ 2ነገ 23፥13 ይመ እንዲሁም የመሳ 2፥13 ማብ ይመ:: *ሚልኮምን፤* 2ሳሙ 12፥30 ይመ:: ይህን የአሞናውያንን አምላክ ማምለክ እግዚአብሔር የሕዝቡ ጌታ ነው የሚለውን ጽኑ እውነት የሚያቃልልና የገዛ ልጆቻቸውን ለጣዖት መሥዋዕት አድርጎ ማቅረብንም ያካትታል (2ነገ 16፥3፤ 17፥17፤ 21፥6፤ ዘሌ 18፥21፤ 20፥2-5 ይመ፤ እንዲሁም የመሳ 10፥6 ማብ ይመ)::

11፥6 *እንደ አባቱ እንደ ዳዊትም... አልተከተለም፤* ምንም እንኳ፣ ዳዊት ከባድ ኀጢአት ቢፈጽምም፣ ፈጥኖ ንስሓ የሚገባና በጣዖት አምልኮም ፈጽሞ ያልተበከለ ነበር::

11፥7 *ማምለኪያ ኮረብታ፤* የ3፥2 ማብ ይመ:: *ለካሞሽ፤* 2ነገ 3፥26-27 ይመ::

11፥9 *ሁለት ጊዜ ከተገለጠለት፤* 3፥4-5፤ 9፥1-9 ይመ::

11፥11 *ኪዳኔንና...ባለመጠበቅህ፤* ሰሎሞን፣ ኪዳኑ የሚያዘውን መሠረታዊ ነገር ከመተላለፉም በላይ (ዘፀ 20፥2-5) በእግዚአብሔርና በሕዝቡ መካከል የተመሠረተውን የኪዳን ግንኙነት አቃለለ::

11፥12 *ስለ አባትህ ስለ ዳዊት ስል፤* እግዚአብሔር ቍጣውን በሰሎሞን ዘመን የማይገልጠው፣ ዳዊት ለእግዚአብሔርና ለኪዳኑ ካሳየው ታማኝነት የተነሣ ነው (2ሳሙ 7፥11-16 ይመ)::

11፥13 *አንድ ነገድ፤* የይሁዳን ነገድ ማለት ነው (የቍ 31-32 እንዲሁም 12፥20 ይመ):: *ስለ መረጥኋት ስለ ኢየሩሳሌም ስል፤* በ2ሳሙ 7፥13 ላይ በተጠቀሰው መሠረት፣ በዳዊት ልጅ የተሠራው ቤተ መቅደስ የሚገኘው በኢየሩሳሌም በመሆኑ፣ የኢየሩሳሌምና የዳዊት ሥርወ መንግሥት ዕጣ ፈንታ አንድ ነው (2ነገ 19፥34፤ 21፥7-8፤ መዝ 132 ይመ):: ቤተ መቅደሱ የሚወክለው የእግዚአብሔርን ቤተ መንግሥት ሲሆን፣ የእግዚአብሔር ምድራዊ ዙፋን (የቃል ኪዳኑ ታቦት) የሚገኘውና እግዚአብሔር የእስራኤል ታላቅ ንጉሥ (9፥3) ሆኖ በመካከላቸው የሚገኘውም በዚሁ ቤተ መቅደስ ውስጥ ነው፤ እግዚአብሔርም በሕዝቡ መካከል ለመገኘት ቃል ገብቷልና::

11፥14 *ሃዳድን፤* በርካታ የኤዶማውያን ነገሥታት በዚህ ስም ተጠርተዋል (ዘፍ 36፥35:39 ይመ)::

11፥15 *ዳዊት ከኤዶም ጋር በተዋጋ ጊዜ፤* 2ሳሙ 8፥13-14 ይመ::

11፥16 *እስራኤላውያን ሁሉ፣ በኤዶም ያሉትን ወንዶች በሙሉ፤* በውጊያው ላይ የተሳተፉትን የሁለቱን ወገን ሰዎች ያመለክታል::

11፥17 *ገና በልጅነቱ፤* ምናልባት የዐሥራ ሦስት ወይም ዐሥራ አራት ዓመት ልጅ እያለ ይሆናል::


11፥18 *ከምድያም፤* በዚህ ጊዜ፣ ምድያማውያን በሞአብና በኤዶም ምሥራቃዊ ጠረፍ የሚገኘውን ክፍል ይዘው ነበር:: *ፋራን፤* በሲና ልሳነ ምድር ማዕከላዊ ክፍል፣ ከቃዴስ በስተ ደቡብ ምሥራቅ የሚገኝ ምድረ በዳ ነው (ዘኍ 10፥12፤ 12፥16፤ 13፥3 ይመ):: *ወደ ግብፅ ንጉሥ ወደ ፈርዖን፤* የ3፥1 ማብ ይመ:: *ለሃዳድ ቤትና መሬት ሰጠው ቀለብም አዘዘለት፤* ግብፅ፣ እስራኤልን በየጊዜው ከሚወጉና ኀይሏንም ከሚፈታተኑ መንግሥታት ጋር ወዳጅነት የምትመሠርተው፣ የእስራኤል ኀይል እየጠነከረ በመጣ ጊዜ ነበር::

11፥21 *ወደ አገሬ እንድመለስ፤* ሃዳድ ወደ ኤዶም የተመለሰው፣ ሰሎሞን በነገሠ በመጀመሪያዎቹ ዓመታት አካባቢ ሳይሆን አይቀርም::

# የተከፋፈለው መንግሥት

930-586 ዓ.ቅ.ክ

የሰሎሞን መንግሥት መከፋፈል ቀደም ሲል የነገዶችን ግጭት መሠረት ያደረገ መልከዐ ምድራዊና ፖለቲካዊ ምክንያቶች ነበሩት። ጢሮስ እስራኤል ከይሁዳ ይልቅ ለፊንቄ ከተሞችና ለዋና ዋና የንግድ መስመሮች ቅርብ ነበረች።




በዘጠነኛው ምእተ ዓመት አብዛኛውን ክፍል በደማስቆና በእስራኤል መካከል የተደረገው የአራማውያን ጦርነት ከባድና አጥፊ ነበር። በአራምና በኤፍሬም ሰዎች መካከል የነበሩት ጦርነቶች ለኢዮርብዓም የድል ለእስራኤልም የታላቅ ብልጽግና ዘመን ነበር።

የምሽግ ጦርነት በታወቀበት ዘመን የአሦራውያን ዘመቻ ከባድ ጥፋት አስከትሎአል። በ732 ዓ.ቅ.ክ የሰሜናዊ መንግሥት ለአሦር ገባር ሆኖ ነበር።

ከረጅም የምሽግ ጦርነት በኋላ በ722/721 ዓ.ቅ.ክ ሰማርያ ተያዘች፤ ወደመችም፤ በዚያ የቀሩት ነዋሪዎች ከአሦር ግዛት ራቅ ወዳለ ስፍራ ተወስደው በምትካቸው በሰማርያ አዲስ ነዋሪዎች እንዲቀመጡ ተደረገ።

በብንያም በኩል ያለው ድንበር ይሁዳንና እስራኤልን ከመጀመሪያ ታሪካቸው ጀምሮ በመካከላቸው ግጭት እንዲፈጠር ምክንያት ሆኖአል። በአሣና በባኦስ መካከል ጦርነት ከተደረገ በኋላ፣ ድንበሩ በብንያም ግዛት በቤቴል ደቡብ በኩል እንዲሆን ተወሰነ።

መጽሐፍ ቅዱስና የሚሻ የድንጋይ ፀምድ ግልጽ እንደሚያደርጉት የሞዓብ ንጉሥ የሚሻ ተግባር መጀመሪያ ገባር ቀጥሎም ዐማፂ መሆን ነበር።

በ930-722 ዓ.ቅ.ክ የነበረው ዘመን የሁለቱ መንግሥታት የመስፋፋትና የማነስ ዘመን ነበር። ይሁዳ ምድራዊ አቀማመጧ ለጥቃት እንዳትጋለጥ ሲጠብቃት፣ እስራኤል ግን አስተማማኝ የሆነ የጦር ኀይል ለመገንባት ተገድዳለች። የአሦራውያን የታሪክ መዝገብ እንደሚያሳየው በ853 ዓ.ቅ.ክ በተደረገው ጦርነት የእስራኤል ንጉሥ አክዓብ 2 000 ሠረገሎች ነበሩት። ይህ የጦር ኀይል ክምችት በአንድ በኩል የሚያመለክተው የተረጋጋ የሥርወ መንግሥት ታሪክ አለመኖሩን ሲሆን፣ ይህም ብዙውን ጊዜ ተቃውሞ የሚነሣው ከጦር አለቆች እንደ ነበረ ያመለክታል።

የይሁዳ ብልጽግና በአብዛኛው የተመሠረተው ወደ ግብፅና ወደ ቀይ ባሕር የተዘረጋውን የንግድ መስመር መቆጣጠር በመቻሏ ነው። በይሁዳ ምድረ በዳ ያሉ የድንበር ምሽጎች ከኤዶም የሚመጣውን ጥቃት ለመከላከል ይችላሉ። የይሁዳ የፊት በሮች በመባል የሚታወቀው ከለኪሶ አንሥቶ በኬብሮንና በኢየሩሳሌም ያለውን የሚያጠቃልል ነበር ዋና ከተማዋ ብዙ ጊዜ ተከብባ ነበር፤ በ701 ዓ.ቅ.ክ የአሦራውያን እና

586 ዓ.ቅ.ክ በባቢሎናውያን ተከብባ ነበር። በዚህ ከበባ ኢየሩሳሌም በናቡከደናፆር ወደመች የሥርወ መንግሥቱም ፍጻሜ ሆነ።

የደቡብ ግዛት ለዳዊት ሥርወ መንግሥት ባሳየው ሉሌነት ይታወቃል፤ ይህም መንግሥቱ የተረጋጋ እንዲሆን ረድቶአል። በተቃራኒው በሰሜናዊው መንግሥት ብዙ አለመረጋጋትና ለውጥ ታይቷል።

ሃዳድም፣ “ምንም የጐደለብኝ የለም፣ ብቻ
እንድሄድ ፍቀድልኝ” አለ።
23እግዚአብሔርም ከጌታው ከሱባ ንጉሥ ኰብ
ልሎ የነበረውን የኤልያዳን ልጅ ሬዞንን ሌላ
ጠላት አድርጎ በሰሎሞን ላይ አስነሣው፤
24ዳዊት የሱባን ጎይል በደመሰሶ ጊዜ፣ ሬዞን
ሰዎቹን በዙሪያው አሰባስቦ የወንበዴ አለቃ
ሆነ፤ ሰዎቹም ወደ ደማስቆ ሄደው ተቀመጡ፤
በዚያም አነገሡት። 25ሃዳድ ካስከተለበት
ችግር ሌላ ሬዞን በሰሎሞን ዘመን ሁሉ ሊላው
የእስራኤል ተቃዋሚ ሆነ፤ ሬዞን ሶርያን
ገዛ፤ እስራኤልንም ይጠላ ነበር።

## ኢዮርብዓም በሰሎሞን ላይ ዐመፀ

26እንዲሁም ከሰሎሞን ሹማምት አንዱ
የሆነው የናባጥ ልጅ ኢዮርብዓም በንጉሡ
ላይ ዐመፀ፤ እርሱም ከጸሬዳ የመጣ ኤፍሬ
ማዊ ሲሆን፣ እናቱ ጽሩዓ የተባለች መበ
ለት ነበረች።
27በንጉሡ ላይ ያመፀበትም ምክንያት እን
ዲህ ነው፤ ሰሎሞን ድጋፍ የሚሆኑ እርከ
ኖች በመሥራት የአባቱን የዳዊትን ከተማ
ቅጥር ይጠግን ነበር። 28ኢዮርብዓም ከፍተኛ
ችሎታ ያለው ሰው ነበር፤ ሰሎሞንም ወጣቱ
ሥራውን እንዴት በሚገባ እንደሚያከናውን
ባየ ጊዜ፣ በዮሴፍ ነገድ ለሚሠራው የጕልበት
ሥራ ሁሉ ኀላፊ አደረገው።
29በዚያ ጊዜም ኢዮርብዓም ከኢየሩሳሌም
ሲወጣ፣ የሴሎው ነቢይ አኪያ በመንገድ ላይ
ተገናኘው፤ አኪያም አዲስ መጐናጸፊያ ለብሶ
ነበር፤ ሁለቱ ብቻቸውን ሳሉ፣ 30አኪያ የለ
በሰውን አዲስ መጐናጸፊያ ይዞ ዐሥራ ሁለት
ቦታ ቀደደው። 31ከዚያም ኢዮርብዓምን እን
ዲህ አለው፤ “ዐሥሩን ቍራጭ ለራስህ ውሰድ፤
የእስራኤል አምላክ እግዚአብሔር እንዲህ
ይላልና፤ ‘እነሆ፤ መንግሥቱን ከሰሎሞን እጅ
እቀዳለሁ፤ ዐሥሩን ነገድ ለአንተ እሰጣለሁ፤
32ነገር ግን ስለ ባሪያዬ ስለ ዳዊትና ከእስራ
ኤል ነገዶች ሁሉ ስለ መረጥኋት ስለ ኢየሩ
ሳሌም ስል አንድ ነገድ ይቀርለታል፤ 33ይህን
የማደርገውም እኔን ትተው[ሰ] የሲዶናውያንን
አምላክ አስታሮትን፣ የሞዓብን አምላክ
ካሞሽን፣ የአሞናውያንን አምላክ ሚልኮምን
ስላመለኩ እንዲሁም አባቱ ዳዊት እንዳደ
ረገው በመንገዴ ስላልሄዱ በፊቴ ትክክለ
ኛውን ነገር ስላላደረጉ፣ ሥርዐቴንና ሕጌን
ስላልጠበቁ ነው።
34“ ‘ይሁን እንጂ መንግሥቱን በሙሉ
ከእጁ አልወስድበትም፤ ስለ መረጥሁት፣
ትእዛዜንና ሥርዐቴን ስለ ጠበቀው ስለ ባሪ
ያዬ ስለ ዳዊት ስል በሕይወት ዘመኑ ሁሉ
እንዲገዛ አድርጌዋለሁ። 35መንግሥትን ከልጁ
እጅ እወስዳለሁ፤ ለአንተም ዐሥሩን ነገድ
እሰጥሃለሁ። 36ስሜ እንዲኖርባት በመረጥ
ኋት በዚያች በኢየሩሳሌም ከተማ ለባሪያዬ
ለዳዊት ምን ጊዜም በፊቴ መብራት እንዲ
ኖረው፣ ለልጁ አንድ ነገድ እሰጣለሁ።
37አንተን ግን እኔ እወስድሃለሁ፤ ልብህ በወ
ደደው ሁሉ ላይ ትነግሣለህ፤ የእስራኤልም
ንጉሥ ትሆናለህ። 38ባሪያዬ ዳዊት እንዳደረገው

11፥23 2ሳሙ8፥31 1ነገ5፥4
11፥24 2ሳሙ8፥5
11፥25 ዘፍ10፥22፤ 2ሳሙ10፥19
11፥26 2ዜና13፥6
11፥27 1ነገ9፥24
11፥28 ዘፍ39፥4፤ ሩት2፥1፤ምሳ22፥29
11፥29 1ነገ12፥15፤ 14፥2፤2ዜና9፥29፤ 10፥15
11፥30 1ሳሙ 15፥27
11፥31 ቍ11፤ 1ሳሙ15፥27
11፥32 2ሳሙ7፥15
11፥33 መሳ2፥13፤ 1ነገ3፥3፤2ነገ21፥22
11፥36 2ሳሙ 21፥17፤1ነገ12፥17
11፥37 2ሳሙ 3፥21፤1ነገ14፥7
11፥38 ዘዐ1፥21፤ ዘዳ12፥25፤17፥19፤ 2ሳሙ8፥15

[ሀ]24 ዕብራይስጡ *በደመሰሳቸው ጊዜ* ይላል።
[ሰ]33 የዕብራይስጡ፣ የሰብዓ ሊቃናት፣ የቩልጌትና የሱርስት ትር ጕሞች፣ *እኔን ስለ ተወ* ይላሉ።

11፥22 *እዚህ ምን ጐደለብህና!* በዚህ ጊዜ፣ ግብፅ ከእስራኤል ጋር ከሞላ ጐደል መልካም ግንኙነት መሥርታ ስለ ነበር (የ3፥1 ማብ ይመ)፣ ሃዳድ ወደ ኤዶም ሲመለስ፣ ከሰሎሞን ጋር ጠብ እንዳይፈጥር የግብፁ ፈርዖን ሰግቶ ነበር።

11፥24 *የወንበዴ አለቃ!* ዳዊት በአንድ ወቅት (1ሳሙ 22፥1-2)፣ ከእርሱም በፊት ዮፍታሔ (መሳ 11፥3) የወንበዴ አለቆች እንደ ነበሩ ሁሉ ማለት ነው። *ሰዎቹም ወደ ደማስቆ ሄደው ተቀመጡ!* ይህ የተፈጸመው ሰሎሞን በነገሠ በመጀመሪያዎቹ ዓመታት ላይ ሊሆን ይችላል (በዳዊት ዘመን በደማስቆ የተፈጸመውን ሁኔታ በ2ሳሙ 8፥6 ላይ ይመ)። ሰሎሞን በሐማትሱባ (ቀድሞ በአድርአዛር ትገዛ የነበረች አገር ናት፤ 2ሳሙ 8፥3-6) ላይ የዘመተው (2ዜና 8፥3) ሬዞን በአስነሣው ዐመፅ ምክንያት ነው። ምንም እንኳ ሰሎሞን ከደማስቆ በስተ ሰሜን በኤፍራጥስ ወንዝ አካባቢ የሚገኙትን ግዛቶች መቈጣጠር ቢችልም (4፥21:24) ሬዞንን ከደማስቆ ማስወጣት አልቻለም ነበር።

11፥26 *በንጉሡ ላይ ዐመፀ!* የቍ 40 ማብ ይመ።

11፥27 *ድጋፍ የሚሆኑ እርከኖች!* 9፥15 እንዲሁም ማብ ይመ።

11፥28 *በዮሴፍ ነገድ ለሚሠራው የጕልበት ሥራ!* 5፥13-18 ይመ። ከኤፍሬምና ከምናሴ ነገድ ተገደው በሚሠሩ ሰዎች ላይ ኀላፊ የሆነው ኢዮርብዓም፣ የሰሎሞን የአገዛዝ ሥርዐት (12፥4 ይመ) በሕዝቡ ዘንድ ምን ያህል ሮሮ እንደ ፈጠረ ማወቅ እንዲችል ረድቶታል።

11፥31-32 *ዐሥሩን ነገድ...አንድ ነገድ!* በሰሜን የሚኖሩትን ዐሥሩን ነገዶች በደቡብ ከሚኖሩት ነገዶች (ከይሁዳና ከስምዖን፤ ሌዊ ምንም ርስት የለውም ማለት ሲሆን፣ ኢሱ 21 ይመ) ለይቶ እንደ አንድ ሕዝብ መቍጠር ከመሳፍንት ዘመን ጀምሮ የነበረና የቈየ ልማድ ነው (መሳ 5፥14-16 ይመ)። የዚህም ምክንያት፣ ሁለቱን የእስራኤላውያን ግዛቶች የሚለዩት የእስራኤላውያን ያልሆኑ ሌሎች ነፃ ግዛቶች (ኢየሩሳሌም፣ የገባዖን ሰዎች ጌዝር) በመኖራቸው ነው። ዳዊት በነገሠበት በመጀመሪያዎቹ ዓመታት ላይ በፖለቲካ ጕዳይ የተከሠተው መከፋፈል፣ እንዲሁም የሰሜኑንና የደቡቡን ክፍል በዳዊት አገዛዝ ሥር እንዲሆን ያደረጉት ልዩ ልዩ ሁኔታዎች (2ሳሙ 2፥4፤ 5፥3 ይመ) መከፋፈሉን አጠናክሮት ነበር። ዳዊት ኢየሩሳሌምን ድል በማድረጉና (2ሳሙ 5፥6-7) ፈርዖን ደግሞ ለሰሎሞን ሚስት ጌዝርን መስጠቱ (9፥16-17) እስራኤል በሙሉ ለመጀመሪያ ጊዜ አንድ ግዛት ሆኑ (አሁን ኢየሩሳሌምና ጌዝር በእስራኤላውያን አስተዳደር ሥር ሆኑ፤ ቀደም ሲልም የገባዖን ሰዎች ለኢያሱ ተገዝተው ነበር፤ ኢሱ 9 ይመ)። እዚህ ላይ በተገለጸው መከፋፈል መሠረት፣ “አንድ ነገድ” የሚለው የሚያመለክተው ለይሁዳ የተሰጠውን ምድር ሲሆን (ለስምዖን የተሰጠውን ጨምሮ፤ ኢሱ 19፥1-9 ይመ)፣ “ዐሥር ነገድ” የሚለው ደግሞ፣ ከጊዜ በኋላ በዳዊት አገዛዝ ሥር የሆነውን ምድር ነው (የዮሴፍ ወንዶች ልጆች ኤፍሬምና ምናሴ እንደ ሁለት ነገድ ተቈጥረዋል፤ ዘፍ 48፥5 ይመ፤ እንዲሁም የኢሱ 14፥4 ማብ ይመ)። ይህ አዲስ ድንበር እንዴት እንደ መጣ በይበልጥ ለመረዳት፣ የ12፥21 ማብ ይመ።

11፥33 *እኔን ትተው!* ቍ 5-7 ይመ። *በመንገዴ ስላልሄዱ!* ቍ 1-2፤ 3፥14 ይመ።

11፥34 *በሕይወት ዘመኑ ሁሉ እንዲገዛ አድርጌዋለሁ!* ቍ 12፥13 ይመ።

11፥35 *ከልጁ እጅ!* ከሮብዓም እጅ ማለት ነው (12፥1-24 ይመ)።

11፥36 *በኢየሩሳሌም...በፊቴ መብራት!* እግዚአብሔር ስሙ እንዲጠራበት በመረጠው ከተማ (ቍ 13 እና ማብ ይመ)፣ የዳዊት ሥርወ መንግሥት ለዘላለም የሚጸና መሆኑን የሚያመለክት ነው። በብዙ ክፍሎች ተጠቅሶ እንደሚገኘው፣ የአንድ ሰው መብራት መጥፋት ወይም መብራት የሰውየውን ሕይወት መጥፋት ወይም መለምለምን ያመለክታል (ኢዮ 18፥6፤ 21፥17፤ ምሳ 13፥9፤ 20፥20፤ 24፥20)። እዚህም ላይ (እንዲሁም 15፥4፤ 2ነገ 8፥19፤ 2ዜና 21፥7፤ መዝ 132፥17) ተጠቅሶ እንደሚገኘው ይሄው ትእምርት የዳዊትን ሥርወ መንግሥት ለመግለጽ ገብቶአል (በመዝ 132፥17 ላይ “ለቀባሁት ሰው መብራትን አዘጋጃለሁ” የሚለው፣ “ለዳዊት ቀንድን አበቅላለሁ” ከሚለው ጋር እንደ ተጉ

ሁሉ አንተም ያዘዝሁህን ሁሉ ብትፈጽም፣
በመንገዴ ብትሄድ፣ ሥርዐቴንና ትእዛዜን
በመጠበቅ ትክክል የሆነውን ነገር በፊቴ
ብታደርግ፣ ከአንተ ጋር እሆናለሁ፤ የዳዊ
ትን ሥርወ መንግሥት እንዳጸናሁ፣ ለአንተም
እንዲሁ እስከ ዘላለም የሚኖር ሥርወ መንግ
ሥት አጸናለሁ፤ እስራኤልንም ለአንተ እሰጣ
ለሁ:: 39ከዚህ የተነሣም የዳዊትን ቤት አዋ
ርዳለሁ፤ ነገር ግን ለዘላለም አይደለም::' "

40ሰሎሞን ኢዮርብዓምን ለመግደል ፈለገ፤
ኢዮርብዓም ግን ወደ ግብፅ ሸሸ፤ ወደ ንጉሡ
ወደ ሺሻቅ ሄዶ፣ ሰሎሞን እስኪሞት ድረስ
በዚያው ተቀመጠ::

## የሰሎሞን መሞት

11፥41-43 ተጓ ምብ – 2ዜና 9፥29-31

41የቀረው በሰሎሞን ዘመነ መንግሥት የተ
ከናወነው፣ የሠራውም ሁሉ፣ ጥበቡም በሰ
ሎሞን የታሪክ መጽሐፍ ተጽፎ የለምን?
42ሰሎሞን በመላው እስራኤል ላይ በኢየሩሳ
ሌም የነገሠው አርባ ዓመት ነው:: 43ከአባ
ቶቹ ጋር አንቀላፋ፤ በአባቱ በዳዊት ከተማ
ተቀበረ፤ ልጁም ሮብዓም በእግሩ ተተክቶ
ነገሠ::

## እስራኤል በሮብዓም ላይ ዐመፀ

12፥1-24 ተጓ ምብ - 2ዜና 10፥1-11፥4

12 እስራኤላውያን ሁሉ ሊያነግሡት
ወደ ሴኬም ስለ ሄዱ፣ ሮብዓም
ወደዚያው ሄደ::[*] 2የናባጥ ልጅ ኢዮርብዓም
ይህን በሰማ ጊዜ፣ ከንጉሥ ሰሎሞን ሸሽቶ
ከሚኖርበት ከግብፅ ተመልሶ መጣ:: 3ስለዚ
ህም ወደ ኢዮርብዓም ላኩበት፤ እርሱና መላው
የእስራኤል ጉባኤም ወደ ሮብዓም መጥተው፣
4"አባትህ ከባድ ቀንበር ጫነብን፤ አንተ ግን
አሁን የአባትህን የጭካኔ አገዛዝ የጫነ
ብንንም ከባድ ቀንበር ብታቀልልን እንገዛል
ሃለን" አሉት::

5ሮብዓምም፣ "እንግዲያውስ ሂዱ፤ ከሦስት
ቀን በኋላ ተመልሳችሁ ወደ እኔ ኑ" አላ
ቸው:: ስለዚህ ሕዝቡ ሄዱ::

6ከዚያም ሮብዓም አባቱ ሰሎሞን በሕይ
ወቱ ሳለ ካገለገሉት ሽማግሌዎች ጋር ተማ
ከረ፤ "ለዚህ ሕዝብ ምን መልስ እንድሰጥ
ትመክሩኛላችሁ?" አላቸው::

7እነርሱም፣ "ዛሬ አንተ ለዚህ ሕዝብ አገ
ልጋይ ብትሆን፣ ብትገዛለትና ደስ የሚያሰኝ
መልስ ብትሰጠው፣ ምን ጊዜም የአንተ
አገልጋይ ይሆናል" ብለው መለሱለት::

8ሮብዓም ግን ሽማግሌዎቹ የሰጡትን ምክር
ንቆ፣ አብሮ አደግ የሆኑትንና እርሱን የሚ
ያገለግሉትን ወጣቶች፣ 9"ሐሳብ ለማግኘት፣
የእናንተስ ምክር ምንድን ነው? 'አባትህ
የጫነብንን ቀንበር አቅልልልን' ለሚሉኝ ለእ
ነዚህ ሰዎች ምን መልስ እንስጥ?" ሲል ጠየ
ቃቸው::

10ወጣት አብሮ አደጎቹም፣ እንዲህ አሉት፣
" 'አባትህ ከባድ ቀንበር ጫነብን፣ አንተ
ግን ቀንበራችንን አቅልልልን' ላሉህ ለእነዚህ
ሰዎች፣ 'ትንሿ ጣቴ ከአባቴ ወገብ ይልቅ
ትወፍራለች፤ 11አባቴ ከባድ ቀንበር ጫነባ
ችሁ፤ እኔ ግን ከዚያ ይብስ አከብደዋለሁ፤
አባቴ በዐለንጋ ገረፋችሁ፤ እኔ ግን በጊንጥ
እገርፋችኋለሁ' በላቸው!" አሉ::

12ንጉሡ፣ "በሦስተኛው ቀን ተመልሳችሁ

*2 ወይም በግብፅ ቀረ ተብሎ መተርጐም ይችላል::

11፥40 1ነገ12፥2፤ 2ዜና10፥2፤12፥2
11፥43 ማቴ1፥7
12፥1 ቊ25፤ዘፍ
12፥6፤ኢሱ24፥32
12፥2 1ነገ11፥40
12፥4 1ሳሙ8፥11-18፤1ነገ4፥20፡28
12፥6 1ነገ4፥2
12፥7 ምሳ15፥1
12፥8 ዘሌ19፥32

ዳኘ ይመ):: በእግዚአብሔር ፊት በኢየሩሳሌም ይህ "መብራት" በዳዊት ልጆች በኩል ለዘላለም ይበራል::

11፥37 *የእስራኤልም፤* በስተ ሰሜን የሚገኙትን ዐሥሩን ነገዶች ናቸው::

11፥38 *ያዘዝሁህን ሁሉ ብትፈጽም…ከአንተ ጋር እሆናለሁ፤* እንደ ዳዊትና እንደ ሰሎሞን ሁሉ፣ ኢዮርብዓምም የኪዳኑን ሕግ በፍጹም ልቡ እንዲታዘዝ፤ ይጠበቅበት ነበር (2፥3-4፤ 3፥14፤ 6፥12-13 ይመ)::

11፥39 *የዳዊትን ቤት አዋርዳለሁ፤* መንግሥቱ ለሁለት መከፈል፣ የዳዊት ቤት የነበረውን ክብርና ኀይል በጣም ቀንሶታል:: *ለዘላለም አይደለም፤* የእስራኤል መንግሥት በዳዊት ቤት አማካይነት፣ እንደ ገና አንድ እንደሚሆን የሚያረጋግጥ ተስፋ ነው (ይህ ሐሳብ ስለ መሲሑ በተነገሩ ትንቢቶች ላይ ተጠቅሶአል፤ ኤር 30፥9፤ ሕዝ 34፥23፤ 37፥15-28፤ ሆሴ 3፥5፤ አሞ 9፥11-12)::

11፥40 *ሰሎሞን ኢዮርብዓምን ለመግደል ፈለገ፤* ምናልባት ኢዮርብዓም በአቢያ በኩል የተነገረው ትንቢት፣ ቦታ ካለመስጠቱም በላይ (ቊ 34-35) መንግሥትን ከሰሎሞን በኀይል ነጥቆ ለመውሰድ ያደረገው ሙከራ ሳይከሸፍ አይቀርም (ቊ 26 ይመ):: *ወደ ንጉሡ ወደ ሺሻቅ፤* 14፥25-26 ይመ:: ይህ በብሉይ ኪዳን ስሙ በግልጽ የተጠቀሰው የግብፅ ፈርዖን፣ ሃያ ሁለተኛውን ሥርወ መንግሥት የመሠረተ ነው (ዓ.ቅ.ክ. 945-924):: ሰሎሞን በጋብቻ የተሳሰረው ከእሱ በፊት ከነበረው ሥርወ መንግሥት ጋር ነው (የ3፥1 ማብ ይመ)::

11፥41 *በሰሎሞን የታሪክ፤* የሰሎሞንን የሕይወት ታሪክ የአገዛዝ ዘመን ለመጻፍ የአንደኛና የሁለተኛ ነገሥት ጸሐፊ መረጃ አድርጎ የተጠቀመው ይህን መጽሐፍ ነው (15፥7:23 ይመ)::

11፥43 *ከአባቶቹ ጋር አንቀላፋ፤* የ1፥21 ማብ ይመ::

12፥1 *እስራኤላውያን ሁሉ፤* በሰሜን የሚገኙትን ዐሥሩን ነገዶች የሚወክሉ ናቸው (ቊ 16 ይመ):: በሰሜን ነገዶች ላይ፣ በኪዳኑ መሠረት የዳዊት መንገሥ (2ሳሙ 5፥3 ይመ) አንድ አዲስ ንጉሥ በነገሠ ቍጥር፣ ሕዝቡ ለንጉሡ ያለውን ታማኝነት ማደስ እንደሚገባው ያስገነዝባል:: *ሴኬም፤* በተራራማው ሰሜናዊ የኤፍሬም ግዛት የምትገኝ ገናና ታሪካዊ ከተማ ናት (ዘፍ 12፥6፤ 33፥18-20፤ ኢሱ 8፥30-35 ይመ እንዲሁም የኢሱ 8፥30 ማብ ይመ፤ 20፥7፤ 21፥21፤ 24፥1-33 ይመ)::

12፥2 *ይህን በሰማ ጊዜ፤* የሰሎሞንን ሞት ማለት ነው (11፥43):: *ከግብፅ ተመልሶ መጣ፤* 2ዜና 10፥2 ይመ::

12፥4 *ከባድ ቀንበር ጫነብን፤* ሰሎሞን ሕዝቡ ከፍተኛ ግብር እንዲከፍል፣ ተገዶ እንዲሠራና የውትድርና አገልግሎት እንዲሰጥ፣ በማድረጉ ሕዝቡ ያሰማው የቍጣ ድምፅ ነው (4፥7:22-23:27-28፤ 5፥13-14፤ 9፥22 ይመ፤ እንዲሁም የ9፥15፤ 11፥28 ማብ ይመ):: ሰሎሞን ከነገሠበት ጊዜ ጀምሮ፣ በሕዝቡ ላይ የተጫነው የአገዛዝ ቀንበር በየጊዜው ይከብድ ነበር (4፥20 ይመ)::

12፥6 *አባቱ ሰሎሞን… ካገለገሉት ሽማግሌዎች ጋር፤* አዶኒራምንና (4፥6) በሰሎሞን መንግሥት የከፍተኛ ሀገር ባለሥልጣኖች የነበሩትን የሚያመለክት ነው (4፥7-19)::

*12፥7፤* በእግዚአብሔር መንግሥት ውስጥ ሹመት የሚሰጠው፣ እግዚአብሔርን ለማገልገል እንጂ፣ የራስን ስም ለማስጠራት አይደለም::

12፥8 *ወጣቶች፤* የሮብዓም አብሮ አደጎች ሲሆኑ፣ በዕድሜ ያቸው በሰሎሞን ዘመነ መንግሥት ካገለገሉ ባለሥልጣኖች ጋር ሲነጻጸሩ፣ በዕድሜ ያነሱ ናቸው:: ሮብዓምም በነገሠ ጊዜ ዕድሜው አርባ አንድ ዓመት ነበር (14፥2):: *እርሱን የሚያገለግሉትን፤* ሮብዓም ሥልጣን በያዘ በጥቂት ጊዜ ውስጥ፣ ለወዳጆቹና ለአብሮ አደጎቹ ሥልጣን ሰጥቶ ነበር::

12፥10 *ትንሿ ጣቴ ከአባቴ ወገብ ይልቅ ትወፍራለች፤*

ኑ” ብሎአቸው ስለ ነበር፣ ኢዮርብዓምና
ሕዝቡ ሁሉ በሦስተኛው ቀን ወደ ሮብዓም
ተመልሰው መጡ:: 13ንጉሡም በሽማግሌ
ዎቹ የተሰጠውን ምክር ትቶ፣ ሕዝቡን
የሚያስከፋ መልስ ሰጣቸው፤ 14ወጣቶቹ
የሰጡትን ምክርም ተቀብሎ፣ “አባቴ ቀንበ
ራችሁን አከበደባችሁ፤ እኔ ደግሞ ከዚያ
ይብስ አከብደዋለሁ፤ አባቴ በአለንጋ ገረ
ፋችሁ፣ እኔ ደግሞ በጊንጥ እገርፋችኋለሁ”
አላቸው:: 15*እግዚአብሔር* በሴሎናዊው በአ
ኪያ አማካይነት ስለ ናባጥ ልጅ ስለ ኢዮር
ብዓም የተናገረው ቀድሞውኑ *እግዚአብሔር*
የወሰነው ስለ ሆነ፣ መፈጸም ነበረበትና ንጉሡ
ሕዝቡን አልሰማም::
16እስራኤልም ሁሉ ንጉሡ ሊሰማቸው
አለመፈለጉን በተረዱ ጊዜ፣ ለንጉሡ እንዲህ
በማለት መለሱ፤

“ከዳዊት ምን ድርሻ አለን?
ከእሴይስ ልጅ ምን የምናገኘው አለ?
እስራኤል ሆይ፤ ወደየድንኳንህ ተመለስ፤
ዳዊት ሆይ፤ እንግዲህ የገዛ
ቤትህን ጠብቅ!

ስለዚህም እስራኤላውያን ወደ ድንኳኖቻቸው
ተመለሱ:: 17ሮብዓምም በይሁዳ ምድር በሚ
ኖሩት እስራኤላውያን ላይ ገዥ ሆነ::
18ንጉሥ ሮብዓም የጕልበት ሠራተኞች
አለቃ የነበረውን አዶኒራምን[a] ላከው፤ ነገር
ግን እስራኤል ሁሉ በድንጋይ ወግረው ገደ
ሉት:: ንጉሡ ሮብዓም ግን እንደ ምንም
ብሎ ሠረገላው ላይ በመውጣት ወደ ኢየሩ
ሳሌም ሸሸ:: 19ስለዚህ ሕዝቡ በዳዊት ቤት
ላይ እስከ ዛሬ ድረስ እንዳመፀ ነው::

20ኢዮርብዓም መመለሱን እስራኤላውያን
ሁሉ በሰሙ ጊዜ፣ ወደ ጉባኤያቸው በማ
ስጠራት በመላው እስራኤል ላይ አነገሡት::
ለዳዊት ቤት በታማኝነት ጸንቶ የተገኘው
የይሁዳ ቤት ብቻ ነው::
21ሮብዓም ኢየሩሳሌም በደረሰ ጊዜ፣ የእ
ስራኤልን ቤት ወግተው መንግሥቱን ለሰ
ሎሞን ልጅ ለሮብዓም እንዲመልሱ መላውን
የይሁዳ ቤትና የብንያምን ነገድ ሰበሰበ፤ የሰ
ራዊቱም ቍጥር አንድ መቶ ሰማንያ ሺህ
ነበር::
22ነገር ግን ይህ የእግዚአብሔር ቃል፣ የእግዚአብሔር
ሰው ወደ ሆነው ወደ ሸማያ መጣ፤ 23“ለይ
ሁዳ ንጉሥ ለሰሎሞን ልጅ ለሮብዓም፣ ለመ
ላው የይሁዳ ቤትና ለብንያም ነገድ፣ ለቀረ
ውም ሕዝብ ሁሉ እንዲህ በል፤ 24‘*እግዚ
አብሔር* የሚለው ይህ ነው፤ ይህ ነገር ከእኔ
የሆነ ነውና ወንድሞቻችሁን እስራኤላውያ
ንን ለመውጋት አትውጡ፤ እያንዳንዳችሁ
ወደየቤታችሁ ተመለሱ::’ ስለዚህ *እግዚአ
ብሔር* እንዳዘዘው *የእግዚአብሔርን* ቃል ሰሙ፤
ወደየቤታቸውም ተመለሱ::

## በቤቴልና በዳን የቆሙ የወርቅ ጥጆች

25ከዚያም ኢዮርብዓም በኰረብታው አገር
በኤፍሬም የምትገኘውን ሴኬምን ምሽግ አድ
ርጎ ሠራ፤ በዚያም ተቀመጠ:: ደግሞም ያንን
ትቶ በመውጣት የጵኒኤልን[+] ምሽግ ሠራ::
26ኢዮርብዓም በልቡ እንዲህ ሲል አሰበ፤
“መንግሥቱ ለዳዊት ቤት የሚመለስ ይመ
ስላል፤ 27ይህ ሕዝብ መሥዋዕት ለማቅረብ

12፥14 ዘፀ1፥14
12፥15 ዘዳ2፥30፤ 1ነገ11፥29፤2ዜና 25፥20
12፥16 ዘፍ31፥14፤ 2ሳሙ20፥1፤ኢሳ7፥17
12፥17 1ነገ 11፥13:36
12፥18 ኢሱ7፥25፤ 2ሳሙ20፥24
12፥19 2ነገ17፥21
12፥20 1ነገ11፥13: 32፤ሕዝ37፥16
12፥21 1ነገ14፥30፤ 15፥6:16፤2ዜና11፥1
12፥22 ዘዳ33፥1፤ 2ነገ4፥7፤2ዜና12፥57
12፥25 ቍ1፤ መሳ8፥8
12፥27 ዘዳ12፥56

[a]18 አንዳንድ የሰብዓ ሊቃናት ቅጆችና የሱርስት ትርጕሞች ከዚህ ጋር ይስማማሉ (1ነገ4፥6፤ 5፥14 ይመ) ዕብራይስጡ፣ *አዶራም* ይላል
[+]25 ዕብራይስጡ *ጶኑኤል* ይለዋል

ቀላል የሆነችው የሮብዓም ትንሿ ቀንበር፣ ብርቱ ከሚባለው ከአባቱ ቀንበር ይልቅ፣ የከፋች መሆኗን የሚገልጽ ምሳሌ ነው::

12፥11 *በጊንጥ፤* ሹል ብረቶች የተሰኩበት ከቈዳ የሚሠራ መግረፊያ ነው:: እየከበደ የሚሄደው የአገዛዙ ቀንበር ብቻ ሳይሆን፣ በሚቃወሙት ላይ የሚደርስባቸው ቅጣት ጭምር ነው::

12፥14 *ወጣቶቹ የሰጡትን ምክርም ተቀብሎ፤* የሮብዓም መልስ ጭካኔን የተሞላ ከመሆኑም በላይ፣ የእስራኤል ነገሥታት በሥልጣን ዘመናቸው ሁሉ ሊያሳዩት ከሚገባው ባሕርይ ጋር የሚቃረን ነው (ዘዳ 17፥14-20 ይመ፤ የ1ሳሙ 10፥25 ማብ ይመ)::

12፥15 *እግዚአብሔር... በአኪያ አማካይነትም ስለ ኢዮርብዓም የተናገረው፤* 11፥29-39 ይመ:: *ቀድሞውኑ እግዚአብሔር የወሰነው፤ ስለ ሆነ፣* የመጽሐፈ ነገሥት ጸሐፊ ይህን ሲል የሮብዓምን ክፉ ተግባር ወይም የሰሜኑን ነገድ ሞገደኛነት እያጸና ወይም ትክክል ነው እያለ መጻፉ አይደለም፤ ነገር ግን ይህ ሁሉ የሆነው ሰሎሞን ጣዖትን በማምለኩና የእግዚአብሔርንም ኪዳን በማቃለሉ (11፥9-13) በዳዊት ቤት ላይ የተወሰነውን መለኮታዊ ቅጣት ለአንባቢው ለማስገንዘብ ብቻ ነው:: በእግዚአብሔር ሉዓላዊነትና ሰው ስለ ሠራው ሥራ ተጠያቂ በመሆኑ መካከል ያለውን ግንኙነት በተመለከተ የ2ሳሙ 24፥1 ማብ ይመ::

12፥16 *እስራኤልም ሁሉ፤* የሰሜኑን ነገድ ማለት ነው (የቍ 1 ማብ ይመ):: *ከዳዊት፤* የዳዊትን ሥርወ መንግሥት ማለት ነው (ቀደም ሲል ለተገለጸው ተመሳሳይ አባባል 2ሳሙ 20፥1 ይመ)::

12፥17 *በይሁዳ ምድር በሚኖሩት እስራኤላውያን ላይ፤* ዘራቸው ከሰሜኑ ነገድ የሆኑና በይሁዳ የሰፈሩ ሕዝቦች ናቸው፤ ከጊዜ በኋላም እግዚአብሔርን ለማገልገልና በቤተ መቅደስም እርሱን ለማምለክ የፈለጉ (2ዜና 11፥16-17 ይመ) ከሰሜኑ ነገድ የመጡ ሌሎች ሰዎች ከእነርሱ ጋር ተቀላቅለዋል::

12፥18 *የጕልበት ሠራተኞች አለቃ የነበረውን አዶኒራምን፤* በዳዊትና (2ሳሙ 20፥24) በሰሎሞን ዘመነ መንግሥት (1ነገ 4፥6፤ 5፥14) በተመሳሳይ ኀላፊነት ያገለገለ ሰው ነበር::

12፥19 *እስከ ዛሬ ድረስ፤* የአንደኛ ነገሥት ጸሐፊ፣ ይህን ታሪክ ለመጻፍ እንደ ምንጭ አድርጎ የተጠቀመበት መጽሐፍ የተጻፈበትን ጊዜ ማለት ነው (በመግቢያው ላይ ጸሐፊው፣ የጽሑፉ ምንጭና የተጻፈበት ዘመን የሚለውን ነው)::

12፥21 *የብንያምን ነገድ፤* ምንም እንኳ፣ የብንያም ድርሻ ከሰሜኑ ነገድ ጋር እንዲቀላቀል ቢደረግም (የ11፥31-32 ማብ ይመ)፣ በኢየሩሳሌም አካባቢ የሚገኘው ግዛት ግን በሮብዓም ቍጥጥር ሥር ነበር (የገባዖን ከተሞችና ጌዝር በቍጥጥሩ ሥር እንደ ነበሩ ሁሉ ማለት ነው):: የይሁዳ ሰሜናዊ ድንበር እስከ ቤቴል ይደርሳል (ከኢየሩሳሌም በስተ ሰሜን ዐሥራ ዘጠኝ ኪሎ ሜትር ትርቃለች)፣ የሮብዓም ልጅ አብያ፣ ቤቴልን ለአጭር ጊዜ በቍጥጥር ሥር አድርጓት ነበር (2ዜና 13፥19 ይመ):: *የሰራዊቱም ቍጥር አንድ መቶ ሰማንያ ሺህ ነበር፤* ይህ ቍጥር ምናልባት በጦርነቱ ላይ ከሚሰለፈው ሰራዊት በተጨማሪ ደጀን የሆነውንም ያጠቃልላል::

12፥22 *የእግዚአብሔር ሰው፤* ነቢያት የሚጠሩበት የተለመደ ስም ነው (13፥1፤ ዘዳ 18፥18፤ 33፥1፤ 1ሳሙ 2፥27፤ 9፥9-10 ይመ):: *ሸማያ፤* የሮብዓምን የአገዛዝ ታሪክ የጻፈ ሰው ነው (2ዜና 12፥15):: የዚህ ሰው ትንቢት በ2ዜና 12፥5-8 ላይ ተጽፎአል::

12፥23 *ለቀረውም ሕዝብ፤* የቍ 17 ማብ ይመ::

12፥24 *ወደየቤታችሁ ተመለሱ፤* ምንም እንኳ የእርስ በርሱ ግጭት ቢቆምም፣ በእስራኤልና በይሁዳ መካከል የተጀመረው ፍልሚያ፣ በሮብዓም፣ በአብያና በአሳ ዘመነ መንግሥትም ቀጥሎአል፤ ይህ የእርስ በርስ ግጭት ለጊዜው ጋብ ያለው፣ ከባኦስ ሞት በኋላ በተፈጠረው የፖለቲካ አለመረጋጋት ነው:: የአሣ ልጅ ኢዮሳፍጥ ከአክዓብ ጋር የወዳጅነት ስምምነት ያደረገው፣ ወንድ ልጁን ኢዮራምን ለአክዓብ ሴት ልጅ ለጎቶልያ በመዳር ነው (14፥30፤ 15፥6:16፤ 22፥2:44፤ 2ነገ 8፥18 ይመ)::

12፥25 *የጵኒኤልን፤* ከዮርዳኖስ ማዶ የሚገኝ ከተማ ሲሆን

ኢየሩሳሌም ወዳለው ወደ *እግዚአብሔር* ቤተ
መቅደስ የሚወጣ ከሆነ፣ እንደ ገና ልቡን
ወደ ጌታው ወደ ይሁዳ ንጉሥ ወደ ሮብዓም
ሊያዞር ነው። ከዚያም እኔን ይገድለኛል፤
ወደ ንጉሡም ወደ ሮብዓም ይመለሳል።”
28ንጉሡ ከመከረበት በኋላ ሁለት የወርቅ
ጥጆች አሠርቶ ሕዝቡን፣ “እስራኤል ሆይ፤
ወደ ኢየሩሳሌም እስካሁን የወጣኸው ይበ
ቃል፤ ከግብፅ ምድር ያወጡህ አማልክትህ
እነዚህ ናቸው” አለ። 29አንዱን በቤቴል ሌላ
ውንም በዳን አቆመው። 30ይህም አድራጎት
ኀጢአት ሆነ፤ ሕዝቡም በዚያ ላለው ለመስ
ገድ እስከ ዳን ድረስ ርቆ ሄደ።
31ኢዮርብዓም በማምለኪያ ኰረብቶች
ላይ አብያተ ጣዖታትን ሠራ፤ ከሕዝቡ የተ
ለያዩ ክፍሎች ሁሉ፣ ሌዋውያን ካልሆኑት
ካህናትን ሾመ። 32በይሁዳ እንደሚደረገው
ሁሉ እርሱም በስምንተኛው ወር ዐሥራ
አምስተኛው ቀን በዓል እንዲሆን ወሰነ፤ በመ
ሠዊያውም ላይ መሥዋዕት አቀረበ። ለሠ
ራቸው ጥጆች መሥዋዕት በማቅረብም እን
ዲህ ያለውን ድርጊት በቤቴል ፈጸመ። በማ
ምለኪያ ኰረብቶች ላይ ላሠራቸው አብ
ያተ ጣዖታት በቤቴል ካህናቱን መደበ። 33ራሱ
በመረጠው በስምንተኛው ወር፣ በዐሥራ አም
ስተኛው ቀን በቤቴል ባቆመው መሠዊያ
ላይ መሥዋዕት አቀረበ፤ ስለዚህ ለእስራኤ
ላውያን በዓል ወሰነላቸው፤ ዕጣንም ለማቅረብ
ወደ መሠዊያው ወጣ።

12፥28 ዘፀ32፥4፡ 8፤2ዜና11፥15
12፥29 ዘፍ12፥8፤ ኢሱ7፥2፤መሳ 18፥27-31፤አሞ8፥14
12፥30 1ነገ13፥34፤ 14፥16፤15፥26:30፤ 16፥2፤2ነገ3፥3፤ 10፥29፤13፥2፤ 17፥21
12፥31 ዘፀ29፥9፤ ዘሌ26፥30፤1ነገ 13፥32:33፤2ነገ 17፥29:32፤2ዜና 11፥1415፤13፥9
12፥32 ዘኍ29፥12፤ 2ነገ10፥29
12፥33 2ነገ23፥15፤ አሞ7፥13
13፥1 ዘዳ33፥1፤ መሳ13፥6፤አሞ7፥13
13፥2 ዘሌ26፥30፤ 2ነገ23፥1516:20፤ 2ዜና34፥5
13፥3 ዘፍ24፥14፤ ዘዳ4፥8፤ዮሐ2፥11
13፥6 ዘፍ20፥7፤ ዘኍ11፥2፤ኤር37፥3፤ ሐሥ8፥24

## ከይሁዳ የመጣ የእግዚአብሔር ሰው

13 ኢዮርብዓም መሥዋዕት ለማቅረብ
በመሠዊያው አጠገብ ቆሞ ሳለ፣ *በእ
ግዚአብሔር* ቃል ታዞ አንድ የእግዚአብሔር
ሰው ከይሁዳ ወደ ቤቴል መጣ። 2መሠዊ
ያውንም *በእግዚአብሔር* ቃል በመቃወም
እንዲህ አለ፤ “አንተ መሠዊያ ሆይ! እንግ
ዲህ *እግዚአብሔር* የሚለው ይህ ነው፤ ‘እነሆ፤
ኢዮስያስ የተባለ ለዳዊት ቤት ይወለዳል፤
እርሱም አሁን እዚህ መሥዋዕት የሚያቀር
ቡትን የኰረብታ ማምለኪያ ካህናት በላይህ
ይሠዋቸዋል፤ የሰዎችም ዐጥንት በአንተ ላይ
ይነዳል።’ ” 3በዚያች ዕለት ያ የእግዚአብሔር
ሰው፣ እንዲህ ሲል ምልክት ሰጠ፤ “*እግዚአ
ብሔር* የሰጠውም ምልክት፣ ‘እነሆ፣ መሠዊ
ያው ይሰነጠቃል፤ በላዩም ላይ ያለው ዐመድ
ይፈሳል’ ” የሚል ነው።
4ንጉሥ ኢዮርብዓምም ያ የእግዚአብሔር ሰው
በቤቴል መሠዊያ ላይ ጮኾ የተናገረውን
ሲሰማ፣ እጁን መሠዊያው ካለበት በመዘር
ጋት፣ “ያዙት!” አለ፤ ነገር ግን ያች የዘረ
ጋት እጁ ደርቃ ቀረች፤ ሊመልሳትም አል
ቻለም 5እንዲሁም ያ የእግዚአብሔር ሰው *በእ
ግዚአብሔር* ቃል ተመርቶ በሰጠው ምል
ክት መሠረት መሠዊያው ተሰነጠቀ፤ ዐመ
ዱም ፈሰሰ።
6ከዚያም ንጉሡ የእግዚአብሔርን ሰው፣ “እጄ
ወደ ቦታዋ እንድትመለስ ወደ አምላክህ ወደ
*እግዚአብሔር* ለምንልኝ፤ ጸልይልኝም” አለው፤

(ዘፍ 32፥31፤ መሳ 8፥9:17 ይመ)፣ በደማስቆ ከሚኖሩ ሶርያውያንና (11፥23-25 ይመ) ከአሞናውያን ራስን ለመከላከል የሚያስችል ምቹና ወሳኝ ቦታ ነው።

12፥26 *ለዳዊት ቤት የሚመለስ፤* ኢዮርብዓም በአኪያ በኩል የተሰጠውን መለኮታዊ ተስፋ (11፥38 ይመ)፣ በሙሉ ልቡ ባለመቀበሉ፣ ንጉሥነቱን በገዛ መንገዱ አስተማማኝ ለማድረግ የራሱን እርምጃ ወሰደ።

12፥28 *ሁለት የወርቅ ጥጆች፤* የአራማውያንና የከነዓናውያን አማልክት የሚመሰሉት በጥጃና በበሬ ሲሆን፣ የኀይልና የልምላሜ አማልክት እንደ ሆኑ ይታመናል (የመሳ 2፥13 ማብ ይመ)። *እስራኤል ሆይ…ከግብፅ ምድር ያወጡህ አማልክትህ እነዚህ ናቸው፤* ኢዮርብዓም እግዚአብሔርን የሚወክል የጥጃ ምስል ባያቆምም፣ አሮን እንደ አደረገው (ዘፀ 32፥4-5) እርሱም የአረማውያንን ኮርማዎች ምስል እግዚአብሔርን ከማምለክ ጋር ለማጣመር ሞክሮአል።

12፥29 *በቤቴል፤* ከኢየሩሳሌም በስተ ሰሜን ዐሥራ ዘጠኝ ኪሎ ሜትር ያህል ርቃ፣ በኤፍሬም ድንበር አቅራቢያ በብንያም ግዛት ውስጥ የምትገኝ (ኢሱ 18፥11-13:22) ከተማ ናት። ቤቴል አምልኮተ እግዚአብሔርን በተመለከተ፣ በእስራኤል ታሪክ ውስጥ ገናና ስፍራ አላት (ዘፍ 12፥8፤ 28፥11-19፤ 35፥6-7፤ መሳ 20፥26-28፤ 1ሳሙ 7፥16 ይመ)። *ዳን፤* በስተ ሰሜን በኩል በሔርሞን ተራራ አቅራቢያ የሚገኝ ቦታ ነው። በመሳፍንት ዘመን በዚህ ስፍራ የጣዖት አምልኮ ይደረግ ነበር (መሳ 18፥30-31)።

12፥30 *ይህም አድራጎት ኀጢአት ሆነ፤* የኢዮርብዓም የሥርዐት አገዛዝ ከዐሠርቱ ትእዛዛት መካከል፣ ሁለተኛውን ትእዛዝ የሚተላለፍ ነው (ዘፀ 20፥4-6)። ይህም እስራኤላውያን የመጀመሪያውን ትእዛዝ እንዲተላለፉ (ዘፀ 20፥3) ከማድረጉም በላይ፣ የአረማውያን ልምምድ (አምልኮተ ጣዖት) ወደ እስራኤል ሃይማኖታዊ ሥርዐት ውስጥ ሰተት ብሎ እንዲገባ በር ከፍቶአል (በተለይም ይህ በአክዓብ ዘመነ መንግሥት ተፈጽሞአል)። ኢዮርብዓም ለፖለቲካዊ ጥቅም ሲል፣ ሃይማኖታዊ ሥርዐትን እርግፍ አድርጎ በመተው፣ በአኪያ በኩል የተሰጠውን የተስፋ ቃል ሳያገኝ ቀረ (11፥38 ይመ)።

12፥31 *ኢዮርብዓም በማምለኪያ ኰረብቶች፤ ላይ አብያተ ጣዖታትን ሠራ፤* የ3፥2 ማብ ይመ። *ሌዋውያን ካልሆኑት፤* ኢዮርብዓም ለሰሜኑ ክፍል ለጣዖታት የሚሰግዱ ካህናትን በመሾሙ (2ዜና 11፥13-14 ይመ) በሰሜኑ መንግሥት ይኖሩ የነበሩ ብዙ ካህናትና ሌዋውያን ወደ ይሁዳ ምድር ፈለሱ።

12፥32 *በይሁዳ እንደሚደረገው…በዓል፤* የዳስ በዓል በይሁዳ የሚከበረው በሰባተኛው ወር ከዐሥራ አምስተኛው ቀን ጀምሮ እስከ ሃያ አንደኛው ቀን ድረስ ነበር (8፥2፤ ዘሌ 23፥34 ይመ። *በመሠዊያውም ላይ መሥዋዕት አቀረበ፤* ኢዮርብዓም ለአንድ የእስራኤል ንጉሥ ከተሰጠው ኀላፊነት በላይ ዐልፎ በመሄድ፣ ለካህናት ብቻ የተሰጠውን ኀላፊነት ወሰደ (2ዜና 26፥16-21 ይመ)።

13፥1 *የእግዚአብሔር ሰው፤* የ12፥22 ማብ ይመ። *ከይሁዳ ወደ ቤቴል መጣ፤* በሰሜኑ መንግሥት ወደምትገኘው ወደ ቤቴል እግዚአብሔር ከደቡብ መንግሥት ነቢይን ላከ። ይህን ያደረገው የሰሜኑና የደቡቡ መንግሥት ለሁለት እንዲከፈል እግዚአብሔር የወሰነው (11፥11:29-39፤ 12፥15:24)፣ በሁለቱ መንግሥታት ውስጥ እርስ በርስ የሚቃረን ሃይማኖታዊ ሥርዐትን ለመፍጠር እንዳልሆነ አጒልቶ ለማሳየት ነው። ከሁለት ምዕተ ዓመት በኋላም፣ ነቢዩ አሞጽ በዳግማዊ ኢዮርብዓም ላይ እግዚአብሔር የተናገረውን ፍርድ ለማሳወቅ፣ በይሁዳ ከምትገኘው ከቴቁሔ ተነ ሥቶ በሰሜኑ መንግሥት ወደምትገኘው ወደ ቤቴል ሄዶ ነበር (አሞ 7፥10-17)።

13፥2 *ኢዮስያስ፤* የእስራኤል መንግሥት ለሁለት ከተከፈለ ከሦስት መቶ ዓመት በኋላ፣ በይሁዳ ላይ ስለሚነግሠው ስለ ንጉሥ ኢዮስያስ አገዛዝ የተነገረ የትንቢት ቃል ነው። *መሥዋዕት የሚያቀርቡትን…ካህናት በላይህ ይሠዋቸዋል፤* ትንቢቱ እንደ ተፈጸመ በ2ነገ 23፥15-20 ላይ ተገልጾአል።

13፥3 *ምልክት፤* በአጭር ጊዜ ውስጥ ይፈጸማል ተብሎ የተነገረው ትንቢት በተነገረው መሠረት መፈጸሙ፣ በረጅም ጊዜ ውስጥ ይፈጸማል ተብሎ የተነገረው ትንቢት እንደሚፈጸም ማረጋገጫ ነው (ዘዳ 18፥21-22)።

13፥5 *ዐመዱም ፈሰሰ፤* ነቢዩ የተነገረውን ትንቢት እግዚአብሔር በራሱ ኀይል መፈጸሙንና ለመፈጸም (የቊ 3 ማብ ይመ)፣ ኢዮርብዓም ያቀረበው መሥዋዕት በእግዚአብሔር ዘንድ

ስለዚህም የእግዚአብሔር ሰው *እግዚአብሔርን*
ለመነ፤ የንጉሡ እጅ ወደ ቦታዋ ተመለ
ሰች፤ እንደ ቀድሞዋም ሆነች።
7ንጉሡም የእግዚአብሔርን ሰው፣ “አብረኸኝ
ወደ ቤት እንሂድ፤ አንድ ነገር ቅመስ፤
ስጦታም አደርግልሃለሁ” አለው።
8የእግዚአብሔር ሰው ግን ለንጉሡ እንዲህ
ሲል መለሰለት፤ “ግማሽ ሀብትህን ብትሰጠኝ
እንኳ፣ አብሬህ አልሄድም፤ እዚህ፣ እንጀራ
አልበላም፤ ውሃም አልጠጣም። 9*በእግዚአ
ብሔር ቃል*፤ ‘እንጀራ እንዳትበላ፣ ውሃም
እንዳትጠጣ፣ በሄድህበትም መንገድ እንዳ
ትመለስ’ ተብዬ *ታዝዣለሁና*።” 10ስለዚህም
በመጣበት ሳይሆን በሌላ መንገድ ወደ ቤቴል
ተመለሰ።
11በዚያን ጊዜ በቤቴል የሚኖር አንድ ሽማ
ግሌ ነቢይ ነበር፤ ልጆቹም መጥተው በዚ
ያች ዕለት የእግዚአብሔር ሰው እዚያ ያደረገ
ውን ሁሉና ንጉሡንም ምን እንዳለው ለአባ
ታቸው ነገሩት። 12አባታቸውም፣ “ለመሆኑ
የተመለሰው በየትኛው መንገድ ነው?” በማ
ለት ጠየቃቸው፤ ልጆቹም ከይሁዳ የመ
ጣው የእግዚአብሔር ሰው የተመለሰበትን መን
ገድ ለአባታቸው አሳዩት። 13ስለዚህም ልጆ
ቹን፣ “በሉ አህያውን ጫኑልኝ” አላቸው።
እነርሱም አህያውን ጫኑለትና ተቀምጦበት
14እየጋለበ ያን የእግዚአብሔር ሰው ተከተለው።
ከዚያም በአንድ የወርካ ዛፍ ሥር ተቀምጦ
አገኘውና፣ “ከይሁዳ የመጣኸው የእግዚአብሔር
ሰው አንተ ነህን?” ሲል ጠየቀው።
እርሱም፣ “አዎን እኔ ነኝ” ብሎ መለሰለት።
15ስለዚህ ነቢዩ፣ “አብረን ወደ ቤት እንሂ
ድና ምግብ ብላ” አለው።
16የእግዚአብሔርም ሰው እንዲህ ሲል መለሰ
ለት፤ “ተመልሼ ከአንተ ጋር አልሄድም፤
በዚህ ቦታም አብሬህ እንጀራ አልበላም፤
ውሃም አልተጣም፤ 17‘እዚያ እንጀራ እንዳ
ትበላ፣ ውሃም እንዳትጠጣ፣ በሄድህበትም
መንገድ እንዳትመለስ’ ተብዬ *በእግዚአብሔር*

13፥7 1ሳሙ 9፥7
13፥8 ቍ 16፤ ዘኍ 22፥18
13፥16 ቍ 8
13፥18 ዘፍ 19፥14፤ ዘዳ 13፥3፤ 1ነገ 22፥6፡ 12፤ 2ዜና 35፥21፤ ኢሳ 36፥10
13፥21 ቍ 26፤ 1ሳሙ 13፥14፤ 1ነገ 20፥35
13፥24 1ነገ 20፥36
13፥26 ቍ 21

*ቃል ታዝዣለሁና*” አለው።
18ሽማግሌው ነቢይ ግን፣ “እኔም እኮ እንዳ
ንተው ነቢይ ነኝ፤ መልአክ *በእግዚአብሔር
ቃል*፣ ‘እንጀራ እንዲበላና ውሃ እንዲጠጣ
መልሰህ ወደ ቤትህ አምጣው’ ብሎኛል ነው”
አለው፤ ነገር ግን ውሸቱን ነበር። 19ስለዚህ
የእግዚአብሔርም ሰው አብሮት ተመልሶ በቤቱ
በላ፤ ጠጣም።
20በማእድ ተቀምጠው ሳለ፣ *የእግዚአብሔር
ቃል* መልሶ ወደ አመጣው ወደ ሽማግሌው
ነቢይ መጣ፤ 21ከይሁዳ ለመጣውም የእግዚአ
ብሔር ሰው፣ “*እግዚአብሔር* የሚለው ይህ
ነው፣ ‘*የእግዚአብሔርን* ቃል አቃለሃል፤ ስምላ
ክህ *እግዚአብሔር* የሰጠህንም ትእዛዝ አልጠ
በቅህም፤ 22ተመልሰህ በመምጣት እንዳትበ
ላና እንዳትጠጣ በነገረህ ቦታ እንጀራ በላህ፤
ውሃም ጠጣህ። ስለዚህ ሬሳህ በአባቶችህ
መቃብር አይቀበርም’ ” ሲል ጮኸ ተናገረው።
23የእግዚአብሔርም ሰው በልቶና ጠጥቶ ካበቃ
በኋላ፣ ያ መልሶ ያመጣው ነቢይ አህያውን
ጫነለት። 24ሲሄድ ሳለም አንበሳ መንገድ ላይ
አግኝቶ ገደለው፤ ሬሳውም በመንገድ ላይ
ተጋደመ፤ አህያውና አንበሳውም አጠገቡ
ቆመው ነበር። 25በዚያ ያለፉ ሰዎች ሬሳው
በመንገድ ላይ ተጋድሞ፣ አንበሳውም አጠ
ገቡ ቆሞ ሲያዩ፣ ሽማግሌው ነቢይ ወዳለበት
ከተማ ሄደው ይህንኑ ተናገሩ።
26ያም ከመንገድ የመለሰው ነቢይ ይህን
ሲሰማ፣ “ይህ *የእግዚአብሔርን ቃል* ያቃለ
ለው ያ የእግዚአብሔር ሰው ነው፤ *እግዚአብሔር*
ባስጠነቀቀው ቃል መሠረት አሳልፎ ሰጥ
ቶት አንበሳ ሰብሮ ገድሎታል” አለ።
27ከዚያም ነቢዩ ልጆቹን፣ “በሉ አህያ
ጫኑልኝ” አላቸውና ጫኑለት። 28ከዚያም ሄዶ
ሬሳው መንገድ ላይ ተጋድሞ አንበሳውና
አህያው በአጠገቡ ቆመው አገኘ፤ አንበሳው
ሬሳውን አልበላውም፤ አህያውንም አልሰበ
ረውም። 29ስለዚህ፣ ነቢዩ የዚያን የእግዚአብሔር
ሰው ሬሳ አንሥቶ በአህያው ላይ ጫነ፤
አልቅሶ ለመቅበርም ራሱ ወደሚኖርበት

---

ተቀባይነት እንደሌለው የሚያሳይ ግልጽ ምልክት ነው (ዘሌ 6፥10-11 ይመ)።

13፥6 *ወደ አምላክህ፤* ኢዮርብዓም እግዚአብሔርን እንደ አምላኩ አድርጎ አለመቍጠሩን የሚያመለክት ተደርጎ መወሰድ የለበትም (ከ2፥3፤ ከዘፍ 27፥20 ጋር ያነጻጽሩ)፤ ነገር ግን ይህ አነጋገር መወሰድ ያለበት፣ በእግዚአብሔር ሥርዐት ውስጥ ነቢዩን ከእርሱ በላይ አድርጎ መቍጠሩን ነው። *የንጉሡ እጅ ወደ ቦታዋ ተመለሰች፤* እግዚአብሔር ለኢዮርብዓም ጥያቄ የሰጠው መልስ፣ የነቢዩን ቃል ለማጽናትና ኢዮርብዓምን ወደ ንስሓ ለማምጣት የተሰጠ ተጨማሪ ምልክት (ቍ 3 ይመ) ነው።

13፥7 *አብረኸኝ ወደ ቤት እንሂድ፤* ኢዮርብዓም፣ በእርሱና በነቢያት ሥርዐት መካከል (1ሳሙ 15፥30 ይመ) መሠረታዊ ልዩነት እንደሌለ በማስመሰል በሕዝቡ ዘንድ ያለውን ክብሬታ ለማደስ ሞከረ።

13፥9 *እንዳትበላ…እንዳትጠጣ…እንዳትመለስ፤* ኢዮርብዓም ላቀረበለት ግብዣ ነቢዩ እምቢ ያለው፣ ቀደም ሲል እግዚአብሔር በሰጠው ትእዛዝ መሠረት ነው። በቤቴል የተጀመረው የጣዖት አምልኮ እግዚአብሔርን እጅግ እንዳሳዘነ ይገልጻል።

13፥18 *እኔም እኮ፣ እንዳንተው ነቢይ ነኝ፤* አባባሉ በከፊል እውነትነት አለው። ይኸውም ባለፉት ዘመናት በቤቴል የነበረው ሽማግሌው ነቢይ፣ የእግዚአብሔርን ቃል በታማኝነት ተና ግሮ ይሆናል፤ ይሁን እንጂ፣ ያ ዘመን ካለፈ ብዙ ጊዜ ሆኖታል።

13፥19 *የእግዚአብሔርም ሰው አብሮት ተመልሶ፤* የሽማግሌው ነቢይ ውሸትም ሆነ ግላዊ ፍላጎት እግዚአብሔር በግልጽ የሰጠውን ትእዛዝ ላለመፈጸሙ በቂ ምክንያት ሊሆን አይችልም። በዚህ ጕዳይ ላይ የወሰደው እርምጃ በቤቴል የተናገረውን ቃል የሚቃረንና የመለኮትን ሥልጣን የሚያቃልል ነው።

13፥20 *የእግዚአብሔር ቃል…ወደ ሽማግሌው ነቢይ መጣ፤* እዚህ ላይ በእውነተኛና በሐሰተኛ ትንቢት መካከል ያለው መሠረታዊ ልዩነት ግልጽ ሆኖአል። የሐሰት ትንቢት የሚመነጨው ከሰዎች ልብ ሲሆን (ኤር 23፥16፤ ሕዝ 13፥2:7) እውነተኛ ትንቢት የሚመጣው ግን ከእግዚአብሔር ነው (ዘፀ 4፥16፤ ዘዳ 18፥18፤ ኤር 1፥9፤ 2ጴጥ 1፥21)።

13፥22 *ሬሳህ በአባቶችህ መቃብር አይቀበርም፤* ከይሁዳ የመጣው የእግዚአብሔር ሰው የሚሞተው፣ በገዛ አገሩና ከቤተ ሰቡ መቀበሪያ ቦታ ርቆ ነው።

13፥24 *ገደለው፤* እግዚአብሔር የተናገረውን ቃል እንዲፈጽም፣ ለኢዮርብዓም የተሰጠ ጥብቅ ማስጠንቀቂያ ነው። *አህያውና አንበሳውም አጠገቡ ቆመው ነበር፤* የአህያው አለመሮጥና አንበሳው አህያውን አለመተናኰሉ ወይም የሰውዬውን ሬሳ አለመገንጣጠል (ቍ 28)፣ ከእግዚአብሔር የመጣ ፍርድ መሆኑን በግልጽ ያመለክታል። ይህ ተጨማሪ ታምር በቤቴል ከመነገሩም

ከተማ አመጣው:: 30ከዚያም ሬሳውን በራሱ
መቃብር ቀበረው፤ "አወይ ወንድሜን" እያ
ሉም አለቀሱለት::
31ከቀበሩትም በኋላ ልጆቹን እንዲህ አላ
ቸው፤ "እኔም በምሞትበት ጊዜ የእግዚአብሔር
ሰው በተቀበረበት መቃብር ቅበሩኝ፤ ዐጥን
ቶቼንም በዐጥንቶቹ አጠገብ አኑሩ:: 32በቤ
ቴል ባለው መሠዊያ፣ በሰማርያ ከተሞችና
በየኰረብታው ባሉ ማምለኪያ ስፍራዎች ላይ
በእግዚአብሔር ቃል ጮኾ ያሰማው መልእ
ክት በትክክል የሚፈጸም ነውና::"
33ይህም ሁሉ ሆኖ ኢዮርብዓም ከክፉ
መንገዱ አልተመለሰም፤ ይልቁንም በኰረ
ብታ ማምለኪያዎች ከየትኛውም ክፍል እንደ
ገና ካህናትን ይሾም ጀመር፤ ካህን ለመሆን
የሚፈልገውንም ሁሉ ለየኰረብታ ማምለኪ
ያዎቹ ለየ:: 34ይህም ኀጢአት የኢዮርብዓም
ቤት እንዲወድቅና ከምድር ገጽም እንዲደ
መሰስ ምክንያት ሆነ::

## አኪያ በኢዮርብዓም ላይ የተናገረው ትንቢት

14 በዚያን ጊዜ የኢዮርብዓም ልጅ
አብያ ታመመ፤ 2ኢዮርብዓም ሚስ
ቱን እንዲህ አላት፤ "ተነሺ፣ የኢዮርብዓም
ሚስት መሆንሽ እንዳይታወቅብሽ ሆነሽ፣
ወደ ሴሎ ሂጂ፤ በዚህ ሕዝብ ላይ እንደም
ነግሥ የነገረኝ ነቢይ አኪያ እነሆ፤ በዚያ
ይገኛል:: 3ስትሄጂም ዐሥር እንጀራ፣ ጥቂት
ሙልሙል ዳቦ እና አንድ እንስራ ማር ይዘሽ
ሂጂ፤ እርሱም በልጁ ላይ የሚደርሰውን
ይነግርሻል::" 4ስለዚህ የኢዮርብዓም ሚስት
ያላትን አድርጋ በሴሎ ወደሚገኘው ወደ
አኪያ ቤት ሄደች::
በዚህ ጊዜ አኪያ ከማርጀቱ የተነሣ ዐይ
ኖቹ ፈዘው ነበር:: 5እግዚአብሔር ግን ለአ
ኪያ፣ "እነሆ፤ የኢዮርብዓም ሚስት ስለ ታመ
መው ልጇ ልትጠይቅህ ሌላ ሴት መስላ
ትመጣለችና እንዲህ ብለህ መልሳት" ብሎ
ነገረው::
6አኪያም የእግሯን ኰቴ ድምፅ እበሩ ላይ
እንደ ሰማ እንዲህ አላት፤ "የኢዮርብዓም
ሚስት ሆይ ግቢ፤ ግን ለምንድን ነው ሌላ
ሴት መስለሽ ለመታየት የፈለግሽው? ለአ
ንቺ ከባድ ነገር እንድነግርሽ ተልኬአለሁ::
7አሁንም ሂጂና ኢዮርብዓምን የእስራኤል
አምላክ እግዚአብሔር የሚለው ይህ ነው
ብለሽ ንገሪው፤ 'ከሕዝቡ መካከል አንሥቼ
የሕዝቤ የእስራኤል መሪ አደረግሁህ፤ 8ከዳ
ዊት ቤት መንግሥቱን ቀድጄ ለአንተ ሰጠ
ሁህ፤ አንተ ግን በፊቴ መልካም ነገር በማ
ድረግ ብቻ ትእዛዜን እንደ ጠበቀው፣ በፍጹም
ልቡም እንደ ተከተለኝ እንደ ባሪያዬ እንደ
ዳዊት አልሆንህም:: 9ከአንተ በፊት ከነበሩት
ሁሉ ይልቅ አንተ የከፋ ሥራ ሠራህ፤ ለራስ
ህም ከቀለጠ ብረት ሌሎች አማልክትን ሠራህ፤
ቍጣዬን አነሣሣህ፤ ወደ ኋላህም ጣልኸኝ::
10" 'ስለዚህ እኔም በኢዮርብዓም ቤት ላይ
ጥፋትን አመጣለሁ፤ ባሪያም ይሁን ነጻ ዜጋ
የኢዮርብዓምን ወንድ ልጅ ሁሉ ከእስራኤል
አስወግዳለሁ፤ ኩበትም ፀመድ እስኪሆን
ድረስ እንደሚቃጠል፣ እኔም የኢዮርብዓምን
ቤት እንዲሁ አቃጥላለሁ:: 11ከኢዮርብዓም
ወገን በከተማ የሞተውን ውሾች፣ በባላገር
የሞተውን ደግሞ የሰማይ አሞሮች ይበሉ
ታል፤ እግዚአብሔር ተናግሮአልና!'

13፥30 2ነገ23፥17፤ ኤር22፥18
13፥32 ዘሌ26፥30፤ 1ነገ12፥31፤16፥24፡ 28፤20፥1፤2ነገ10፥11፤ 15፥13፤23፥16
13፥33 1ነገ12፥31፤ 15፥26
13፥34 1ነገ12፥30፤ 14፥10፤15፥29፤2ነገ 9፥9፤ኤር35፥17፤ አሞ7፥9
14፥2 1ነገ11፥29
14፥3 1ሳሙ9፥7
14፥6 1ሳሙ28፥12
14፥7 1ነገ11፥37፤ 15፥29
14፥8 1ሳሙ 15፥27፤2ሳሙ8፥15፤ 1ነገ3፥3፤15፥5፤2ነገ 14፥3፤15፥3:34፤16፥2 ፤18፥3፤20፥3፤22፥2
14፥9 ዘፀ20፥4፤ 32፥4፤ዘዳ32፥16፤1ነገ 16፥2:30:33፤21፥25፤ 2ነገ21፥9:11፤24፥3፤ 2ዜና11፥15፤ነህ9፥26፤ መዝ50፥17፤78፥58፤ ኤር2፥27፤7፥18፤ 8፥19፤32፥32:33፤ 44፥3፤ሕዝ8፥17፤ 16፥26፤23፥35
14፥10 ዘዳ32፥36፤ ኢሱ23፥15፤1ሳሙ 12፥25፤15፥26፤1ነገ 13፥34፤15፥29፤2ነገ 9፥89፤ሆሴ13፥11
14፥11 ዘፍ40፥19፤ ዘዳ28፥26፤1ነገ16፥4፤ 21፥24

በላይ (ቍ 25)፣ በኢዮርብዓም መሠዊያ አጠገብ፣ ከይሁዳ የመ
ጣው የእግዚአብሔር ሰው የተናገረው ትንቢት እውነተኛ መሆ
ኑን የሚያረጋግጥ ሌላ ምልክት ነው:: ይህም ሆኖ ግን፣ ኢዮር
ብዓም ልቡን ለንስሓ አላዘጋጀም ነበር (ቍ 33)::

13፥30 *ሬሳውን በራሱ መቃብር ቀበረው፤* ቍ 22 ይመ:: ሽማግሌው ነቢይ፣ ቀደም ሲል ሆን ብሎ የፈጸመውን ተንኰል ማስተካከል የሚችለው ይህን በማድረግ ብቻ ነበር::

13፥31 *የእግዚአብሔር ሰው በተቀበረበት መቃብር፤ ቅበሩኝ፤* ከይሁዳ የመጣው የእግዚአብሔር ሰው በቤቴል ከተናገረው ትንቢት ጋር፣ ሽማግሌው ነቢይ መስማማቱን ያሳየው በዚህ ዐይነት ነው::

13፥32 *በሰማርያ፤* የሰሜኑ መንግሥት ዋና ከተማ እንደ መሆኑ መጠን፣ በሰሜን የሚኖሩትን የዐሥሩን ነገዶች ጠቅላላ ግዛት የሚያመለክት ስም ነው (የ16፥24 ማብ ይመ):: ይሁን እንጂ፣ ሰማርያ ይህ ታሪክ ከተፈጸመ ከአምሳ ዓመት በኋላ እንኳ ገና አልተቈረቈረችም ነበር (16፥23-24)፤ እዚህ ላይ ስሟ መጠቀሱ፣ የመጽሐፈ ነገሥትን ጸሓፊ አመለካከት ያንጸባርቃል (የዘፍ 14፥14 ማብ ይመ)::

13፥33 *ከየትኛውም ክፍል... ካህናትን...ይሾም ጀመር፤* 12፥31 እና ማብ ይመ::

13፥34 *ኀጢአት፤* በ12፥30 ላይ ኀጢአት ተብሎ የተጠቀሰው የጣዖት አምልኮ ሲሆን፣ እዚህ ላይ ደግሞ ኀጢአት የተባለው በዚሁ በጣዖት አምልኮ መቀጠልና ከዚህ ጋር የተያያዘ ክፉ ነገር ሁሉ ነው::

14፥1 *በዚያን ጊዜ፤* ምናልባት በም 13 ላይ የተነገረው ትረካ ከተፈጸመ፣ ብዙ ሳይርቅ ያለውን ጊዜ የሚያመለክት ሊሆን ይችላል:: *አብያ፤* የስሙ ትርጕም፣ "አባቴ (አምላኬ) እግዚአብሔር ነው" ማለት ሲሆን፣ ኢዮርብዓም እግዚአብሔርን የሚያመልክ መሆኑን ለማሳየት ያወጣው ስም ነው::

14፥2 *እንዳይታወቅብሽ ሆነሽ፤* የታመመውን ልጅ በሚመለከት አኪያ መልካም ትንቢት እንዲናገር ኢዮርብዓም ያደረገው ሙከራ የሚያመለክተው:- (1) የፈጸመውን በደል እርሱ ራሱ የሚያውቅ መሆኑን (2) ትንቢትን እንደ ጥንቈላ መጠቀሙንና (3) የተምታታበት ቢሆንም እንኳ፣ ለእግዚአብሔር ነቢይ ያለውን አክብሮት ነው:: *በዚህ ሕዝብ ላይ እንደምነግሥ የነገረኝ፤* 11፥29-39 ይመ::

14፥3 *ዐሥር እንጀራ፤* አንድ ተራ ገበሬ የሚሰጠው ስጦታ እንጂ (በ1ሳሙ 9፥7-8 ላይ ሳኦል እንዳደረገው)፣ አንድ ንጉሥ የሚሰጠው ስጦታ አይደለም (2ነገ 8፥7-9 ይመ)::

14፥5 *እግዚአብሔር ግን ለአኪያ...ነገረው፤* በመለኮታዊ መገለጥ፣ ወዲያውኑ ስለሚደርስ ነገር የተነገረውን በተመለከተ 1ሳሙ 9፥15-17፤ 2ነገ 6፥32 ይመ::

14፥6 *የኢዮርብዓም ሚስት ሆይ ግቢ፤* አኪያ የሴትዮዋን ማንነትና ለምንስ እንደ መጣች ለይቶ ማወቁ፣ የሚናገረው መልእክት በእርግጥ የእግዚአብሔር ቃል መሆኑን ያረጋግጣል::

14፥7-8 *አንሥቼ...መሪ አደረግሁህ...መንግሥቱን ቀድጄ፤* እነዚህ ሐረጎች እግዚአብሔር ለኢዮርብዓም ያደረገለትን በጎነት ሁሉ እንዲያስታውስ የሚያደርጉ ናቸው (11፥26:30-38 ይመ)::

14፥8 *እንደ ባሪያዬ እንደ ዳዊት አልሆንህም፤* ኢዮርብዓም እግዚአብሔር ላደረገለት በጎነት ቀና ምላሽ ካለመስጠቱም በላይ፣ ንጉሥ እንደሚሆን አኪያ በነገረው ጊዜ (11፥38 ይመ)፣ ተግቶ እንዲጠብቅ የነገረውን መመሪያ ችላ አለ::

14፥9 *ከአንተ በፊት ከነበሩት ሁሉ፤* ኢዮርብዓም የሰሜኑን መንግሥት ሕዝብ ጣዖት አምላኪ እንዲሆን በማድረጉ፣ የእርሱ ክፋት ከሳኦል፣ ከዳዊትና ከሰሎሞን እጅግ የሚበልጥ ነው:: *ሌሎች አማልክትን፤* የ12፥28:30 ማብ ይመ::

14፥10 *ባሪያም ይሁን ነጻ ዜጋ፤* ማንም ሳይቀር ሁሉም ለማ

12“እንግዲህ አንቺም ወደ ቤትሽ ሂጂ፤
የምትኖሪበትን ከተማ እግርሽ እንደ ረገጠ፣
ልጁ ይሞታል፤ 13እስራኤልም ሁሉ አልቅ
ሰው ይቀብሩታል። የእስራኤል ስምባክ *እግ
ዚአብሔር* ከኢዮርብዓም ቤት ሁሉ መል
ካም ነገር ያገኘበት እርሱ ብቻ ስለ ሆነ፣
በወግ በማዕረግ የሚቀበር እርሱ ብቻ ነው።
14“ከዚህም በላይ፣ *እግዚአብሔር* የኢዮር
ብዓምን ቤተ ሰብ የሚያስወግድ ንጉሥ በእ
ስራኤል ላይ ለራሱ ያስነሣል፤ ይህም ዛሬ፣
አሁኑኑ ይሆናል።[ቸ] 15*እግዚአብሔር* እስራኤ
ልን በውሃ ውስጥ እንደሚንቀጠቀጥ ሸንበቆ
ያንቀጠቅጠዋል፤ የአሼራን ምስል ዐምድ[ገ]
በመሥራት *እግዚአብሔርን* ለቍጣ ያነሣ
ሡት ስለ ሆነ፣ *እግዚአብሔር* ለቀድሞ አባ
ቶቻቸው ከሰጣቸው ከዚህች ከመልካሚቱ
ምድር እስራኤልን ይነቅላቸዋል፤ ከወንዙም
ማዶ[ነ] ይበትናቸዋል። 16ኢዮርብዓም ኀጢአት
ሠርቶ፣ እስራኤልንም እንዲሠሩ በማድረጉ፣
*እግዚአብሔር* እስራኤልን ይተዋቸዋል።
17የኢዮርብዓም ሚስትም ተነሥታ ወደ
ቴርሳ ሄደች፤ የቤቱን መድረክ ወዲያው
እንደ ተራመደች ልጁ ሞተ፤ 18ከዚያም
ቀበሩት፤ *እግዚአብሔር* በባሪያው በአኪያ
አማካይነት እንደ ተናገረ፣ እስራኤል ሁሉ
አለቀሱለት።
19የቀረው የኢዮርብዓም ታሪክ፣ ያደረገው
ጦርነትና አገዛዙም ሁሉ በእስራኤል ነገሥ
ታት ታሪክ ተጽፎአል። 20እርሱም ሃያ ሁለት
ዓመት ነግሦ ከአባቶቹ ጋር አንቀላፋ፤ ልጁ
ናዳብም በእግሩ ተተክቶ ነገሠ።

14፥13 .2ዜና 12፥12፤19፥3
14፥15 ዘዳ12፥3፤ 29፥28፤2ዜና7፥20፤ ኤር44፥3
14፥16 1ነገ12፥30፤ 15፥26
14፥17 ኢሱ12፥24፤ 1ነገ15፥33
14፥21 1ነገ11፥1
14፥22 ዘዳ32፥21፤ 2ነገ17፥19፤2ዜና12፥1፤መዝ78፥58፤ኤር 44፥3፤1ቆሮ10፥22
14፥23 ዘፀ23፥24፤ ዘዳ12፥2:3፤16፥22፤ ሕዝ6፥13፤ሆሴ10፥1፤
14፥24 ዘዳ23፥17፤ 1ነገ11፥5-7፤2ነገ21፥2፤ዕዝ9፥11፤ምሳ 21፥27፤ ኢሳ1፥13፤ ኤር16፥18፤32፥35፤ 44፥4

## የይሁዳ ንጉሥ ሮብዓም

14፥21:25-31 ተጓ ምብ - 2ዜና 12፥9-16

21የሰሎሞን ልጅ ሮብዓም በይሁዳ ነገሠ፤
በነገሠም ጊዜ ዕድሜው አርባ አንድ ዓመት
ነበር፤ እርሱም *እግዚአብሔር* ለስሙ መጠ
ሪያ እንድትሆን ከእስራኤል ነገድ ሁሉ በመ
ረጣት በኢየሩሳሌም ዐሥራ ሰባት ዓመት ገዛ።
እናቱ ናዕማ የተባለች አሞናዊት ነበረች።
22ይሁዳ *በእግዚአብሔር* ፊት ክፉ ነገር
አደረገ፤ ከአባቶቻቸው ይልቅ እነርሱ በሠሩት
ኀጢአት ይበልጥ የቅናት ቍጣውን አነሣሡ፤
23እንዲሁም በእያንዳንዱ ኰረብታና በየት
ልልቁ ዛፍ ጥላ ሥር የማምለኪያ ኰረብ
ቶችን አዕማደ ባዖታት፣ የአሼራን ምስል
ዐምድ ለራሳቸው አቆሙ። 24ከዚያም ይልቅ፣
የቤተ ጣዖት ወንደቃዎች በምድሪቱ ላይ
ነበሩ፤ *እግዚአብሔር* ከእስራኤላውያን ፊት
አሳዶ ያስወጣቸው አሕዛብ የፈጸሙትን አስ
ጸያፊ ድርጊት ሁሉ እነዚህም ፈጸሙ።

[ቸ]14 በዕብራይስጡ የዚህ ዐረፍተ ነገር ትርጒም በትክክል አይታ ወቅም
[ገ]15 በዚህም ሆነ በሌሎቹም የመጽሐፈ ነገሥት ቀዳማዊ ክፍሎች፣ የአሼራ ጣዖት አምላክ ምስል ነው
[ነ]15 የኤፍራጥስ ወንዝ ነው

ለት ነው (21፥21፤ 2ነገ 9፥8፤ 14፥26 ይመ)።

14፥11 *በባላገር የምተውን...የሰማይ አሞሮች ይበሉታል፤* የ16፥4 ማብ ይመ። በዘዳ 28፥26 የተጠቀሰው የኪዳን ርግማን በኢዮርብዓም ወንዶች ልጆች ሁሉ ላይ ስለሚደርስ፣ ማንኛቸውም ቢሆኑ ክብር ባለው ሁኔታ አይቀበሩም።

14፥12 *ልጁ፤* በዕብራይስጥ ይህ ቃል ሰፊ የዕድሜ ክልልን የሚያካትት ነው። የሮብዓም ወጣት አማካሪዎችም ይጠሩ የነበሩት በዚሁ ቃል ነው (12፥8 እና ማብ ይመ)። *ይሞታል፤* የአብያ ሞት ለኢዮርብዓምና ለሚስቱ ከባድ ሐዘን የሚያስከትል ቢሆንም፣ ለልዑሉ ግን የእግዚአብሔር ምሕረት ነበር፤ ይኸውም በአባቱ ቤት የሚደርሰውን ውርደትና ሥቃይ (ኢሳ 57፥1-2 ይመ) ከማየት ስለሚያድነው ነው።

14፥13 *እስራኤልም ሁሉ አልቅሰው ይቀብሩታል፤* ምናልባት አብያ አልጋ ወራሽ እንደሚሆን፣ በሕዝቡም ዘንድ እንደሚወደድ የሚያመለክት ሊሆን ይችላል። *የሚቀበር፤* ከኢዮርብዓም ልጆች በክብር የሚቀበር እሱ ብቻ ነው።

14፥14 *የኢዮርብዓምን ቤተ ሰብ የሚያስወግድ ንጉሥ፤* አኪያ፣ ከኢዮርብዓም ልጅ ከናዳብ አጭር ዘመነ መንግሥት (15፥25-26) በኋላ፣ የሚሆነውን የባአስን ዐመፅ (15፥27-16፥7) አስመልክቶ የተናገረው ነው።

14፥15 *በውሃ ውስጥ እንደሚንቀጠቀጥ ሸምበቆ፤* በሰሜኑ መንግሥት ንጉሣዊ ቤተ ሰብ ዘንድ ንጉሣዊ ሥልጣን እንደማይጸና አለመረጋጋት የተነሣ ግድያና ዐመፅ እየተስፋፉ እንደሚሄድ የሚያመለክት አባባል ነው (15፥27-28፤ 16፥16፤ 2ነገ 9፥24፤ 15፥10:14:25:30 ይመ)። *የአሼራን ምስል ዐምድ፤* ኢዮርብዓም ከወርቅ የተሠራ የበሬ ምስልን ማምለኩ፣ ሌሎችንም የከነዓናውያንን የሃይማኖት ልማዶች ለመከተል እንደሚገፋፋው፣ አኪያ ተገንዝቦ ነበር። አሼራ የምትባለው የጣዖት አምላክ የበኣል ሚስት እንደ ሆነች ይታመናል (ከመሳ 3፥7፤ ከ2ነገ 23፥4 ጋር ያነጻጽሩ)። *እስራኤልን ይነቅላቸዋል፤* ቃል ኪዳንን ካለመጠበቃቸው (ካለማክበር) የተነሣ ከሚደርሱባቸው በዘዳግም ከተዘረዘሩት ርግማኖች ውስጥ ከፍተኛው፣ የእግዚአብሔር ሕዝብ ከተስፋዪቱ ምድር በምርኮ መጋዝ ነው (ዘዳ 28፥63-64፤ 29፥25-28)።

14፥16 *ኢዮርብዓም ኀጢአት ሠርቶ፤* 12፥26-33፤ 13፥33-34 ይመ። *እስራኤልንም እንዲሠሩ በማድረጉ፤* በአንደኛና በሁለተኛ ነገሥት ውስጥ ተደጋግሞ የተነገረ ሐረግ ነው (15፥26፤ 16፥2:13:19:26)።

14፥17 *ቴርሳ፤ የምሪ ሰማርያን ገዝቶ ዋና ከተማ አድርጎ* እስከ ገነባበት ጊዜ ድረስ (16፥2)፣ የእስራኤል ነገሥታት ዋና ከተማ ነበረች። ከሴኬም በስተ ሰሜን ዐሥራ አንድ ኪሎ ሜትር ያህል ርቃ የምትገኝ ሲሆን፣ ቴልአል ፋራ ተብላ የምትጠራው ከተማ ሳትሆን አትቀርም (የማሕ 6፥4 ማብ ይመ)።

14፥19 *ያደረገው ጦርነትና፤* ቍ 30፤ 15፥6፤ 2ዜና 13፥2-20 ይመ። *በእስራኤል ነገሥታት ታሪክ፤* የሰሜኑን ነገሥታት ዘመነ መንግሥት በተመለከተ የተጻፈ ታሪክ ነው፤ የአንደኛና የሁለተኛ ነገሥት ጸሐፊም የተጠቀመው ከዚሁ ጽሑፍ ሲሆን፣ ስለ እስራኤል ነገሥታት ዘመነ መንግሥት በዚህ የታሪክ ጽሑፍ በሰፋት ተጽፎ ይገኛል። ይህ የታሪክ ጽሑፍ ከነገሥት መጻሕፍት በኋላ የተጻፈውን የይሁዳን ነገሥታት ዘመነ መንግሥት በተመለከተ፣ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የምናገኘው የአንደኛና የሁለተኛ ዜና መጻሕፍት አይደለም (ከመግቢያው ላይ “ጸሐፊው፣ የጽሑፉ ምንጭና የተጻፈበት ዘመን” የሚለውን ይመ)።

14፥20 *ሃያ ሁለት ዓመት፤* ከ930-909 ዓ.ቅ.ክ. ማለት ነው። *ከአባቶቹ ጋር አንቀላፋ፤* የ1፥21 ማብ ይመ። *ናዳብም፤* 15፥25-32 ይመ።

14፥21 *ዕድሜው አርባ አንድ ዓመት፤* ሮብዓም የተወለደው ዳዊት ከመሞቱ ጥቂት ቀደም ብሎ ነው (11፥42 ይመ፣ እንዲሁም የ2፥24 ማብ ይመ)። *እግዚአብሔር ለስሙ መጠሪያ እንድትሆን...በመረጣት፤* 9፥3፤ መዝ 132፥13 ይመ።

14፥22 *ይሁዳ በእግዚአብሔር ፊት ክፉ ነገር አደረገ፤* በ2ዜና 11-12 ላይ ስለ ሮብዓም ዘመነ መንግሥት ሰፋ ባለ ሁኔታ ተገልጾአል። ከሰሜኑ መንግሥት ወደ ይሁዳ የፈለሱት ካህናትና ሌዋውያን፣ በሮብዓም ዘመነ መንግሥት ለመጀመሪያው ሦስት ዓመታት (12፥24፤ 2ዜና 11፥17 ይመ)፣ አገሪቱ የዳዊትንና የሰሎሞንን መንገድ እንድትከተል አድርገው ነበር። ወደ ኋላ ባሉት ዓመታት ግን፣ ሮብዓምና የይሁዳ ሕዝብ ፊታቸውን ከእግዚአብሔር መለሱ (2ዜና 12፥1)።

14፥23 *የማምለኪያ ኰረብቶችን፤ አዕማደ ጣዖታት፤* የ3፥2 ማብ ይመ። ከመሠዊያዎች ቀጥለው የሚገኙ፣ ሃይማኖታዊ ተፈላጊነት የነበራቸው የድንጋይ ዐምዶች ናቸው። እንደነዚህ ያሉትን ዐምዶች መጠቀም በከነዓናውያን ዘንድ የተለመደ ቢሆንም፣ በሙሴ ሕግ መሠረት ለእስራኤላውያን በግልጽ የተከለከለ ነበር (ዘፀ 23፥24፤ ዘሌ 26፥1፤ ዘዳ 16፥21-22)። የድንጋይ ዐምዶችን የሚጠቀሙት አማልክትን ለመወከል ነበር (2ነገ 3፥2)። የዐምደ ጣዖትን አጠቃቀም በተመለከተ ዘፍ 28፥18፤ 31፥45፤ ዘፀ 24፥4 ይመ። *የአሼራን ምስል ዐምድ፤* የቍ 15 ማብ ይመ።

## የእስራኤልና የይሁዳ ነገሥታት በጊዜ ቅደም ተከተል

| | የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል | ነገሥታት | በተመሳሳይ ጊዜ የገዛ ንጉሥ | የንግሥና ዘመን | | ዘመን |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 1. | 1ነገ12÷24፤ 14÷21-30 | ሮብዓም (ይሁዳ) | | 17 ዓመት | | 930-913 |
| 2. | 1ነገ 12÷25-14÷20 | ቀዳማዊ ኢዮርዓም (እስራኤል) | | 22 ዓመት | | 930-909 |
| 3. | 1ነገ 15÷1-8 | አብያ (ይሁዳ) | ከኢዮርብዓም በ20ኛ ዓመት | 3 ዓመት | | 913-910 |
| 4. | 1ነገ 15÷9-24 | አሳ (ይሁዳ) | ከኢዮርብዓም በ18ኛ ዓመት | 41 ዓመት | | 910-869 |
| 5. | 1ነገ 15÷25-31 | ናዳብ (እስራኤል) | ከአሳ በ2ኛ ዓመት | 2 ዓመት | | 909-908 |
| 6. | 1ነገ 15÷32-16÷1 | ባእስ (እስራኤል) | ከአሳ በ3ኛ ዓመት | 24 ዓመት | | 908-886 |
| 7. | 1ነገ 16÷3-14 | ኤላ (እስራኤል) | ከአሳ በ26ኛ ዓመት | 2 ዓመት | | 886-885 |
| 8. | 1ነገ 16÷15-20 | ዘምሪ (እስራኤል) | ከአሳ በ27ኛ ዓመት | 7 ዓመት | | 885 |
| 9. | 1ነገ 16÷21-22 | ታምኒ (እስራኤል) | | | ከዘንበሪ ጋር | 885-880 |
| 10. | 1ነገ 16÷23-28 | ዖምሪ (እስራኤል) | ከአሳ በ27ኛ ዓመት<br>ከአሳ በ31ኛ ዓመት | 12 ዓመት | በሕዝቡ ንጉሥ የተደረገ<br>ከታምኒ ጋር የተደራረበ<br>በግሃድ የነገሠበት 11<br>ለብቻው መግሥ የጀመረበት | 885<br>885-880<br>885-874<br>880 |
| 11. | 1ነገ 16÷29-22÷40 | አክዓብ (እስራኤል) | ከአሳ በ38ኛ ዓመት | 22 ዓመት | በገሃድ የነገሠበት 21 ዓመት | 874-853 |
| 12. | 1ነገ 22÷41-50 | ኢዮሣፍጥ (ይሁዳ) | ከአክዓብ በ4ኛ ዓመት | 25 ዓመት | ከአሳ ጋር የተደራረበ<br>በገሃድ የነገሠበት<br>ለብቻው መንገሥ የጀመረበት<br>ኢዮርብዓም በውክልና የነገሠበት | 872-869<br>872-848<br>869<br>853-848 |
| 13. | 1ነገ 22÷51-2ነገ 1÷18 | አካዝያስ (እስራኤል) | ከኢዮሣፍጥ በ17ኛ ዓመት | 2 ዓመት | በገሃድ የነገሠበት | 853-852 |
| 14. | 2ነገ 1÷17፤ 3÷1-8÷15 | ኢዮራም (እስራኤል) | ከኢዮራም በ2ኛ ዓመት<br>ከኢዮሣፍጥ በ18ኛ ዓመት | 12 ዓመት | በገሃድ የነገሠበት 11 ዓመት | 852<br>852-841 |
| 15. | 1ነገ 8÷16-24 | ኢዮራም (ይሁዳ) | ከኢዮራም በ5ኛ ዓመት | 8 ዓመት | ለብቻው መንገሥ የጀመረበት<br>በገሃድ የነገሠበት 7 ዓመት | 848<br>848-841 |
| 16. | 2ነገ 8÷25-29 | አካዝያስ (ይሁዳ) | ከኢዮራም በ12ኛ ዓመት | 1 ዓመት | ዙፋን ላይ ሳይቀመጥ የገዛበት<br>ዙፋን ላይ የተቀመጠበት ዓመት | 841<br>841 |
| 17. | 2ነገ 9÷30-10÷36 | ኢዩ (እስራኤል) | | 28 ዓመት | | 841-814 |
| 18. | 2ነገ 11 | ጎቶልያ (ይሁዳ) | | 7 ዓመት | | 841-835 |
| 19. | 2ነገ 12 | ኢዮአስ (ይሁዳ) | ከኢዩ በ7ኛ ዓመት | 40 ዓመት | | 835-796 |
| 20. | 2ነገ 13÷1-9 | ኢዮአካዝ (እስራ ኤል) | ከኢዮአስ በ23ኛ ዓመት | 17 ዓመት | | 814-798 |
| 21. | 2ነገ 13÷10-25 | ዮአስ (እስራኤል) | ከኢዮአስ በ37ኛ | 16 ዓመት | | 798-782 |

| | የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል | ነገሥታት | በተመሳሳይ ጊዜ የገዛ ንጉሥ | የንግሥና ዘመን | | ዘመን |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 22. | 2ነገ 14፥1-22 | አሜስያስ (ይሁዳ) | ከኢዮአስ በ2ኛ ዓመት | 29 ዓመት | ከአዛርያስ ጋር የተደራረበ | 796-767<br>792-767 |
| 23. | 2ነገ 14፥23-29 | ዳግማዊ ኢዮርብዓም (እስራኤል) | ከአሜስያስ በ15ኛ ዓመት | 41 ዓመት | ከኢዮስያስ ጋር የተደራረበ<br>በአጠቃላይ የነገሠበት<br>ለብቻው መንግሥ የጀመረበት | 793-782<br>793-753<br>782 |
| 24. | 2ነገ 15፥1-7 | ዓዛርያስ (ይሁዳ) | ከኢዮርብዓም በ27ኛ ዓመት | 52 ዓመት | ከአሜስያስ ጋር የተደራረበ<br>በአጠቃላይ የነገሠበት<br>ለብቻው መንግሥ የጀመረበት | 792-767<br>792-740<br>767 |
| 25. | 2ነገ 15፥8-12 | ዘካርያ (እስራኤል | ከዘካርያስ በ38ኛ ዓመት | 6 ወር | | 753 |
| 26. | 2ነገ 15፥13-15 | ሰሎም (እስራኤል) | ከዓዛርያስ በ39ኛ ዓመት | 1 ወር | | 752 |
| 27. | 2ነገ 15፥16-22 | ምናሔም (እስራኤል) | ከዓዛርያስ በ39ኛ ዓመት | 10 ዓመት | በሰማርያ የነገሠ | 752-742 |
| 28. | 2ነገ 15፥23-26 | ፋቂስያስ (እስራኤል) | ከዓዛርያስ በ50ኛ ዓመት | 2 ዓመት | | 742-740 |
| 29. | 2ነገ 15፥27-31 | ፋቁሔ (እስራኤል) | ከዓዛርያስ በ52ኛ ዓመት | 20 ዓመት | በገለዓድ የተደራረቡ ዓመታት<br>በአጠቃላይ የነገሠበት<br>ለብቻው መንግሥ የጀመረበት ዘመን | 752-740<br>752-730<br>740 |
| 30. | 2ነገ 15፥32-38<br>2ነገ 15፥30 | ኢዮአታም (ይሁዳ) | ከፋቁሔ በ2ኛ ዓመት | 16 ዓመት | ከዓዛርያስ ጋር የተወከለበት<br>በገሃድ የነገሠበት<br>እስከ 20ኛው ዓመት የነገሠበት<br>በአንድ ላይ የተወከለበት ጅማሬ | 750-740<br>750-735<br>750-732<br>750 |
| 31. | 2ነገ 16 | አካዝ (ይሁዳ) | ከፋቁሔ በ17ኛ ዓመት | 16 ዓመት | በአጠቃላይ የነገሠበት<br>ከኢዮአታም በ20ኛ ዓመት | 735-715<br>735<br>732-715 |
| 32. | 2ነገ 15፥30፤ 17 | ሆሴዕ (እስራኤል) | ከአካዝ በ12ኛ ዓመት | 9 ዓመት | በኢዮአታም 20ኛ ዓመት | 732<br>732-722 |
| 33. | 2ነገ 18፥1-20፥21 | ሕዝቅያስ (እስራኤል) | ከሆሴዕ በ3ኛው ዓመት | 29 ዓመት | | 715-686 |
| 34. | 2ነገ 21፥1-18 | ምናሴ (ይሁዳ) | | 55 ዓመት | ከሕዝቅያስ ጋር የነገሠበት<br>በአጠቃላይ የነገሠበት | 697-686<br>697-642 |
| 35. | 2ነገ 21፥19-26 | አሞን (ይሁዳ) | | 2 ዓመት | | 642-640 |
| 36. | 2ነገ 22፥1 23፥30 | ኢዮስያስ (ይሁዳ | | 31 ዓመት | | 640-609 |
| 37. | 2ነገ 23፥31-33 | ኢዮአክስ (ይሁዳ) | | 3 ወር | | 609 |
| 38. | 2ነገ 23፥34-27፥7 | ኤልያቄም (ይሁዳ) | | 11 ዓመት | | 609-598 |
| 39. | 2ነገ 24፥8-17 | ዮአኪን (ይሁዳ) | | 3 ወር | | 598-597 |
| 40. | 2ነገ 24፥18-25፥26 | ሴዴቅያስ (ይሁዳ) | | 11 ዓመት | | 597-586 |

25ሮብዓም በነገሠ በአምስተኛው ዓመት
የግብፅ ንጉሥ ሺሻቅ በኢየሩሳሌም ላይ አደጋ
ጣለ፤ 26የእግዚአብሔርን ቤተ መቅደስና የቤተ
መንግሥቱን ሀብት ወሰደ፤ ሰሎሞን ያሠራ
ቸው የወርቅ ጋሻዎች እንኳን ሳይቀሩ ሁሉ
ንም ነገር ኢጋዘ። 27ስለዚህ ንጉሥ ሮብዓም እነ
ዚህን ለመተካት ሲል፣ የናስ ጋሻዎች አሠ
ርቶ የቤተ መንግሥቱን በር የሚጠብቁት
ዘበኞች አዛዦች እንዲይዙ አደረገ። 28ንጉሡ
ወደ እግዚአብሔር ቤተ መቅደስ በሚሄድ
በት ጊዜ ሁሉ፣ ዘቦቹ ጋሻዎቹን ያነግባሉ፤
ከዚያም በዘብ ጥበቃው ክፍል መልሰው
ያስቀምጡ ነበር።
29የቀረው የሮብዓም አገዛዝ፣ ያደረገውም
ሁሉ በይሁዳ ነገሥታት ታሪክ ተጽፎ የሚ
ገኝ አይደለምን? 30በሮብዓምና በኢዮርብዓም
መካከል ያላቋረጠ ጦርነት ተደርጎ ነበር።
31ሮብዓምም ከአባቶቹ ጋር አንቀላፋ፤ እነ
ርሱ በተቀበሩበትም በዳዊት ከተማ ተቀ
በረ። እናቱ ናዓማ የተባለች አሞናዊት ነበ
ረች። ልጁ አብያምፕ በእግሩ ተተክቶ ነገሠ።

## የይሁዳ ንጉሥ አብያ

15፥12:6-8 ተጓ ምብ - 2ዜና 13፥1-2:22-14፥1

15የናባጥ ልጅ ኢዮርብዓም በነገሠ በዐ
ሥራ ስምንተኛው ዓመት አብያኦ
በይሁዳ ነገሠ፤ 2በኢየሩሳሌም ሆኖ ሦስት
ዓመት ገዛ፤ እናቱ መዓካ የተባለች የአቤሴ
ሎም ልጅ ነበረች።
3እርሱም አባቱ ከእርሱ በፊት የሠራውን
ኀጢአት ሁሉ ሠራ፤ እንደ አባቱ እንደ
ዳዊትም በፍጹም ልቡ በታማኝነት ለእግዚ
አብሔር አልተገዛም። 4ነገር ግን ከእርሱ
ቀጥሎ እንዲነግሥና ኢየሩሳሌምን እንዲያ
ጸናት፣ ስምባክ እግዚአብሔር ስለ ዳዊት
ሲል በኢየሩሳሌም መብራት ሰጠው። 5ዳዊት
በኬጢያዊው በኦርዮ ላይ ካደረሰው በደል
በቀር፣ በእግዚአብሔር ፊት ትክክል የሆነ
ውን ነገር አድርጓል፤ በሕይወት ዘመኑም
ሁሉ ከእግዚአብሔር ትእዛዝ ፈቀቅ ያለበት
ጊዜ አልነበረም።
6አብያምከ በሕይወት በነበረበት ዘመን ሁሉ
በሮብዓምና በኢዮርብዓም መካከል ጦርነት
ነበር። 7ሌላው አብያ በዘመኑ የፈጸመውና
ያደረገው ሁሉ፣ በይሁዳ ነገሥታት ታሪክ
ተጽፎ የሚገኝ አይደለምን? በአብያና በኢ
ዮርብዓም መካከልም ጦርነት ነበር። 8አብ
ያም ከአባቶቹ ጋር አንቀላፋ፤ በዳዊትም ከተማ
ተቀበረ። ልጁም አሳ በእግሩ ተተክቶ ነገሠ።

## የይሁዳ ንጉሥ አሳ

15፥9-22 ተጓ ምብ - 2ዜና 14፥2-3፤ 15፥16-16፥6
15፥23-24 ተጓ ምብ - 2ዜና 16፥11-17፥1

9የእስራኤል ንጉሥ ኢዮርብዓም በነገሠ
በሃያኛው ዓመት፣ አሳ የይሁዳ ንጉሥ ሆነ፤
10በኢየሩሳሌምም አርባ አንድ ዓመት ነገሠ፤
አያቱ መዓካ ትባላለች፤ እርሷም የአቤሴ
ሎም ልጅ ነበረች።
11አሳ አባቱ ዳዊት እንዳደረገው ሁሉ፣
በእግዚአብሔር ፊት መልካም የሆነውን
ነገር አደረገ። 12የቤተ ጣዖት ወንደቃዎችን
ከምድሪቱ አባረረ፤ አባቶቹ የሠሯቸውን
ጣዖታት ሁሉ አስወገደ። 13አስጸያፊውን የአ
ሼራ ምስል ዐምድ በማቆሟ፣ አያቱን መዓካን

14፥25 2ዜና12፥2
14፥26 2ሳሙ8፥7፤ 1ነገ15፥15:18
14፥27 1ነገ11፥5
14፥30 2ሳሙ3፥1፤ 1ነገ12፥21
14፥31 1ነገ11፥1
15፥2 ቍ10:13፤ 2ዜና11፥20
15፥3 1ነገ8፥61
15፥4 2ሳሙ21፥17
15፥5 ዘዳ5፥32፤ 2ሳሙ11፥2-27፤ 12፥9፤1ነገ9፥4
15፥6 ቍ16:32፤ 1ነገ12፥21፤2ዜና 16፥9
15፥10 ቍ2
15፥11 1ነገ9፥4
15፥12 ነገ14፥24፤ 2ዜና15፥8
15፥13 ቍ2፤ዘፀ 34፥13፤1ነገ12፥19

ፕ31 አንዳንድ የዕብራይስጥና የሰብዓ ሊቃናት ትርጒሞች ከዚህ ጋር ይስማማሉ፤ አብዛኞቹ የዕብራይስጥ ትርጒሞች ግን፣ *አቢ ጃም* ይላሉ

ኦ1 በዚህ ስፍራና በቍ 7 እና 8 ላይ አንዳንድ የዕብራይስጥና የሰብዓ ሊቃናት ትርጒሞች ከዚህ ጋር ይስማማሉ፤ አብዛኞቹ የዕብርይስጥ ትርጒሞች ግን፤ *አቢጃም* ይላሉ

ከ6 አብዛኞቹ የዕብራይስጥ ቅጆች ከዚህ ጋር ይስማማሉ አንዳንድ የዕብራይስጥና የሱርስት ትርጒሞች ግን፣ *አቢጃም* ይላሉ

14፥24 *የቤተ ጣዖት ወንደቃዎች፤* ግብረ ሰዶም መፈጸም የከነዓናውያን ልማድ ነበር። እስራኤላውያን፣ እንዲህ ዐይነቱን አስነዋሪ ተግባር እንዳይፈጽሙ ሙሴ አስጠንቅቆአቸዋል (ዘዳ 23፥17-18፤ 1ነገ 15፥12፤ 2ነገ 23፥7፤ ሆሴ 4፥14 ይመ)።

14፥25 *ሮብዓም በነገሠ በአምስተኛው ዓመት፤* ዓ.ቅ.ክ. በ926 ማለት ነው። *ሺሻቅ፤* የ3፥1፤ 11፥40 ማብ ይመ። *በኢየሩ ሳሌም ላይ አደጋ ጣለ፤* በ2ዜና 12፥2-4 ላይ የሺሻቅ ወረራ ምን እንደሚመስል በግልጽ ተጠቅሶአል። ይህም ቴቤስ በሚገኘው በአሙን ቤተ ጣዖት ግድግዳ ላይ፣ ሺሻቅ የዘረፋቸው የይሁዳና የሰሜኑ መንግሥት የነበሩት ከተሞች ዝርዝር በሚያሳየው የድል ጽሑፍ ላይ ተገልጾአል። ድንገት ሳይታሰብ ይደርሳል ተብሎ ከሚጠበቀው ወረራ ሥጋት የተነሣ፣ በይሁዳ ጊዜያዊ መሻሻል (ለውጥ) ተደርጎ እንደ ነበረ በ2ዜና 12፥5-8 ላይ ተመልክቶአል።

14፥26 *ሰሎሞን ያሠራቸው የወርቅ ጋሻዎች፤* 10፥16-17 ይመ።

14፥27 *የናስ ጋሻዎች፤* ሰሎሞን የወርቅ ጋሻዎችን ለማሠራት ካዋለው ሀብት ጋር ዋጋቸው አይመጣጠንም (10፥21:23:27 ይመ)።

14፥29 *በይሁዳ ነገሥታት ታሪክ፤* ከሰሜኑ ነገሥታት ታሪክ ጋር የሚመሳሰል፣ ስለ ይሁዳ ነገሥታት ዘመነ መንግሥት የተጻ ፈው ታሪክ ነው (የቍ 19 ማብ ይመ)፤ በመግቢያው ላይ ጸሓ ፊው፣ የጽሑፉ ምንጭና የተጻፈበት ዘመን የሚለውን ይመ)።

14፥30 *ያላቋረጠ ጦርነት፤* የቍ 19፤ 12፥24 ማብ ይመ።

14፥31 *ከአባቶቹ ጋር አንቀላፋ፤* የ1፥21 ማብ ይመ።

15፥1 *ኢዮርብዓም በነገሠ በዐሥራ ስምንተኛው ዓመት፤* በሰሜኑ ነገሥታትና በይሁዳ ነገሥታት ዘመነ መንግሥት ያለ ውን የጊዜ ሁኔታ አስመልክቶ፣ በአንደኛና በሁለተኛ ነገሥት፣ ከተጠቀሱት ብዙ ቦታዎች መካከል ይህ የመጀመሪያው ነው (ቍ 9:25:33፤ 16፥8:15:29 ይመ)። *አብያ፤* የ14፥1 ማብ ይመ። ሮብዓምና ኢዮርብዓም ሁለቱም በዚህ ስም የሚጠራ ልጅ ነበራቸው።

15፥2 *ሦስት ዓመት፤* በዓ.ቅ.ክ. ከ913-910 ማለት ነው። *መዓካ ... የአቤሴሎም ልጅ፤* የአብያ እናት፣ የጊብዓ ሰው የኡር ኤል ልጅ ስለ መሆኗ በ2ዜና 13፥2 ላይ ተጠቅሶአል። መዓካ፣ የአቤሴሎም ልጅ ትዕማር (2ሳሙ 14፥27 ይመ)፣ ኡርኤልን አግ ብታ የወለደቻት፣ የአቤሴሎም የልጅ ልጅ ልትሆን ትችላለች። የአቤሴሎም እናትም መዓካ ተብላ ትጠራ ነበር (2ሳሙ 3፥3)።

15፥3 *አባቱ ከእርሱ በፊት የሠራውን ኀጢአት፤* 14፥22-24 ይመ። *እንደ አባቱ እንደ ዳዊትም በፍጹም ልቡ በታማኝነት ለእግዚአብሔር አልተገዛም፤* ዳዊት በከፋ ኀጢአት ቢወድቅም፣ ልቡ እግዚአብሔርን ከማገልገል ርቆ የከነዓናውያንን አማልክት አልተከተለም።

15፥4 *በኢየሩሳሌም መብራት፤* እግዚአብሔር የዳዊትን ቤት እንደማያጠፋና፣ የገባውንም ኪዳን እንደሚጠብቅ ያመለክታል (የ11፥36 ማብ ይመ)።

15፥5 *በኬጢያዊው በኦርዮ ላይ፤* 2ሳሙ 11 ይመ።

15፥6 *በሮብዓምና፤* የ12፥24 ማብ ይመ።

15፥7 *ሌላው አብያ በዘመኑ የፈጸመውና፤* 2ዜና 13 ይመ። *በይሁዳ ነገሥታት ታሪክ፤* የ14፥29 ማብ ይመ። *በአብ ያና በኢዮርብዓም መካከልም ጦርነት፤* ከቍ 6፤ 14፥30 ጋር ያነ ጻጽሩ። በአብያና በኢዮርብዓም መካከል፣ ለብዙ ጊዜ የቈየው ግጭት፣ ወደ ከፋ ጦርነት ተለውጦ፣ አብያም ኢዮርብዓምን አሸ ንፎ ቤቴልን ጭምር (2ዜና 13፥19) ብዙ ከተሞችን እንደ ወሰደ በት፣ በ2ዜና 13 ላይ ተገልጾአል።

15፥8 *ከአባቶቹ ጋር አንቀላፋ፤* የ1፥21 ማብ ይመ።

15፥9 *ኢዮርብዓም በነገሠ በሃያኛው ዓመት፤* ዓ.ቅ.ክ. 910 ማለት ነው (የ14፥20 ማብ ይመ)።

ከእቴጌነቷ ሻራት፤ ጣዖቷንም ሰባብሮ በቄ
ድሮን ሸለቆ አቃጠለው። [14]አሳ የማምለኪያ
ኮረብታዎችን ፈጽሞ ባያስወግድም እንኳ
በሕይወት ዘመኑ ሁሉ፣ ልቡ ለእግዚአብሔር
የተገዛ ነበር። [15]አባቱና እርሱ ለእግዚአብሔር
የቀደሱትን ብርና ወርቅ እንዲሁም ዕቃዎ
ችን አምጥቶ ወደ እግዚአብሔር ቤት አስገባ።
[16]አሳና የእስራኤል ንጉሥ ባኦስ ዘመነ
መንግሥታቸውን ያሳለፉት፣ እርስ በርስ
በመዋጋት ነበር። [17]የእስራኤል ንጉሥ ባኦስ
ይሁዳን ለመውጋት ወጣ፤ ከዚያም ወደ ይሁዳ
ንጉሥ ወደ አሳ ግዛት ማንም እንዳይገባና
እንዳይወጣ ለመቈጣጠር ራማን ምሽግ አድ
ርጎ ሠራት።
[18]አሳም በእግዚአብሔር ቤትና በቤተ
መንግሥቱ ግምጃ ቤት የቀረውን ብርና
ወርቅ በሙሉ ወሰደ፤ ከዚያም በታማኝ ሹማ
ምቱ እጅ በደማስቆ ይገዛ ለነበረው፣ ለጠብ
ሪሞን ልጅ፣ የአዚን የልጅ ልጅ ለሆነው
ለሶርያ ንጉሥ ለቤን ሀዳድ ላከው። [19]እንዲ
ህም አለ፤ "በአባቴና በአባትህ መካከል የስ
ምምነት ውል እንደ ነበረ ሁሉ፣ አሁንም
በእኔና በአንተ መካከል ይኑር፤ እነሆ፣ የብ
ርና የወርቅ ገጸ በረከት ልኬልሃለሁ። አሁ
ንም የእስራኤል ንጉሥ ባኦስ ወደ መጣበት

15፥14 1ነገ8፥61፤ 2ዜና14፥5፤17፥6
15፥15 2ሳሙ8፥11
15፥16 ቍ6፤ 1ነገ12፥21
15፥17 ኢሱ18፥25
15፥18 ቍ18-20፤ 1ነገ14፥26፤20፥1፤ 2ነገ6፥24፤12፥18፤ 13፥3፤16፥8፤18፥14-16፤15፤ኤር49፥27፤ ኢሳ3፥5
15፥19 ዘፀ23፥32፤ 1ነገ5፥12
15፥20 1ነገ20፥34
15፥21 ኢሱ18፥25፤ 1ነገ16፥15-17
15፥22 ቍ9፥24፤ ኢሱ11፥3፤18፥24፤ 2ነገ23፥8፤ኤር41፥9
15፥24 ማቴ1፥8

እንዲመለስ፣ ሄደህ ከእርሱ ጋር ያደረግኸ
ውን የስምምነት ውል አፍርስ።"
[20]ቤን ሀዳድም የንጉሥ አሳን ሐሳብ ተቀ
ብሎ፣ የጦር አዛዦቹን በእስራኤል ከተሞች
ላይ አዘመተ፤ ዒዮንን፣ ዳንን፣ አቤልቤት
ማዕካን እንዲሁም ንፍታሌምን ጨምሮ ጌን
ሳሬጥን በሙሉ ድል አደረገ። [21]ባኦስም ይህን
ሲሰማ፣ በራማ የጀመረውን የምሽግ ሥራ
አቁሞ ወደ ቴርሳ ተመለሰ። [22]ንጉሥ አሳ
አንድም ሰው እንዳይቀር በይሁዳ ሁሉ ዐዋጅ
አስነገረ፤ ከዚያም ሕዝቡ ባኦስ በራማ እስ
ቀምጦት የነበረውን ድንጋይና ዕንጨት አጋዘ፤
ንጉሡም በዚሁ ምጽጳንና በብንያም ውስጥ
ጌባን ሠራ።
[23]በአሳ ዘመነ መንግሥት የተከናወነው
ሌላው ነገር በሙሉ፣ ያደረገውም ሁሉና የሠ
ራቸውም ከተሞች በይሁዳ ነገሥታት ታሪክ
ተጽፈው የሚገኙ አይደሉምን? ንጉሥ አሳ
በሸመገለ ጊዜ ግን እግሮቹ ታመሙ። [24]አሳ
ከአባቶቹ ጋር አንቀላፋ፤ እነርሱ በተቀበሩ
በትም በአባቱ በዳዊት ከተማ ተቀበረ፤ ልጁ
ኢዮሣፍጥም በእግሩ ተተክቶ ነገሠ።

## የእስራኤል ንጉሥ ናዳብ

[25]በይሁዳ ንጉሥ በአሳ ዘመነ መንግሥት
በሁለተኛው ዓመት የኢዮርብዓም ልጅ ናዳብ

15፥10 *አርባ አንድ ዓመት፤* ዓ.ቅ.ክ. 910-869 ማለት ነው። *መዓካ ... የአቤሴሎም ልጅ፤* የቍ 2 ማብ ይመ።

15፥12 *የቤተ ጣዖት ወንደቃዎችን፤* የ14፥24 ማብ ይመ። *አባቶቹ የሠሯቸውን ጣዖታት ሁሉ አስወገደ፤* የ14፥23 ማብ ይመ።

15፥13 *አስጸያፊውን የአሼራ ምስል ዐምድ በማቆሟ፣* የ14፥15 ማብ ይመ መዓካ የፈጸመችው ድርጊት፣ አሳ የጀመረውን ተሐድሶ ሆን ብላ ለመቃወም ያደረገችው ሙከራ ይመስላል። *ኢያቱን መዓካን...ሻራት፤* አሳ የጀመረው ተሐድሶ ለብዙ ዓመት እንደ ቀጠለ በ2ዜና 14፥1-15፥16 ላይ ተጠቅሶአል። አሳ በመንግሥቱ መጀመሪያ ላይ፣ የአሕዛብን ጣዖታት ቢያፈርስም (2ዜና 14፥2-3)፣ በነገሠ በዐሥራ አምስተኛው ዓመት (2ዜና 15፥10)፣ በኢትዮጵያዊው ዝራ ላይ ድል እስከ ተቀዳጀበት ጊዜ ድረስ (2ዜና 14፥8-15)፣ የአዴድ ልጅ ነቢዩ ዓዛርያስ ለተናገረው መልእክት ቀና መልስ በመስጠት፣ ኪዳን ለማደስ በኢየሩሳሌም ጉባኤ አልጠራም። ከዚህ ጉባኤ በኋላ፣ አሳ፣ ኢያቱን መዓካን ጣዖት በማምለኳ (2ዜና 15፥16) ሻራት።

15፥14 *የማምለኪያ ኮረብታዎችን...ባያስወግድም፤* በዚህ ቍጥር ላይና፣ በ2ዜና 15፥17 የተጠቀሰው ሐሳብ፣ እግዚአብሔር ይመለክባቸው የነበሩትን ኮረብቶች የሚያመለክት ነው (እግዚአሔር በኮረብቶች ላይ እንደ ተመለከ የ3፥2 ማብ ይመ)። በ2ዜና 14፥3 ላይ አሳ ያስወገደው የማምለኪያ ኮረብታዎች የከነዓናውያን የአምልኮ ማዕከል የሆኑትን የማምለኪያ ኮረብታዎች ነው (2ዜና 17፥6፤ 20፥33 ይመ)። አሳ ስለ ፈጸመው መልካም ተግባር፣ ከሕዝቅያስ በፊት በነበሩ አምስት የይሁዳ ነገሥታት ታሪክም ተጠቅሶአል (ኢዮሳፍጥ፣ 22፥43፤ ኢዮአስ፣ 2ነገ 12፥3፤ አሜስያስ፣ 2ነገ 14፥4፤ አዛርያስ፣ 2ነገ 15፥4፤ ኢዮአታም፣ 2ነገ 15፥35)። *ልቡ ለእግዚአብሔር የተገዛ፤* የቍ 3 ማብ ይመ።

15፥15 *ብርና ወርቅ እንዲሁም ዕቃዎችን፤* አብያ ከኢዮርብዓም በጦርነት የዘረፋቸው ዕቃዎች ሲሆኑ (2ዜና 13)፣ እነዚህንም ዕቃዎች አሳ ከኢትዮጵያዊው ዝራ መልሶ ወስዶአቸዋል (2ዜና 14፥8-15)።

15፥16 *አሳና...ባኦስ ዘመነ መንግሥታቸውን ያሳለፉት... በመዋጋት ነበር፤* የእርስ በርስ ጦርነትን ሳይሆን፣ መንግሥታቸው ለሁለት ከተካፈሉ በኋላ፣ በመካከላቸው የተፈጠረውን የጠነከረ ጠላትነት የሚገልጽ ነው (የቍ 7፤ 12፥24፤ ማብ ይመ፤ እንዲሁም 2ዜና 15፥19 ይመ)።

15፥17 *ወደ አሳ ግዛት ማንም እንዳይገባና እንዳይወጣ፤* 2ዜና 15፥9-10 ይመ። *ራማን ምሽግ አድርጎ ሠራት፤* ራማ ከኢየሩሳሌም በስተ ሰሜን ስምንት ኪሎ ሜትር ያህል ርቃ ከቤቴል በስተ ደቡብ የምትገኝ ሲሆን፣ አብያ ከኢዮርብዓም የወሰዳቸውን ግዛቶች ባኦስ መልሶ ይዞአቸዋል (የቍ 7 ማብ ይመ፤ እንዲሁም 2ዜና 13፥19 ይመ)።

15፥18 *የቀረውን ብርና ወርቅ፤* የግብፁ ሺሻቅ ኢየሩሳሌምን በበዘበዘበት ወቅት ሳይወሰድ የቀረው ማለት ነው (14፥25 ይመ)። *አዚን፤* የደማስቆው ሬዞን ይሁን (11፥23-25 ይመ) ወይም አዲስ ሥርወ መንግሥት የመሠረተው አዚን አይታወቅም።

15፥19 *በአባቴና በአባትህ መካከል የስምምነት ውል፤* በአብያና በጠብሪሞን መካከል የተደረገውን፣ ቀደም ሲልም ያልተጠቀሰውን ስምምነት የሚያመለክት ነው። ባኦስ፣ ጠብሪሞን ከሞተ በኋላ በእርሱ እግር ከተተካው ከቤን ሀዳድ ጋር ስምምነት ማድረግ ችሎ ነበር። ከአራም ጋር የነበረውን የቀድሞ ስምምነት በማደስ ድጋፍ ካልተገኘ፣ ባኦስን ድል ማድረግ፣ ተስፋ እንደሌለው አሳ ተረዳ። ዕቅዱ የሚሳካ ቢመስልም፣ ከንቱ የሆነ ሙከራና በእግዚአብሐር ያለ መታመን በመሆኑ ነቢዩ ሐናኒ ነቅፎታል (2ዜና 16፥7-10 ይመ)። በእግዚአብሐር የተሾመ ንጉሥ፣ ስለ ህልውናው ለገባው ታማኝ በሆነ ኪዳኑን በሚጠብቅ በእግዚአብሐር ሊታመን እንጂ፣ ጠላቶቹን ሊፈራ አይገባውም (የ1ሳሙ 17፥11 ማብ ይመ)። አካዝ፣ ከእስራኤልና ሶርያ ጥቃት ባደረሱበት ጊዜ (2ነገ 16፥5-9፤ ኢሳ 7 ይመ) የአሳን መጥፎ ፈለግ በመከተል፣ የአሦርን ርዳታ ጠየቀ።

15፥20 *ንፍታሌምን፤* ቤን ሀዳድ ድል አድርጎ የያዛቸው በንፍታሌም የሚገኙ ከተሞች ተፈላጊነት ያላቸው ነበሩ፤ ምክንያቱም ከደማስቆ ወደ ምዕራብ ጢሮስና ወደ ደቡብ ምዕራብ በኢይዝራኤል ሜዳ አድርጎ በባሕር ዳርቻ አካባቢ ወደሚገኙ ሜዳዎችና ወደ ግብፅ የሚያደርስ ዋና የንግድ መንገድ በመሆኑ ነው። ከጊዜ በኋላም የአሦር ንጉሥ ሣልሳዊ ቴልጌልቴልፌልሶር ይህንኑ ቦታ ይዞ ነበር (2ነገ 15፥29)።

15፥21 *ቴርሳ፤* የ14፥17 ማብ ይመ።

15፥22 *በይሁዳ ሁሉ ዐዋጅ አስነገረ፤* አሳ ያደረገው ነገር፣ በሰሎሞን ዘመነ መንግሥት በገባርነት ይሠሩ የነበሩትን ሠራተኞች የሚያስታውስ ነው (5፥13-14፤ 11፥28)። *ምጽጳንና... ጌባን፤* ግዛቱን ወደ ደቡብ ለማስፋት ባኦስ ያለውን ዕቅድ ለመቈጣጠር፣ አሳ እነዚህን ሁለት የጠረፍ ከተሞች፣ ምሽግ አድርጎ ሠራ። ጊባ ከራማ በስተ ምሥራቅ፣ ምጽጳ ደግሞ ከራማ በስተ ደቡብ ምዕራብ ይገኙ ነበር።

15፥23 *በአሳ ዘመነ መንግሥት የተከናወነው ሌላው ነገር፤* 2ዜና 14፥2-16፥14 ይመ። *በይሁዳ ነገሥታት ታሪክ፤* የ14፥29 ማብ ይመ። *እግሮቹ ታመሙ፤* 2ዜና 16፥12 ይመ።

በእስራኤል ላይ ነገሠ፤ ሁለት ዓመትም ገዛ።
[26]እርሱም በአባቱ መንገድ በመሄድ፣ አባቱ
የሠራውንና እስራኤልም እንዲሠሩ ያደረገ
ውን ኀጢአት በመሥራት *በእግዚአብሔር*
*ፊት ክፉ* ድርጊት ፈጸመ።
[27]ናዳብና መላው እስራኤል በፍልስጥኤም
የምትገኘውን የገባቶንን ከተማ ከበው ሳሉ፣
ከይሳኮር ነገድ የተወለደው የአኪያ ልጅ
ባኦስ ዐምፆ በመነሣት ናዳብን በገባቶን ገደ
ለው። [28]ባኦስ ናዳብን የገደለውና በእግሩ
ተተክቶ የነገሠው፣ የይሁዳ ንጉሥ አሳ በነገሠ
በሦስተኛው ዓመት ነው።
[29]ወዲያውኑ እንደ ነገሠም የኢዮርብዓምን
ቤተ ሰብ በሙሉ ፈጀ። *እግዚአብሔር* በሴ
ሎናዊው ባሪያው በአኪያ በኩል እንደ ተና
ገረው፣ ከኢዮርብዓም ቤተ ሰብ አንድም
ሰው በሕይወት ሳያስቀር፣ ሁሉንም አጠፋ
ቸው፤ [30]ይህም የሆነው ኢዮርብዓም በሠራው
ኀጢአትና እስራኤልም እንዲሠሩ በማድ
ረጉ ምክንያት፣ የእስራኤል ሰምላክ *እግዚአ*
*ብሔርን* ለቍጣ በማነሣሣቱ ነው።
[31]ሌላው በናዳብ ዘመነ መንግሥት የተከ
ናወነው፣ እርሱም ያደረገው ሁሉ በእስራ
ኤል ነገሥታት ታሪክ ተጽፎ የሚገኝ አይ
ደለምን? [32]አሳና የእስራኤል ንጉሥ ባኦስ
ዘመነ መንግሥታቸውን ያሳለፉት እርስ
በርስ በመዋጋት ነበር።

**የእስራኤል ንጉሥ ባኦስ**

[33]የይሁዳ ንጉሥ አሳ በነገሠ በሦስተኛው
ዓመት የአኪያ ልጅ ባኦስ በቴርሳ ከተማ፣
በእስራኤል ሁሉ ላይ ነገሠ፤ ሃያ አራት ዓመ
ትም ገዛ። [34]በኢዮርብዓም መንገድ በመሄ
ድና እስራኤልም እንዲሠሩ ያደረገውን ኀጢ
አት በመፈጸም *በእግዚአብሔር ፊት ክፉ*
*ሥራ* ሠራ።

**16** ከዚያም *የእግዚአብሔር* ቃል በባ
ኦስ ላይ እንዲህ ሲል ወደ አናኒ
ልጅ ወደ ኢዩ መጣ፤ [2]"ከትቢያ አንሥቼ፣
የሕዝቤ የእስራኤል መሪ አደረግሁህ፤ አንተ
ግን በኢዮርብዓም መንገድ ሄድህ፤ ሕዝቤ
እስራኤል ኀጢአት እንዲሠራ፣ በኀጢአቱም
ለቍጣ እንዲያነሣሣኝ አሳሳትኸው። [3]ስለዚ
ህ ባኦስንና ቤቱን ፈጽሜ አጠፋለሁ፤ ቤትህ
ንም እንደ ናባጥ ልጅ እንደ ኢዮርብዓም
ቤት አደርገዋለሁ። [4]በከተማዪቱ ውስጥ
የሚሞቱትን የባኦስን ወገኖች ሁሉ ውሾች
ይበሏቸዋል፤ በገጠር የሚሞቱትንም ሁሉ
የሰማይ አሞሮች ይቀራመቷቸዋል።"
[5]በባኦስ ዘመነ መንግሥት የተከናወነው፣
ሌላው ያደረገው ሥራው በሙሉ በእስራኤል
ነገሥታት ታሪክ ተጽፎ የሚገኝ አይደለምን?
[6]ባኦስ፣ ከአባቶቹ ጋር አንቀላፋ፤ በቴርሳም
ተቀበረ። ልጁም ኤላ በእግሩ ተተክቶ ነገሠ።
[7]ከዚህም በቀር *የእግዚአብሔር* ቃል በነ
ቢዩ ኢዩ አማካይነት በባኦስና በቤቱ ላይ
የመጣበት ምክንያት፣ በእጁ ሥራ ያስቈጣው
ዘንድ እንደ ኢዮርብዓም ቤት ሁሉ *በእግዚ*
*አብሔር ፊት ክፉ ሥራን* ሁሉ በማድረጉና
ኢዮርብዓምን በማጥፋቱም ጭምር ነው።

**የእስራኤል ንጉሥ ኤላ**

[8]የይሁዳ ንጉሥ አሳ በነገሠ በሃያ ስድስ
ተኛው ዓመት የባኦስ ልጅ ኤላ በእስራኤል
ላይ ነገሠ፤ በቴርሳ ተቀምጦም ሁለት ዓመት
ገዛ።

15፥26 ዘኁ4፥25፤ 1ነገ12፥30
15፥27 ኢሱ19፥44፤ 1ነገ14፥14
15፥29 1ነገ13፥34
15፥30 1ነገ12፥30፤16፥26፤2ነገ3፥3፤14፥24፤15፥28፤21፥16
15፥31 1ነገ11፥41
15፥32 ቍ6
15፥33 1ነገ14፥17፤16፥6፡23፤2ነገ15፥14፤ማሕ6፥4
15፥34 ቍ26
16፥1 ቍ7፤2ዜና 16፥7፤19፥2፤20፥34
16፥2 1ሳሙ2፥8፤ 1ነገ12፥30፤14፥7፥9
16፥3 ቍ11፤ 1ነገ21፥22፤2ነገ9፥9
16፥4 ዘዳ40፥19፤ 1ነገ14፥11
16፥5 1ነገ15፥31
16፥6 1ነገ15፥33
16፥7 ቍ1፤ 1ነገ6፥11

15፥24 *ከአባቶቹ ጋር አንቀላፋ፤* የ1፥21 ማብ ይመ። *ልጁ ኢዮሳፍጥም በእግሩ ተተክቶ ነገሠ፤* ስለ ኢዮሳፍጥ ዘመነ መንግ ሥት 22፥41-50፤ 2ዜና 17፥1-21፥1 ይመ።

15፥25 *በአሳ ዘመነ መንግሥት በሁለተኛው ዓመት፤* የቍ 1 ማብ ይመ። የይሁዳ ንጉሥ የአሳ ዘመነ መንግሥት ሁለ ተኛው ዓመት፣ ለእስራኤል ንጉሥ ኢዮርብዓም ሃያ ሁለተኛና የዘመነ መንግሥቱ የመጨረሻ ዓመት ነበር (ቍ 9፤14-20 ይመ)። *ሁለት ዓመትም፣* ዓ.ቅ.ክ. 909-908 ማለት ነው።

15፥26 *የሠራውንና እስራኤልም እንዲሠሩ ያደረገውን ኀጢአት በመሥራት፤* ኢዮርብዓም ያደረገውን ኀጢአት ማለት ነው (የ14፥16 ማብ ይመ)። በኢዮርብዓም ዘመነ መንግሥት፣ የይሁዳ ንጉሥ አብያ ቤቴልን በመያዙ (የቍ 7 ማብ ይመ)፣ ባኦስ ቤቴልን መልሶ እስከ ያዘበት ጊዜ ድረስ፣ በኢዮርብዓም የተጀ መረው የጣዖት አምልኮ ወደ ሌሎች ቦታዎች መዛመቱ ግልጽ አይደለም።

15፥27 *ገባቶን፤* በኢየሩሳሌምና በኢዮጴ መካከል፣ ከጌዝር በስተ ምዕራብ ጥቂት ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ የምትገኝ በመጀ መሪያ ለዳን ነገድ ተሰጥቶ በነበረው ግዛት ውስጥ (ኢሱ 19፥43-45) የምትገኝ ከተማ ናት። ይህች የሌዋውያን ከተማ (ኢሱ 21፥23) በፍልስጥኤማውያን እጅ የወደቀችው፣ ምናልባት በመሳ ፍንት ዘመን ፍልስጥኤማውያን እየተስፋፉ በነበረበት ጊዜ ሊሆን ይችላል።

15፥28 *አሳ በነገሠ በሦስተኛው ዓመት፤* ዓ.ቅ.ክ. 908 ነው (የቍ 10 ማብ ይመ)። ባኦስ የናዳብ ሰራዊት ጦር አዛዥ ስለ ነበረ፣ ባካሄደው ዐመፅ የወታደሩን ድጋፍ ማግኘት የቻለ ይመስላል።

15፥29 *በአኪያ በኩል እንደ ተናገረው፤* 14፥10-11 ይመ።

15፥30 *ኢዮርብዓም፣ በሠራው ኀጢአትና፣ እስራኤልም እንዲሠሩ በማድረጉ፤* የ14፥16 ማብ ይመ።

15፥31 *በእስራኤል ነገሥታት ታሪክ፤* የ14፥19 ማብ ይመ።

15፥32 *ዘመነ መንግሥታቸውን ያሳለፉት...በመዋጋት ነበር፤* የቍ 16 ማብ ይመ። የኢዮርብዓም ሥርወ መንግሥት መውደቅ፣ በሁለቱ መንግሥታት መካከል የነበረውን ግንኙነት አላሻሻለም።

15፥33 *አሳ በነገሠ በሦተኛው ዓመት፤* ዓ.ቅ.ክ. 908 ማለት ነው (የቍ 10 ማብ ይመ)። *በቴርሳ፤* የ14፥17 ማብ ይመ። *ሃያ አራት ዓመትም፤* በሥልጣን የቈየበት ጊዜ፣ ሃያ ሦስት ዓመት ቢሆንም፣ በይፋ የሚታወቀው ግን፣ ሃያ አራት ዓመት እንደ ሆነ ነው (16፥8 ይመ)።

15፥34 *እስራኤልም እንዲሠሩ ያደረገውን ኀጢአት በመ ፈጸም፤* የ14፥16 ማብ ይመ። የባኦስ ዘመነ መንግሥት፤ (ቍ 26 ይመ) በናዳብ ዘመነ መንግሥት ቢተካም፣ ምንም ዐይነት መሻ ሻል እንዳልታየበት ያመለክታል።

16፥1 *ኢዩ፤* አባቱ ከእርሱ በፊት እንደ ነበረው (2ዜና 16፥7-10)፣ ኢዩም ለንጉሥ የእግዚአብሔርን የፍርድ ቃል አመጣ። በይሁዳ የነበረው የእግዚአብሔር ሰው የ13፥1 ማብ ይመ። ኋላም ነቢዩ አሞጽ እንደ አደረገው፣ ኢዩ ከደቡብ ወደ ሰሜኑ ንጉሥ ተላከ። ኢዮሳፍጥ በይሁዳ ንጉሥ እስከ ሆነበት ጊዜ ድረስ ኢዩ ለአምስት ዓመታት ያህል አገልግሎ ነበር (2ዜና 19፥2፤ 20፥34)።

16፥2 *ከትቢያ አንሥቼ፤* ከ14፥7 ጋር ያነጻጽሩ። *በኢዮር ብዓም መንገድ ሄድህ፤* የ14፥16 ማብ ይመ።

16፥3 *ባኦስንና ቤቱን ፈጽሜ አጠፋለሁ፤* ከ14፥10 (ኢዮር ብዓም ቤት)፤ 21፥21 (ከየምሪና ከአምዓብ ቤት) ጋር ያነጻጽሩ።

*16፥4፤* በ14፥11 ላይ የኢዮርብዓምን ሥርወ መንግሥት በሚመለከት፣ ከተነገረው ትንቢት ጋር ተመሳሳይ ነው።

16፥5 *የተከናወነው፤ የመጽሐፈ ነገሥት* ጸሓፊ፣ ባኦስ ከአከናወናቸው ነገሮች አንዳች እንኳ፣ መጥቀስ አልፈለገም። በወታደራዊና በፖለቲካዊ ረገድ ሲታይ፣ ባኦስ ዝነኛ ገዥ ነበር። *በእስራኤል ነገሥታት ታሪክ* የ14፥19 ማብ ይመ።

16፥6 *ከአባቶቹ ጋር አንቀላፋ፤* የ1፥21 ማብ ይመ።

16፥7 *እንደ ኢዮብርዓም ቤት...ክፉ ሥራን በማድረጉና፤* ቍ 2፤ 15፥34 ይመ። *በማጥፋቱም ጭምር ነው፤* ባኦስ የኢዮር

9ከሹማምቱ አንዱና የግማሽ ሠረገሎቹ
አዛዥ የሆነው ዘምሪ ዐምፆ ተነሣበት፤ በዚ
ያን ጊዜ ኤላ በቴርሳ ከተማ የቤተ መንግ
ሥቱ ኀላፊ በሆነው በአርጻ ቤት ጠጥቶ
ሰክሮ ነበር፤ 10ዘምሪም ገብቶ ኤላን ገደ
ለው፤ እርሱም በኤላ እግር ተተክቶ፣ የይ
ሁዳ ንጉሥ አሳ በነገሠ በሃያ ሰባተኛው
ዓመት ነገሠ።

11ዘምሪ ወዲያው እንደ ነገሠና በዙፋን
እንደ ተቀመጠ፣ የባአስን ቤተ ሰብ በሙሉ
ገደለ፤ የሥጋ ዘመድም ሆነ ወዳጅ አንድም
ወንድ አላስቀረም። 12በዚህ ሁኔታም በነቢዩ
በኢዩ አማካይነት በባኦስ ላይ በተነገረው
*በእግዚአብሔር ቃል* መሠረት፣ የባአስን
ቤተ ሰብ ሁሉ ፈጀ።

13ይህም የሆነው ባአስና ልጁ ኤላ፣ በማ
ይረቡ ጣዖቶቻቸው ምክንያት የእስራኤልን
ስምባክ *እግዚአብሔርን* ያስቈጡት ዘንድ በሠ
ሩት ኀጢአት ሁሉና፣ እስራኤልም እንዲ
ሠሩ በማድረጉ ነበር።

14ሌላው ኤላ በዘመኑ የፈጸመውና ያደረ
ገው ሁሉ በእስራኤል ነገሥታት ታሪክ
ተጽፎ የሚገኝ አይደለምን?

### የእስራኤል ንጉሥ ዘምሪ

15የይሁዳ ንጉሥ አሳ በነገሠ በሃያ ሰባተ
ኛው ዓመት ዘምሪ በቴርሳ ሆኖ ሰባት ቀን
ብቻ ገዛ። በዚህ ጊዜ ሰራዊቱ የፍልስጥኤ
ማውያን ከተማ የሆነችውን ገባቶንን ከቦ
ሰፍሮ ነበር። 16በዚያም ሰፈር የነበሩ እስራ
ኤላውያን ዘምሪ ዐምፆ ንጉሡን መግደሉን
እንደ ሰሙ፣ የሰራዊቱን አዛዥ ዖምሪን በዚ
ያኑ ዕለት እዚያው ሰፈር ውስጥ በእስራ
ኤል ላይ ማንገሣቸውን ዐወጁ። 17ከዚያም
ዖምሪና አብረውት ያሉት እስራኤላውያን
ሁሉ ከገባቶን ወደ ላይ ወጥተው ቴርሳን
ከበቡ። 18ዘምሪ ከተማዪቱ መያዟን ሲያይ፣
ቤተ መንግሥቱ ውስጥ ወዳለው ግንብ ገብቶ
በቤተ መንግሥቱ ላይ እሳት ለቀቀበትና
በዚሁ ሞተ። 19ይህ የሆነውም *በእግዚአብሔር*
ፊት የተጠላ ክፉ ሥራ በመሥራትና በኢዮ
ርብዓም መንገድ በመሄድ፣ እንዲሁም ራሱ
በሠራው ኀጢአትና እስራኤልም እንዲሠሩ
ባደረገው ኀጢአት ምክንያት ነው።

20ሌላው ዘምሪ በዘመኑ የፈጸመው ድርጊ
ትና ያካሄደውም ዐመፅ በእስራኤል ነገሥ
ታት ታሪክ ተጽፎ የሚገኝ አደለምን?

### የእስራኤል ነጉሥ ዖምሪ

21ከዚያም የእስራኤል ሕዝብ ከሁለት ተከ
ፈለ፣ ይህም ግማሹ የጎናትን ልጅ ታምኒን
ለማንገሥ ሲሆን፣ የቀረው ደግሞ ዖምሪን
በመደገፍ ነበር። 22ሆኖም የዖምሪ ተከታዮች
ከጎናት ልጅ ከታምኒ ተከታዮች ይልቅ በረቱ፤
ስለዚህ ታምኒ ሞተ፤ ዖምሪም ነገሠ።

23የይሁዳ ንጉሥ አሳ በነገሠ በሠላሳ አን
ደኛው ዓመት፣ ዖምሪ በእስራኤል ላይ ነገሠ፤
ዐሥራ ሁለት ዓመትም ገዛ፤ ከዚህም ውስጥ
ስድስቱን ዓመት የገዛው በቴርሳ ሆኖ ነው።
24እርሱም የሰማርያን ኰረብታ በሁለት መክ
ሊት[ነ] ጥሬ ብር ከሳምር ላይ ገዝቶ ከተማ
ሠራበት፤ ስሚንም በቀድሞው የተራራዋ ባለ
ቤት በሳምር ስም ሰማርያ ብሎ ጠራት።

[ነ]24 70 ኪሎ ግራም ያህል ነው

16፥9 1ነገ18፥3፤ 1ነገ20፥12:16፤ ምሳ31፥45
16፥10 2ነገ9፥31
16፥11 ቊ3
16፥13 ዘዳ32፥21
16፥15 ኢሱ19፥44
16፥23 ኢሱ12፥24፤ 1ነገ15፥33
16፥24 1ነገ13፥32፤ ማቴ10፥5

ብዓምን ቤት በማጥፋት፣ የእግዚአብሔርን ፈቃድ ቢፈጽምም (14፥10:14)፣ ስለ አከናወነው የጭካኔ ተግባር ግን፣ ተጠያቂ ነው (ከዘፍ 50፥20፤ ከኢሳ 10፥5-7:12 ጋር ያነጻጽሩ)።

16፥8 *አሳ በነገሠ በሃያ ስድስተኛው ዓመት፤* ዓ.ቅ.ክ. 886 ማለት ነው (የ15፥10 ማብ ይመ)። *ሁለት ዓመት፤* ዓ.ቅ.ክ. 886-885 ድረስ ማለት ነው።

16፥9 *ሰክሮ ነበር፤* ሰራዊቱ ገባቶንን ከቦ እያለ፣ ኤላ በቴርሳ ሆኖ መስከሩ፣ ንጉሥ ሆኖ ሳለ ኀላፊነቱን እንዳልተወጣ ያመለክታል።

16፥10 *አሳ በነገሠ በሃያ ሰባተኛው ዓመት፤* ዓ.ቅ.ክ. 885 ማለት ነው።

16፥11 *የባአስን ቤተ ሰብ በሙሉ ገደለ፤* 15፥29፤ 2ነገ 10፥1-7፤ 11፥1 ይመ። *ወዳጅ፤* የንጉሡ ዋና አማካሪ የነበረ ሰው ሊሆን ይችላል (የ2ሳሙ 15፥37 ማብ ይመ)።

16፥12 *በነቢዩ በኢዩ አማካይነት...በተነገረው በእግዚአብሔር ቃል፤* ቊ 1-4 ይመ። ዘምሪ የኢዩን ትንቢት ለመፈጸም የተነሣው ሆን ብሎ አልነበረም፤ ነገር ግን በኤላ ላይ ባሤረና የባአስን ሥርወ መንግሥት ባጠፋ ጊዜ፣ ሳያስተውለው ለኢዩ ትንቢት መፈጸም ምክንያት ሆነ (የቊ 7 ማብ ይመ)። በአርባ ስድስት ዓመት ጊዜ ውስጥ ሁለት ሥርወ መንግሥት (የኢዮርብዓምና የባአስ) የተፈራረቀ ሲሆን፣ ሦስተኛው ሥርወ መንግሥት ማለትም የዘምሪ የቈየው ለሰባት ቀናት ብቻ ነበር (ቊ 15 ይመ)።

16፥13 *ባአስና ልጁ ኤላ...በሠሩት ኀጢአት፤* 15፥34 ይመ። *በማይረቡ ጣዖቶቻቸው፤* የወርቅ ጥጃን ጭምር (12፥28፤ 14፥9 ይመ) በእስራኤል የሃይማኖታዊ በዓላት ውስጥ የተካተቱትን የአረማውያንን በዓላት ያመለክታል።

16፥14 *በእስራኤል ነገሥታት ታሪክ፤* የ14፥19 ማብ ይመ።

16፥15 *አሳ በነገሠ በሃያ ሰባተኛው ዓመት፤* ዓ.ቅ.ክ. 885 ማለት ነው (የ15፥1:10 ማብ ይመ)። *ገባቶንን፤* የቊ 9፤ 15፥27 ማብ ይመ።

16፥16 *ዐምፆ ንጉሡን መግደሉን፤* ቊ 9-12 ይመ። *የሰራዊቱን አዛዥ ዖምሪን፤* በኤላ ዘመነ መንግሥት ዘምሪ፣ ከነበረው ደረጃ የበለጠ ማዕረግ ነበረው (ቊ 9 ይመ)።

16፥17 *ቴርሳ፤* የንጉሡ መኖሪያ የነበረች ከተማ ናት (ቊ 8-10 ይመ፤ እንዲሁም የ14፥17 ማብ ይመ)።

16፥19 *በኢዮርብዓም መንገድ፤* የ14፥16 ማብ ይመ።

16፥20 *በእስራኤል ነገሥታት ታሪክ፤* የ14፥19 ማብ ይመ።

16፥22 *ታምኒ ሞተ፤* ታሞ ይሁን ወይም አገሪቱን ለመቈጣጠር በተደረገው ወታደራዊ ትንንቅ ምክንያት፣ አሟሟቱ በግልጽ አይታወቅም።

*16፥23 አሳ በነገሠ በሠላሳ አንደኛው ዓመት፤* ዓ.ቅ.ክ. 880 ማለት ነው (የ15፥10 ማብ ይመ)። *ነገሠ፤* ለብቻው ንጉሥ ሆነ። የሰሜኑን መንግሥት ለመቈጣጠር በዖምሪና በታምኒ መካከል የተደረገው ፍልሚያ ለአራት ዓመት ያህል ቈይቶ ነበር ከቊ 15 ጋር ያነጻጽሩ። *ዐሥራ ሁለት ዓመትም፤* ዓ.ቅ.ክ 885-874 ማለት ነው። ዐሥራ ሁለት ዓመት የቈየው የዖምሪ ዘመነ መንግሥት፣ በእርሱና በታምኒ መካከል የተደረገውን የአራት ዓመት የፍልሚያ ጊዜ ይጨምራል (ከቊ 15:29 ጋር ያነጻጽሩ)። *በቴርሳ፤* የ14፥17 ማብ ይመ። ዘንበሪ በጥቂት ቀናት ውስጥ ቴርሳን በቍጥጥሩ ሥር ሊያደርግ ችሎአል (ቊ 15-19)።

16፥24 *ሰማርያ፤* ከሴኬም በስተ ሰሜን ምዕራብ ዐሥራ ሦስት ኪሎ ሜትር ያህል ርቃ የምትገኝ ሲሆን፣ በአካባቢው ካሉ ለም ሸለቆ ቦታዎች ሦስት መቶ ጫማ ከፍ ብላ የምትገኝ ነበረች (በኢሳ 28፥1 ላይ፣ "የአበባ እቅፍ" በመባል ተጠቅሳለች)። መጀመሪያ በዚች ቦታ ባለቤት የነበረው ሰው፣ ቦታው በስሙ እንዲጠራ በመስማማት (ከሩት 4፥5 ጋር ያነጻጽሩ) ይዞታውን እንዲሸጥ ተደርጎ ይሆናል (21፥3 ይመ)። ይህች ቦታ ለሰሜኑ መንግሥት የጸናች ዋና ከተማ ሆና እንድትቆይ ምቹ የሆነ አቀማመጥ ነበራት (20፥1-21፤ 2ነገ 6፥25፤ 18፥9-10 ይመ)። ከዚህ የንጉሥ ከተማ ምሥረታ በኋላ፣ እንደ ዳዊት ሥርወ መንግሥት የሰሜኑ መንግሥታትም አምባይቱን ከተማ (2ሳሙ 5፥6-12) የራሳቸው ምሽግ አደረጓት። ሰሎሞን በኢየሩሳሌም ካሠራቸው ሕንጻዎች

25 ይሁን እንጂ *ዖምሪ በእግዚአብሔር ፊት*
ክፉ ድርጊት ፈጸመ፤ ከእርሱ አስቀድሞ
ከነበሩትም ይልቅ የበለጠ ኀጢአት ሠራ።
26 እርሱም እስራኤል በማይረቡ *ጣዖቶቻቸው*፣
የእስራኤልን ስም*ባከ እግዚአብሔርን ለቊጣ*
እንዲያነሣሡት ባደረገው በናባጥ ልጅ በኢ
ዮርብዓም መንገድ ሁሉና እርሱም ኀጢአት
ሠርቶ እስራኤልም እንዲሠሩ ባደረገው ኀጢ
አት ተመላለሰ።
27 ሌላው *ዖምሪ* በዘመኑ የፈጸመው፣ ያደ
ረገውና ያከናወነው ሁሉ በእስራኤል የነገሥ
ታት ታሪክ ተጽፎ የሚገኝ አይደለምን?
28 *ዖምሪ* ከአባቶቹ ጋር አንቀላፋ፤ በሰማር
ያም ተቀበረ፤ ልጁም አክዓብ በእግሩ ተተ
ክቶ ነገሠ።

## አክዓብ የእስራኤል ንጉሥ ሆነ

29 የይሁዳ ንጉሥ አሳ በነገሠ በሠላሳ ስም
ንተኛው ዓመት፣ የ*ዖምሪ* ልጅ አክዓብ በእ
ስራኤል ላይ ነገሠ፤ በሰማርያም ሆኖ እስራ
ኤልን *ሃያ* ሁለት ዓመት ገዛ። 30 የ*ዖምሪ*
ልጅ አክዓብ ከእርሱ አስቀድሞ ከነበሩት
ሁሉ ይልቅ፣ *በእግዚአብሔር* ፊት ክፉ ነገር
አደረገ። 31 የናባጥን ልጅ የኢዮርብዓምን
ኀጢአት እንደ ቀላል ነገር ከመቍጠሩም
በላይ የሲዶናውያንን ንጉሥ የኤትበኣልን
ልጅ ኤልዛቤልን አገባ፤ ሄዶም በኣልን አመ
ለከ፤ ሰገደለትም። 32 ሰማርያ ላይ በሠራውም
የበኣል ቤተ ጣዖት ለበኣል መሠዊያ አቆመ
ለት። 33 ደግሞም አክዓብ የአሼራን ምስል
ዐምድ በማቆም ከእርሱ በፊት ከነበሩት የእ
ስራኤል *ነገሥታት* ይልቅ የእስራኤልን ስም*
ባከ እግዚአብሔርን ለቊጣ የሚያነሣሣ* ድር
ጊት *ፈጸመ*።
34 የቤቴል ሰው አኪኤል፣ በአክዓብ ዘመን
ኢያሪኮን *መልሶ ሠራት*። *እግዚአብሔር*
በነዌ ልጅ በኢያሱ አማካይነት የተናገረው
ቃል ይፈጸም ዘንድ መሠረቷን ሲያኖር
በኵር ልጁ አቢሮን ሞተ፤ የቅጽር በሮቿ
ንም በሚሠራበት ጊዜ የመጨረሻው ልጁ
ሠጉብ ሞተ።

## ኤልያስን ቍራዎች መገቡት

17 በዚህ ጊዜ ከገለዓድ ነዋሪዎች አንዱ
የሆነው ቴስብያዊው ኤልያስ አክዓ
ብን፣ "*የማመልከው ሕያው እግዚአብሔርን*
በእኔ ቃል ካልሆነ በቀር፣ በሚቀጥሉት ዓመታት

16፥25 ቍ25-26፤ ዘዳ4፥25ሚክ6፥16
16፥26 ዘዳ32፥21፤ 1ነገ15፥30
16፥28 1ነገ13፥32
16፥30 1ነገ14፥9
16፥31 መሳ2፥11፤ 3፥6፤1ነገ11፥2ነገ 9፥34
16፥32 መሳ6፥28፤ 2ነገ10፥27፤11፥18፤ ኤር43፥12
16፥33 መሳ3፥7፤ 1ነገ14፥9፤21፥25፤ 2ነገ13፥6
16፥34 ኢሱ6፥26
17፥1 ዘዳ11፥17፤ 28፥24፤መሳ12፥4፤ 2ሳሙ1፥21፤1ነገ8፥36 ፤ኢዮ12፥15ሚል4፥5፤ ማቴ11፥14፤17፥3፤ ሉቃ4፥25

ጋር የሚስተካከል፣ *ዖምሪና* አክዓብ ውብ የሆኑ ሕንጻዎችን በመገ ንባት ይህችን ከተማ እንድታሸበርቅ ማድረጋቸውን፣ የሥነ ቅርስ ተመራማሪዎች አረጋግጠዋል። የደቡብ *መንግሥት* በዋናው ከተማ በኢየሩሳሌም ይጠራ እንደ ነበር ሁሉ (21፥1፤ ኢሳ 10፥10፤ አሞ 6፥1)፣ ከዚህ ጊዜ ጀምሮ የሰሜኑ *መንግሥት* በዋናው ከተማ ስም መጠራት ጀመረ።

16፥25 *ከእርሱ አስቀድሞ ከነበሩትም ይልቅ የበለጠ ኀጢአት ሠራ፤* ዖምሪ ከሲዶንና ከጢሮስ ንጉሥ ከኤትበአል ጋር ግንኙነት በመፍጠሩ (ወዳጅነቱን ለማጠናከር የ*ዖምሪ* ልጅ አክዓብ የኤትበኣልን ሴት ልጅ ኤልዛቤልን አገባ)፣ በሰሜኑ መንግሥት የበኣል አምልኮ ተስፋፋ (ቍ 31፥33)፤ በመጨረሻም በደቡብ መንግሥት የሚገኘው የዳዊት ዘር እስከመጥፋት ደረሰ (2ነገ 11 ይመ፤ እንዲሁም የ2ነገ 8፥18 ማብ ይመ)። *ዖምሪ*፣ በዘመነ መን ግሥቱ የመጀመሪያዎቹ ዓመታት ላይ (የቍ 23 ማብ ይመ)፣ ከኤትበኣል ጋር ይህን የጋብቻ ግንኙነት የመሠረተው፣ ታምኒን ለመውጋት፣ ኀይል ለማግኘት አስቦ ያደረገው ይመስላል (ቍ 21-22 ይመ)።

16፥26 *እስራኤልም እንዲሠሩ ባደረገው ኀጢአት፤* 12፥26-33 ይመ እንዲሁም የ14፥16 ማብ ይመ። *በማይረቡ ጣዖ ቶቻቸው፤* የቍ 13 ማብ ይመ።

16፥27 *በዘመኑ...ያከናወነው፤* ዖምሪ ያከናወናቸውን ወታደ ራዊና ፖለቲካዊ የሆኑ፣ ጕዳዮችን መጥቀስ የመጽሐፈ ነገሥት ጸሓፊ አልፈለገም። ሰማርያን የሰሜኑ መንግሥት ዋና ከተማ አድርጎ ከመመሥረቱም በቀር፣ ስለ ዖምሪ የሚጠቀሰው ሌላው ነገር፣ ልጁ አክዓብ የሰሜኑን ክፍል በሚገዛበት ጊዜ (20፥14-15 ይመ) የተጠቀመበትን መንግሥታዊ መዋቅር ማዘጋጀቱ ነው። ይሁን እንጂ፣ የዖምሪ ሥርወ መንግሥት የቈየው ከአርባ ዓመት በላይ ነው። አሦራዊው ቴልጌልቴልፌልሶር ከአንድ ምዕተ ዓመት ተኩል በኋላ፣ (ዓ.ቅ.ክ. 732)፣ እስራኤልን፣ "የዖምሪ ቤት" በማ ለት በታሪኩ ውስጥ ጠቅሶታል። *በእስራኤል የነገሥታት ታሪክ፤* የ14፥19 ማብ ይመ።

16፥28 *ከአባቶቹ ጋር አንቀላፋ፤* የ1፥21 ማብ ይመ።

16፥29 *አሳ በነገሠ በሠላሳ ስምንተኛው ዓመት፤* ዓ.ቅ.ክ. 874 ማለት ነው (የ15፥9-10 ማብ ይመ። *ሃያ ሁለት ዓመት፤* ዓ. ቅ.ክ ከ874-853 ድረስ ማለት ነው።

16፥30 *ከእርሱ አስቀድሞ ከነበሩት ሁሉ ይልቅ...ክፉ ነገር አደረገ፤* ዖምሪ ከእርሱ በፊት የነበሩት ነገሥታት ከፈጸሙት ሁሉ የከፋ ኀጢአት አደረገ (ቍ 25 ይመ)፤ አክዓብ ደግሞ አባቱ ዖምሪ ካደረገው ይልቅ የከፋ ኀጢአት ፈጸመ። በሰሜኑ መንግሥት፣ ንጉሣዊ ቤት ውስጥ፣ ኀጢአት መሥራት እየጨመረ ሲሄድ ይታ ያል። አንድ ሦስተኛ የሚሆነው በሁለቱ የነገሥት መጻሕፍት ውስጥ የተጻፈው ታሪክ፣ የአክዓብንና የሁለት ልጆቹን የአካዝያ ስንና የኢዮራምን የሠላሳ አራት ዓመት አገዛዝ ታሪክ የሚመለ ከት ነው።

16፥31 *የኤትበኣልን ልጅ ኤልዛቤልን አገባ፤* አይሁዳዊው የታሪክ ጸሓፊ ዮሴፍ ወልደ ኮሪዮን፣ ኤትበኣል በጢሮስና በሲዶን ላይ ለሠላሳ ሁለት ዓመት ካህንና ንጉሥ በመሆን እንደ ገዛ በጽሑፉ ጠቅሶታል። አክዓብ ኤልዛቤልን ያገባው በአባቱ ዘመነ መንግ ሥት ነበር (የቍ 25 ማብ ይመ)። *በኣል፤* ሜልካርት በመባል የሚታወቀው ይሆናል፤ ይህ ጣዖት በእስራኤል እንዲመለክ ያደረገ ችው ኤልዛቤል ናት። አክዓብ ጋብቻ በፈጸመበት ጊዜ፣ ይህን ጣዖት ማምለክ እንደ ጀመረ ይገመታል። አክዓብ ሁለቱንም አጣምሮ ማምለክ እንጂ፣ እግዚአብሔርን ማምለክን፣ በኣልን በማ ምለክ የመተካት ፍላጎት እንዳልነበረው የልጆቹ ስም ያመለክታል (አካዝያስ፣ ትርጕሙም እግዚአብሔር ያቅፋል ማለት ሲሆን፣ ኢዮ ራም ደግሞ እግዚአብሔር ከፍ ከፍ አለ ማለት ነው)።

16፥32 *ሰማርያ ላይ በሠራውም የበኣል ቤተ ጣዖት፤* ሰሎሞን በኢየሩሳሌም ለእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ እንደ ሠራ፣ አክዓብ ደግሞ ሚስቱ ኤልዛቤል ለምታመልከው ለፊንቃውያን አምላክ በኣል በሰማርያ ቤተ ጣዖት በማሠራት፣ የበኣል አምልኮ ወደ ሰሜኑ መንግሥት እንዲገባ አደረገ። ቈይቶም፣ ኢዩ ይህን የአረማውያን ቤተ ጣዖት ከማምለኪያ ድንጋዩ ጋር (የ14፥23 ማብ ይመ) እንዲወድም አደረገ (2ነገ 10፥21-27)።

16፥33 *የአሼራን ምስል ዐምድ፤* የ14፥15 ማብ ይመ። *ከእርሱ በፊት ከነበሩት የእስራኤል ነገሥታት ይልቅ፤* የቍ 30 ማብ ይመ። በዘመነ መንግሥቱ መጀመሪያ ላይ፣ አክዓብ የበኣል አምልኮ በሰሜኑ መንግሥት በይፋ እንዲታወቅ አደረገ።

16፥34 *ኢያሪኮን መልሶ ሠራት፤* ቅጥር ያልነበራት ከተማ ሆና መቈየቷን ለማመልከት እንጂ፣ ኢያሪኮ በኢያሱ ከወደመች ጊዜ አንሥቶ (18፥21፤ መሳ 1፥16፤ 3፥13፤ 2ሳሙ 10፥5) ሰው አልኖረባትም ለማለት አይደለም። በአክዓብ ዘመነ መንግሥት፣ አኪኤል ቅጥሮቹንና በሮቹን (9፥17 ይመ) መልሶ በመገንባት፣ ከተማዋን ምሽግ አደረገ። የኢያሪኮ መደምሰስ (ኢሱ 6፥26)፣ እስ ራኤላውያን የከነዓንን ምድር ከእግዚአብሔር እጅ በጸጋ መቀበላ ቸውን፣ ለዘለቄታው የሚያስታውስ ስለ ነበር፣ ይህ ሁኔታ፣ የእግ ዚአብሔርን ፈቃድ የሚቃረን ነበር። ስለዚህም በአኪኤል ላይ፣ ኢያሱ የተናገረው ርግማን ደረሰበት።

17፥1 *ኤልያስ፤* ይህ ስም (ትርጕሙ "እግዚአብሔር አም ላኬ ነው" ማለት ነው) የመልእክቱን መሠረታዊ ሐሳብ የያዘ ነው (18፥21:39)፤ የእርሱም ተልእኮ የበኣልን አምልኮና የሚያመልኩ ትን ሰዎች በቃልና በድርጊት አጥብቆ መቃወም ነበር። *ከገለዓድ... ቴስብያዊው፤* ገለዓድ በዮርዳኖስ ማዶ ሰሜናዊ ክፍል የሚገኝ ቦታ ነበር። ቴስብ የት እንደሚገኝ በግልጽ አይታወቅም። *የማመል ከው፤* ቃል በቃል ሲተረጐም፣ "በፊቱ የቆምሁት" ማለት ሲሆን፣

ዝናብ ወይም ጠል አይኖርም” አለው::
[2]ከዚያም እንዲህ የሚል *የእግዚአብሔር*
ቃል ለኤልያስ መጣለት፤ [3]“ከዚህ ተነሥ
ተህ ወደ ምሥራቅ ሂድ፤ ከዮርዳኖስ በስተ
ምሥራቅ ባለው በኮራት ወንዝ ተሸሸግ::
[4]ውሃ ከወንዙ ትጠጣለህ፤ ቍራዎችም እዚ
ያው እንዲመግቡህ አዝዣለሁ::”
[5]ስለዚህ *እግዚአብሔር* ያዘዘውን ፈጸመ፤
ከዮርዳኖስ በስተ ምሥራቅ ወዳለው ወደ
ኮራት ወንዝ ሄዶ በዚያ ተቀመጠ:: [6]ቍራ
ዎችም ጧትና ማታ እንጀራና ሥጋ ያመጡ
ለት ነበር፤ ውሃም ከወንዙ ይጠጣ ነበር::

## የሰራፕታዪቱ መበለት

[7]በምድሪቱ ላይ ዝናብ ባለመጣሉ ከጥቂት
ጊዜ በኋላ ወንዙ ደረቀ:: [8]ከዚያም እንዲህ
የሚል *የእግዚአብሔር* ቃል ወደ ኤልያስ
መጣ፤ [9]“ተነሥና ሲዶና ውስጥ ወዳለችው
ወደ ሰራፕታ ሄደህ ተቀመጥ፤ በዚያም አን
ዲት መበለት እንድትመግብህ አዝዣለሁ::”
[10]ስለዚህ ተነሥቶ ወደ ሰራፕታ ሄደ:: ወደ
ከተማዪቱ በር እንደ ደረሰም፣ አንዲት
መበለት ጭራሮ ስትለቃቅም አገኛት፤ ጠር
ቶም፣ “የምጠጣው ውሃ በዕቃ ታመጪልኛ
ለሽን?” ሲል ለመናት:: [11]ልታመጣለት ስት
ሄድ አሁንም ጠራትና፣ “እባክሽን፣ ቍራሽ
እንጀራም ይዘሽልኝ ነይ” አላት::
[12]እርሷም መልሳ፣ “ስለምታመልከው ሕያው እግ
ዚአብሔርን! በማድጋ ካለው ዕፍኝ ዱቄ
ትና በማሰሮ ካለው ጥቂት ዘይት በቀር
ምንም የለኝም:: እነሆ፤ ለራሴና ለልጄ ምግብ
አዘጋጅቼ በልተን እንድንሞት ጭራሮ ለቃ
ቅሜ ወደ ቤት ልወስድ ነው” አለችው::
[13]ኤልያስም መልሶ እንዲህ አላት፤ “አይ
ዞሽ አትፍሪ፤ ወደ ቤት ገብተሽ እንዳል
ሽው አድርጊ፤ በመጀመሪያ ግን ከዚያችው
ካለችሽ ትንሽ እንጎቻ ጋግረሽ አምጪልኝ፤
ከዚያም ለራስሽና ለልጅሽ ጋግሪ፤ [14]የእስራ
ኤል ስለምታመልከው *እግዚአብሔር* እንዲህ ይላል፤
‘*እግዚአብሔር* ለምድሪቱ ዝናብ እስከሚሰ
ጥበት ዕለት ድረስ፤ ከማድጋው ዱቄት
አይጠፋም፤ ከማሰሮውም ዘይት አያልቅም::’”
[15]እርሷም ሄዳ ኤልያስ እንደ ነገራት አደ
ረገች፤ በዚህ ሁኔታም ኤልያስ፣ መበለቲ
ቱና ቤተ ሰቧ ብዙ ቀን ተመገቡ፤ [16]በኤል
ያስ በተነገረው *የእግዚአብሔር* ቃል መሠረት
ከማድጋው ዱቄት አልጠፋም፤ ከማሰሮውም
ዘይት አላለቀም ነበርና::
[17]ከጥቂት ጊዜ በኋላም የባለቤቲቱ ልጅ
ታመመ፤ ሕመሙ እየጠናበት ሄደ፣ በመ
ጨረሻም ትንፋሹ ቀጥ አለ:: [18]እርሷም ኤል
ያስን፤ “የእግዚአብሔር ሰው ሆይ፤ እኔ ምን አደረ
ግሁህ? እዚህ የመጣኸው ኀጢአቴን አስታ
ውሰህ ልጄን ለመግደል ነውን?” አለችው::

17፥3 1ነገ18፥4፡ 10፤ኢር36፥19፡26
17፥4 ዘፍ8፥7
17፥6 ዘፀ16፥8
17፥9 አብ1፥20፤ ሉቃ4፥26
17፥10 ዘፍ24፥17፤ ዮሐ4፥7
17፥12 2ነገ4፥2
17፥14 ቍ1
17፥18 ሉቃ5፥8

በንጉሥ ፊት ቆሞ ማገልገልን የሚያመለክት አገላለጽ ነው:: በእ
ስራኤል፣ ነገሥታትና ካህናት የእግዚአብሔር ሕዝብ ለአም
ላካቸው ለእግዚአብሔር ታማኝ ሆነው እንዲኖሩና እንዲሁም የኪ
ዳኑ በረከትና ጥበቃ ለሕዝቡ እንዲደርስ ታላቁን የእስራኤል ንጉሥ
እግዚአብሔርን ወክለው እንዲያገለግሉ ይቀቡ ነበር:: ከኢዮርብዓም
ዘመነ መንግሥት ጀምሮ የሰሜኑ መንግሥት ካህን አልነበረውም
(12፥31)፤ ነገሥታቱም ቢሆኑ ታማኞች አልነበሩም:: አክዓብ፣
በኣል እንዲመለክ በማድረጉ ከፍተኛ ችግር ተፈጥሮ ነበር፣ ከዚ
ህም የተነሣ እግዚአብሔር ኤልያስን (ከእርሱም በኋላ ኤልሳዕ)
ጥንት ሙሴ እንዳገለገለው፣ በንጉሥና በካህን ፈንታ እግዚአብሔ
ርን ወክሎ እንዲያገለግል ላከው:: የመጽሐፈ ነገሥት ጸሓፊ፣
በኤልያስና በሙሴ አገልግሎት መካከል ብዙ ተመሳሳይ ነገር
እንዳለ አመልክቷል:: *ዝናብ ወይም ጠል፤* ድርቅ ወደ ጣዖት
አምልኮ በተመለሰ ሕዝብ ላይ የመጣ የአምላክ ፍርድ ብቻ
ሳይሆን፣ በኣል የልምላሜና የዝናብ ጌታ እንደ ሆነ ቢቈጠርም፣
ዝናብን መስጠት እንደማይችል የሚያሳይም ነው (ከዘሌ 26፥3-4፤
ከሆሴ 2፥5:8 ጋር ያነጻጽሩ)::

17፥3 *ከዚህ ተነሥተህ... ሂድ፤* እግዚአብሔር በዚህ የትእ
ዛዝ ቃል የራሱን ነቢይ ከአገሩና ከወገኑ ለይቶ በማውጣት፣ ሕዝቡ
ከቃሉና ከበረከቱ የተገለለ እንዲሆን አደረገ:: የነቢዩ በዚያ አለ
መገኘት የፍርድ አይቀሬነትና ጽናትን የሚያረጋግጥ ነው::
*ከዮርዳኖስ በስተ ምሥራቅ ባለው በኮራት ወንዝ፤* ኮራት የት
እንደሚገኝ በግልጽ አይታወቅም:: ከሰሜን ወደ ያርሙክ ወንዝ
ከሚፈሱት ገባር ወንዞች አንዱ የሠራው ሸለቆ ሊሆን ይችላል::

17፥4 *ቍራዎችም እዚያው እንዲመግቡህ፤* እስራኤላው
ያን በተስፋዪቱ ምድር እየተራቡ ሳሉ፣ የእግዚአብሔር ታማኝ
አገል ጋይ ኤልያስ ግን በዮርዳኖስ ማዶ በታምር ምግብ ይዘጋ
ጅለት ነበር፤ ይህም እስራኤላውያን በኣልን መታመናቸው፣ እግዚ
አብሔር መቃወሙን በግልጽ የሚያሳይ ነበር:: ኤልያስ ከራሱ
ወገኖች ተለይቶ በታምር የሚያስፈልገውን ምግብ ማግኘቱ፣
በእግዚአብሔር ቃል ላይ መደገፍ ያለበት ሕዝቡ እንጂ፣ የእግዚ
አብሔር ቃል በሕዝቡ ላይ የሚደገፍ አለመሆኑን ያሳያል::

17፥9 *ሲዶና ውስጥ ወዳለችው ወደ ሰራፕታ፤* በጢሮስና
በሲዶና መካከል፣ የኤልዛቤል አባት ኤትበኣል (16፥31) በሚያስ
ተዳድረው ግዛት ውስጥ በባሕር ዳር የምትገኝ ከተማ ናት:: ኤል
ያስ፣ የበኣል አምልኮ ማዕከል ወደ ሆነችውና ይህንም አምልኮ
ወደ እስራኤል ምድር ወደ አስገባችው አገር እንዲሄድና በዚያም
እንዲኖር ታዘዘ:: *በዚያም አንዲት መበለት እንድትመግብህ
አዝዣለሁ፤* የእግዚአብሔርን ቃል የያዘው ኤልያስ፣ በሰው
እጅ፣ ያውም እየተራበች ባለች ድኻ መበለት እጅ (ቍ 12) ሊመ
ገብ መጣ:: ከዚህም በላይ ይህች ሴት፣ የእግዚአብሔር ሕዝብ
ወገን ሳትሆን፣ (ከሉቃ 4፥25-26 ጋር ያነጻጽሩ) ይልቁንም የእግዚ
አብሔርን መንግሥት ከሚቃወሙ ኀይሎችና (ቀደም ሲል ግብፅ
ውስጥ ኋላም ባቢሎንን በመሳሰሉት) በእግዚአብሔር ከማያምኑ
ወገኖች መካከል ነበረች::

17፥10 *ስለዚህ ተነሥቶ ... ሄደ፤* ኤልያስ በእግዚአብሔር
ላይ የነበረው እምነት፣ እስራኤላውያን በእግዚአብሔር ላይ ሊኖ
ራቸው ይገባ የነበረውን እምነት ይገልጻል::

17፥12 *“ለምታመልከው ሕያው እግዚአብሔርን!”* ይህች ሴት
በእግዚአብሔር ስም መማሏ፣ ኤልያስ እስራኤላዊ መሆኑን ስለ ዐወ
ቀች (የ5፥7፤ 10፥9 ማብ ይመ)፣ ወይም ቀደም ብላ የእስራኤልን
አምላክ ማወቋንና፣ ለእርሱም መገዛቷን ከልብ መግለጿ ይሆናል::

17፥13 *በመጀመሪያ ... ትንሽ እንጎቻ ጋግረሽ አም
ጪልኝ፤ ከዚያም ለራስሽና ለልጅሽ ጋግሪ፤* ነቢይ እንደ መሆኑ
መጠን፣ የኤልያስ ቃል የእግዚአብሔር ትእዛዝ ነው:: መበለቲቱ
የተጠየቀችው፣ የእግዚአብሔርን ቃል የያዘውን ነቢይ ለመመገብ
ያላትን ሁሉ እንድትሰጥ ነው:: ያላትን ሁሉ እንድትሰጥ መጠየቁ፣
ከኪዳኑ አኳያ እስራኤላውያን ማድረግ ሲገባቸው ሳያደርጉ የቀሩ
ትን የሚያመለክት ነው::

17፥14 *የእስራኤል አምላክ እግዚአብሔር፣ እንዲህ ይላል፤*
ኤልያስ፣ መበለቲቱን “አትፍሪ” (ቍ 13) ያለው፣ የኪዳኑ
ግዴታ፣ ከኪዳን ተስፋ ጋር አብሮ የተሰጠ በመሆኑ ነው:: እግዚ
አብሔር ራሱ ሊሰጥ ተስፋ ከገባው በላይ ሰው እንዲሰጥ አይጠ
ይቅም::

17፥15 *ኤልያስ እንደ ነገራት አደረገች፤* በፈጸመችው የእ
ምነት ተግባር ተስፋ የተሰጠበትን በረከት፣ ተቀበለች:: እስራኤል
ብልጥግናን ለማግኘት ስትል፣ በኣልንና አሼራን ተከተለች:: በአረ
ማዊ መንግሥት ውስጥ የምትኖር ይህች መበለት፣ የእግዚአብሔ
ርን ቃል በእምነት መታዘዟ ወደ ሕይወት የሚመራ መንገድ
መሆኑን አስተዋለች::

17፥16 *ከማድጋው ዱቄት አልጠፋም፤* በእግዚአብሔር ቃል
በመታመን ሕይወቷን በትክክለኛው መንገድ ለመራችው፣ ከእስ
ራኤል ወገን ላልሆነች ለዚች ሴት እግዚአብሔር በታምር የሚያ
ስፈልጋትን ምግብ አዘጋጀላት:: በተስፋዪቱ ምድር ለሚኖሩ፣
ነገር ግን ታማኝ ላልነበሩ ሕዝቡ ምግብ ሳይሰጥ፣ ለእርሷ ግን
ከሰማይ “መና” ሰጣት:: በዚህ ጊዜ በዘዳ 32፥21 ላይ የተነገረው

19ኤልያስም መልሶ፣ "ልጅሽን ስጪኝ"
አላት፤ ልጁንም ከዕቅፏ ወስዶ እርሱ ወደ
ሚኖርበት ሰገነት በማውጣት በዐልጋው
ላይ አስተኛው። 20ከዚያም፣ "አምላኬ እግዚ
አብሔር ሆይ፤ ልጇን እንዲሞት በማድረግ
ተቀብላ በምታስተናግደኝ በዚህች መበለት
ላይም መከራ ታመጣባታለህን?" ብሎ ወደ
እግዚአብሔር ጮኸ። 21በልጁም ላይ ሦስት
ጊዜ ተዘርግቶ፣ "አምላኬ እግዚአብሔር ሆይ፤
የዚህ ልጅ ነፍስ ትመለስለት" ብሎ ወደ
እግዚአብሔር ጮኸ።
22እግዚአብሔርም የኤልያስን ጩኸት ሰማ፤
የልጁም ነፍስ ተመለሰችለት፤ እርሱም ዳነ።
23ከዚያም ኤልያስ ልጁን አስነሥቶ ከሰገነቱ
ወደ ምድር ቤት አወረደው፤ ለእናቱም
ልጅሽ ይኸውልሽ፤ ድኖልሻል!" ብሎ ሰጣት።
24ከዚያም ሴቲቱ ኤልያስን፣ "አሁን የእግ
ዚአብሔር ሰው መሆንህን፣ ከአንደበትህም
የወጣው የእግዚአብሔር ቃል እውነት መሆ
ኑን ዐወቅሁ" አለችው።

### ኤልያስና አብድዩ

18 ከብዙ ጊዜ በኋላም በሦስተኛው
ዓመት እንዲህ የሚል የእግዚአብሔር
ቃል ለኤልያስ መጣለት፤ "ሂደህ ለአክዓብ
ተገለጥ፤ እኔም በምድሪቱ ላይ ዝናብ አዘን
ባለሁ።" 2ስለዚህም ኤልያስ ራሱን በአክዓብ
ፊት ለመግለጥ ሄደ።
በዚህ ጊዜ ራብ በሰማርያ ክፉኛ ጸንቶ
ነበር። 3አክዓብም የቤተ መንግሥቱን አዛዥ
አብድዩን ጠራው፤ አብድዩም እግዚአብሔ
ርን በጣም የሚፈራ ሰው ነበር። 4ኤልዛቤል
የእግዚአብሔርን ነቢያት እያስገደለች በነበ
ረበት ጊዜ፣ አብድዩ መቶውን ነቢያት ወስዶ
አምሳ አምሳውን በሁለት ዋሻ ውስጥ ሸሽጎ
እንጀራና ውሃ ይሰጣቸው ነበር። 5አክዓብም
አብድዩን፣ "ተነሣና በአገሪቱ ውስጥ ወዳ
ሉት ምንጮችና ሸለቆዎች ሂድ፤ ፈረሶቻ
ችንና በቅሎዎቻችን እንዳይሞቱ በሕይወት
እንዲቈዩ ምናልባት ሣር እናገኝ ይሆናል።"
አለው። 6ስለዚህ የሚሄዱበትን ምድር ተከ
ፋፈሉ፤ አክዓብ በአንድ በኩል፣ አብድዩም
በሌላ በኩል ሄደ።
7አብድዩ በመንገድ ላይ ሳለም ኤልያስን
አገኘው። አብድዩም ዐወቀው፤ ወደ መሬት
ለጥ ብሎ እጅ በመንሣት፣ "ጌታዬ ኤል
ያስ ሆይ፤ በእርግጥ አንተ ነህን?" አለው።
8እርሱም፣ "አዎን እኔ ነኝ፤ ሂድና ለጌ
ታህ፣ 'ኤልያስ እዚሁ አለልህ' ብለህ ንገ
ረው" ሲል መለሰለት።
9አብድዩም እንዲህ አለው፤ "ምነው ምን
አጠፋሁና ነው ባሪያህ እንዲሞት ለአክዓብ
አሳልፈህ የምትሰጠው? 10አምላክህን ሕያው
እግዚአብሔርን! ጌታዬ አንተን ለመፈለግ
መልእክተኛ ያላከበት ሕዝብና መንግሥት
የለም፤ የትኛውም ሕዝብ ሆነ መንግሥት
አንተ በዚያ አለመኖርህን ባስታወቀው ጊዜ
ሁሉ አንተን አለማግኘቱን ለማረጋገጥ ያስ
ምለው ነበር። 11አሁን ግን አንተ ወደ ጌታዬ
ሂጄ፣ 'ኤልያስ እዚህ አለልህ' እንድለው
ትፈልጋለህ፤ 12ተለይቼህ ስሄድ የእግዚአ
ብሔር መንፈስ የት እንደሚወስድህ አላው
ቅም፤ ታዲያ ሂጄ ለአክዓብ ከነገርሁት
በኋላ ሳያገኝህ ቢቀር እኔን ይገድለኛል፤
ነገር ግን እኔ ባሪያህ ከጕልማሳነቴ ጀምሮ
እግዚአብሔርን አመልካለሁ። 13ጌታዬ ሆይ፤
ኤልዛቤል የእግዚአብሔርን ነቢያት ባስገደ
ለች ጊዜ ምን እንዳደረግሁ አልሰማህምን?
መቶውን የእግዚአብሔር ነቢያት ወስጄ አምሳ

17፥20 2ነገ4፥33
17፥21 2ነገ4፥34
1ሐሥ20፥10
17፥23 ዕብ11፥35
17፥24 ቍ18፤ዮሐ
22፥16፤መዝ119፥43፤
ዮሐ16፥30፤17፥7
18፥1 ቍ15፤ዘዳ
28፥12፤1ነገ17፥1፤
ሉቃ4፥25
18፥2 ዘሌ26፥26
18፥3 1ነገ16፥9፤
ነህ7፥2
18፥4 1ነገ17፥3፤
21፥23፤2ነገ9፥7፤
ኢሳ16፥3፤25፥4፤
32፥2፤ኤር26፥24፤
አብ1፥14
18፥5 ዘፍ47፥4፤
ኤር14፥3
18፥7 2ነገ1፥8፤
ዘካ13፥4
18፥10 1ነገ17፥3
18፥12 2ነገ2፥16
፤ሕዝ3፥14፤
ሐሥ8፥39

ቃል ተፈጸመ (ከሮሜ 10፥19፤ 11፥11:14 ጋር ያነጻጽሩ)።

17፥18 *እዚህ የመጣኸው ኀጢአቴን አስታውሰህ ልጄን ለመግደል ነውን?* ኤልያስ በእርሷ ቤት መገኘቱ፣ እግዚአብሔርን ወደ እርሷ ኀጢአት ይመለከት ዘንድ እንዳደረገው፣ የልጇም ሞት ስለ ኀጢአቷ ከአምላክ የተሰጠ ቅጣት መሆኑን አሰበች። ይሰማት የነበረው የበደለኝነት ስሜት፣ ከአረማዊ አስተሳሰብ የመነጨ ቢመስልም የሕይወትን ተስፋ የሰጠ አምላክ፣ ለምን ሞትን እንዳመጣ በእርሷና በኤልያስ ላይ ጥያቄ ፈጥሮባቸው ነበር።

17፥21 *በልጁም ላይ ሦስት ጊዜ ተዘርግቶ፤* ነቢዩ በልጁ ላይ በዚህ ዐይነት መዘርጋቱ፣ ለልጁ ሙቀት ለመስጠት ነበር። የኤልያስ ጸሎት፣ ልጁ በሕይወት የሚኖረው፣ ከጸሎቱ መልስ የተነሣ እንጂ፣ ከሰውነቱ ከወጣው ሙቀት የተነሣ አለመሆኑን ያስገነዝባል። *የዚህ ልጅ ነፍስ ትመለስለት፤* የእግዚአብሔር ቃል እውነተኛነትና ታማኝነት ይገለጽ ዘንድ፣ አብርሃም እንዳደረገው (ሮሜ 4፥1፤ ዕብ 11፥19)፣ ኤልያስም፣ የሞተው ልጅ ሕይወት እንዲያገኝ በእምነት ጸለየ።

17፥22 *የልጁም ነፍስ ተመለሰችለት፤* ለመጀመሪያ ጊዜ ከሞት ስለ ተነሣ ሰው በመጽሐፍ ቅዱስ የተጠቀሰው ይህ ነው። ከእስራኤል ወገን ሳልሆንች ለዚህች መበለት ከሞት ኀይል ተላቆ ሕይወትን የማግኘት ታላቅ የኪዳን በረከት ተሰጣት። በጥንት ኀብረተሰብ አመለካከት መሠረት ይህ በረከት (2ነገ 4፥14፤ ሩት 1፥11-12፤ 4፥15-17፤ ሉቃ 7፥12 ይመ) የመበለት ብቸኛ ተስፋ ልጅ ሲሆን፣ ይህችም መበለት ይህን በረከት ያገኘችው፣ በልጇ በኩል ነው።

17፥24 *የእግዚአብሔር ሰው መሆንህን፤* ይህች መበለት ኤልያስ የእግዚአብሔር ሰው መሆኑን (ቍ 18) አስቀድማ ተናግራ ነበር። አሁን ግን ተጨባጭ በሆነ መንገድ፣ በእርግጥ የእግዚአብሔር ነቢይ (የ12፥12 ማብ ይመ) መሆኑን ዐወቀች። *ከአንደበትህም የወጣው የእግዚአብሔር ቃል እውነት መሆኑን፤* ቃሉ ፍጹምና እውነት መሆኑን ለዚች ፊንቃዊት መበለት ለመግለጽ እግዚአብሔር ይህን መንገድ ተጠቀመ። ሴትዮዋ የተናገረችው እውነት፣ በእስራኤል ከነበሩት የእግዚአብሔር ሕዝብ ያልተገኘ ነበር።

18፥1 *በሦስተኛው ዓመት፤* ድርቅን የሚያመለክት ነው። ድርቁ ለሦስት ዓመት ከግማሽ ያህል እንደ ቈየ ወግ ይነገራል። (ከሉቃ 4፥25፤ ከያዕ 5፥17 ጋር ያነጻጽሩ)፤ ይህም የድርቁ ጊዜ ማጠሩን ለመግለጽ የቆመ ትእምርታዊ ቍጥር ይሆናል (የሰባት ዓመት ግማሽ፤ ዘፍ 41፥27፤ 2ነገ 8፥1 ይመ)። *ሂደህ ለአክዓብ ተገለጥ፤ እኔም በምድሪቱ ላይ ዝናብ አዘንባለሁ፤* ኤልያስ ወደ ሕዝቡ የተመለሰው እነርሱ በንስሓ ወደ እግዚአብሔር ስለተመለሱ ሳይሆን፣ እግዚአብሔር በጸጋው ራሱን ለሕዝቡ ለመግለጽ ፈልጎ ስለ አዘዘው ነው።

18፥3 *አብድዩ፤* በብሉይ ኪዳን የተለመደ ስም ሲሆን፣ ትርጕሙም "የእግዚአብሔር አገልጋይ" ማለት ነው። *የቤተ መንግሥቱን አዛዥ፤* የ4፥6 ማብ ይመ።

*18፥5፤* አክዓብ በዚህም ራብ እንኳ በንስሓ አልተመለሰም (ቀደም ሲል በዳዊት ዘመን የነበረውን ራብ (2ሳሙ 21፥1) ከአክዓብ ምላሽ ጋር ያነጻጽሩ)። ነገር ግን የሰራዊቱ ኀይል ተዳክሞ በነበረበት ጊዜ፣ ምግብና ውሃ ለማግኘት ምድሪቱን አሰሰ (10፥26 ይመ፤ በአሦር ንጉሥ በሜልሳዊ ሻልማንስር ታሪክ ውስጥ እንደ ተጠቀሰው አክዓብ ሁለት ሺህ የሠረገላ ሰራዊት ነበረው)።

18፥8 *ሂድና ለጌታህ 'ኤልያስ እዚሁ አለልህ' ብለህ ንገረው፤* አብድዩ ቀደም ሲል ኤልዛቤል ልትገድላቸው ትፈልጋቸው የነበሩትን ነቢያት በምስጢር መመገቡንና የኤልያስም ደጋፊ መሆኑን በግልጽ የሚያሳይ ነው (ቍ 4:13 ይመ)።

18፥12 *የእግዚአብሔር መንፈስ የት እንደሚወስድህ አላውቅም፤* ቀደም ብሎ የኤልያስ መሰወርና አሁን ደግሞ በድንገት

አምሳውን በሁለት ዋሻ በመሸሸግ እህልና
ውሃ ስጠኋቸው:: 14ታዲያ አንተ ሂጄ ለጌታዬ፤
'ኤልያስ እዚህ አለልህ' እንድለው ትፈልጋለህ፤
እርሱም ይገድለኛል!"
15ኤልያስም፣ "በፊቱ የቆምሁት ሁሉን
የሚገዛ ጌታ *እግዚአብሔርን*፣ ዛሬ አክዓብ
ፊት በእርግጥ እገለጣለሁ" አለ::

## ኤልያስ በቀርሜሎስ ተራራ ላይ

16ስለዚህ አብድዩ ሄዶ ይህንኑ ለአክዓብ
ነገረው፤ አክዓብም ኤልያስን ለማግኘት ሄደ::
17ኤልያስንም ባየው ጊዜ፤ "እስራኤልን የም
ታውክ አንተ ነህን?' አለው::
18ኤልያስም መልሶ እንዲህ አለ፤ "አን
ተና የአባትህ ቤት እንጂ እኔ እስራኤልን
አላወክሁም:: *የእግዚአብሔርን* ትእዛዝ ተዋ
ችሁ፣ እነበአልንም ተከተላችሁ:: 19አሁንም
ሕዝቡ በቀርሜሎስ ተራራ እንዲገናኘኝ ለመ
ላው እስራኤል ጥሪ አድርግ:: ከኤልዛቤል
ማእድ የሚቀለቡትን አራት መቶ አምሳ
ውን የበአል ነቢያት፣ አራት መቶውንም
የአሼራ ነቢያት አምጣቸው::"
20ስለዚህ አክዓብ በመላው እስራኤል ጥሪ
አደረገ፣ ነቢያቱንም በቀርሜሎስ ተራራ
ሰበሰበ:: 21ኤልያስም በሕዝቡ ፊት ቀርቦ፣
"በሁለት ሐሳብ የምትዋልሉት እስከ መቼ
ድረስ ነው? ስምላከ *እግዚአብሔር* ከሆነ
*እግዚአብሔርን* ተከተሉ፤ በአል አምላክ
ከሆነም በአልን ተከተሉ" አለ::
ሕዝቡ ግን አንዲት ቃል አልመለሱም::
22ከዚያም ኤልያስ እንዲህ አላቸው፤ "*ከእ
ግዚአብሔር* ነቢያት የተረፍሁ እኔ ብቻ ነኝ፤
በአል ግን አራት መቶ አምሳ ነቢያት አሉት::
23ሁለት ወይፈኖች ስጡን፤ እነርሱም አን
ዱን መርጠው ይውሰዱ፤ በየብልቱም ቈራ
ርጠው፣ በዕንጨት ላይ ያኑሩት፤ ግን እሳት
አያንድዱበት፤ እኔም ሁለተኛውን ወይፈን
አዘጋጃለሁ፤ በዕንጨትም ላይ አኖረዋለሁ፤
እሳት አላነድበትም:: 24ከዚያ እናንተ የአ
ምላካችሁን ስም ጥሩ፤ እኔም *የእግዚአብሔ
ርን* ስም እጠራለሁ፤ ሰምቶ በእሳት የሚ
መልሰውም እርሱ እውነተኛ አምላክ ነው::"
ከዚያም ሕዝቡ ሁሉ፣ "ያልኸው መልካም
ነው" አሉ::
25ኤልያስም ለበአል ነቢያት፣ "እናንተ ብዙ
ስለ ሆናችሁ በመጀመሪያ አንዱን ወይፈን
መርጣችሁ አዘጋጁ፤ የአምላካችሁን ስም
ጥሩ፤ ግን እሳት አታንድዱበት" አላቸው::
26ስለዚህ የተሰጣቸውን ወይፈን ወስደው አዘ
ጋጁት::
ከዚያም ከጧት እስከ እኩለ ቀን የበአልን
ስም ጠሩ፤ "በአል ሆይ ስማን" እያሉ ጮኹ፤
ድምፅ ግን የለም፤ የሚመልስ አልነበረም፤
በሠሩት መሠዊያ ዙሪያም ጨፈሩ::
27እኩለ ቀንም ላይ ኤልያስ፣ "ድምፃች
ሁን ከፍ አድርጋችሁ ጩኹ እንጂ! አምላክ
አይደለም እንዴ! ምናልባት በሐሳብ ተውጦ
ወይም ሥራ በዝቶበት፣ አልያም በጕዞ ላይ
ይሆናል፤ ተኝቶም ከሆነ ቀስቅሱት" እያለ
ያፌዝባቸው ጀመር:: 28ስለዚህ እየጮኹ
እንደ ልማዳቸው ደማቸው እስኪፈስ ድረስ
ሰውነታቸውን በሰይፍና በጦቤ ያቈስሉ
ነበር:: 29እኩለ ቀን ዐለፈ፤ እነርሱም የሠ
ርክ መሥዋዕት እስኪቀርብ ድረስ እየተራ
ወጡ ይዘላብዱ ነበር፤ አሁንም ድምፅ የለም፤
የመለሰና ከቁም ነገር የቈጠረውም አልነ
በረም::
30ከዚያም ኤልያስ ሕዝቡን በሙሉ፣ "ወደ
እኔ ቅረቡ" አላቸው፤ ሕዝቡም ሁሉ ወደ

18፥15 ቍ1
18፥17 ኢሱ7፥25፤ 1ሳሙ14፥29፤1ነገ 21፥20፤ኤር38፥4
18፥18 ዘዳ31፥16፤ 1ነገ16፥33፤21፥25
18፥19 ኢሱ19፥26፤ 2ነገ9፥22፤10፥19
18፥20 2ነገ2፥25፤ 4፥25
18፥21 ቍ39፤ኢሱ 24፥15፤2ነገ17፥41፤ መዝ100፥3፤118፥27፤ 119፥113፤ማቴ6፥24
18፥22 1ነገ19፥10፤ ኤር2፥8፤23፥13
18፥24 ቍ38፤ዘፍ 4፥26፤ዘፀ19፥18፤ዘሌ 9፥24፤1ሳሙ7፥8
18፥26 መዝ115፥ 45፤135፥16፤ኢሳ 41፥26፡28፤44፥17፤ 45፥20፤46፥7፤ኤር 10፥5፤1ቆሮ8፥4፤ 12፥2
18፥27 ዕን2፥19
18፥28 ዘሌ19፥28
18፥29 ዘፀ29፥41፤ 2ነገ19፥12፤ኢሳ 16፥12፤ኤር10፥5
18፥30 1ነገ19፥10

መምጣት፣ የእግዚአብሔር መንፈስ *ታምራዊ* በሆነ መንገድ ነቢዩን ከአንድ ቦታ ወደ ሌላ ቦታ እየወሰደው እንደ ሆነ አብድዩ ተገነዘበ (2ነገ 2፥16 *ይመ*)::

18፥13 *ኤልዛቤል...ነቢያት ባስገደለች ጊዜ፤* ዝናብ እንዲ ያዘንብ፣ በአልን ደስ ለማሰኘት ያደረገችው ሊሆን ይችላል:: *የእግዚአብሔር ነቢያት፤* በእስራኤል፣ ብዙዎች እምነታቸውን በተዉበት ወቅት (የ20፥35 ማብ ይመ) እግዚአብሔር ያስነሣቸው "የነቢያት" ጉባኤ አባላት ሊሆኑ ይችላሉ::

*18፥17 እስራኤልን የምታውክ፤* ኤልያስን፣ በእስራኤል ላይ ስለ ደረሰው ድርቅ የሞት ቅጣት የሚያስከትል ወንጀል በመንግሥት ላይ ፈጽመሃል ብሎ አክዓብ ወነጀለው:: ("*ሁከት ፈጣሪ*" ብሎም ይጠራዋል፤ ኢሱ 7፥25 *ይመ*)::

18፥18 *የእግዚአብሔርን ትእዛዝ ተዋችሁ፤ የበአልንም አማልክት ተከተላችሁ፤* በእስራኤል ላይ ለተፈጠረው ሁከት ምክንያቱ ኤልያስ ወይም ድርቁ ሳይሆን፣ ሕዝቡ የኪዳን እምነቱን በመተዉ ነው::

18፥19 *በቀርሜሎስ ተራራ፤* በሜዲትራንያን ባሕር አካባቢ የሚገኝ ከፍተኛ ተራራ ሲሆን፣ የድርቁ ሁኔታ ጐልቶ የማይታይበትና (አሞ 1፥2) የሕይወት ልምላሜን ለመስጠት የበአልን ኀይል አስተማማኝ የሚያደርግ ቦታ ነው:: *ከኤልዛቤል ማእድ የሚቀለቡትን፤* የ2፥7 ማብ ይመ:: *የበአል ነቢያት...የአሼራ ነቢያት፤* ቍ 29 እና ማብ ይመ:: *አሼራ፤* የ14፥15 ማብ ይመ::

18፥21 *የምትዋልሉት፤* በዕብራይስጡ ይህ ቃል በቍ 26 ላይ "እየዘለሉ ጨፈሩ" ተብሎ ተገልጾአል:: ኤልያስ የምፀት ቃል በመናገር፣ በእምነቷ እየዋለለች በነበረችበት ጊዜ፣ እስራኤል ያልተለመደና ከንቱ ሃይማኖታዊ "ጭፈራ" ታደርግ እንደ ነበር ይናገራል:: እግዚአብሔር አምላክ ከሆነ እግዚአብሔርን ተከተሉ፤ በአልም አምላክ ከሆነም በአልን ተከተሉ፤ ሕዝቡ የሚከተሉትን እንዲመርጡ ኤልያስ ያስታውቃቸዋል:: እግዚአብሔርንና በአልን በአንድ ላይ ማምለክ ይቻላል፣ የሚለውን የተሳሳተ አስተሳሰብ ለማረም፣ እግዚአብሔርንና በአልን በማምለክ መካከል ያለውን የጐላ ልዩነት ኤልያስ በማነጻጸር አቅርቧል::

18፥22 *ከ...ነቢያት የተረፍሁ እኔ ብቻ ነኝ፤* ንጉሡንና የበአልን ነቢያት ፊት ለፊት በድፍረት ለመቃወም የቻለ ብቸኛ ሰው ነበር (ሆኖም ግን ቍ 4፤ 19፥10:14፤ 20፥13:28:35፤ 22፥6:8 *ይመ*)::

*18፥24 ሰምቶ በእሳት የሚመልሰውም እርሱ እውነተኛ አምላክ ነው፤* እውነተኛው አምላክ፣ ዐውሎ ነፋስ መለኮታዊ ሠረገላው (*መዝ* 104፥3 እንዲሁም ማብ *ይመ*)፣ ነጐድጓድ ድምፁ (*መዝ* 29፥3-9 እንዲሁም ማብ *ይመ*)፣ መብረቅም መጣሪያው እንደ ሆነ (*መዝ* 18፥14 እንዲሁም ማብ *ይመ*) ተጠቅሶአል:: የኤልያስ ጥያቄ ቀጥተኛ ነው፤ ከዘሌ 9፥24 ጋር ያነጻጽሩ::

18፥26 *በሠሩት መሠዊያ ዙሪያም ጨፈሩ፤* አረማውያን ከሚፈጽሙት የአምልኮ ሥርዐት አንዱ ሲሆን፣ አማልክታቸው የሚፈልጉትን እንዲያደርጉላቸው ለማነሣሣት ሲሉ፣ በታላቅ ደስታ የሚገለጽ የአምልኮ ጭፈራ ነው::

18፥27 *በሐሳብ ተውጦ ... ተኝቶም፤* ኤልያስ በፌዝ መልክ የተናገረው፣ የበአልን ምንነት የሚያውቅ መሆኑን ያመለክታል::

18፥28 *ደማቸው እስኪፈስ ድረስ፤* ራስን አቍስሎ ደም እንዲፈስ ማድረግ፣ ራስን አሳልፎ የመስጠት ምሳሌ ሲሆን፣ አማልክትን ለተግባር የሚያነሣሣ ዘዴ እንደ ሆነ ይታመናል:: በዚህ ዐይነት ሰውነትን ማቍሰል በሙሴ ሕግ የተከለከለ ነበር (ዘሌ 19፥28፤ ዘዳ 14፥1)::

18፥29 *ይዘላብዱ ነበር፤* የአምልኮ ከፍተኛ ደረጃ ሥርዐት

እርሱ ቀረቡ፤ እርሱም ፈርሶ የነበረውን የእ
ግዚአብሔር መሠዊያ ሠራ:: [31]ከዚያም ኤል
ያስ፣ "ስምህ እስራኤል ይባላል" ተብሎ የእ
ግዚአብሔር ቃል በመጣለት በያዕቆብ ልጆች
ነገድ ቍጥር ልክ ዐሥራ ሁለት ድንጋይ
ወስዶ፤ [32]በድንጋዮቹም ለእግዚአብሔር ስም
መሠዊያ ሠራ፤ በመሠዊያውም ዙሪያ ዐሥራ
አምስት ሊትር ውሃ* የሚይዝ ጕድጓድ
ቈፈረ፤ [33]ዕንጨቱን ረበረበ፤ የወይፈኑንም
ሥጋ በየብልቱ ከቈረጠ በኋላ በዕንጨቱ
ላይ አኖረው:: ከዚያም፣ "ውሃ በአራት ጋን
ሞልታችሁ፣ በመሥዋዕቱና በዕንጨቱ ላይ
አፍስሱ" አላቸው::

[34]ደግሞም፣ "እንደ ገና ጨምሩበት" አላ
ቸው፤ እነርሱም ጨመሩበት::

"ሦስተኛም ጨምሩበት" ሲል አዘዛቸው፤
እነርሱም ለሦስተኛ ጊዜ ጨመሩበት:: [35]ውሃ
ውም በመሠዊያው ዙሪያ ፈሰሰ፤ ጕድጓዱንም
ሞላው::

[36]የሠርክ መሥዋዕት በሚቀርብበትም ጊዜ
ኤልያስ ወደ መሠዊያው ቀረብ ብሎ እን
ዲህ ሲል ጸለየ፤ "የአብርሃም፣ የይስሐቅና
የእስራኤል ስምላክ እግዚአብሔር ሆይ፤ አንተ
የእስራኤል ስምላክ መሆንህ፣ እኔም የአንተ
አገልጋይ መሆኔና ይህን ሁሉ በትእዛዝህ
እንዳደረግሁ ዛሬ ይታወቅ:: [37]ይህ ሕዝብ፣
አንተ ስምላክ እግዚአብሔር እውነተኛ መሆ
ንህንና ልባቸውን የመለስኸው አንተ መሆ
ንህን ያውቁ ዘንድ እባክህ ስማኝ፤ እግዚአ
ብሔር ሆይ፤ እባክህ መልስልኝ::"

[38]ከዚያም የእግዚአብሔር እሳት ወርዳ
መሥዋዕቱን፣ ዕንጨቱን፣ ድንጋዩንና ዐፈሩን
ፈጽማ በላች፤ በጕድጓዱ ውስጥ ያለውንም
ውሃ ላሰች::

[39]ሕዝቡም ሁሉ ይህን ሲያዩ፣ በግንባራ
ቸው ተደፍተው፣ "ስምላክ እግዚአብሔር እርሱ
እውነተኛ ነው! እግዚአብሔር እርሱ እውነ
ተኛ ስምላክ ነው!" አሉ::

[40]ከዚያም ኤልያስ፣ "የበአልን ነቢያት
ያዟቸው! አንድም ሰው እንዳያመልጥ" ሲል
አዘዘ፤ ሕዝቡም ያዟቸው፤ ኤልያስም ወደ
ቂሶን ወንዝ አውርዶ አሳረዳቸው::

[41]ኤልያስም አክዓብን፣ "የከባድ ዝናብ
ድምፅ ይሰማልና ሂድና ብላ፤ ጠጣም" አለው::
[42]ስለዚህ አክዓብ ሊበላና ሊጠጣ ሄደ፤ ኤል
ያስ ግን ወደ ቀርሜሎስ ተራራ ጫፍ ወጣ፤
ፊቱንም በጕልበቶቹ መካከል አድርጎ ወደ
መሬት አቀረቀረ::

[43]አገልጋዩንም፣ "ውጣና ወደ ባሕሩ ተመ
ልከት" አለው::

አገልጋዩም ሄዶ ተመለከተና፤ "በዚያ ምንም
የለም" አለው::

ኤልያስ ሰባት ጊዜ፣ "እንደ ገና ሂድ"
አለው::

[44]በሰባተኛው ጊዜ አገልጋዩ፣ "እነሆ፤
የሰው እጅ የምታህል ትንሽ ደመና ከባሕሩ
እየወጣች ነው" አለው::

ኤልያስም፣ "ሂድና አክዓብን፣ 'ዝናቡ
ሳያግድህ፣ ሠረገላህን ጭነህ ውረድ' ብለህ
ንገረው" አለው::

[45]ወዲያውኑም ሰማዩ በጥቍር ደመና
ተሸፈነ፤ ነፋሱ ነፈሰ፤ ከባድ ዝናብ ጣለ፤
አክዓብም በሠረገላ ተቀምጦ ወደ ኢይዝራ
ኤል ሄደ:: [46]የእግዚአብሔርም ኀይል
በኤልያስ ላይ ወረደ፤ ኤልያስም ልብሱን
ከፍ አድርጎ በቀበቶው ካጠበቀ በኋላ እስከ
ኢይዝራኤል ድረስ በአክዓብ ፊት ሮጠ::

## ኤልያስ ወደ ኮሬብ ኰበለለ

**19** አክዓብ በዚህ ጊዜ፣ ኤልያስ ያደረ
ገውን በሙሉ፣ ነቢያቱንም ሁሉ
እንዴት በሰይፍ እንዳስገደላቸው ለኤልዛ
ቤል ነገራት:: [2]ስለዚህም እርሷ፣ "ነገ በዚህ
ሰዓት ያንተንም ነፍስ ከእነዚያ እንደ አንዱ
ነፍስ ሳላደርጋት ብቀር አማልክት እንዲህ

*32 15 ሊትር ያህል ነው

18፥31 ዘፍ17፥5፤ 2ነገ17፥34
18፥32 ዘጸ18፥7፤ ቆላ3፥17
18፥33 ዘፍ22፥9
18፥36 ዘፍ24፥12፤ ዘፀ4፥5፤29፥39፡41፤ ዘኍ16፥28፤ኢሱ4፥24፤1ሳሙ17፥46፤ መዝ46፥10፤ ማቴ22፥32
18፥37 ኢሱ4፥24
18፥38 ቍ24፤ዘፀ19፥18፤ዘሌ9፥24፤2ነገ1፥10፤1ዜና21፥26፤ 2ዜና7፥1፤ኢዮ1፥16
18፥39 ቍ21፤ዘሌ9፥24፤መዝ46፥10
18፥40 ዘፀ22፥20፤ ዘዳ17፥12፤መሳ4፥7፤2ነገ11፥18
18፥42 1ሳሙ12፥ 17፤ያዕ5፥18
18፥44 ኢሱ6፥15፤ ሉቃ12፥54
18፥45 1ሳሙ29፥1፤1ነገ8፥36፤ ኢዮ37፥13፤ሆሴ1፥4
18፥46 መሳ3፥10፤ 1ሳሙ11፥6፤2ነገ4፥29፤9፥1፤ ሉቃ1፥35፤4፥14
19፥1 ዘፀ22፥20፤ 1ነገ16፥31
19፥2 ሩት1፥17፤ መዝ13፥4፤ኤር20፥10፤26፥21፤ 36፥26

ሲሆን፣ በደስታ መፈንጠዛቸውን ያመለክታል (የ1ሳሙ 10፥5፤ 18፥10 ማብ ይመ):: የሠርክ መሥዋዕት፤ ዘፀ 29፥38-41፤ ዘኍ 28፥3-8 ይመ:: የመለሰና... አልነበረም፤ በአል ችሎታ እንደ ሌለው የሚገልጽ አስደናቂ ትዕይንት ነው (መዝ 115፥ 5-8፤ 135፥15-18፤ ኤር 10፥5 ይመ)::

18፥30 ፈርሶ የነበረውን የእግዚአብሔር መሠዊያ፤ የእስ ራኤል መንግሥት ለሁለት ከተከፈለ በኋላ፣ መሠዊያው በሰሜን በሚኖሩ ዐሥሩ ነገድ ሕዝቦች ተሠርቶ (የ3፥2 ማብ ይመ) ኤልዛቤል እንዲፈርስ አስደርጋ ይሆናል (ቍ 4:13፤ 19፥10:14)::

18፥31 በያዕቆብ ልጆች ነገድ ቍጥር ልክ ዐሥራ ሁለት ድንጋይ፤ እስራኤል በፖለቲካ ምክንያት ለሁለት ብትከፈልም፣ በኪዳን አንድ የእግዚአብሔር ሕዝብ በመሆናቸው ኤልያስ በዚህ ሁኔታ ሊያስገነዝባቸው ችሏል። ሲሆን ያለው ነገር የሰሜኑን ዐሥር ነገድ ብቻ የሚመለከት ሳይሆን፣ የተቀሩትንም ነገዶች የሚመ ለከት ነበር::

18፥33 ውሃ፤ ኤልያስ በመሠዊያው ላይ በተደጋጋሚ ውሃ በመጨመር፣ ድርጊቱ ማታለል እንደሌለበት ለሁሉም ገለጸ::

18፥36 ጸለየ፤ እውነተኛ የሆነው የኤልያስ ግልጽ ጸሎት፣ ሰውነትን በማቍሰል፣ ብባዶ ጩኸትና ጭፈራ ታጅቦ ከቀረበው ከበኣል ነቢያት ጸሎት ጋር በጉላ ልዩነት ተወዳድሯል:: የአብር ሃም፣ የይስሐቅና የእስራኤል አምላክ፤ እግዚአብሔር ጥንት ከር እሳን አበው ጋር ያደረገውን ኪዳኑን እንዲያስብ፣ የቀረበ ልመናና እስራኤልም ከርእሳን አበው ዘመን ጀምሮ እግዚአብሔር ያደረገ ላትን ውለታ የሚያስታውስ ነው::

18፥38 የእግዚአብሔር እሳት ወርዳ፤ የቍ 24 ማብ ይመ::

18፥40 አሳረዳቸው፤ ኤልያስ፣ በላከው በአምላኩ በእግዚአ ብሔር ሥልጣን፣ በሙሴ ሕግ መሠረት በአረማውያን የአማል ክት ነቢያት ላይ ሊደርስ የሚገባውን ቅጣት ፈጸመባቸው (ዘዳ 13፥13-18፤ 17፥2-5)::

18፥41 የከባድ ዝናብ ድምፅ፤ የበኣል አምልኮ በጽኑ ስለ ተመታ፣ ዝናብ እንደሚዘንብ የሚያመለክት ተስፋ ነው (17፥1 ይመ):: አክዓብ በሙሴ ሕግ መሠረት ቅጣት ለመፈጸም ወይም ኤልያስን ለመከልከል ምንም ዐይነት እርምጃ አልወሰደም ነበር::

18፥42 ኤልያስ ... ፊቱንም በጕልበቶቹ መካከል አድርጎ ወደ መሬት አቀረቀረ፤ እግዚአብሔር ብቻ እውነተኛ አምላክ እንደ ሆነ ሕዝቡ ስለ ዐወቀ፣ የኪዳኑ ርግማን እንዲወገድና (የ17፥1 ማብ ይመ)፣ ዝናብ እንዲዘንብ (8፥35፤ 2ዜና 7፥13-14 ይመ) ኤልያስ ጸለየ::

18፥43 ሰባት ጊዜ፤ ፍጹምነትን የሚያመለክት ቍጥር ነው::

18፥44 ከባሕሩ እየወጣች፤ ደመናው የታየው በስተ ምዕራ ብ በኩል እንደ ነበር ያመለክታል::

18፥46 እስከ ኢይዝራኤል ድረስ በአክዓብ ፊት ሮጠ፤ አስደናቂ በሆነ በመለኮት ሥልጣን ኤልያስ፣ እስከ ኢይዝራኤል ድረስ በአክዓብ ሠረገላ ፊት ሮጠ:: የእግዚአብሔር ነቢይ ከንጉሡ ፊት መሮጡና እግዚአብሔርም በዐውሎ ነፋስ ሠረገላ ሆኖ (የቍ

ያድርጉብኝ፤ ከዚህ የባሰም ያምጡብኝ” ስትል
ወደ ኤልያስ መልእክተኛ ላከች::
[3]ኤልያስም ፈርቶ[ዐ] ስለ ነበር፣ ሕይወቱን
ለማትረፍ ሲል ሸሸ:: በይሁዳ ምድር ወዳለ
ችው ወደ ቤርሳቤህ እንደ መጣም አገልጋ
ዩን በዚያ ተወው፤ [4]በምድረ በዳም ውስጥ
የአንድ ቀን መንገድ ተጓዘ፤ ወደ አንድ
ክትክታ ዛፍ እንደ መጣም፣ ከሥሩ ተቀምጦ፣
ይሞት ዘንድ “እግዚአብሔር ሆይ፤ በቃ
ኝል፤ እኔ ከቀደሙት አባቶቼ አልበልጥ
ምና ነፍሴን ውሰዳት” ብሎ ጸለየ:: [5]ከዚያም
ከዛፍ ሥር ተጋደመ፤ እንቅልፍም ወሰደው::
በድንገትም አንድ መልአክ ነካ አደረገ
ውና፣ “ተነሥና ብላ” አለው:: [6]ዞወር ብሎ
ሲመለከትም፣ እነሆ፣ በፍም የተጋገረ እንጎ
ቻና አንድ ገንቦ ውሃ ከራስጌው አገኘ፤ ከበ
ላና ከጠጣም በኋላ ተመልሶ ተኛ::
[7]የእግዚአብሔርም መልአክ እንደ ገና መጥቶ
ነካ አደረገውና፣ “ሩቅ መንገድ ስለምትሄድ
ተነሥና ብላ” አለው:: [8]ስለዚህም ተነሥቶ
በላ፤ ጠጣም፤ በምግቡም ብርታት አግኝቶ
ወደ እግዚአብሔር ተራራ ወደ ኮሬብ እስ
ኪደርስ አርባ ቀንና አርባ ሌሊት ተጓዘ፤
[9]በዚያም ወደ አንዲት ዋሻ ገብቶ ዐደረ::

## እግዚአብሔር ለኤልያስ ተገለጠለት

የእግዚአብሔርም ቃል ወደ እርሱ መጣ፤
“ኤልያስ ሆይ፤ እዚህ ምን ታደርጋለህ?”
አለው::
[10]እርሱም፣ “እኔ ለሰራዊት ጌታ ለእግዚ
አብሔር እጅግ ቀንቻለሁ፤ እስራኤላውያን
ኪዳንህን ትተዋል፤ መሠዊያዎችህን አፍርሰ
ዋል፤ ነቢያትህንም በሰይፍ ገድለዋልና:: የቀ
ረሁት እኔ ብቻ ነኝ፤ አሁንም እኔን ለመ
ግደል ይፈልጋሉ” አለ::
[11]እግዚአብሔርም “እግዚአብሔር በዚያ
ያልፋልና ወደ ተራራው ወጥተህ በእግዚአ
ብሔር ፊት ቁም” አለው::
ከዚያም ታላቅና ኀይለኛ ነፋስ ተራሮቹን
ሰነጣጠቀ፤ አለቶችንም በእግዚአብሔር ፊት
ብትንትናቸውን አወጣ፤ እግዚአብሔር ግን
በነፋሱ ውስጥ አልነበረም፤ ከነፋሱም ቀጥሎ
የምድር መነዋወጥ ሆነ፤ እግዚአብሔር ግን
በምድር መነዋወጡ ውስጥ አልነበረም:: [12]ከም
ድር መነዋወጡም ቀጥሎ እሳት መጣ፤ እግ
ዚአብሔር ግን በእሳቱ ውስጥ አልነበረም፤
ከእሳቱም ቀጥሎ ለስለስ ያለ ድምፅ ተሰማ::
[13]ኤልያስም ይህን ሲሰማ፣ ፊቱን በመጐና
ጸፊያው ሸፍኖ ወጣና በዋሻው ደጃፍ ቆመ::
ከዚያም፣ “ኤልያስ ሆይ፤ እዚህ ምን
ታደርጋለህ?” የሚል ድምፅ ሰማ::
[14]እርሱም፣ “እኔ ሁሉን ለሚችል ጌታ ለእግ
ዚአብሔር እጅግ ቀንቻለሁ፤ እስራኤላውያን
ኪዳንህን ትተዋል፤ መሠዊያዎችህን አፍርሰ
ዋል፤ ነቢያትህንም በሰይፍ ገድለዋልና::
የቀረሁት እኔ ብቻ ነኝ፤ አሁንም እኔን
ለመግደል ይፈልጋሉ” አለ::
[15]እግዚአብሔርም እንዲህ አለው፤ “በመ
ጣህበት መንገድ ተመልሰህ ወደ ደማስቆ
ምድረ በዳ ሂድ፤ እዚያ ስትደርስም አዛሄልን

[ዐ]3 ወይም ኤልያስ አይቶ ተብሎ ሊተረጐም ይችላል

19፥3 ዘፍ19፥17፤ 31፥21፤ኢሱ19፥2
19፥4 ዘኍ11፥15፤ ኢዮ6፥9፤7፥16፤ 10፥1፤30፥41መዝ69፥ 19፤ኤር20፥18፤ ዩና4፥18
19፥5 ዘፍ16፥7፤ 28፥11
19፥8 ዘፀ3፥1፤ 24፥18፤ማቴ4፥2
19፥9 ዘፍ3፥9፤ ዘፀ33፥22
19፥10 ዘኍ25፥13፤ ዘዳ31፥16፤1ነገ18፥22 ፡30፤ኤር5፥11፤9፥21 ሐሥ22፥3፤ሮሜ 11፥13፤ገላ4፥18
19፥11 ዘፀ14፥21፤ 33፥19፤34፥2፤2ነገ 2፥1፤ናሆ1፥6፤ ማቴ17፥13
19፥12 ቍ11፤ዘፀ 3፥2፤1ሳሙ14፥6፤ ኢዮ4፥16፤ዘካ4፥6፤ 2ቆሮ12፥9
19፥13 ዘ3፥6
19፥14 1ነገ 18፥22፤ሮሜ11፥3
19፥15 2ነገ8፥7-15

24 ማብ ይመ) ነቢዩን መከተሉ ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ አክዓብ በአልን ማምለክ ትቶ፣ እንደ እግዚአብሔር አገልጋይ፣ ሕዝቡን እንዲመራ የሚያደርግ ጥሪ ነበር::

19፥2 *ከእነዚያ እንደ አንዱ፤* ከሞቱት የበአል ነቢያት ማለት ነው (ቍ 1):: *አማልክት እንዲህ ያድርጉብኝ፤ ከዚህ የባሰም ያምጡብኝ፤* የተለመደ የርግማን አገላለጽ ነው (1ሳሙ 3፥17 ማብ ይመ)::

19፥3 *ኤልያስም ፈርቶ ስለ ነበር፤ ሕይወቱን ለማትረፍ ሲል ሸሸ፤* በቀርሜሎስ ተራራ ላይ የኤልያስ አምላክ የሰማይና የምድር ጌታ እግዚአብሔር፣ የእስራኤልም የበረከት ምንጭ መሆኑን በማስመስከር ኤልያስ ታላቅ ድል ያገኘ ቢሆንም፣ ኤልዛቤል በሁኔታው ተስፋ አልቆረጠችም:: ኤልዛቤል እንዲህ ቈርጣ ስትነሣ አክዓብ በማይታወቅ ምክንያት ከክፉ አድራጎቷ ሊመልሳት አልቻለም ነበር:: እስራኤል የጣዖት አምልኮን እንድትለማመድ ካደረጉት መካከል ከፍተኛ አስተዋፅኦ ያደረገችው ኤልዛቤል በሕይወቱ ላይ አደጋ ለማድረስ እንደ ተዘጋጀች ኤልያስ ተረድቷል:: *ቤርሳቤህ፤* በይሁዳ ደቡባዊ ጫፍ የምትገኝ ከተማ ናት (የዘፍ 21፥31፤ የአሞ 5፥5 ማብ ይመ እንዲሁም መሳ 20፥1 ይመ)::

19፥4 *ክትክታ ዛፍ፤* ትልቅ በሚሆንበት ጊዜ ጥላ መስጠት የሚችል፣ በምድረ በዳ የሚገኝ የቍጥቋጦ ዛፍ ነው:: *ነፍሴን ውሰዳት አለ፤* ከዮና 4፥3:8 ጋር ያነጻጽሩ:: ኤልያስ አገልግሎቱ ፍሬ ቢስ እንደሆነና በሕይወት መኖሩ ትርጒም እንደሌለው አድርጎ አሰበ:: ስለ እግዚአብሔር መንግሥት አሸናፊነት የነበረውን ትምክህት በማጣቱ፣ ከአገልግሎቱ ማፈግፈግ ጀመረ::

19፥7 *የእግዚአብሔርም መልአክ፤* የዘፍ 16፥7 ማብ ይመ:: እግዚአብሔር ተስፋ ለቈረጠው አገልጋዩ በምሕረቱ የሚበላውን ምግብና ዕረፍትን ሰጠው:: *ሩቅ መንገድ ስለምትሄድ፤* ኤልያስ፣ እግዚአብሔር ከሕዝቡ ጋር ኪዳን ወደ አደረገበት ወደ ኮሬብ ተራራ እንዲሄድ ወስኖ ነበር:: ቀደም ሲል እግዚአብሔር ኤልያስን ወደ ኮራት (17፥2-3)፣ ወደ ሰራፕታና (17፥8-9)፣ አክዓብንም ያገኝ ዘንድ (18፥1) እንደመራው ሁሉ፣ በዚህ ጊዜ ግን መርቶት እንደ ሆነ የሚያመለክት ነገር የለም::

19፥8 *አርባ ቀንና አርባ ሌሊት፤* ሙሴ በሲና ተራራ (ዘፀ 24፥18፤ 34፥28)፣ ኢየሱስም በምድረ በዳ (ማቴ 4፥2:11) የቈየውን ያህል፣ ኤልያስንም እንዲሁ በኮሬብ ተራራ እንዲቈይ እግዚአብሔር አደረገው:: *ወደ እግዚአብሔር ተራራ ወደ ኮሬብ፤* የሲና ተራራ የሚጠራበት ሌላው ስሙ ሊሆን ይችላል (ዘፀ 3፥1፤ 19፥1-3 ይመ)፤ የሚገኘውም ከቤርሳቤህ በስተ ደቡብ አራት መቶ ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ ባለው ምድረ በዳ ውስጥ ነው::

19፥9 *ኤልያስ ሆይ፤ እዚህ ምን ታደርጋለህ?* ኤልያስ ወደ ሲና የመጣው እግዚአብሔር ልኮት ሳይሆን፣ በራሱ ምክንያት እንደ ሆነ ጥያቄው ያመለክታል::

*19፥10፤* እግዚአብሔር ለጠየቀው ጥያቄ፣ ቀጥተኛ የሆነ መልስ ባይሰጥም፣ ኤልያስ የሰጠው መልስ፣ ከመቶ ዓመት በፊት በሲና ተራራ ላይ እግዚአብሔር ከሕዝቡ ጋር ከገባው ኪዳን የተነሣ፣ የጀመረው ሥራ ውጤት አልባ ሆኖ እንደቀረ ያመለክታል:: እስራኤላውያን የወርቅ ጥጃ በማምለክ እግዚአብሔርን በበደሉ ጊዜ (ዘፀ 32፥11-13)፣ ሙሴ ስለ እነርሱ በጸሎት ማለደ፤ ኤልያስ ግን ኪዳኑን በማፍረሳቸው፣ በእስራኤላውያን ላይ በመፍረድ፤ የራሱንም ድካም ፍሬ ቢስ አድርጎ በመቁጠር እጅግ አማረረ:: *የቀረሁት እኔ ብቻ ነኝ፤* የ18፥22 ማብ ይመ::

19፥12 *ለስለስ ያለ ድምፅ፤* የእግዚአብሔር አገልጋይ ኤልያስ በእስራኤል ላይ ያቀረበው ክስ፣ እግዚአብሔር ሕዝቡን በዐውሎ ነፋስ፣ በመሬት መንቀጥቀጥና በእሳት እንዲቀጣ ፈልጎ ቢሆንም፣ እግዚአብሔር ግን ሕዝቡን በዚህ ሁኔታ ሊቀጣ አለመፍቀዱን በዚህ ትእምርት ለነቢዩ በግልጽ ስለአሳወቀው (ቍ 11-12)፣ ነቢዩ እግዚአብሔር የሰጠውን ተልእኮ ለመፈጸም ወደ ሕዝቡ መመለስ ነበረበት፤ ይህንም ተልእኮ ለመፈጸም በኤልያስ ፈንታ የተተካው ነቢይ ኤልሳዕ ነው (ቍ 16)::

19፥13 *ኤልያስ ሆይ እዚህ ምን ታደርጋለህ?* በነፋስ፣ በምድር መናወጥና በእሳቱ ውስጥ ሳይሆን፣ ረጋ ባለ ድምፅ ውስጥ እግዚአብሔር ራሱን መግለጹ ቀደም ሲል ኤልያስ ይህንኑ ጥያቄ ተጠይቆ በነበረበት ጊዜ የሰጠውን መልስ እንደገና እንዲያጤነው ተጨማሪ ዕድል ለመስጠት ነው (ቍ 9-10)::

*19፥14፤* ኤልያስ ሳያስተውል የሰጠው መልስ፣ የተሰጠውን

በሶርያ ላይ እንዲነግሥ ቅባው:: [16]እንዲሁም
የናሜሲን ልጅ ኢዩን በእስራኤል ላይ እንዲ
ነግሥ ቅባው፤ ደግሞም ነቢይ ሆኖ በእግርህ
እንዲተካ የአቤል ምሖላን ሰው የሣፋጥን
ልጅ ኤልሳዕን ቅባው:: [17]ከአዛሄል ሰይፍ
ያመለጠውን ኢዩ ይገድለዋል፤ ከኢዩ ሰይፍ
ያመለጠውን ደግሞ ኤልሳዕ ይገድለዋል::
[18]እኔም ጕልበታቸው ለበኣል ያልተንበረከ
ከውንና አፋቸው ምስሉን ያልሳመውን ሰባት
ሺህ ሰዎች በእስራኤል አስቀራለሁ::”

## የኤልሳዕ መጠራት

[19]ስለዚህ ኤልያስ ከዚያ ተነሥቶ ሲሄድ
የሣፋጥን ልጅ ኤልሳዕን ዐሥራ ሁለት ጥማድ
በሬ አውጥቶ ራሱ በዐሥራ ሁለተኛው ጥማድ
በሬ ሲያርስ አገኘው:: ኤልያስም ወደ እርሱ
ወጥቶ መጐናጸፊያውን በላዩ ጣለበት:: [20]ከዚ
ያም ኤልሳዕ በሬዎቹን ትቶ ኤልያስን ተከ
ትሎ እየሮጠ፣ “አባቴንና እናቴን ስሜ እን
ድሰናበታቸው ፍቀድልኝ፤ ከዚያም እከተ
ልሃለሁ” አለው::

ኤልያስም መልሶ፣ “እኔ ምን ያደረግሁህ
ነገር አለ? ልትመለስ ትችላለህ” አለው::

[21]ስለዚህም ኤልሳዕ ትቶት ተመለሰ:: ሁለ
ቱን በሬዎቹን ወስዶ ዐረደ፤ የዕርሻ ዕቃውን
አንድዶ ሥጋቸውን በመቀቀል ለሕዝቡ
ሰጠ፤ እነርሱም በሉ:: ከዚያም ኤልያስን
ለመከተል ሄደ፤ ረዳቱም ሆነ::

19፥16 ቍ21፤ መሳ7፥22፤2ነገ2፥1፤ 3፥11፤9፥6
19፥17 2ነገ8፥12፡ 29፤10፥32፤12፥17፤ 13፥3:7:22፤ኤር 48፥44፤አሞ1፥4
19፥18 ሆሴ13፥2፤ ሮሜ11፥4
19፥19 ዘፍ41፥42፤ 2ነገ2፥8:14፤
19፥20 ሉቃ9፥61
19፥21 ቍ16፤ 1ሳሙ6፥14
20፥1 1ነገ13፥32፤ 15፥18
20፥7 1ሳሙ11፥3፤ 2ነገ5፥7

## ቤን ሀዳድ ሰማርያን ወጋ

20 በዚህ ጊዜ የሶርያ ንጉሥ ቤን ሀዳድ
መላ ሰራዊቱን በአንድነት አሰባሰበ፤
ከእርሱም ጋር ሠላሳ ሁለት ነገሥታት ከነ
ፈረሶቻቸውና ከነሠረገሎቻቸው አብረውት
ነበሩ፤ ወጥቶም ሰማርያን ከቦ ወጋት:: [2]ወደ
ከተማዪቱም መልእክተኞች በመላክ የእስራ
ኤልን ንጉሥ አክዓብን እንዲህ አለው፤ “ቤን
ሀዳድ እንዲህ ይላል፤ [3]‘ብርና ወርቅህ የእኔ
ነው፤ የሚያማምሩት ሚስቶችህና ልጆችህም
የእኔ ናቸው::’ ”

[4]የእስራኤልም ንጉሥ፣ “ንጉሥ ጌታዬ ሆይ፤
ልክ እንዳልኸው ነው እኔም ሆንሁ የእኔ
የሆነው ሁሉ የአንተ ነው” ሲል መለሰለት::

[5]መልክተኞቹም እንደ ገና መጥተው እን
ዲህ አሉት፤ “ቤን ሀዳድ የሚለው ይህ ነው፤
‘ብርህንና ወርቅህን፣ ሚስቶችህንና ልጆች
ህን እንድትሰጠኝ ልኬብህ ነበር፤ [6]ሆኖም ነገ
በዚሁ ጊዜ ቤተ መንግሥትህንና የሹማምት
ህን ቤቶች እንዲበረብሩ፣ ሹማምቴን እል
ካቸዋለሁ:: እነርሱም ማናቸውንም ለአንተ
ዋጋ ያለውን ሁሉ በእጃቸው በማስገባት
ይወስዱታል::’ ”

[7]የእስራኤልም ንጉሥ የአገሩን ሽማግሌ
ዎች ሁሉ ጠርቶ፣ “ይህ ሰው እንዴት ጠብ
እንደሚፈልግ ታያላችሁ! ሚስቶቼንና ልጆ
ቼን፣ ብሬንና ወርቄን እንዳስረክበው በጠየ
ቀኝ ጊዜ አልከለከልሁትም” አላቸው::

[8]ሽማግሌዎቹና ሕዝቡም ሁሉ፣ “የሚልህን

---

መለኮታዊ መገለጥ፣ በቅጡ ያልተረዳው መሆኑን ያመለክታል::

19፥15 *እግዚአብሔርም እንዲህ አለው፤* እግዚአብሔር፣ ለኤልያስ የሰጠው መመሪያ፣ በሕዝቦችና በነገሥታት ላይ ያለውን ሉዐላዊ ሥልጣን የሚያሳይ ነው:: በአዛሄል፣ በኢዩና በኤልሳዕ አማካኝነት በእስራኤል ላይ መለኮታዊ ፍርድ የሚደርስ ቢሆንም፣ ከሕዝቡ መካከል ታማኝ የሆኑ ሰዎችን እግዚአብሔር ለራሱ ለይቶ እንደሚጠብቅ ግልጽ ነው:: *ወደ ደማስቆ ምድረ በዳ ሂድ፤* ኤልያስ፣ ከሙት ባሕርና ከዮርዳኖስ ወንዝ በስተ ምሥራቅ ባለው መንገድ ተመልሶ መሄድ እንዳለበት ያመለክታል:: ሦስቱ የተቀቡት አዛሄል፣ ኢዩና ኤልሳዕ ከዮርዳኖስ ወንዝ በስተ ምሥራቅ ቢሆንም፣ ሁለቱን ነገሥታት የቀባው ግን ኤልሳዕ ነው:: *ቅባው፤* እዚህ ላይ “በእግዚአብሔር የተመረጠ ሹም” መሆኑን ብቻ የሚያመላክት ይመስላል:: መቀባቱ የተፈጸመው በኤልያስ ፈንታ በተተካው በኤልሳዕ ነው (2ነገ 8፥7-15 ይመ):: *አዛሄል፤* በኢዮራም፣ በኢዩና በኢዮአካዝ ዘመነ መንግሥት እስራኤልን በጽኑ የሚፈታተን ጠላት ነበር (2ነገ 8፥28-29፤ 10፥32-33፤ 12፥17-18፤ 13፥3:22 ይመ)::

19፥16 *ኢዩን…ቅባው፤* በአክዓብና በልጁ በኢዮራም ዘመነ መንግሥት፣ ኢዩ የጦር አዛዥ ነበር (2ነገ 9፥5-6):: በኤልሳዕ ትእዛዝ መሠረት (2ነገ 9፥1-16) “ከነቢያት ጉባኤ በሆነ አንድ ሰው” የአክዓብን ቤት እንዲያፈርስ ተቀባ:: *ኢልሳዕ፤* እንደ ኤልያስ (የ17፥1 ማብ ይመ) የኤልሳዕ ስም ትርጕሙ “እግዚአብሔር ድነት ነው” ወይም “እግዚአብሔር ያድናል” ማለት ሲሆን፣ ሊፈጽም ከሚገባው አገልግሎት ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት አለው:: የስሙ ትርጕም የኢያሱን ስም የሚያስታውስ ነው:: ሙሴ የጀመረውን አገልግሎት ከዳር በማድረስ የእስራኤልን ሕዝብ ወደ ተስፋዪቱ ምድር እንዲያስገባ ኢያሱ በእግሩ እንደ ተተካ ሁሉ፣ በኤልያስ ፈንታ በእስራኤል ለሚኖሩ ታማኝ የእግዚአብሔር ሰዎች የኪዳኑን በረከት እንዲያስተላልፍ የተተካው ኤልሳዕ ነው (የኤልሳዕን አገልግሎት በተመለከተ፣ 2ነገ 2፥19-8፥15፤ 9፥1-3፤ 13፥14-20፤ ይመ):: በአዲስ ኪዳን ኢየሱስ (“ኢያሱ” ማቴ 1፥21)፣ የእግዚአብሔርን የማዳን ሥራ ይፈጽም ዘንድ፣ ከመጥምቁ ዮሐንስ (“ኤልያስ” ማቴ 11፥14፤ 17፥12) በኋላ መጥቶ ነበር:: *የአቤል ምሖላን ሰው፤* እንደ ኤልያስ፣ ኤልሳዕም የዮርዳኖስ ማዶ አገር ሰው ነበር:: *የሣፋጥን ልጅ፤* ሣፋጥ ማለት “እግዚአብሔር ይፈርዳል” ማለት ሲሆን፣ ይህም ከኤልሳዕ አገልግሎት ጋር የሚስማማ ነው::

19፥17 *ከአዛሄል ሰይፍ ያመለጠውን ኢዩ ይገድለዋል፤* 2ነገ 9፥24 ይመ:: *ከኢዩ ሰይፍ ያመለጠውን ደግሞ ኤልሳዕ ይገድለዋል፤* ይህ እንዴት ሆኖ እንደሚፈጸም አልተገለጸም፤ ሆኖም 2ነገ 2፥24፤ 8፥1 ይመ (እንዲሁም ሆሴ 6፥5 ይመ)::

19፥18 *ምስሉን ያልሳመውን፤ ሰባት ሺህ፤* ሆሴ 13፥2 ይመ:: በአምላክ ኀይል የተጠበቁትን የእግዚአብሔር ቅሬታዎች (ሮሜ 11፥2-4) የሚያመለክት ፍጹም ቁጥር ነው:: ሆኖም፣ ኤልያስ በዚያን ጊዜ ለእግዚአብሔር ታማኝ ሆኖ የተገኘ እርሱ ብቻ እንደ ሆነ መቍጠሩ ስሕተት ነበር (ቍ 10:14፤ 18፥22 ይመ)::

19፥19 *መጐናጸፊያውን በላዩ ጣለበት፤* ኤልሳዕ፣ በኤልያስ ፈንታ የሚተካ መሆኑን ያመለክታል (የቍ 16 ማብ ይመ)::

19፥21 *በሬዎቹን ወስዶ ዐረደ፤ የእርሻ ዕቃውን አንድዶ፤* ከሀብታም ቤተ ሰብ የሆነው ኤልሳዕ፣ ቀደም ሲል ይሰራ የነበረውን ሥራ ሙሉ በሙሉ ትቶ ተከተለው:: *ለመከተል፤* ይህ ቃል በዕብራይስጥ ኢያሱ ከሙሴ ጋር የነበረው ግንኙነት የተገለጠበት ነው:: (“ረዳት”፤ ዘፀ 24፥13፤ 33፥11)::

20፥1 *የሶርያ ንጉሥ ቤን ሀዳድ፤* የቀዳማዊ ቤን ሀዳድ ልጅ ወይም የልጅ ልጅ የሆነው ዳግማዊ ቤንሀዳድ ሲሆን፣ እርሱም ዓ.ቅ.ክ. 900-895 ድረስ ሶርያን ይገዛ ነበር (የ15፥9-10:18-20:33 ማብ ይመ):: በዚህ ምዕራፍ ውስጥ የተጠቀሰው ታሪክ የተፈጸመው በሁለት ዓመት ጊዜ ውስጥ ሲሆን (ቍ 22-26 ይመ)፣ ከዚህም ቀጥሎ በእስራኤልና በሶርያ መካከል የሦስት ዓመት የሰላም ጊዜ ነበር (22፥1 ይመ):: የሦስት ዓመቱ የሰላም ጊዜ እንደበቃም ከሶርያውያን ጋር በተደረገው ጦርነት ማለትም በዓ.ቅ.ክ. 853 አክዓብ ሞተ (22፥37):: ስለዚህ በዚህ ምዕራፍ ውስጥ የተጠቀሱት ሁኔታዎች የተከናወኑት ዓ.ቅ.ክ. 857 ነው:: ሠላሳ ሁለት ነገሥታት፤ የዳግማዊ ቤን ሀዳድ ሎሌዎች የነበሩ የነገድ መሪዎች ወይም የከተማ ገገርዎች ናቸው::

20፥4 *እኔም ሆንሁ የእኔ የሆነው ሁሉ የአንተ ነው፤* አክዓብ፣ የቤን ሀዳድን ፍላጎት ለመፈጸም ያሳየው ፈቃደኝነት፣ በሶርያውያን ላይ ድል ለመቀዳጀት እስራኤል ያላት ተስፋ እጅግ

አትቀበለው፤ የጠየቀህንም እሺ አትበለው”
አሉት።
9ስለዚህ ለቤን ሀዳድ መልእክተኞች፣ “ለጌ
ታዬ ለንጉሡ፣ ‘እኔ ባሪያህ በመጀመሪያ
ያልኸኝን ሁሉ አደርጋለሁ፤ ያሁኑን ጥያቄ
ህን ግን ልፈጽመው አልችልም’ ብላችሁ
ንገሩት” አላቸው። መልእክተኞቹም ይህንኑ
ይዘው ተመለሱ።
10ከዚያም ቤን ሀዳድ፣ “ለሚከተለኝ ሰው
ሁሉ የሰማርያ ዐፈር እንዳንድ ዕፍኝ የሚ
ዳረስ ሳይሆን ቢቀር፣ አማልክት ይህን ያድ
ርጉብኝ፤ ከዚህ የባሰም ያምጡብኝ” ሲል
ሌሎች መልክተኞችን ወደ አክዓብ ላከ።
11የእስራኤልም ንጉሥ፣ “ ‘ታጥቆ ለጦር
ነት የሚወጣ ሰው የጦር ትጥቁን እንደ ፈታ
ሰው መደንፋት የለበትም’ ብላችሁ ንገሩት”
አላቸው።
12ቤን ሀዳድ ይህን መልእክት የሰማው
አብረውት የነበሩት ነገሥታት በድንኳኖቻ
ቸው* ውስጥ ሆነው በሚጠጡበት ጊዜ ነበር፤
ቤን ሀዳድ ሰዎቹን፣ “ቡሉ ለጦርነት ተዘጋጁ”
አላቸው፤ ስለዚህ ከተማዪቱን ለመውጋት
ተዘጋጁ።

## አክዓብ ቤን ሀዳድን ድል አደረገ

13በዚያን ጊዜ አንድ ነቢይ ወደ እስራኤል
ንጉሥ ወደ አክዓብ መጥቶ፣ “እግዚአብሔር
እንዲህ ይላል፤ ‘ይህን ብዙ ሰራዊት ታያለ
ህን? ዛሬ በእጅህ አሳልፌ እሰጥሃለሁ፤ ከዚ
ያም እኔ እግዚአብሔር መሆኔን ታውቃ
ለህ’ ” አለው።
14አክዓብም፣ “ይህን የሚያደርገው ማን
ነው?” ሲል ጠየቀ።
ነቢዩም፣ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፤
‘ይህን የሚያደርጉት የየአውራጃው አዛዥ
የሆኑ ወጣት መኰንኖች ናቸው’ ” አለው።
“ታዲያ ጦርነቱን የሚጀምረው ማን ነው?”
ሲል ጠየቀ።
ነቢዩም፣ “አንተው ትጀምራለህ” ብሎ
መለሰ።
15ስለዚህ አክዓብ የየአውራጃው አዛዥ
የሆኑትን ሁለት መቶ ሠላሳ ሁለት ወጣት
መኰንኖች ጠራ፤ ከዚያም የቀሩትን እስራ
ኤላውያን ሰበሰበ፤ እነዚህም በአጠቃላይ ሰባት
ሺህ ነበሩ። 16እነርሱም ቤን ሀዳድና ከእርሱ

20፥10 2ሳሙ 22፥43
20፥11 ምሳ27፥1፤ ኤር9፥23፤አሞ2፥14
20፥12 1ነገ16፥9
20፥13 ዘፀ6፥7፤ መሳ6፥8
20፥14 መሳ1፥1
20፥16 1ነገ16፥9

የመነመነ መሆኑን ያሳያል። ሰማርያ እንዳትከበብ፣ የአክዓብን ሕይወት ለማትረፍና ከተማዋ እንዳትዘረፍ የተደረገው ድርድር ጠቅሟል።

20፥6 *ቤተ መንግሥትህንና የሹማምትህን ቤቶች እንዲበረብሩ፣ ሹማምቱን እልካቸዋለሁ፤* ቤን ሀዳድ ያቀረበው ይህ አዲስ ሐሳብ፣ የሰማርያ ከተማ በእርሱ ሰራዊት ቁጥጥር ሥር እንድትውል የሚያደርግ ነበር።


20፥9 *ያሁኑን ጥያቄህን ግን ልፈጽመው አልችልም፤* አክዓብ የቤን ሀዳድን የበላይነት ባይክድም (“ለጌታዬ ለንጉሡ፣ እኔ ባሪያህ”)፣ የከተማውን ሕዝብ ለእርሱ አሳልፎ ላለመስጠት ጽኑ አቋም ነበረው።

20፥10 *አማልክት ይህን ያድርጉብኝ፤ ከዚህ የባሰም ያምጡብኝ፤* መሐላን የሚያመለክት የተለመደ አባባል ነው (የ1ሳሙ 3፥17 ማብ ይመ)።

20፥11 *ታጥቆ ለጦርነት የሚወጣ ሰው፣ የጦር ትጥቁን እንደ ፈታ ሰው መደንፋት የለበትም፤* “ገና ሳይፈለፈሉ ይህን ያህል ጫጩቶች አሉኝ ብለህ አትቍጠር” ከሚለው የተለመደ አባባል ጋር የሚመሳሰል ነው።

20፥13 *እኔ እግዚአብሔር መሆኔን ታውቃለህ፤* ከተማዪቱ ከገጠማት ችግር የተነሣ፣ አክዓብ የእግዚአብሔርን ርዳታ ባይፈልግም፣ እግዚአብሔር ግን ቀደም ሲል ለንጉሡና ለሕዝቡ ራሱን የገለጠ ሲሆን (18፥36-37)፣ በዚህም ጊዜ በምሕረቱ ራሱን ሊገልጥላቸው ወደደ።

20፥14 *የየአውራጃው አዛዥ የሆኑ ወጣት መኰንኖች፤*



ጋር ተባብረው የነበሩት ሠላሳ ሁለቱ ነገ
ሥታት በድንኳኖቻቸው ውስጥ ሰክረው ሳለ
እኩለ ቀን ላይ መጡ:: 17በግንባር ቀደም
ትነት የወጡት ግን፣ የየአውራጃው አዛዥ
የሆኑት ወጣት መኰንኖች ነበሩ::
በዚህ ጊዜ ቤን ሀዳድ ሰላዮች ልኮ ነበርና
እነርሱም፣ "ሰዎች ከሰማርያ ወጥተው ወደ
ዚህ በመምጣት ላይ ናቸው" ብለው ነገሩት::
18እርሱም፣ "አመጣጣቸው ለሰላምም ይሁን
ለጦርነት ከነሕይወታቸው ይዛችሁ አምጧ
ቸው" አለ::
19የየአውራጃው አዛዥ የሆኑ ወጣት መኰ
ንኖችም ሰራዊቱን አስከትለው ከከተማዪቱ
ወጡ፤ 20እያንዳንዱም በፊቱ የገጠመውን
ጠላት ገደለ፤ ሶርያውያን ሸሹ፤ እስራኤላ
ውያንም ያሳድዷቸው ጀመር:: የሶርያ ንጉሥ
ቤን ሀዳድ ግን በፈረሱ ላይ ሆኖ ከጥቂት
ፈረሰኞቹ ጋር አመለጠ:: 21የእስራኤል ንጉሥ
አክዓብም ወደ ፊት በመግፋት ፈረሶችንና
ሠረገሎችን ማረከ፤ በሶርያውያንም ላይ ከባድ
ጒዳት አደረሰባቸው::
22ከዚያም በኋላ ነቢዩ ወደ እስራኤል ንጉሥ
መጥቶ፣ "በሚመጣው የጸደይ ወራት የሶ
ርያ ንጉሥ ተመልሶ ይመጣብሃልና በርታ፤
ምን ማድረግ እንዳለብህም ዕወቅ" አለው::
23በዚያኑ ጊዜም የሶርያ ንጉሥ ሹማምት
እንዲህ ሲሉ መከሩት፤ "አማልክታቸው
የኰረብታ አማልክት ናቸው፤ ያየሉብንም
ከዚህ የተነሣ ነው:: በሜዳ ላይ ብንገጥማ
ቸው ግን እኛ እንደምናይልባቸው አያጠራ
ጥርም:: 24እንግዲህ እንዲህ አድርግ፤ ነገሥ
ታቱን በሙሉ ከአዛዥነታቸው አስነሣ፤ በቦ
ታቸውም ሌሎች ሹማምት አድርግ:: 25ከእ
ስራኤል ጋር በሜዳው ላይ እንዲጋጠም በፈ
ረሱ ፈንታ ፈረስ፣ በሠረገላው ፈንታ ሠረ
ገላ በመተካት፣ እንደ ተደመሰሰው ያለ ስራ
ዊት አቋቁም፤ ከዚያ በኋላ ከእነርሱ ይበልጥ

20፥22 መሳ6፥8፤ 2ሳሙ11፥1
20፥23 ቍ28፤ኢሳ 36፥20፤ሮሜ1፥21-23
20፥26 ቍ30፤ 1ሳሙ4፥1፤2ሳሙ 11፥1፤2ነገ13፥17
20፥27 መሳ6፥6፤ 1ሳሙ13፥6
20፥28 ቍ23፤ዘፀ 6፥7፤ኢር16፥19-21
20፥30 ቍ26፤ 1ነገ22፥25፤መዝ62፥4 ፤ኢሳ26፥21፤30፥13
20፥31 ዘፍ37፥34፤ ኢዩ41፥3

እኛ እንደምንበረታ አያጠራጥርም::" ንጉሡም
ባቀረቡት ሐሳብ ተስማማ፤ እንዳሉትም አደ
ረገ::
26በተከታዩም የጸደይ ወራት ቤን ሀዳድ
ሶርያውያንን አሰባስቦ እስራኤልን ለመው
ጋት ወደ አፌቅ ወጣ:: 27እስራኤላውያንም
እንደዚሁ ተሰብስበው ስንቅ ከተሰጣቸው
በኋላ ሊገጥሟቸው ተሰልፈው ወጡ:: ሶርያ
ውያን አገር ምድሩን ሞልተውት ሳለ፣ እስ
ራኤላውያን ግን እንደ ሁለት ትናንሽ የፍ
የል መንጋ ሆነው ከፊት ለፊታቸው ሰፈሩ::
28የእግዚአብሔርም ሰው ወጥቶ ለእስራኤል
ንጉሥ፣ "*እግዚአብሔር* እንዲህ ይላል፤ 'ሶር
ያውያን *እግዚአብሔር* የኰረብታ እንጂ የሸ
ለቆ አምላክ አይደለም ብለዋልና ይህን ስፍር
ቍጥር የሌለው ሰራዊት በእጅህ አሳልፌ
እሰጥሃለሁ፤ አንተም እኔ *እግዚአብሔር* መሆ
ኔን ታውቃለህ' " አለው::
29በየሰፈሩበትም ቦታ ሰባት ቀን ከተፋጠጡ
በኋላ በሰባተኛው ቀን ጦርነት ገጠሙ:: እስ
ራኤላውያንም በአንዲት ጀምበር ከሶርያ
ውያን ሰራዊት መቶ ሺህ እግረኛ ገደሉ::
30የቀሩት ወደ አፌቅ ከተማ ሸሹ፤ በዚያም
በሃያ ሰባቱ ሺህ ላይ ቅጥሩ ተንዶ ወደቀባ
ቸው:: ቤን ሀዳድም ወደ ከተማዪቱ ሸሽቶ
በመሄድ ወደ አንዲት እልፍኝ ገብቶ ተደ
በቀ::
31ሹማምቱም፣ "የእስራኤል ቤት ነገሥ
ታት መሓሪዎች መሆናቸውን ሰምተናል፤
አሁንም እንነሣና በወገባችን ላይ ማቅ ታጥ
ቀን፣ በራሳችን ላይ ገመድ ጠምጥመን ወደ
እስራኤል ንጉሥ እንሂድ፤ ምናልባትም ሕይ
ወትህን ያተርፉት ይሆናል" አሉት::
32እነርሱም በወገባቸው ላይ ማቅ ታጥቀው፣
በራሳቸው ላይ ገመድ ጠምጥመው ወደ እስ
ራኤል ንጉሥ በመሄድ፣ "አገልጋይህ ቤን ሀዳድ፣

[n]12 ወይም፣ *ሱኮት* ተብሎ ሊተረጐም ይችላል፤ በቍ16 ላይም እንደዚሁ

የ16፥27 ማብ ይመ:: በሰሜኑ መንግሥት አውራጃ አስተዳደር ውስጥ ያለው ድርጅታዊ አሠራር አይታወቅም::

20፥15 *ሁለት መቶ ሠላሳ ሁለት ... በአጠቃላይ ሰባት ሺህ፤* ተከባ ካለች ከተማ ይህን ያህል መገኘቱ የሚያስደንቅ ቢሆንም፣ የሰራዊቱ ቍጥር ከፍተኛ አልነበረም፤ ነገር ግን ድሉ በእስራኤል ወታደራዊ የበላይነት ሳይሆን፣ በእግዚአብሔር ታላቅነት ላይ መሆኑን ለመግለጽ በቂ ቍጥር ነበር (ከመሳ 7፥2 ጋር ያነጻጽሩ)::

20፥20 *እያንዳንዱም በፊቱ የገጠመውን ጠላት ገደለ፤* ብዛቱ ከእነርሱ ቍጥር ጋር ተመጣጣኝ ካልሆነ ቀድሞ ከወጣ የጠላት ሰራዊት ጋር መግጠማቸውን ያመለክታል (2ሳሙ 2፥15-16 ይመ):: *በፈረሱ ላይ ሆኖ፣* ከጥቂት ፈረሰኞቹ ጋር አመለጠ፤ በፈረስ ላይ ተቀምጦ መዋጋት በኋላ ቈይቶ የመጣ የውጊያ ስልት በመሆኑ፣ በዚህ ቦታ የተጠቀሰው ሠረገላ ስለሚጐትቱ ፈረሶችና ሠረገላውን ስለሚነዱ ሰዎች ነው:: ድል ከሆኑ በኋላ፣ ሶርያውያን ወደ ደማስቆ የሸሹ ይመስላል::

20፥22 *የሶርያ ንጉሥ ተመልሶ ይመጣብሃልና፤* በራሱ መመካቱ አግባብ እንዳልሆነ፣ ይህ ስሙ ያልተጠቀሰ ነቢይ (ቍ 13 ይመ) አክዓብን አስጠንቅቀው:: ቤን ሀዳድ ወደፊት ወረራ እንደሚያደርግ ነቢዩ ማስታወቁ፣ አክዓብ በቀርሜሉስ ተራራ ላይና ድልን በመስጠት ራሱን በገለጠው በእግዚአብሔር ላይ ሙሉ በሙሉ እምነት እንዲኖረው ነው::

20፥23 *የኰረብታ አማልክት፤* የአማልክት ኀይል፣ ባሉበት የሥልጣን ክልል ብቻ የተወሰነ ነው በማለት አረማውያን ያላቸውን አመለካከት የሚያንጸባርቅ ነው:: *ያየሉብንም ከዚህ የተነሣ ነው፤* በጦር ሜዳ የሚገኘው ድልም ሆነ ሽንፈት፣ ወደረኞቹ ከሚያመልኩአቸው አማልክት የተነሣ እንጂ፣ በሁለቱም ወገን ካሉት ሰራዊት ጥንካሬ እንዳልሆነ ሶርያውያን ያምኑ ነበር:: በዚህም ምክንያት ለወደፊቱ ጦርነት ድል ለማግኘት ያሰቡት የውጊያ ስልት የአማልክቶቻቸው ኀይል የሚችሉብትን አመቺ ሁኔታ መከተል ነበር::

20፥26 *አፌቅ፤* ከገሊላ ባሕር በስተ ምሥራቅ ጥቂት ኪሎ ሜትር ርቆ የሚገኘው ቦታ ሊሆን ይችላል:: ውጊያው የተካሄደው በዮርዳኖስ ሸለቆ ውስጥ፣ የያርሙላና የዮርዳኖስ ወንዞች በሚገናኙበት አካባቢ ነው::

20፥28 *የእግዚአብሔርም ሰው፤* በቍ 13፥22 ላይ የተጠቀሰው ነቢይ ሊሆን ይችላል:: *አንተም እኔ እግዚአብሔር መሆኔን ታውቃለህ፤* የቍ 13 ማብ ይመ:: እግዚአብሔር በፍጥረትና በታሪክ ሁሉ ላይ የበላይ ገዢና ተቈጣጣሪ እንደሆነ፣ የአረማውያን አማልክትም በእርሱ ፊት ኀይል የሌላቸው መሆኑን ይገልጻል::

20፥29 *መቶ ሺህ እግረኛ፤* ድጋፍ የሚሰጡትን ሰዎችና ከሜዳና ከሶርያውያን የጦር ሠፈር ያሳደዷቸውን ሁሉ የሚያካትት ይሆናል::

20፥30 *ቅጥሩ ተንዶ፤* የእስራኤል አምላክ፣ ለእስራኤል ሰራዊት በጦርነቱ ድል ከመስጠቱም ሌላ በሶርያ ሰራዊት ላይ ተጨማሪ አደጋ አደረሰባቸው:: *ሃያ ሰባት ሺህ፤* የአፌቅ ግንብ ተንዶ፣ ይህን ያህል ሕዝብ መግደሉ፣ ከተማዪቱ ያን ያህል ትልቅ አልነበረችም፤ ምናልባት በአፌቅ ተሸሽገው የነበሩ፣ ቅጥሩም በተደረመሰ ጊዜ ያለ ተገን የቀሩ የወታደሮችን ቍጥር የሚያመለክት ይሆናል::

'እባክህ በሕይወት እንድኖር ፍቀድልኝ'
ብሎ ይለምንሃል" አሉት።
ንጉሡም፣ "እስካሁን በሕይወት አለን?
ወንድሜ እኮ ነው" አለ።
[33]ሰዎቹም ይህን በደግ በመተርጐም ቃሉን
ከአፉ ቀበል አድርገው፤ "አዎን ቤን ሀዳድ
ወንድምህ ነው" አሉት።
ንጉሡም፣ "በሉ ሂዱና አምጡት" አላ
ቸው፤ ቤን ሀዳድም በመጣ ጊዜ፣ አክዓብ
ሠረገላው ላይ እንዲወጣ አደረገው።
[34]ቤን ሀዳድም፣ "አባቴ ከአባትህ የወሰዳ
ቸውን ከተሞች እመልሳለሁ፤ አባቴ በሰማ
ርያ እንዳደረገው ሁሉ፣ አንተም በደማስቆ
የራስህን ገበያ ማቋቋም ትችላለህ" አለው።
አክዓብም፣ "እንግዲያውስ ስምምነት አድ
ርገን በነጻ እለቅሃለሁ" አለው፤ ስለዚህም ከእ
ርሱ ጋር የውል ስምምነት አድርጎ ለቀቀው።

## አንድ ነቢይ በአክዓብ ላይ ፈረደ

[35]ከነቢያት ልጆች አንዱ ጓደኛውን *በእግ
ዚአብሔር ቃል* ታዞ፣ "ምታኝ" አለው፤
ሰውየው ግን ፈቃደኛ አልሆነም።
[36]ስለዚህም ነቢዩ፣ "*ለእግዚአብሔር* ባለ
*መታዘዝህ*፣ ከእኔ ተለይተህ እንደ ሄድህ
አንበሳ ይገድልሃል" አለው። ሰውየው ከሄደ
በኋላ አንበሳ አግኝቶ ገደለው።
[37]ነቢዩም ሌላ ሰው አግኝቶ፣ "እባክህ
ምታኝ" አለው። ስለዚህ ያ ሰው መትቶ
አቈሰለው። [38]ከዚያም ነቢዩ ሄዶ ከመንገድ
ዳር በመቆም፣ ንጉሡን ይጠባበቅ ጀመር።
የራሱን መጠምጠሚያ ወደ ታች አውርዶ
ዐይኖቹን በመሸፈንም፣ ማንነቱ እንዳይታ

20፥34 ዘፍ10፥22፤ 14፥15፤ዘዐ23፥32፤ 2ሳሙ8፥6፤1ነገ15፥20 ፤ኤር49፥23-27
20፥35 1ሳሙ 10፥5፤1ነገ13፥21፤ አሞ7፥14
20፥36 1ነገ13፥24
20፥39 ኢሱ2፥14
20፥40 2ሳሙ 12፥5፤14፥13
20፥42 ኢሱ2፥14፤ 2ሳሙ12፥7፤ኤር 48፥10
20፥43 1ነገ21፥4

ወቅ አደረገ። [39]ንጉሡ በዚያ በሚያልፍበ
ትም ጊዜ፣ ነቢዩ ጠርቶት እንዲህ አለው፤
"እኔ አገልጋይህ በተፋፋመው ጦርነት መካ
ከል ገብቼ ሳለሁ፣ አንድ ሰው ምርኮኛ ይዞ
መጥቶ 'ይህን ሰው ጠብቅ፤ ቢያመልጥ በገ
መዱ ትገባለህ ወይም አንድ መክሊት[*] ብር
ትከፍላለህ' አለኝ። [40]'ታዲያ እኔ አገልጋይህ
ሥራ በዝቶብኝ ወዲያ ወዲህ ስል ሰውየው
አምልጦ ሄደ።' "
የእስራኤልም ንጉሥ፣ "ራስህ ፈርደሃል፤
ይኸው ይፈጸምብሃል" አለው።
[41]ከዚያም ነቢዩ መጠምጠሚያውን በፍጥ
ነት ከዐይኑ ላይ አነሣ፤ የእስራኤልም ንጉሥ
ያ ሰው ከነቢያት አንዱ መሆኑን ዐወቀ። [42]ነቢ
ዩም ንጉሡን አለው፤ "*እግዚአብሔር* እንዲህ
ይላል፤ 'እኔ ፈጽሞ ይገደል[†] ያልሁትን ሰው
ለቀኸዋልና በገመዱ ትገባለህ፤ በሕዝቡም
ፈንታ ያንተ ሕዝብ በገመዱ ይገባል።"
[43]የእስራኤልም ንጉሥ ተበሳጭቶና ተቈጥቶ
ሰማርያ ወዳለው ቤተ መንግሥቱ ሄደ።

## የናቡቴ የወይን ተክል ቦታ

**21** ከጥቂት ጊዜ በኋላ በኢይዝራኤላዊው
በናቡቴ የወይን ተክል ቦታ ላይ አንድ
ነገር ደረሰ፤ ቦታውም በኢይዝራኤል ውስጥ
ከሰማርያ ንጉሥ ከአክዓብ ቤተ መንግሥት
አጠገብ ነበር። [2]አክዓብም ናቡቴን፣ "የወ
ይን ተክል ቦታህ ከቤተ መንግሥቴ አጠገብ
ስለ ሆነ፣ የአትክልት ቦታ እንዳደርገው
ልቀቅልኝ፤ በምትኩ ከዚህ የበለጠ የወይን
ተክል ቦታ እሰጥሃለሁ፤ የተሻለ ሆኖ ከታየህም

[*]39 34 ኪሎ ግራም ያህል ነው
[†]42 የዕብራይስጡ ቃል ሰውን ወይም ዕቃን ፈጽሞ በማጥፋት ለእግዚአብሔር መስጠት የሚለውን ያመለክታል

20፥31 *የእስራኤል ቤት ነገሥታት መሓሪዎች መሆናቸውን፤* የእስራኤል ነገሥታት በጣም ጨካኝ ከሆኑት የአሦራውያን ነገሥታት ልዩ መሆናቸውን ሶርያውያን ተገንዝበዋል። *ማቅ ... ገመድ፤* ምናልባት የትሕትናና የመገዛት ትእምርት ይሆናል።

20፥32 *አገልጋይህ፤* ቤንሀዳድ፣ በወቅቱ የአነጋገር ፈሊጥ ራሱን የአክዓብ አገልጋይ አድርጎ በማቅረቡ፣ የእርሱ የበታች መሆኑን እንደ ተቀበለ ይገልጻል (የቍ 9 ማብ ይመ)። *ወንድሜ፤* አክዓብ፣ ቤን ሃዳድ ለተናገረው ነገር ዋጋ ሳይሰጥ፣ ራሳቸውን ከሌሎች መሪዎች እኩል አድርገው የሚመለከቱ መሪዎች የሚና ገሩበትን ቃል በመጠቀም ምላሽ ሰጠ (9፥13 ይመ)። በዚህም አክዓብ፣ ቤን ሀዳድ ከጠየቀውና ከጠበቀውም በላይ አደረገለት።

20፥33 *ሠረገላው ላይ እንዲወጣ፤* አክዓብ ያደረገው በጦርነት ለተሸነፈ ጠላት የሚደረግ የተለመደ አቀባበል አይደለም።

20፥34 *አባቴ ከአባትህ የወሰዳቸውን ከተሞች፤* ምናልባት ሬማት ዘገለዓድንና (22፥3 ይመ) ቀደም ሲልም ቀዳማዊ ቤን ሀዳድ ከባእስ የወሰዳቸውን ከተሞች (15፥20) ሳይሆን አይቀርም። *የራስህን ገበያ፤* ብዙ ሀብት የሚያስገኝ ዓለም አቀፋዊ ንግድ ማዕከል ስለ ሆነ፣ እንዲህ ዐይነቱ የንግድ እንቅስቃሴ በመንግሥታት ቍጥጥር ይደረግ ነበር። *ከእርሱ ጋር የውል ስምምነት አድርጎ ለቀቀው፤* እኩል ደረጃ ባላቸው መካከል የሚደረግ የሰላም ስምምነት ሲሆን፣ በቤን ሀዳድ የቀረበውን የፖለቲካና የንግድ ስምምነት የሚያጠቃልል ነው።

20፥35 *ከነቢያት ልጆች፤* ከነቢያት ወገን የሆኑትን ሰዎች የሚያመለክት አገላለጽ ነው (2ነገ 2፥3:5:7:15፤ 4፥1:38፤ 5፥22፤ 6፥1፤ 9፥1 ይመ)፤ "ልጆች" የሚለው ቃል "ወንድ ልጅ" ወይም "ትውልድ" ማለት ሳይሆን፣ የአንድን ቡድን አባል የሚያመለክት ነው። ቸልተኝነትና ከእምነት ማፈግፈግ በበዛበት ወቅት እነዚህ የነቢያት ጉባኤ ብቅ ያሉ ቢሆንም ዋና ተግባራቸው የእግዚአብሔርን ሕዝብ መንፈሳዊ ሕይወት ማነጽና እግዚአብሔርን እንዲያውቅ ማድረግ ነበር፤ ነቢያት ተብለው የተጠሩትም መንፈሳዊ ተግባራቸው ትንቢት መናገር ስለ ነበር ሳይሆን አይቀርም (18፥29፤ ዘኍ 11፥25-27፤ 1ሳሙ 10፥5-6:10-11፤ 18፥10፤ 19፥20-24 ይመ)። ሳሙኤል፣ ኤልያስንና ኤልሳዕን የመሳሰሉ ታላላቅ የእግዚአብሔር ነቢያት፣ ከነቢያት ማኅበር ጋር የቅርብ ግንኙነት የነበራቸውና የእግዚአብሔር ነቢያትም መንፈሳዊ አማካሪዎች ነበሩ።

20፥36 *ከእኔ ተለይተህ እንደ ሄድህ አንበሳ ይገድልሃል፤* ከይሁዳ የመጣው የእግዚአብሔር ሰው የደረሰበትን ቅጣት የሚያመለክት ነው (13፥23-24)።

20፥39 *መክሊት፤* ጥቂት ወታደሮች ብቻ ብዙ ስለሚከፈላቸው፣ የሰውየው ሕይወት አደጋ ላይ መውደቁን አክዓብ የተረዳ ይመስላል።

20፥40 *ራስህ ፈርደሃል፤* አክዓብ ምሕረት ሊያደርግለት አልወደደም፤ በራሱ ላይም የሞት ፍርድ እየፈረደ መሆኑን አል ተገነዘበም (በ2ሳሙ 12፥1-12) ነቢዩ ናታን ከተጠቀመበት ተመሳሳይ ዘይቤ ጋር ያነጻጽሩ።

20፥42 *እኔ ፈጽሞ ይገደል ያልሁትን ሰው፤* የዘሌ 27፥28፤ የኢሱ 6፥17 ማብ ይመ። አክዓብ፣ ቤን ሀዳድን የለቀቀው ቀደም ሲል የተሰጠውን ትእዛዝ ጥሶ ይሁን ወይም እግዚአብሔርን መጠየቅ ችላ ብሎ እንደ ሆነ ግልጽ አይደለም። ሆኖም ግን እግዚአብሔር ቤን ሀዳድን ለአክዓብ በእጁ አሳልፎ ሰጥቶት ነበር (ቍ 28 ይመ)፤ አክዓብም ኀላፊነቱን ባለመወጣቱ በእግዚአብሔር ፊት ተጠያቂ ሆነ። *በገመዱ ትገባለህ፤ በሕዝቡም ፈንታ ያንተ ሕዝብ በገመዱ ይገባል፤* አክዓብ ንጉሥ በመሆኑ ስለ ፈጸመው ኀጢአት የሚፈረደው በእርሱ ላይ ብቻ ሳይሆን፣ በሰሜኑ መንግሥት ሕዝብም ላይ ነው። አክዓብ ከሶርያውያን ጋር በተደረገው ጦርነት ሞተ (22፥29-39)፣ በኢዩና በኢዮአካዝ ዘመነ መንግሥት እስራኤል በሶርያውያን እጅ ክፉኛ ተዋረደች (2ነገ 10፥32፤ 13፥3)።

21፥1 *ከአክዓብ ቤተ መንግሥት አጠገብ፤* አክዓብ በሰማርያ ከነበረው ቤተ መንግሥት በተጨማሪ በኢይዝራኤል መኖርያ ቤት ነበረው (18፥45፤ 2ነገ 9፥30 ይመ)። *ሰማርያ፤* ዋና ከተማ

የሚያወጣውን ገንዘብ እከፍልሃለሁ” አለው::
3ናቡቴ ግን፣ “ዐፅመ ርስቴን እለቅልህ
ዘንድ *እግዚአብሔር* አይበለው” ሲል መለሰ
ለት::
4ኢይዝራኤላዊው ናቡቴ፣ “ዐፅመ ርስቴን
አልለቅልህም” ስላለው፣ አክዓብ ተበሳጭቶና
ተቈጥቶ ወደ ቤቱ ገባ፤ አኵርፎም በዐል
ጋው ላይ ተኛ፤ ምግብም መብላት ተወ::
5ሚስቱ ኤልዛቤልም ወደ እርሱ ገብታ፣
“እስከዚህ የተበሳጨኸው፣ ምግብስ የማት
በላው ለምንድን ነው?” ብላ ጠየቀችው::
6እርሱም፣ “ኢይዝራኤላዊውን ናቡቴን፣
‘የወይን ተክል ቦታህን ሽጥልኝ፤ ከፈለግህም
በምትኩ ሌላ የወይን ቦታ እሰጥሃለሁ’ አል
ሁት፤ እርሱ ግን፣ ‘የወይን ተክል ቦታዬን
አልለቅልህም’ ስላለኝ ነው” አላት::
7ሚስቱ ኤልዛቤልም፣ “አንተ አሁን የእስ
ራኤል ንጉሥ ትባላለህ? በል ተነሥና እህል
ቅመስ፤ ደስም ይበልህ፤ የኢይዝራኤላዊውን
የናቡቴን የወይን ተክል ቦታ እኔ እንድታገኝ
አደርግሃለሁ” አለችው::
8ስለዚህ በአክዓብ ስም ደብዳቤዎች ጻፈች፤
በገዛ ማኅተሙም አትማ በናቡቴ ከተማ
አብረውት ለሚኖሩ ሽማግሌዎችና መኳን
ንት ላከች:: 9በደብዳቤዎቹም ላይ እንዲህ
ስትል ጻፈች፤

> “የአንድ ቀን ጾም ዐውጁ፤ ናቡቴንም
> በሕዝቡ መካከል ከፍ ባለ ቦታ ላይ አስ
> ቀምጡት:: 10እንዲሁም ሁለት የሐሰት
> ምስክሮች ከፊት ለፊቱ አስቀምጡና፣
> ‘እግዚአብሔርንም ንጉሡንም ሰድቦአል’
> ብለው ይመስክሩበት፤ ከዚያም አውጥ
> ታችሁ በድንጋይ ወግራችሁ ግደሉት::”

11ስለዚህ በናቡቴ ከተማ የሚኖሩ ሽማግ
ሌዎችና መኳንንት በደብዳቤዎቹ ላይ እንደ
ጻፈችላቸው አደረጉ:: 12የአንድ ቀን ጾም ዐወጁ፤
ናቡቴንም በሕዝቡ መካከል ከፍ ባለ ቦታ
ላይ አስቀመጡት:: 13ከዚያም ሁለት የሐሰት
ምስክሮች መጥተው ከፊት ለፊቱ ተቀመጡ፤
በሕዝቡም ፊት፣ “ናቡቴ እግዚአብሔርንና ንጉ
ሡን ሰድቦአል” ብለው መሰከሩበት:: ስለዚህ
ከከተማዪቱ ውጭ ወስደው በድንጋይ ወግ
ረው ገደሉት:: 14ከዚያም ለኤልዛቤል፣ “ናቡቴ
በድንጋይ ተወግሮ ሞቶአል” ብለው ላኩባት::
15ኤልዛቤልም በድንጋይ ተወግሮ መሞቱን
ወዲያው እንደ ሰማች አክዓብን፣ “ናቡቴ
በድንጋይ ተወግሮ ሞቶአል፤ በል ተነሣና
ኢይዝራኤላዊው ናቡቴ ሊሸጥልህ ያልፈለገ
ውን የወይን ተክል ቦታ በርስትነት ውሰ
ደው” አለችው:: 16አክዓብ የናቡቴን ሞት
ሲሰማ የናቡቴን የወይን ተክል ቦታ በርስ
ትነት ለመያዝ ተነሥቶ ወረደ::
17ከዚያም *የእግዚአብሔር* ቃል ወደ ቴስ
ብያዊው ወደ ኤልያስ እንዲህ ሲል መጣ፤
18“ተነሣና በሰማርያ ሆኖ የሚገዛውን የእስ
ራኤልን ንጉሥ አክዓብን ትገናኝ ዘንድ
ውረድ፤ የናቡቴን የወይን ተክል ቦታ በር
ስትነት ለመያዝ ሄዶ አሁን እዚያው ይገ
ኛል:: 19እንዲህም በለው፤ ‘*እግዚአብሔር* እን
ዲህ ይላል፤ ሰውየውን ገደልኸው፤ ደግሞ
ርስቱን ልትወስድ? ከዚያም እንዲህ በለው፤
‘*እግዚአብሔር* እንዲህ ይላል፤ ውሾች የናቡ
ቴን ደም በላሱበት ቦታ የአንተንም ደም
ውሾች እንዲሁ ይልሱታል!’ ”
20አክዓብም ኤልያስን፣ “ጠላቴ ሆይ አገ
ኘኸኝን?” አለው::
ኤልያስም መልሶ እንዲህ አለው፤ “*በእግ
ዚአብሔር* ፊት የተጠላውን ነገር ለማድረግ
ራስህን ሸጠሃልና አዎን አግኝቼሃለሁ:: 21‘እነሆ
ክፉ ነገር አመጣብሃለሁ፤ ዘርህን ፈጽሜ
አጠፋለሁ፤ ባሪያም ይሁን ነጻ እያንዳንዱን
የአክዓብን የመጨረሻ ወንድ ልጅ ከእስራ
ኤል እጠርጋለሁ:: 22ለቍጣ ስላነሣሣኸኝና
እስራኤልንም ስላሳትሃቸው ቤትህን እንደ
ናባጥ ልጅ እንደ ኢዮርብዓም ቤት፣ እንደ
አኪያም ልጅ እንደ ባኦስ ቤት አደርገዋለሁ::’

21፥1 1ሳሙ 29፥1፤2ነገ9፥21፤ 10፥1
21፥3 ዘሌ25፥23
21፥4 1ሳሙ 28፥23፤1ነገ20፥43
21፥7 1ሳሙ8፥14
21፥8 ዘፍ38፥18፤ 2ሳሙ11፥14
21፥10 ዘፀ22፥28፤ ዘሌ24፥1516፤ዘዳ13፥13፤ሐሥ6፥11
21፥12 ኢሳ58፥4
21፥13 ዘሌ24፥16
21፥15 1ሳሙ8፥14
21፥19 1ነገ22፥38፤ 2ነገ9፥26፤ኢዮ 24፥6፤ 31፥39፤ መዝ9፥12፤68፥23፤ ኢሳ14፥20፤ኤር15፥3
21፥20 1ነገ18፥17፤ 2ነገ17፥17፤ሮሜ7፥14
21፥21 ዘዳ32፥36፤ መሳ9፥5፤2ነገ10፥7
21፥22 1ነገ12፥30፤ 16፥3

ሲሆን፣ የሚወክለውም የሰሜኑን መንግሥት ነው (የ16፥24 ማብ ይመ)::

21፥2 *የወይን ተክል ቦታህ... ልቀቅልኝ፤* በእስራኤል የነገሥታት ሥልጣን በኪዳን ሕግ የተወሰነ ገደብ ስለ ነበረው (ዘዳ 17፥14-20፤ 1ሳሙ 10፥25 ይመ)፤ ከነዓናውያን ነገሥታት ያደርጉት እንደ ነበር (የቍ 7 ማብ እንዲሁም 1ሳሙ 8፥9-17 ይመ)፣ የግለሰብ ይዞታ የሆነውን መሬት አክዓብ መንጠቅ አይችልም ነበር::

*21፥3፤* ናቡቴ መሬቱን ሊሰጥ ፈቃደኛ አልሆነም፤ ምክንያቱም መሬት የእግዚአብሔር እንደ ሆነ ለእያንዳንዱ እስራኤላዊ ቤተ ሰብም ቋሚ ርስት አድርጎ እግዚአብሔር መስጠቱ፣ በተስፋዪቱ ምድር ለቤተ ሰብ ቋሚ ሆኖ እንዲተላለፍ ያምን ስለ ነበር ነው::

21፥7 *አንተ አሁን የእስራኤል ንጉሥ ትባላለህ፤* ይህ የምፀት አነጋገር የግል ፍላጎታቸውን ለማርካት ያላቸውን ኀይል ከመጠቀም ለአፍታ እንኳ ወደ ኋላ የማይሉትን የፊንቂያውያንና የከነዓናውያን ነገሥታት የጭካኔ ድርጊት የሚከተል ሰው የሚናገረው ነው፤ ሳሙኤል የተሰጠውን ሥልጣኑን ከተጠቀመበት ሁኔታ ጋር ያነጻጽሩ፤ 1ሳሙ 12፥3-4)::

21፥9 *የአንድ ቀን ጾም ዐውጁ፤* ከእግዚአብሔር ፍርድ የተነሣ፣ ጥፋት በሕዝቡ ላይ እንደ መጣና ይህም ጥፋት ሊመለስ የሚችለው፣ ሕዝቡ ራሱን አዋርዶ በጾም ሲቀርብና ኀጢአት የሠራውን ሰው በሞት ሲያስወግድ ብቻ ነው የሚል አስተሳሰብ ሕዝቡ እንዲኖረው ኤልዛቤል አደረገች (ከመሳ 20፥26፤ ከ1ሳሙ 7፥5-6፤ ከ2ዜና 20፥2-4 ጋር ያነጻጽሩ)::

21፥10 *ሁለት፤* በሙሴ ሕግ ቅጣት የሚፈጸመው በሁለት ሰዎች ሲመሰከርበት ነው (ዘኍ 35፥30፤ ዘዳ 17፥6፤ 19፥15):: *የሐሰት ምስክሮች፤* የዘዳ 13፥13 ማብ ይመ:: *ይመስክሩበት፤* ጠቅላላ ሁኔታው ሕጋዊ ይዘት ያለው ለማስመሰል የታቀደ ነበር (ዘፀ 20፥16፤ 23፥7፤ ዘሌ 19፥16 ይመ):: *እግዚአብሔርንም ንጉሡንም ሰድቦአል፤* ለእንዲህ ዐይነቱ ተግባር፣ የሙሴ ሕግ የሚያዘው በድንጋይ ተወግሮ መሞትን ነው (ዘሌ 24፥15-16)::

21፥13 *ከከተማዪቱ ውጭ፤* በሙሴ ሕግ መሠረት የተደረገ ነው (ዘሌ 24፥14፤ ዘኍ 15፥35-36)፤ ናቡቴ በእርሻ ቦታው ላይ ተወግሮ ሞተ (ቍ 19፤ ከ2ነገ 9፥21:26 ጋር ያነጻጽሩ)፤ ልጆቹም ከእርሱ ጋር ተወግረው ሞቱ (2ነገ 9፥26 ይመ፤ በኢ ሱ 7፥24-25 ላይ ስለ አካን ከተጠቀሰው ጋር ያነጻጽሩ)፤ ይኸውም ወራሽ እንዳይኖረው ለማድረግ ነበር::

21፥19 *ሰውየውን ገደልኸው፤ ደግሞ ርስቱን ልትወስድ?* አክዓብ በኤልዛቤል ክፉ ሥራ በመተባበሩ፣ በግድያና በስርቆት ወንጀል ተጠያቂ እንዲሆን አድርጎታል:: *ውሾች የናቡቴን ደም በላሱበት ቦታ የአንተንም ደም ውሾች እንዲሁ ይልሱታል፤* አክዓብ ወዲያው ንስሓ በመግባቱ (ቍ 29)፣ በዚህ ትንቢት እንደ ተጠቀሰው ሬሳው በናቡቴ ዕርሻ ላይ መጣሉ (2ነገ 9፥25-26) እስከ ልጁ ኢዮራም ዘመን ድረስ ሊዘገይ ችሎአል:: አክዓብ የተገ

23“ስለ ኤልዛቤልም *እግዚአብሔር*፣ ‘በኢ
ይዝራኤል ቅጥር አጠገብ[a] ውሾች ኤልዛቤ
ልን ይበሏታል’ ይላል::
24“ደግሞም ከአክዓብ ወገን ሆኖ በከተማ
የሞተውን ውሾች ይበሉታል፤ በገጠር የሞ
ተውንም የሰማይ አሞሮች ይበሉታል::”
25በሚስቱ በኤልዛቤል ተገፋፍቶ *በእግዚአ
ብሔር* ፊት ክፉ ለማድረግ ራሱን የሸጠ
እንደ አክዓብ ያለ ሰው ከቶ አልነበረም::
26*እግዚአብሔር* ከእስራኤል ፊት ያሳደዳ
ቸው አሞራውያን እንዳደረጉት ሁሉ፣ እር
ሱም ጣዖታትን በማምለክ እጅግ የሚያስ
ጸይፍ ርኵሰት ፈጸመ::
27አክዓብም ይህን ቃል ሲሰማ ልብሱን
ቀደደ፤ ማቅ ለብሶ፤ ጾመ፤ በማቅ ላይ ተኛ
በሐዘን ኵርምት ብሎም ይሄድ ነበር::
28ከዚያም እንዲህ የሚል *የእግዚአብሔር*
ቃል ወደ ቴስብያዊው ወደ ኤልያስ መጣ፤
29አክዓብ ራሱን በፊቴ እንዴት እንዳዋረደ
አየህን? ራሱን ስላዋረደ ይህን መከራ በዘ
መኑ አላመጣበትም፤ ነገር ግን ይህን በቤቱ
ላይ የማመጣው በልጁ ዘመን ነው::”

## ሚክያስ በአክዓብ ላይ ትንቢት ተናገረ

22፥1-28 ተን ምብ - 2ዜና 18፥1-27

22 በሶርያና በእስራኤል መካከል ለሦ
ስት ዓመት ጦርነት አልነበረም::
2በሦስተኛው ዓመት ግን የይሁዳ ንጉሥ ኢዮ
ሣፍጥ የእስራኤልን ንጉሥ ለመጐብኘት
ወረደ:: 3የእስራኤልም ንጉሥ ሹማምቱን፣
“በገለዓድ የምትገኘው ሬማት የእኛ ሆና ሳለች፣
ከሶርያው ንጉሥ እጅ ለመመለስ ምንም
እንዳላደረግን አታውቁምን?” አላቸው::
4ስለዚህ ኢዮሣፍጥን፣ “በገለዓድ የምትገ
ኘው ሬማት ላይ ለመዝመት አብረኸኝ
ለመሄድ ትፈቅዳለህን?” ሲል ጠየቀው::
ኢዮሣፍጥም፣ “እኔ ያው እንደ አንተው
ነኝ፤ ሕዝቤ እንደ ሕዝብህ፣ ፈረሶቼም እንደ
ፈረሶችህ ናቸው” አለ:: 5ኢዮሣፍጥም የእስ
ራኤልን ንጉሥ፣ “በመጀመሪያ ግን *የእግዚ
አብሔርን* ሐሳብ ጠይቅ” አለው::
6ስለዚህ የእስራኤል ንጉሥ አራት መቶ
ነቢያትን በአንድነት ሰብስቦ፣ “በገለዓድ
በምትገኘው ሬማት ላይ ልዝመት ወይስ
ልተው?” ሲል ጠየቃቸው::
እነርሱም፣ “*እግዚአብሔር* በንጉሡ እጅ
አሳልፎ ይሰጣታልና ዝመትባት” አሉት::
7ኢዮሣፍጥ ግን፣ “የምንጠይቀው *የእግዚ
አብሔር* ነቢይ እዚህ የለምን?” አለ::
8የእስራኤልም ንጉሥ ለኢዮሣፍጥ፣ “መኖ
ሩንማ በእርሱ አማካይነት *የእግዚአብሔርን*
ፈቃድ የምንጠይቀው አንድ ሰው አሁንም
አለ፤ ነገር ግን ምን ጊዜም ቢሆን ስለ እኔ
ክፉ እንጂ አንዳችም መልካም ትንቢት
ተናግሮ ስለማያውቅ እጠላዋለሁ፤ ይህም ሰው
የይምላ ልጅ ሚክያስ ነው” አለ::
ኢዮሣፍጥም፣ “ንጉሡ እንዲህ ማለት አይ
ገባውም” ሲል መለሰ::
9ስለዚህ የእስራኤል ንጉሥ ከሹማምቱ
አንዱን ጠርቶ፣ “በል የይምላን ልጅ ሚክ
ያስን በፍጥነት አምጣው” አለው::
10የእስራኤል ንጉሥና የይሁዳ ንጉሥ ኢዮ
ሣፍጥ አልባሰ መንግሥታቸውን ለብሰው፣
በሰማርያ ቅጥር በር አጠገብ ባለው አውድማ
ላይ በየዙፋናቸው ተቀምጠው ሳለ፣ ነቢያቱ
ሁሉ በፊታቸው ትንቢት ይናገሩ ነበር::
11በዚህ ጊዜ ሴዴቅያስ የተባለው የክንዓና
ልጅ የብረት ቀንዶች አበጅቶ፣ “*እግዚአብሔር*

21፥23 1ነገ19፥10፤ 34፥36
21፥24 ዘኁ40፥19፤ ዘዳ28፥26፤1ነገ14፥11
21፥25 1ነገ14፥9፤ 16፥33
21፥26 ዘፍ15፥16
21፥27 ዘፍ37፥34፤ ኢሳ38፥15፤ኢር4፥8
21፥29 ዘፀ10፥3፤ 20፥5፤32፥14፤2ነገ 9፥26፤10፥6-10፤ 22፥20
22፥3 ዘዳ4፥43
22፥4 2ነገ3፥7
22፥5 ዘፀ33፥7፤ 2ነገ3፥11፤ኢዮ38፥2፤ መዝ32፥8፤73፥24፤ 107፥11
22፥6 መሳ18፥6፤ 1ነገ13፥18
22፥7 ዘኍ27፥21፤ ዘዳ18፥15፤1ነገ3፥11፤ 5፥8
22፥8 ቍ13፤ኢሳ 5፥20፤30፥10፤ኤር 23፥17፤አሞ5፥10
22፥11 ቍ24፤ ዘዳ33፥17፤ኤር27፥2፤ 28፥10፤ዘካ1፥8-21

[a]23 አብዛኞቹ የዕብራይስጥ ቅጆች ከዚህ ጋር ይስማማሉ፤ ነገር ግን አንዳንድ የዕብራይስጥ ቅጆች፣ ቩልጌትና የሱርስቱ ትርጕም (2ነገ9፥26 ይመ)፣ *በዕርሻው ማሳ ላይ* ይላሉ

ደለው በሬማት ዘገለዓድ ላይ በተደረገው ጦርነት ሲሆን (22፥29-37)፣ ሬሳው ወደ ሰማርያ በመጣ ጊዜ ሠረገላው ሲታጠብ ደሙን ውሾች ልሰውታል (22፥38)::

21፥21 *ባሪያም ይሁን ነጻ፤* የ14፥10 ማብ ይመ::

21፥22 *እንደ ኢዮርብዓም ቤት፤* 14፥10፤ 15፥28-30 ይመ:: እንደ ባኦስ፤ 16፥3-4፤ 11፥13 ይመ::

21፥24 የ14፥11፤ የ16፥4 ማብ ይመ::

21፥25 *በኤልዛቤል ተገፋፍቶ፤* 16፥31፤ 18፥4፤ 19፥1-2፤ 21፥7 ይመ::

21፥26 *አሞራውያን፤* እዚህ ላይ፣ ከእስራኤላውያን በፊት በከነዓን የነበሩትን ሰዎች በአጠቃላይ ያመለክታል (ዘፍ 15፥16፤ ዘዳ 1፥7 ይመ)::

21፥27 *ማቅ ለብሶ፤* የዘፍ 37፥34 ማብ ይመ::

21፥29 *በልጁ ዘመን፤* ፍርዱ እንዲዘገይ ተደረገ እንጂ ጨርሶ አልተሻረም (የቍ 19 ማብ ይመ)::

22፥1 *በሶርያና በእስራኤል መካከል…ጦርነት አልነበረም፤* የእስራኤል ንጉሥ አክዓብና የደማስቆ ንጉሥ ቤን ሀዳድ፣ ከአሦር ጋር ከተዋጉት ዐሥራ ሁለቱ ኅብረ ብሔር ገዦች ጋር አብረው በዓ.ቅ.ክ. 853 ቂርቃር ላይ በሚገኘው አሮንቲስ በሚባል ወንዝ አጠገብ ተዋግተው እንደ ነበር በአሦር ንጉሥ በሣልሳዊ ሽልማን ሰር ታሪክ ውስጥ ተጽፎ ይገኛል:: አሦራውያን እንደ ጻፉት፣ አክ ዓብ ሁለት ሺህ ሠረገሎችና ዐሥር ሺህ እግረኛ ወታደሮች እንዲ ሳተፉ አድርጎ ነበር:: አሦራውያን ከመሸሻቸውም በላይ፣ ለአራት ወይም ለአምስት ዓመታት ያህል ፊታቸውን ወደ ምዕራብ ለማቅ ናት ስለ አልደፈሩ፣ አገኘን ያሉት ድል የተጋነነ ይመስላል (የቍ 1፤ የ2ዜና 18፥2 ማብ ይመ):: *ሦስት ዓመት፤* የ20፥1 ማብ ይመ::

22፥3 *በገለዓድ…ሬማት፤* በዮርዳኖስ ማዶ፣ በያሙክ ወንዝ አጠገብ የምትገኝና ከሙሴ ዘመን ጀምሮ የእስራኤላውያን ከተ ማም ነበረች (4፥13፤ ዘዳ 4፥43፤ ኢሱ 20፥8 ይመ):: *የእኛ ሆና ሳለች፤* ከጥቂት ዓመት በፊት ከቤን ሀዳድ ጋር በተደረገውና ሊያ ከብረው ባልቻለው ስምምነትም አንጻር (20፥34 ይመ) እስራኤል በሬማት ዘገለዓድ ላይ የይገባኛል ጥያቄ ማቅረብ ችላለች::

22፥4 *አብረኸኝ ለመሄድ ትፈቅዳለህን?* አክዓብ፣ አሦርን ለመውጋት ከሶርያውያን ጋር ግምባር ቢፈጥርም፣ በአሦር ላይ የተደረገው ጦርነት ስላበቃ፣ ሬማት ዘገለዓድን ከአሦር ቍጥጥር ሥር ነጻ ለማውጣት አጋጣሚውን ከመጠቀም ወደ ኋላ አላለም:: *እኔ ያው እንደ አንተው ነኝ፤ ሕዝቤ እንደ ሕዝብህ፣ ፈረሶቼም እንደ ፈረሶችህ ናቸው፤* ኢዮሳፍጥ ከአክዓብ ጋር አብሮ ለጦርነት በመሰለፍ የእግዚአብሔርን ፈቃድ ስለ ጣሰ፣ ነቢዩ ኢዩ ነቅፎ ታል (2ዜና 19፥2):: ኢዮሳፍጥ ይህን ስምምነት በመፈጸሙ፣ የሰሜኑ መንግሥት ባእሰን ለመውጋት አባቱ አሳ ከሶርያውያን ጋር አድርጎት የነበረውን ውል ሳይፈጽም ቀረ (15፥17-23 ይመ)::

22፥5 *በመጀመሪያ ግን የእግዚአብሔርን ሐሳብ ጠይቅ፤* እግዚአብሔር ከእነርሱ ጋር መሆኑን አስቀድሞ ሳያውቅ በታቀ ደው ጦርነት ውስጥ ለመሳተፍ አመነታ (1ሳሙ 23፥1-4፤ 2ሳሙ 2፥1 ይመ)::

22፥6 *ነቢያትን፤* በቤቴል ከነበረው አረማዊ አምልኮ ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት ያላቸው ሲሆን (የ12፥28-29 ማብ ይመ) የነቢ ይነት አገልግሎታቸውንም ንጉሡን ለማስደሰት ተጠቅመውበታል (አሞ 7፥10-13)::

22፥7 *የእግዚአብሔር ነቢይ እዚህ የለምን?* አራት መቶዎቹ ነቢያት አመኔታ የሚጣልባቸው እንዳልሆኑ ተረዳ (ሕዝ 13፥2-3 ይመ፤ ስለዚህም እውነተኛ የእግዚአብሔርን ነቢይ መጠ

እንዲህ ይላል፤ ‘ሶርያውያን እስኪጠፉ ድረስ
የምትወጋቸው በእነዚህ ነው’” አለው።
12የቀሩትም ነቢያት ሁሉ፣ “*እግዚአብሔር*
በንጉሡ እጅ አሳልፎ ይሰጣታልና በገለዓድ
የምትገኘውን ሬማትን ወግተህ ድል አድ
ርግ” በማለት በአንድ ቃል ትንቢት ይና
ገሩ ነበር።
13ከዚያም ሚክያስን ሊጠራ የሄደው መል
እክተኛ፣ “እነሆ፤ ሌሎቹ ነቢያት ንጉሡ
ድል እንደሚያደርግ በአንድ ቃል ትንቢት
እየተናገሩለት ነውና ያንተም ቃል ከእነርሱ
ጋር አንድ እንዲሆን እባክህ መልካም ነገር
ተናገር” አለው።
14ሚክያስ ግን፣ “ሕያው *እግዚአብሔርን*!
ለእርሱ የምነግረው *እግዚአብሔር* የነገረኝን
ብቻ ነው” አለ።
15እዚያም እንደ ደረሰ ንጉሡ፣ “ሚክያስ
ሆይ፤ በገለዓድ በምትገኘው ሬማት ላይ እን
ዝመትባት ወይስ እንተው?” ሲል ጠየቀው።
እርሱም፣ “*እግዚአብሔር* በንጉሡ እጅ
አሳልፎ ይሰጣታልና ዘምተህ ድል አድርጋት”
ብሎ መለሰለት።
16ንጉሡም፣ “ከእውነት በቀር *በእግዚአ
ብሔር* ስም አንዳች ነገር እንዳትነግረኝ የማ
ምልህ ስንት ጊዜ ነው?” አለው።
17ከዚያም ሚክያስ እንዲህ ሲል መለሰ፣
“እስራኤል ሁሉ ጠባቂ እንደሌላቸው በጎች
በየተራራው ላይ ተበትነው አየሁ፣ *እግዚአ
ብሔርም*፣ ‘ይህ ሕዝብ ጌታ የለውም፤ እያ
ንዳንዱ በሰላም ወደየቤቱ ይሂድ’ አለ።”
18የእስራኤልም ንጉሥ ለኢዮሣፍጥ፣ “ስለ
እኔ ክፉ ብቻ እንጂ ከቶ መልካም ትንቢት
አይናገርም አላልሁህምን?” አለው።
19ከዚያም ሚክያስ እንዲህ አለ፤ “እንግዲህ
የ*እግዚአብሔር* ቃል የሚለውን ስማ፤ ‘*እግ
ዚአብሔር* በዙፋኑ ላይ ተቀምጦ፣ የሰማይ
ሰራዊት ሁሉ በቀኝና በግራው ቆመው አየሁ፤
20*እግዚአብሔርም* “በገለዓድ በምትገኘው
ሬማት ላይ ዘምቶ እዚያው እንዲሞት፣
አክዓብን ማን ያስተው?” አለ።’

22፥13 ቍ 8
22፥14 ዘኍ 22፥18፤ 1ሳሙ 3፥17
22፥17 ዘፍ 11፥4፤ ዘኍ 27፥17፤ ሕዝ 13፥14፤ናሆ 3፥18፤ ማቴ 9፥36
22፥19 ኢዮ 1፥6፤ 15፥8፤38፥7፤መዝ 47፥8፤103፥20-21፤ 148፥2፤ኢሳ 6፥1፤ 63፥15፤ኤር 23፥18፤ 22፤ሕዝ 1፥26፤ ዳን 7፥9፤ሉቃ 2፥13
22፥22 መሳ 9፥23፤ 2ተሰ 2፥11
22፥23 ዘጸ 13፥3፤ 31፥29፤ሕዝ 14፥9
22፥24 ቍ 11፤ ኢዮ 26፥4፤ሐሥ 23፥2
22፥25 1ነገ 20፥30
22፥27 2ዜና 16፥10፤ኤር 20፥2፤ 26፥21፤37፥15፤ ዕብ 11፥36
22፥28 ዘዳ 18፥22
22፥30 1ሳሙ 28፥8

“ታዲያ አንዱ ይህን፣ ሌላውም ያን አለ፤
21በመጨረሻም፣ ‘አንድ መንፈስ ወጣ፤ ከዚ
ያም በ*እግዚአብሔር* ፊት ቆሞ፣ “እኔ አስ
ተዋለሁ” አለ።’
22*እግዚአብሔርም*፣ ‘እንዴት አድርገህ?’
ሲል ጠየቀው።
“እርሱም፣ ‘እኔ እወጣለሁ፤ በገዛ ነቢያቱም
አፍ ሁሉ የሐሰት መንፈስ እሆናለሁ’ አለ።
*እግዚአብሔርም*፣ “ሂድ እንግዲያው ውጣና
አስተው፤ ይሳካልሃል” አለው።
23“ስለዚህ እነሆ *እግዚአብሔር* በእነዚህ
ሁሉ ነቢያትህ አፍ የሐሰት መንፈስ አኖረ፤
በአንተም ላይ መዓቱን እንደሚያመጣብህ
ተናገረ።”
24ከዚያም የክንዓና ልጅ ሴዴቅያስ ወጥቶ
ሚክያስን በጥፊ መታውና፣ “ለመሆኑ የ*እግ
ዚአብሔር* መንፈስ ከእኔ በየት በኩል ዐልፎ
ነው አንተን መጥቶ ያናገረህ?” ሲል ጠየ
ቀው።
25ሚክያስም፤ “ይህንማ ለመደበቅ ወደ
አንዲት እልፍኝ በሄድህ ዕለት ታውቀዋለህ”
አለው።
26ከዚያም የእስራኤል ንጉሥ እንዲህ ሲል
አዘዘ፤ “በሉ ሚክያስን ይዛችሁ ወደ ከተ
ማዪቱ ገዥ ወደ አሞንና ወደ ንጉሡ ልጅ
ወደ ኢዮአስ መልሱት፤ 27ከዚያም፣ ‘ንጉሡ፣
“በደኅና እስክመለስ ድረስ፣ ይህን ሰው በእ
ስር ቤት አቈዩት፤ ከደረቅ እንጀራና ከውሃ
በስተቀር ሌላ እንዳትሰጡት” ብሎአል በሉት’
አለ።
28ሚክያስም፣ “አንተ በደኅና ከተመለስህ
*እግዚአብሔር* በእኔ አልተናገረማ!” አለ፤
ከዚያም በመቀጠል፣ “በዚህ ያለኸው ሕዝብ
ሁሉ ይህን ቃሌን ልብ ብለህ ያዘው!” አለ።

## አክዓብ በገለዓድ በምትገኘው በሬማት ተገደለ

22፥29-36 ተጓ ምብ - 2ዜና 18፥28-34

29ስለዚህ የእስራኤል ንጉሥና የይሁዳ ንጉሥ
ኢዮሣፍጥ በገለዓድ ወደምትገኘው ሬማት
ወጡ። 30የእስራኤል ንጉሥ ኢዮሣፍጥን፣

---

የቅ እንደሚያስፈልግ ተናገረ።

22፥8 ***መልካም ትንቢት ተናግሮ ስለማያውቅ*** ነቢይ በአክዓብ ዘንድ ተወዳጅነትን የሚያገኘው ለእርሱ በሚናገረው በጎ ትንቢት ነበር (18፥11፤ 21፥20 ይመ)።

22፥11 ***ሴዴቅያስ*** አራት መቶዎቹን ነቢያት ወክሎ የሚናገር ነቢይ ነበር። ***የብረት ቀንዶች*** የሥልጣን ምልክት ነው (ዘዳ 33፥17 ይመ)።

22፥13 ***ያንተም ቃል ከእነርሱ ጋር አንድ እንዲሆን*** በጠቅላላ እነዚህ ነቢያት የራሳቸውን ሐሳብ እያገለገሉ እንደ ነበር ፍንጭ የሚሰጥ ምክር ነው።

22፥15 ***እንዝመትባት*** ኢዮሳፍጥ የዕቅዱ ተባባሪ እንደ ሆነ በማመልከት አዎንታዊ ምላሽ የሚፈልግ ተንኰል ዐዘል ጥያቄ ነው (ቍ 6 ይመ)። ***እግዚአብሔር በንጉሡ እጅ አሳልፎ ይሰጣታልና ዘምተህ ድል አድርጋት*** ሚክያስ አራት መቶ ሐሰተኛ ነቢያት የተናገሩትን በምፀት መልክ ደግሞ ተናገረ (ቍ 12 ይመ)።

22፥16 ***ከእውነት በቀር… አንዳች ነገር እንዳትነግረኝ*** አባባሉ ትክክል አለመሆኑ ከአነጋገሩ ስለሚታወቅ አክዓብ ቶሎ መረዳት የቻለ ይመስላል።

22፥17 ***ጠባቂ እንደሌላቸው በጎች… ይህ ሕዝብ ጌታ የለውም*** እረኛንና በጎችን የሚያመለክት ምስል በመጠቀም (ዘኍ 27፥16-17፤ ዘካ 13፥7፤ ማቴ 9፥36፤ 26፥31)፣ አክዓብ በሚደረገው ጦርነት እንደሚሞት ሚክያስ ተናገረ።

22፥19 ***እግዚአብሔር በዙፋኑ ላይ ተቀምጦ … አየሁ*** እውነተኛ ነቢይ፣ እግዚአብሔር ሊያደርግ የሚችለውን ነገር በትክክል ይናገር ዘንድ የእግዚአብሔርን ዙፋን የሚያመለክት ነው (ኢሳ 6፥1፤ ኤር 23፥16-22)።

22፥23 ***እግዚአብሔር በእነዚህ ሁሉ ነቢያትህ አፍ የሐሰት መንፈስ አኖረ*** አንዳንዶቹ የሐሰት መንፈስ የሚለውን ሰይጣን ወይም የእርሱን ጉዳይ ከሚፈጽሙት መናፍስት አንዱ ነው ብለው ያምናሉ፤ (ነገር ግን 1ሳሙ 15፥29 ይመ)፤ እንዲሁም ሌሎች ይህ የሐሰት መንፈስ፣ ሐሰት ያለውን ኀይል የሚያመለክት ትእምርት ነው ይላሉ። ስለዚህም፣ የገዛ ልባቸውን ፍላጎት በመናገር ሐሰትን (ኤር 14፥14፤ 23፥16:26፤ ሕዝ 13፥2-3:17 እንዲሁም የ2ሳሙ 24፥1 ማብ ይመ)፣ የመረጡትን አራት መቶዎቹን ነቢያት እግዚአብሔር የውሸት ኀይል እንዲሠለጥንባቸው አሳልፎ ሰጣቸው።

"እንዳልታወቅ እኔ ልብስ ለውጬና ሌላ
ሰው መስዬ እገባለሁ፤ አንተ ግን ልብሰ
መንግሥትህን ልበስ" አለው:: ስለዚህ የእስ
ራኤል ንጉሥ ራሱን ደብቆ ወደ ጦርነቱ ገባ::
31በዚህ ጊዜ የሶርያ ንጉሥ ሠላሳ ሁለቱን
የሠረገላ አዛዦች፣ "ከራሱ ከእስራኤል ንጉሥ
በቀር ትንሽም ይሁን ትልቅ ከማንም ጋር
እንዳትገጥሙ" ሲል አዞአቸው ነበር፤ 32የሠ
ረገላ አዛዦቹ ኢዮሣፍጥን ሲያዩት፣ "ያለ
ጥርጥር ይህ የእስራኤል ንጉሥ ነው" አሉ፤
ስለዚህ አደጋ ሊጥሉበት ከበቡት፤ ኢዮሣ
ፍጥ ሲጮህ ግን 33የሠረገላ አዛዦቹ እርሱ
የእስራኤል ንጉሥ አለመሆኑን አውቀው
መከታተሉን ተዉት::
34ነገር ግን አንዱ ቀስቱን ሳያልም እንዲሁ
ሲያስፈንጥር በጦር ልብሱ መጋጠሚያ ላይ
የእስራኤልን ንጉሥ ወጋው፤ ንጉሡም ሠረገላ
ነጂውን፣ "ቈስያለሁና ወደ ኋላ አዙረህ
ከጦሩ ሜዳ አውጣኝ" አለው:: 35ጦርነቱም
ቀኑን ሙሉ ተፋፍሞ ዋለ፤ በዚህ ጊዜም
ንጉሡ በሶርያውያን ፊት ለፊት ሠረገላው
ላይ ቀና ብሎ እንደ ተደገፈ ነበር፤ የቍ
ስሉ ደም በሠረገላው ወለል ላይ ይወርድ
ነበር፤ በዚያኑ ዕለት ማታም ንጉሡ ሞተ::
36ፀሓይ ስትጠልቅም በሰራዊቱ መካከል፣
"እያንዳንዱ ሰው ወደ ቤቱ፣ እያንዳንዱም
ወደ ሀገሩ ይሂድ!" የሚል ጩኸት አስተ
ጋባ::
37ንጉሡ ስለ ሞተም ወደ ሰማርያ አምጥ
ተውት እዚያው ተቀበረ:: 38ሠረገላውንም
አመንዝሮች በታጠቡበት በሰማርያ[x] ኵሬ
አጠቡት፤ እግዚአብሔርም እንደ ተናገረው
ቃል ደሙን ውሾች ላሱት::
39ሌላው በአክዓብ ዘመነ መንግሥት የተ
ፈጸመውና ያደረገው ሁሉ፣ ቤተ መንግሥ
ቱን መሥራቱና በዝሆን ጥርስ መለበጡ

22፥31 ዘኍ10፥22፤ 2ዜና10፥19፤17፥2
22፥34 2ነገ9፥24፤ 2ዜና35፥23
22፥36 2ነገ14፥12
22፥38 1ነገ21፥19
22፥39 2ዜና 9፥17፤መዝ45፥8፤ አሞ3፥15
22፥43 1ነገ3፥2፤ 8፥61፤2ዜና17፥3
22፥46 ዘዳ23፥17
22፥47 1ነገ11፥14-18፤2ነገ3፥9፤8፥20
22፥48 ዘኍ33፥35፤ 1ነገ9፥26

እንዲሁም የሠራቸው የምሽግ ከተሞች በእ
ስራኤል ነገሥታት ታሪክ የተጻፈ አይደለ
ምን? 40አክዓብም ከአባቶቹ ጋር አንቀላፋ፤
ልጁ አካዝያስም በእግሩ ተተክቶ ነገሠ::

### የይሁዳ ንጉሥ ኢዮሣፍጥ

22፥41-50 ተጓ ምብ - 2ዜና 20፥31-21፥1

41የእስራኤል ንጉሥ አክዓብ በነገሠ በአራ
ተኛው ዓመት የአሳ ልጅ ኢዮሣፍጥ በይ
ሁዳ ነገሠ:: 42ኢዮሣፍጥ ሲነግሥ ዕድሜው
ሠላሳ አምስት ዓመት ነበር፤ እርሱም በኢ
የሩሳሌም ሃያ አምስት ዓመት ገዛ:: እናቱ
ዓዙባ ትባላለች፤ እርሷም የሺልሒ ልጅ
ነበረች:: 43በአካሄዱም ሁሉ የአባቱን የአሳን
መንገድ ተከተለ፤ ከዚያች ፈቀቅ አላለም፤
በእግዚአብሔርም ፊት መልካም የሆነውን
አደረገ፤ ይሁን እንጂ በየኰረብታው ላይ
ያሉትን የማምለኪያ ቦታዎች አላጠፋም፤ ሕዝ
ቡም በዚያ መሥዋዕት ይሠዋ፣ ዕጣንም ያጥን
ነበር:: 44እንዲሁም ኢዮሣፍጥ ከእስራኤል
ንጉሥ ጋር በሰላም ኖረ::
45ሌላውም ኢዮሣፍጥ በዘመነ መንግሥቱ
የፈጸመው፣ ያከናወነውና ያደረገው ጦርነት
ሁሉ በይሁዳ ነገሥታት ታሪክ የተጻፈ አይ
ደለምን? 46ከአባቱ ከአሳ ዘመን በኋላ እንኳ
ተርፈው በጣዖት ማምለኪያ ቦታዎች የነበሩ
ትን የወንደቃ ቅሬታዎች ከምድሪቱ አስወ
ገደ:: 47በዚያን ጊዜ ኤዶም ንጉሥ አልነበ
ራትም፤ የሚገዛት እንደራሴ ነበር::
48ኢዮሣፍጥ ወርቅ ለማምጣት ወደ ኦፊር
የሚሄዱ የንግድ መርከቦች[ˀ] አሠርቶ ነበር፤
ይሁን እንጂ በዔጽዮንጋብር ስለ ተሰበሩ
ከቶ ወደዚያ መሄድ አልቻሉም ነበር::
49በዚያን ጊዜም የአክዓብ ልጅ አካዝያስ ኢዮ
ሣፍጥን "ሰዎቼ ከሰዎችህ ጋር በመርከብ

[x]38 ወይም፣ *የጦር መሣሪያ በሚታጠብበት በሰማርያ* ተብሎ መተርጐም ይችላል
[ˀ]48 ዕብራይስጡ *የተርሴስ መርከቦች* ይላል

22፥24 *የእግዚአብሔር መንፈስ ከእኔ በየት በኩል ዐልፎ ነው አንተን መጥቶ ያናገረህ?* በዚህ ምፀታዊ ንግግር ማንኛውም ሰው እንደሚዋሽ ሁሉ፣ ነቢይም ሊዋሽ እንደሚችል ሴዴቅያስ ይጠቍማል::

22፥25 *ለመደበቅ ወደ አንዲት እልፍኝ፤* ሴዴቅያስ መሸሸጊያ ሲፈልግ ማለት ነው (ከ20፥30 ጋር ያነጻጽሩ):: ይህም የሚክያስን የነቢይነት ሥልጣን እውነተኛነት ይገልጻል::

22፥30 *ሌላ ሰው መስዬ፤* የሰዎች ትኵረት በእርሱ ላይ እንዳይሆን ይህን ዘዴ በመጠቀም ሚክያስ የተናገረው ትንቢት በእርሱ ላይ እንዳይፈጸም ለማድረግ ሞከረ::

22፥31 *ከእስራኤል ንጉሥ በቀር፤* በጥንት ዘመን፣ በጦርነት መሪው ቢሞት ወይም ቢማረክ፣ ሰራዊቱ ይበተን ነበር (ከቍ 35-36 ጋር ያነጻጽሩ)::

22፥34 *ሠረገላ ነጂው፤* የጦር ሠረገላ የሚይዘው ሁለት ሰው ሲሆን፣ ይኸውም ተዋጊውንና ሠረገላ ነጂውን ነው:: አንዳንድ ጊዜ በሠረገላው ላይ ሦስት ሰዎች ይቀመጣሉ፤ ሦስተኛው ግን የሠረገላው አለቃ ነው (9፥22፤ 2ነገ 9፥25፤ ዘፀ 14፥7፤ 15፥4 ይመ፤ በእነዚህ ክፍሎች፣ እነዚህ አለቆች ቃል በቃል "ሦስተኛው" ተብለው ይጠራሉ)::

22፥35 *በዚያኑ ዕለት ማታም... ሞተ፤* ሚክያስ የተናገረው ትንቢት መፈጸሙን ያመለክታል (ቍ 17:28)::

22፥38 *እግዚአብሔርም እንደ ተናገረው ቃል፤* የአክዓብን አሟሟት በተመለከተ፣ ኤልያስ የተናገረው ትንቢት በከፊል መፈጸሙን ያሳያል (የ21፥19 ማብ ይመ)::

22፥39 *ቤተ መንግሥቱን መሥራቱና በዝሆን ጥርስ መለበጡ፤* በሰማርያ ቍፋሮ ያካሄዱ ተመራማሪዎች በዚህን ዘመን የተሠሩ በዝሆን ጥርስ የተለበጡ ዕቃዎች በአንዳንድ ሕንጻዎች ውስጥ አግኝተዋል:: አክዓብ በዚህ መልክ የዝሆን ጥርስ መጠቀሙ፣ በእርሱ ዘመነ መንግሥት የነበረውን የኢኮኖሚ ብልጽግና ያመለክታል:: *የሠራቸው የምሽግ ከተሞች፤* አክዓብ መጊዶንና ሐጾርን ምሽግ በማድረግ አጠናክሮ እንደ ሠራቸው፣ ተመራማሪዎች አረጋግጠዋል:: በእስራኤል ነገሥታት ታሪክ፤ የ14፥19 ማብ ይመ::

22፥40 *ከአባቶቹ ጋር አንቀላፋ፤* የ1፥21 ማብ ይመ:: *ልጁ አካዝያስም በእግሩ ተተክቶ ነገሠ፤* ስለ አካዝያስ ዘመነ መንግሥት ቍ 51፥53፤ 2ነገ 1 ይመ::

22፥41 *አክዓብ በነገሠ በአራተኛው ዓመት ... ኢዮሳፍጥ በይሁዳ ነገሠ፤* በዓ.ቅ.ክ. 869 ለብቻው ንጉሥ የሆነበትን፣ የኢዮሳፍጥን ዘመነ መንግሥት አጀማመር የሚያመለክት ይመስላል (የቍ 42፤ 16፥29 ማብ ይመ)::

22፥42 *ሃያ አምስት ዓመት፤* ከዓ.ቅ.ክ. 872-848 ሲሆን የኢዮሳፍጥ ሙሉ ዘመነ መንግሥት የሚቈጠረው፣ ንጉሥ አሳ የአባቱ ባለ ሙሉ ሥልጣን እንደራሴ ከሆነበት ከሠላሣ ዘጠነኛው ዓመት ጀምሮ ነው (የ15፥10 ማብ ይመ፤ እንዲሁም 2ዜና 16፥12 ይመ)::

22፥43 *ይሁን እንጂ በየኰረብታው ላይ ያሉትን የማምለኪያ ቦታዎች አላጠፋም፤* የ3፥2፤ 15፥14 ማብ ይመ::

22፥44 *ንጉሥ፤* በደቡቡ መንግሥት ኢዮሳፍጥ ይገዛ በነበረበት ዘመን (የቍ 4 ማብ ይመ)፣ በሰሜኑ ክፍል ይመሩ የነበሩትን አክዓብን፣ አካዝያስንና ኢዮራምን ሁሉ በጥቅሉ የሚያመለክት ነው::

22፥45 *ያደረገው ጦርነት ሁሉ፤* 2ነገ 3፤ 2ዜና 17፥11፤ 20 ይመ:: *በይሁዳ ነገሥታት ታሪክ፤* የ14፥29 ማብ ይመ::

ይሂዱ" ሲል ጠይቆት ነበር፤ ኢዮሣፍጥ ግን
እሺ አላለውም።
50ኢዮሣፍጥ ከአባቶቹ ጋር አንቀላፋ፤ እነ
ርሱ በተቀበሩበት በአባቱ በዳዊት ከተማ
ተቀበረ። ልጁ ኢዮራምም በእግሩ ተተክቶ
ነገሠ።

## የእስራኤል ንጉሥ አካዝያስ

51የይሁዳ ንጉሥ ኢዮሣፍጥ በነገሠ በዐሥራ
ሰባተኛው ዓመት የአክዓብ ልጅ አካዝያስ
የእስራኤል ንጉሥ ሆኖ በሰማርያ ነገሠ፤
እስራኤልንም ሁለት ዓመት ገዛ። 52እርሱም
የአባቱንና የእናቱን፣ እንዲሁም እስራኤልን
ያሳተውን የናባጥን ልጅ የኢዮርብዓምን
መንገድ በመከተሉ፣ *በእግዚአብሔር ፊት*
የተጠላ ክፉ ሥራ ሠራ። 53አባቱ እንዳደ
ረገው ሁሉ፣ እርሱም በኣልን አመለከ፤
ሰገደለትም። በዚህም የእስራኤልን አምላክ
እግዚአብሔርን ለቍጣ እንዲነሣሣ አደረገ።

22፥52 1ነገ15፥26
22፥53 መሳ2፥11፤ 1ነገ21፥25

22፥46 *የወንደቃ፤* የ14፥24 ማብ ይመ።

22፥47 *ኤዶም ንጉሥ አልነበራትም፤ ኤዶም፣* በይሁዳ ትገዛ እንደ ነበር ያመለክታል (2ሳሙ 8፥14፤ 2ነገ 8፥20 ይመ)።

22፥48 *ኦፊር፤* የ9፥28 ማብ ይመ። *በዔጽዮንጋብር ስለ ተሰበሩ፤* የመርከቦቹ መሰበር፣ ኢዮሳፍጥ ከሰሜኑ መንግሥት ንጉሥ ከአካዝያስ ጋር ኅብረት በመፍጠሩ ከእግዚአብሔር የመጣ ፍርድ ነበር (2ዜና 20፥35-37 ይመ)።

22፥50 *ከአባቶቹ ጋር አንቀላፋ፤* የ1፥21 ማብ ይመ። *ልጁ ኢዮራምም በእግሩ ተተክቶ ነገሠ፤* ስለ ኢዮራም ዘመነ መንግሥት 2ነገ 8፥16-24፤ 2ዜና 21 ይመ።

22፥51 *ኢዮሳፍጥ በነገሠ በዐሥራ ሰባተኛው ዓመት፤* በዓ.ቅ.ክ. 853 ማለት ነው (የቀ 41-42 ማብ ይመ)። *ሁለት ዓመት፤* ከዓ.ቅ.ክ. 853-852 ማለት ነው (የ2ነገ 1፥17 ማብ ይመ)።

22፥52 *የአባቱንና የእናቱን ... መንገድ፤* 16፥30-33 ይመ። *የኢዮርብዓምን መንገድ፤* 12፥28-33 ይመ።